# በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና

በ

አበበ መርዕድ

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሚያዝያ፣ 2000 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና

በ

አበበ መርዕድ

ኣማካሪ

ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ዲግሪ
ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሚያዝያ፣ 2000 ኣ.ም.
ኣዲስ ኣበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና

በ

አበበ መርዕድ

ሚያዝያ፣ 2000 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ማውጫ

## ኣርእስት ገጽ

ምስጋና iv
በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ የስንጠረዣዊ መረጃዎች ዝርዝር v
የፎቶግራፍ ዝርዝር ማውጫ vi
ኣጠቃሎ viii
1. መግቢያ 1
1.1. የጥናቱ መንስኤ 1
1.2. የጥናቱ ዋና ኣላማና ዝርዝር ኣላማዎች 2
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ 2
1.4. የኣጠናን ዘዴ 3
1.5. በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች 4
1.6. የጥናቱ ወሰን 4
1.7. የጥናቱ ግብ 5
1.8. ያጋጠሙ ችግሮች 6
2. ትውራዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ 10
2.1. ትውራዊ ዳራ 11
2.1.1. ባህል ምንድነው? 12
2.1.2. ቁሳዊ ባህል 13
2.1.3. መንፈሳዊ ባህል 15
2.2. ቅርስና የቅርስ ኣስፈላጊነት 16
2.3. በጎባ ወረዳ የቅርሶች ኣጠባበቅና ይዞታ 19
2.4. ፎክሎርና የመመገቢያ ቁሳቁስ 22
2.5. ፎክሎርና ትእምርታዊ ፋይዳው 25
2.6. የመመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ ከጥንት እስከዛሬ 27
2.7. በጥናታዊ ጽሁፉ ዙሪያ የተከናወኑ ኣገራዊ ስራዎች ክለሳ 30
3. የጎባ ወረዳ ማስተዋወቂያ 32
3.1. የጎባ ወረዳ 34
3.1.1. መልክኣ ምድራዊ ኣቀማመጥ 34
3.1.2. መስህብነት ያላቸው ቦታዎች 36
3.1.3. የህዝብ ብዛት 38
3.1.4. የብሄረሰብ ስብጥር 39
3.1.5. የቋንቋ ስብጥር 39

3.1.6. የአየር ጠባይ 40
3.2. የህዝቡ የኑሮ መሰረት 41
3.2.1. የግብርና ስራ 41
3.2.2. ከብት እርባታ 43
3.3. ሀይማኖትና ልዩ ልዩ እምነቶች 45
3.4. የጎባ ወረዳ ርእሰ ከተማ ስም የትመጣ (Origin) 47
4. የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያና የመጠጫ ቁሳቁስ 50
4.1. ከእንጨት የሚሰሩ ቁሳቁስ 52
4.2. ትውራዊ ዳራ 52
4.2.1. ገበታ (GABATAA) 53
4.2.2. ቆሪ (QORII) 63
4.2.3. ቁዲ ሶረታ (QUUDII SOORATAA) 69
4.2.4. ኦኮሌ (OKOLEE) 73
4.2.5. ኪላ (KILLA) 74
4.2.6. ቁሉ ሙከ ሰላታ (Quluu Muka Salaataa) ከእንጨት የተሰራ የሰላታ (የስግደት) ውሀ መያገር 77
4.2.7. ቦቤ (BOOBEE) 79
4.3. ከሸክላ የሚሰሩ መመገቢያ እቃዎች 79
4.3.1. ትውራዊ ዳራ 79
4.3.2. ኦኮቴ (OKKOTEE) ማሰሮ 85
4.3.3. ጢሊቴ (XILIITEE) 90
4.3.4. ጡዌ (XUWWEE) 94
4.3.5. ጃዩ (JAAYII) 97
4.3.6. ወሾ (WASHOO) 98
4.3.7. በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ባህል የቡና ስርኣት ማከናወኛ ቁሳቁስ 100
4.4. ከቅል የሚሰሩ ቁሳቁስ 106
4.4.1. ትውራዊ ዳራ 106
4.4.2. የተለያየ መጠንና ቅርጽ ያላቸው የቅል ቁሳቁስ 107
4.4.2.1. ቁሉ ኡናታ (Quluu Unaataa) የማማጊያ ቅል 108
4.4.2.2. ቡቄ ቡና (Buqqee Buna) የቡና ማስቀመጫ ቅል 111
4.4.2.3. ቁሉ ቡና (Quluu Buna) የቡና መጠጫ ቅል 111
4.4.2.4. ጉቹማ (Guchuma) 112

4.4.2..5. የውሀ ቅል ወይም የስግደት፣ የሰላታ ቅል (QULUU BISHAAN YOOKAN QULUU SALAATAA) 113
4.5. የስፌት እቃዎች 114
4.5.1. ትውራዊ ዳራ 115
4.5.2. ኤሌምቱ (ELEMTUU) ማለበ.ያ 117
4.5.3. ጪጮ ወይም ጩጮ «CIICOO (CUUCOO)» 120
4.5.4. ጡንጦ (XUUNXOO) 124
4.5.5. ባሬ (BAARREE) 128
4.5.6. ኮቦ (KOBOO) 130
4.5.7. ሌማት (LEEMATII) ሌማቲ 131
4.5.8. ቡሬ (BUURREE) 133
4.6. ከቆዳ የሚሰሩ እቃዎች 137
4.6.1. ትውራዊ ዳራ 137
4.6.2. የቆዳ ኦኮሌ (OKOLEE GOGAA) 138
4.6.3. ኣገልግል (GILGILII) ጊልጊሊ 140
4.7. ከቀንድ የሚሰሩ እቃዎች 142
4.7.1. ትውራዊ ዳራ 142
4.7.2. ዋንጫ (WAANCAA) 143
4.7.3. የቀንድ ማንኪ.ያ (FAL'AANA GAAFAA) 146
5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚ.ያ እና የመፍትሄ ሀሳብ 149
5.1. ማጠቃለያ 149
5.2. መደምደሚ.ያ 152
5.3. የመፍትሄ ሀሳብ 153

የተጠቀሱ ምንጮች

አባሪ ኣንድ:- የመረጃ ሰጪዎች ዝርዝር
አባሪ ሁለት:- ናሙና ጥያቄዎች
ኣባሪ ሦስት:- የፎቶግራፍ መረጃ
ኣባሪ አራት:- የጎባ ወረዳ ካርታ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የተሟላ እንዲሆን ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ከመጽሀፍቶቻቸው፣ ከልዩ ልዩ መጣጥፎቻቸውና ጽሁፎቻቸው ካገኘሁዋቸው ንድፈ ሀሳቦች በተጨማሪ ምሁራዊ አስተያየታቸውን፣ ወንድማዊ ኣመለካከታቸውንና ገንቢ የሆኑ ሀሳቦቻቸውን ለለገሱኝ፣ ስራዬ በስኬት እንዲቋጭ ውድ ጊዜያቸውን ለሰጡኝ ኣስተማሪዬና ኣማካሪዬ ዶ/ር ፈቃደ ኣዘዘ ያለኝ ምስጋና ልባዊ ነው።

በጎባ ወረዳ የረጅም ጊዜ ነዋሪ የሆኑት ሀጂ ፈቂ ሀሰኖ መረጃን በመስጠት ብቻ ሳይወሰኑ የመረጃ ምንጮችን በመጠቆምና በኣስተርጓሚነትም መኣልትና ለሊት ሳይሉ ጊዜያቸውን መስዋእት ኣድርገውልኛልና እጅግ በጣም ኣመሰግናቸዋለሁ።

ኣቶ ኣለሙ ወርቁ የባቱ ኣጠቃላይ 2ኛ ደረጃ የመሰናዶ ት/ቤት የኦሮምኛ ቋንቋ መምህር መረጃ በመስጠት፣ መረጃ ሰጪዎችን በመጠቆም፣ ቁሳቁሶቹን በማዋስና ኣስተርጓሚም በመሆን ጭምር ላሳዩኝ ሰናይ ምግባርና ድርጊት ምስጋናዬ የላቀ ነው።

ቪዲዮ (ምስል) ቀራጭ ባለሙያዎች እርስበርስ በመመሳጠር እንደከፍላቸው የጣሉብኝን ከፍተኛ የዋጋ ጫና መወጣት ባልቻልኩበትና ግራ በተጋባሁበት ጊዜ «ቪዲዮ ቀራጭ እኔ ኣስተዋውቅሃለሁ» በማለትና ከመረጃ ኣቀባዮች ጋርም በማገናኘት ላበረከቱልኝ ኣስተዋጽኦ ኣቶ ሚሊዮን ገብረማሪያም ባለውለተኛዬ ናቸው።

በኦሮምኛ ቋንቋ የተጻፉ ኣንዳንድ መረጃዎችን ወደ ኣማርኛ ቋንቋ በመመለስ ኣቶ ከበደ ገበየሁ፣ ደጀኔ ኣድማሱ፣ እንዳለ ጫላና ጸጋዬ ሄይ በተለይም ኣቶ በቀለ ቱፋ ከመተርጎም ባሻገር ለተደጋጋሚ ጊዜ መረጃ በመስጠትም ስለተባበሩኝ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

በገንዘብ በኩል ይገጥመኝ የነበረውን ችግር ያቃለሉልኝ ኣቶ ኣማረ ስዩም፣ መሰለ ገብረሚካኤል፣ በቀለ ጉታ፣ ግዛው ደበላና ሙላቱ ከበደ፣ በሌላ በኩልም በኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ በስነ ልሳን የ2ኛ ዲግሪ ተማሪ የነበሩት ኣቶ ግርማ መንግስቱ የተዛቡ ሀሳቦችን በማስተካከል ገንቢ ሀሳብ ስለ ሰጡኝ ሁሉንም በጣም ኣመሰግናለሁ።

የቤተሰብ ሀላፊነቷን ከመወጣት በተጨማሪ ላበረከተችልኝ ሞራላዊና ማቴሪያላዊ ድጋፍ ባለቤቴን ፣ ወ/ሮ እታለማሁ ጋረደውን ከልብ ኣመሰግናለሁ። በተጨማሪም በወጡ በገቡ ቁጥር «ኣብዬ ኣሁንም እየጻፍክ ነው?» ካሉኝ በሁዋላ «በርታ እሺ!» የሚለው ኣዎንታዊ ድምጻቸው ላልተለየኝ ልጆቼ ለቤተልሄም ኣበበ እና ለሰላማዊት ኣበበ ምስጋናዬን ኣቀርባለሁ።

የባቱ ኣጠቃላይ 2ኛ ደረጃ የመሰናዶ ት/ቤት ርእሰ መምህር ኣቶ ታምራት ስዩም ስራዬን ስራቸው ኣድርገው ስለተባበሩኝ፣ እንዲሁም መምህራንን፣ ተማሪዎችንና ሰራተኞችን፣ በኣጠቃላይ ሌሎች የተባበሩኝን ሁሉ በጣም ኣመሰግናለሁ። ከቃለ መጠይቅ በሁዋላ በወረቀት ላይ በማሰፍርበት ጊዜ ኣንዳንድ ብልጭ ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የማፈላልገው በተንቀሳቃሽ ስልክ (Mobile Telephone) ነበር። እናም ይህን ቴክኖሎጂ የጠነሰሰውን ኣእምሮ እና ለተገበሩት እጆች ኣድናቆቴና ኣክብሮቴ ከፍተኛ በመሆኑ ፈጣሪዎቹን ኣመሰግናለሁ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ የሰንጠረዣዊ መረጃዎች ዝርዝር

**ኣርእስት** **ገጽ**


**ሰንጠረዥ 1:** በጎባ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ዝርዝር ........ 35

**ሰንጠረዥ 2:** የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ........ 37

**ሰንጠረዥ 3:** በባሌ ዞን፣ በጎባ ወረዳ የገጠርና ከተማ ነዋሪዎች በቆጠራና በግምት የተገኘ የህዝብ ብዛት በጾታ (እ.ኤ.ኣ. 1994) ........ 38

**ሰንጠረዥ 4:** በጎባ ወረዳ በሁለቱም የምርት ወቅቶች የግል ገበሬዎች ግምታዊ የእርሻ ይዞታና ወቅታዊ የሰብል ውጤት ........ 42

# የፎቶግራፍ ዝርዝር ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


ፎቶግራፍ 1:- በተለያዩ መጠኖች የተሰሩ ገበታዎች ከስፌት መክደኛዎቻቸው ጋር:: 56

ፎቶግራፍ 2:- የ«ቡራቶ» ዝግጅትና ገበታ አይለያዩም:: የ«ቡራቶ» ዝግጅት በህብረት 60

ፎቶግራፍ 3:- የገበታ «ቡራቶ» በጡንጦ ከተያዘው የማወራረጃ ወተት ጋር:: 61

ፎቶግራፍ 4:- የቆሪን አገልግሎት በማስተዋወቅ ላይ:: 64

ፎቶግራፍ 5:- በተለያየ ቅርጽና መጠን ከእንጨት የተሰሩ ቆሪዎች:: 65

ፎቶግራፍ 6:- በተለያየ መጠን ከእንጨት የተሰሩ ቁዲዎች:: 70

ፎቶግራፍ 7:- የእንጨትና የቆዳ አኮሌ:: 74

ፎቶግራፍ 8:- በልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ያሸበረቁና የተለያየ መጠን ያላቸው ከእንጨት የተሰሩ ኪላዎች:: 76

ፎቶግራፍ 9:- ቂቤ በኪላ ዘመድ ጥየቃ:: 77

ፎቶግራፍ 10:- የቅልና እንጨት ስራት የሆኑ ባህላዊ የውሃ መያገ እቃዎች:: 78

ፎቶግራፍ 11:- የገንፎ ማገንፊያ ማስሮዎች፣ ማቅረቢያው ቆሪ እና መመገቢያ የቀንድ ማንኪያዎች:: 88

ፎቶግራፍ 12:- የገንፎ ማብሰያና መመገቢያ እቃዎችን በማስተዋወቅ ላይ:: 89

ፎቶ ግራፍ 13:- በተለያየ መጠንና ቅርጽ የተሰሩ ጢሲቴዎችና መክደኞዎቻቸው:: 94

ፎቶግራፍ 14:- የነጠረ ቅቤ ማቅረቢያ ጡዌዎች:: 96

ፎቶግራፍ 15:- የቡና ስርአት ማከናወኛ ልዩ ልዩ ቁሳቁስ:: 101

ፎቶግራፍ 16:- የማማጊያ ወተት የምትይዘዋን ቅል (ቁሉ ኡነታ) በማስተዋወቅ ላይ:: 104

ፎቶግራፍ 17:- -የጀበና አገልግሎት እንዲህ ነው:: 105

ፎቶግራፍ 18:- ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ የቅል ስራት የሆኑ ቁሳቁስ:: 109

ፎቶግራፍ 19:- የስፌት ሙያተኛዋ ወይዘሮ ሌይላ ኢብሮ በመስፋት ላይ1 እያሉ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው:: 118

ፎቶግራፍ 20:- የስፌት ውጤት የሆኑ ልዩ ልዩ መጠን ያላቸው የወተት መያገ ቁሳቁስ:: 121

ፎቶግራፍ 21:- ጡንጦ ይዞ ጭፈራ ለደስታ 125

ፎቶግራፍ 22:- እናት የዳረቻትን ልጅ ለመጠየቅ ወተቷን በጡንጦ እና የሰላም አርማ ሲቄዋን ይዛ በጉዞ ላይ:: 127

ፎቶግራፍ 23፡- ልዩ ልዩ ባህላዊ የስፌት እቃዎች፡፡ 131
ፎቶግራፍ 24-ሀ፡- ሃያ አምስት ኪሎ ይይዛል የሚባለው መለስተኛው የዱቄት መያገር ቡሬ 133
ፎቶግራፍ 24-ለ፡- ሁለት ኩንታል ይይዛል የተባለው ትልቁ የዱቄት መያገር ቡሬ፡፡ 134
ፎቶግራፍ 25፡- በልዩ የአሰራር ጥበብ የሚሰራው ቡሬ 136
ፎቶግራፍ 26፡- የቆዳውን አኮሲ በማስተዋወቅ ላይ 139
ፎቶግራፍ 27፡- ትልቅና ትንሽ አገልግል 141
ፎቶግራፍ 28፡- የቀንድ ስራት የሆኑ ዋንጫዎች 144
ፎቶግራፍ 29፡- የቀንድ ዋንጫዎችን አሰራርና ቅርጽ ሲመለከቱ 146
ፎቶግራፍ 30፡- ስርኣተ አቴቴ በቀንድ ማንኪያና በጢሲቴ 147

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ኣጠቃሎ


የጥናታዊ ጽሁፉ ዋና ኣላማ በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ መመገቢያ ቁሳቁስ ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳን መግለጽ ነው፡፡ ኣላማውን ስኬታማ ለማድረግም ምልከታንና ቃለመጠይቅን የኣጠናን ስልቱ ኣድርጓል፡፡ «ማየት ማመን ነው» እንዲሉ በምልከታ የቁሳቁሶቹን ቅርጽ በፎቶግራፍ ለማስቀረት የተቻለ ሲሆን ኣሰራራቸውን፣ ኣጠቃቀምና ባህላዊ ፋይዳቸውን በተመለከተ ደግሞ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ በዋቢነት ተካቷል፡፡ መረጃውን የተሟላ ለማድረግም ባህላቸው ነውና ግንዛቤው ይኖራቸዋል የተባሉ፣ በኣጋጣሚ፣ በግል እውቂያና በጥቆማ የተገኘ ፣ ከወጣት እስከ ኣዛውንት የእድሜ እርከን ላይ ያሉ የብሄረሰቡ ኣባላትና በባህሉ ውስጥ ኣድገዋል የተባሉ ጥቂት የሌሎች ብሄረሰብ ወገኖች፣ በኣጠቃላይ 28 ግለሰቦች ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡

ከጥናቱ መንስኤዎች ውስጥ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች የታሪካቸው ኣሻራ፣ የማንነታቸው ማሳወቂያ ወዘተ. የሚሆኑ ምን ፣ ምን ኣይነት የመመገቢያ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ? የሚለው ኣንዱ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የብሄረሰቡ ኣባላት የእንስሳት፣ የእጽዋት ተዋጽኦ እና የሸክላ ኣፈር ስሪት የሆኑ ልዩ ልዩ ቁሳቁስን በጥቅም ላይ ሲያውሉ እንደነበርና በኣሁኑም ወቅት በተለይ የስፌት እና የሸክላ እቃዎችን በስፋት እንደሚገለገሉባቸው ታውቋል፡፡ ስለሆነም 28 ቁሳቁሶችን በተናጠል፣ የቡና ስርኣት ማከናወኛና የወተትና የቅቤ መያገ እቃዎችን በመመገቢያነትና በመጠጫነት ከሚሰጡት ጥምር ግልጋሎት ኣኳያ በጥቅሉ ለማየት ተችሏል፡፡

መረጃዎቹ እንደጠቆሙት የእቃዎቹ ቅርጽ ቢለያይም የኣሰራር ጥበባቸውና ኣጠቃቀማቸው ከመመሳሰሉም በላይ ጥንታዊነታቸው እምብዛም ሳይለወጥ እስከዘመናችን ዘልቀዋል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ የኣንዳንድ ቁሳቁስ የውበት ኣጠባበቅ የብሄረሰቡ ኣባላት በተለይም ከሴቶቹ የውበት ኣጠቃቀምና ኣጋጊያጥ ስልት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ተምሳሌትነታቸው ከፍ ያለ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በቁሳቁሶቹ ላይ የሚታቡቱት «ሳምሳዎች» ወይም የጠፍር ጥብጣቦች ከጌጥነታቸውና ማንጠልጠያ በመሆን ከሚሰጡት ጥቅም በላይ በተለይ በሰርግ ወቅት የድንግልናን መኖርና ኣለመኖር በማብሰርና በማርዳት ረገድ በመልእክት ኣስተላላፊነት የሚጫወቱት ሚና ጉልህ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም ሌላ ልዩ ልዩ መመገቢያና መጠጫ ቁሳቁስ (ቆሬ፣ ጮጮ፣ ማለቢያ ወዘተ.) በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በደቦ፣ በእምነትና በመሳሰሉት ስርኣታዊ ክዋኔዎች ወቅት የተለያዩ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳዎችን ከማመልከት ኣልፈው ምሳሌያዊ ኣነጋገሮችንና ዘይቤዎችን ከማጎልበት ኣኳያ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ከምልከታውና ከቃለመጠይቆቹ በተገኘው መረጃ መሰረት ምንም እንኳን ቁሳቁሶቹ ታሪክንና ባህልን የማሳየታቸው ፋይዳ ጉልህ ቢሆንም ኣንዳንድ ቁሳቁስ ቴክኖሎጂ ወለድ በሆኑ ኣገር በቀልና ባህር ተሻጋሪ ዘመነኛ እቃዎች እየተተኩ ከጠቀሜታነት ክልል ወጥተዋል፣ እየወጡም ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ብዙዎች ቁሳቁስ በጎልማሳ የእድሜ እርከን ላይ ባሉት የባህሉ ባለቤቶች ዘንድ እንኳን የተፈለገውን ያህል እንደማይታወቁ የጥናቱ ግኝት ጠቁሟል፡፡ ስለሆነም ዘመነኛው ትውልድ ለጥንታዊው ቁሳዊ ባህል ባይተዋር የመሆኑ ሁኔታ በጉልህ ይታያል፡፡ የእነዚህ ሁሉ ድምር፣ ታሪክን፣ ባህልን ፣ ወግንና በኣጠቃላይም ባህላዊ ትውፊትን ወደ ከርሰ መቃብር እያወረደው እንደሆነ ኣዛውንቶች ጠቁመዋል፡፡

ስለሆነም ጥናታዊ ጽሁፉ በማጠቃለያው፣ የተጠቀሱት ኣሉታዊ እና ኣሳሳቢ ሁኔታዎች እንዲስተካከሉና የብሄረሰቡ ታሪክ በቁሳዊ ባህሉ በኩል ለተከታዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ተተኳሪውን ወረዳ ባገናዘበ መልኩ መወሰድ የሚገባቸውን ኣዎንታዊ እርምጃዎች በመጠቆምና የመፍትሄ ሀሳቦችን በመስጠት ያበቃል፡፡

# 1. መግቢያ




አንድ ጥናት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሀ ፈሳሽ በድንገት የሚመጣ ሳይሆን የመነሻ ምክንያት እና የመድረሻ ግብም ይኖረዋል:: በጥናቱ መመለስ ያለባቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ እና የመጨረሻውን የጥናቱን ግብ በስኬት ለማጠናቀቅ የአጠናን ዘዴውን ይቀይሳል:: በአጠናን ዘዴው ላይ ተመስርቶ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሰረት የሚቀርቡ - የጥናቱ መንስኤ፣ ዋናና ዝርዝር አላማዎች፣ የአጠናን ዘዴውና በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ወሰንና ግብ እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮች የሚሉ ንኡሳን አርእስት በቀዳሚው የጥናቱ ክፍል ተካትተዋል::

## 1.1. የጥናቱ መንስኤ

ቁሳዊ ባህል በአግባቡ ከተያዘ የታሪክ ቅርስ፣ የማንነት መግለጫ ነው:: እውነታው ሚዛን የሚያነሳ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በመጤ ባህልና በህዝቦች የእለት እለት ግንኙነት የአንዱ ባህል በሌላው እየተዋጠ፣ የነበረው እንዳልነበረ በመሆን ላይ ነው:: በሌላ በኩልም የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ሰፊ የባህል ቅርስ፣ ልማድ እና ትውፊታዊ የታሪክ መረጃ ያለው ቢሆንም በስፋት የተጠና አይመስልም:: በወረዳው፣ በስነቃል ላይ የተሰሩ በጣት የሚቆጠሩ ስራዎች ያሉ ሲሆን በቁሳዊ ባህል ላይ ግን የተሰሩ ምንም አይነት ጥናታዊ ጽሁፎች ለዚህ ጥናት አቅራቢ አላጋጠሙትም:: ይህንንም እውነታ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የስነቃል ስብስብ ስራዎችን ዝርዝር (Ethiopian collection catalog ውስጥ)፣ እንዲሁም በባሌ መስተዳድር ዞን እና በጎባ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት በቅርብ በመገኘት ለማረጋገጥ ተችሏል:: ስለሆነም ይህ አሉታዊ ሁኔታ የቆረቆረው የዚህ ጥናት አቅራቢ አንዳንድ ጥያቄዎችን ማንሳቱ አልቀረም:: ከጥያቄዎቹ ውስጥ አንዳንዶቹ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች የታሪካቸው አሻራ፣ የማንነታቸው ማሳወቂያ ወዘተ. የሚሆኑ ምን-ምን የመመገቢያ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ? እንዴትና ከምን ይሰሯቸዋል? የሚሉ ናቸው:: ጥያቄዎቹ አግባብነት ያላቸው በመሆናቸው ተገቢ ምላሽ ይፈልጋሉና ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ለመጻፍ አበይት ምክንያት ሆኑ::

## 1.2. የጥናቱ ዋና ኣላማና ዝርዝር ኣላማዎች

የዚህ ጥናት ቀዳሚ ኣላማ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ መመገቢያ እቃዎች ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ፣ የኣንዳንዶቹንም ታሪካዊና ማህበራዊ ፋይዳ ተንትኖ ማሳወቅ ነው:: ቀጥሎ ደግሞ ዝርዝር ኣላማዎቹን ኣንድ በኣንድ እንመለከታለን::

- የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያና የመጠጫ ቁሳቁስ ኣሰራርና ኣጠቃቀም እንዴት እንደሆነ መግለጽ::
- ባህላዊ የመመገቢያ ቁሳቁስ በቅርስነት ቢቀመጡ የሚያበረክቱትን ጠቀሜታ ማሳወቅ::
- የመመገቢያ ቁሳቁሶቹን የብሄረሰቡ ኣባላት ለምን ኣላማ፣ መቼ እና እንዴት የባህላቸው ማንጸባረቂያ እንደሚያደርጓቸው ማሳወቅ::
- የኣንዳንድ መመገቢያ ቁሳቁስ በተለይም የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ሴቶች የሚሰፏቸው እቃዎች ከቅርጻቸው ኣኳያ ምን ትእምርት እንዳላቸው መግለጽ::
- መመገቢያ ቁሳቁሶቹ ኣኩሪ ቅርሶች ናቸውና እንዴት መጠበቅ እንደሚገባቸው ፍንጭ መስጠት::
- በፎቶግራፍ የተደገፈ ገለጻ ከማድረግ ጎን ለጎን ኣንዳንድ ቁሳቁሶችን በቪዲዮ ቀርጾና መዝግቦ በመሰነድ (Documented በማድረግ) መያዝና ለትውልድ ማስተላለፍ::

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል::

- በጎባ ወረዳ የሚገኙ የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት ባህላዊ የመመገቢያ እቃዎቻቸውን እንዴት እንደሚሰሯቸውና እንደሚጠቀሙባቸው ያሳውቃል:: ምክንያቱም «ወጣቱን የማስተማርና የማሰልጠን ተግባር ኣሮጌው ማህበረሰብ ካቆየልን ቅርስ መነሳት ኣለበት» (ፈቃደ ኣዘዘ፣ 1984፣ 14)::
- የተተኳሪውን ብሄረሰብ ባህላዊ መመገቢያ እቃዎች በጽሁፍ መሰነድ፣ ምስላቸውን በፎቶግራፍ፣ የኣንዳንዶቹንም ኣሰራርና ጠቀሜታ በቪዲዮ ቀርጾ ለተከታዩ ትውልድ የማቆየትና የማስተላለፍ ጠቀሜታ ይኖረዋል::
- ያለው ትውልድም ሆነ ወደፊት የሚመጣው፣ በጥቅም ላይ ሲውሉ ከነበሩትና በማገልገል ላይ ካሉት ልዩ ልዩ የመመገቢያ እቃዎች ያለፈውን ትውልድ ባህል፣ ታሪክ፣ ወግና ልማድ ማወቅ ኣለበት፣ ይህ ደግሞ የሚገኘው በስርኣት ከተቀመጠ ሰነድ ነው፤ ስለሆነም በዚህ ደረጃ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ኣንዳች ፋይዳ ያበረክት ይሆናል::



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

➢ ወደፊት መሰል ርእስ ይዘው ለሚነሱ ተመራማሪዎች እንደ መንደርደሪያ ሊያገለግልም ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.4. የአጠናን ዘዴ

ጥናታዊ ጽሁፉ በአላማው የተቀመጠውን ግብ እንዲመታ የሚከተሉት የአጠናን ዘዴዎች በስራ ላይ ይውላሉ፡፡ ቀዳሚው የአጠናን ስልት የመመገቢያ እቃዎቹን አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ መተንተን ነው፡፡ በዚህም ያውቃሉ፣ ባህሉ ውስጥ ኖረዋል የተባሉ ኣዛውንት እናቶችና ኣባቶች እንዲሁም ወጣቶች ይጠየቃሉ፡፡ ተከታዩ የአጠናን ዘዴ ከቃለ-መጠይቅ የተገኘውን ሀሳብ ከፎቶግራፍ መረጃ ጋር በተቀናጀ መልኩ መተንተን እና የኣንዶንዶቹንም መመገቢያ ቁሳቁስ ኣሰራርና ኣገልግሎት በቪዲዮ መቅረጽ ነው፡፡

የእቃዎቹን ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ለማወቅ የመጀመሪያዎቹ ተተኳሪዎች የወረዳው ኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት ናቸው፡፡ ይህ የሆነው እውነተኛውን ነገር ከምንጩ ለማወቅ ሲባል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባህሉን ያውቃሉ፣ በውስጡ ኖረዋል የሚባሉ የሌሎች ብሄረሰብ ኣባላትም የቃለ-መጠይቁ እድምተኞች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ኣንዳንድ የኣገላለጽ ችግር የሚፈጠርባቸውን ተጠያቂዎች ሀሳብ ከማቃናት ውጭ የእያንዳንዱ ተጠያቂ ግለሰብ ሀሳብ እንዳለ (እንደወረደ) ተቀምጧል፤ እንደወረደ እንዲቀመጥ የሚደረገው የሚሰጧቸው መልሶች እንዳይዛቡ ሲባል ነው፡፡

በጥቅሉ 28 መረጃ ሰጪዎች ተካፋይ ሆነዋል፡፡ ከ28ቱ መረጃ ሰጪዎች 26ቱ የወረዳው ኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል 1 (ኣንድ) ከቅርብ አጎራባች በተለይ ከመና ኣንጌቱ ወረዳ ነዋሪዎች፣ ሌላ ኣንድ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ወለጋ ዞን ነዋሪ የሆነና በኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ ልሳን ተማሪ በቃለ-መጠይቁ ተካፍለዋል፡፡ መረጃ ሰጪዎቹ በጥቆማ፣ በእውቂያ፣ ከሙያቸው ኣንጻር እና በልዩ ልዩ ኣጋጣሚዎች (በገቢያ፣ በሰረግ ቤት፣ በሀዘን ቤት፣ በሀዝብና ሀይማኖታዊ በኣላት፣ በትምህርት ቤት በመንግድ ላይ ወዘተ.) የተገኙ ናቸው፡፡ ቁጥራቸው በ28 የተወሰነውም ኣቅምንና ጊዜን በማገናዘብ ነው፡፡

ምልከታና ቃለመጠይቅ ዋነኞቹ የጥናቱ ማከናወኛ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ምልከታ የተተኳሪዎቹን ቁሳቁስ ቅርጽ፣ ኣይነት፣ የኣሰራር ጥበብ ወዘተ. ለመገምገም የሚያስችል ሲሆን በተጨማሪም ቁመትና ወርዳቸውን፣ በጥቅሉ መጠናቸውን ለመለካት እድል ይሰጣል፡፡ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ደግሞ እቃዎቹ እንዴት እንደሚሰሩ፣ ኣገልግሎት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ምን-ምን ጊዜ ሊተገበር እንደሚችል ለማወቅ ያስችላል፡፡ ከዚህም ጋር «ገላጭ የምርምር ዘዴ»ም (Descriptive Research Method) በጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ምክንያቱም ገላጭ የምርምር ዘዴን በተመለከተ፣ ቤስት (1981፣ 25)

የጸሩትን ኣለም እሸቱ (1994፣ 148) እንደጠቀሱት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ በመፈለግ ረገድ ትልቅ እገዛ ከማድረጉም በላይ ገለጻን፣ ትንታኔንና ኣተረጓጎምን መሰረት የሚያደርግ ነው፡፡ በተጨማሪም ምን፣ ምንድነው? እያለ ለማብራራት የሚሞክርም ነው፡፡

## 1.5. በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች

ጥናታዊ ጽሁፉ ለተከታዮቹ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

- በጎባ ወረዳ ያሉ የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት የሚገለገሉባቸው ልዩ ልዩ መመገቢያ እቃዎች ምን-ምን ናቸው?
- የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎቻቸው በተለይ መመገቢያና መጠጫዎቻቸው ከምን-ከምን እና እንዴት ይሰራሉ?
- ባህላዊ መመገቢያ ቁሳቁሶቻቸው የብሄረሰቡን ታሪክ፣ ልማድ፣ ወግ፣ በኣጠቃላይም ባህልን የመግለጽ ፋይዳቸውና፣ በቅርስነት የማገልገላቸው ሁኔታ እንዴት ይታያል? ምንስ ይመስላል?
- ከውጭ በሚመጣ ባህል ምክንያት፣ በህዝቦችም የተቀራረበ ኑሮ ሳቢያ የኣንዱ ባህል በሌላው እየተዋጠ ነባር የባህል መገለጫዎች ከመስመር እየወጡ፣ የብሄረሰቦች ባህል ብሎም ታሪካቸው በየዘመኑ ሳይቀረስ እየተለዋወጠ ነውና ቅርስን ለመጠበቅ ምን ኣይነት መፍትሄ ሊኖር ይገባል?
- ኣንዳንዶቹ መመገቢያ ቁሳቁስ ትእምርታዊ ፋይዳን እና የብሄረሰቡን ባህል ኣንጥሮ ለማሳየት እንዴት ያገለግላሉ?
- የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ከቁሳዊ ባህሉ ያመነጨውን ባህላዊ ፋይዳ ኣመላካች ቁሳቁስ በምን-በምን ወቅት እና እንዴት ያንጸባርቅበታል?

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጽሁፍ ከኣራቱ የፎክሎር ዘርፎች ማለትም ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል በተለይ በቁሳዊ ባህል ላይ ከእሱም ውስጥ የተወሰኑ ኣይነቶችን (Genres) ብቻ ወስዶ በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰቦች ተተኳሪነት ኣንድ መጠነኛ ጥናታዊ ጽሁፍ ለማቅረብ የሚሞክር ነው፡፡

ፎክሎር እጅግ በጣም ሰፊ ይዘት ያለው የጥናት መስክ በመሆኑ የሚያካትታቸው ኣራቱ ዘርፎች እያንዳንዳቸው እንኳን ቢታዩ በብዙ ኣይነት (Genres) የሚከፋፈሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ታዲያ፣ ለብቻቸው ድንበር ከልለው የተቀመጡ ሳይሆን ኣንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ ቁርኝት ኣላቸው፤ ኣንዱ ሲጠራ ሌላውም ብቅ ይላል፡፡ «በመሀከላቸው ግንኙነት፣ መስተጋብር እና ተደጋግፎ ያላቸው ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም» (ፈቃደ ኣዘዘ 1991፣ 15)፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ይህ ሀቅ እንዳለ ሆኖ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦችን የመመገቢያ እቃዎቻቸውን አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ የአንዳንዶቹንም ታሪካዊና ማህበራዊ ፋይዳን ይመለከታል፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ የመመገቢያ እቃዎቻቸው ተብሎ የተጠቀሰው የብሄረሰቡ አባላት በቀጥታ ምግቦቻቸውንና የሚጠጡትን ፈሳሽ አቅርበው የሚመገቡባቸውንና የሚጠጡባቸውን ለማለት ነው፡፡ ባህላዊ ፋይዳ ሲባልም ቁሳቁሶቹ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለምሳሌ በሰርግ፣ በሀዘን፣ በደቦ ስራ፣ በእምነትና በመሳሰሉት ስርአታዊ ክዋኔዎች ላይ የብሄረሰቡ አባላት ባህላቸውን በሚያንጸባርቅ መልኩ እንዴት እንደሚገለገሉባቸው ለመግለጽ ነው፡፡ ከጊዜ እጥረትና ከአቅም ውስንነት የተነሳ ሌሎች ወረዳዎች በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ በዚህም ወረዳ ቢሆን በዋናነት የሚተኮርባቸው መመገቢያ እቃዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የቅቤና የወተት መያዣ ቁሳቁስ የብሄረሰቡ አባላት ስለሚመገቡባቸውና ስለሚጠጡባቸው የዚህ ጥናት አካል ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም ሌላ የቡናን ስርአታዊ ክዋኔ የሚያመለክቱ ባህላዊ ቁሶች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ምክንያቱም የቡናው መጠጫ ሲነሳ ጀበናው መጠቀሱ አይቀርምና ነው፤ በሌላ በኩል እንደዱቄትና ጥራጥሬ መያዣ የሆኑ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ ምንም እንኳን በቀጥታ ለምግብ ማቅረቢያነት ባይውሉም በተዘዋዋሪም ቢሆን ከምግብ ጋር ግንኙነት ስላላቸው በዚህ ጥናት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ግብ

ቁሳዊ ባህል በእጅጉ መጠናት ያለበት የፎክሎር አንድ ዘርፍ ነው፤ ምክንያቱም የአንድን ህዝብ ባህል፣ ወግና ታሪክ በቁሳዊ ባህሉ በኩል መፈለግና ማግኘት ይቻላልና፡፡ በተለይ ደግሞ የጽሁፍ ቅርስ የሌላቸው ወይም የጠፋባቸው ህዝቦች ያለፈ ታሪካቸውን ለመመርመር ግንባር ቀደም ሚና ከሚጫወቱት ከትውፊት፣ ከአፈታሪክ፣ ከተረትና ከመሳሰሉት ጋር በተጓዳኝ መታየት ያለበት ቁሳዊ ባህል ነው፡፡ «ቁሳዊ ባህል ህዝቦች በጥበብና በቴክኖሎጂ አማካኝነት ያገኟቸውን ተጨባጭና ትርጉም ያላቸውን ቁሶች ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና ነው፡፡» (http://www.elearn.arizonaedu/sfair).

ቁሳዊ ባህል ከዘመነኛው ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮና ከዚያም በሁዋላ የሰው ልጅ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል በጥረቱ ያስገኘው፣ ተመልሶም ያንኑ ሰብአዊ ፍጡር የሚያገለግል ማንነትን፣ ምንነትን የሚገልጽ ተጨባጭ ቅርስ ነው፡፡ ፈቃደ አዘዘ በዚህ ጉዳይ ላይ ተከታዩን ብለዋል፡፡

> *ቁሳዊ ባህል በአይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ. አሰራርን፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሳሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው (1991፣ 15)፡፡*

አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ የመነሻ አላማ እንዳለው ሁሉ የመድረሻ ግብም ይኖረዋል:: በዚሁም መሰረት የመመገቢያ እቃዎቹ ከሚሰጡት አገልግሎትና ትእምርታዊ ፋይዳ በመነሳት የጎባ ወረዳን ኦሮሞ ብሄረሰብ ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህልና ልማድ በበለጠ የሚገልጹበት ሁኔታ እንዲመቻችና አሰራራቸውና አገልግሎታቸው ይበልጥ ዳብሮ እንዲታይ የብሄረሰቡ አባላት በላቀ ደረጃ የሚነሳሱበትን ሁኔታ መጠቆም ሌላው የጥናቱ ግብ ነው::

## 1.8. ያጋጠሙ ችግሮች

የመስክ ላይ ጥናት ኣያሌ እንቅፋቶች የሚታዩበት መሆኑ በብዙ ተመራማሪዎች ሲነገር የቆየ ሀቅ ነው:: የመረጃ ሰጪዎች ቀጠሮ ኣለማክበር እና በዚህ ሳቢያ የሚከሰቱ ሌሎች ተዛማጅ እንቅፋቶች (የጊዜ፣ የገንዘብ ክስረት ወዘተ.) ተጠቃሽ ናቸው:: በተጨማሪም የኣንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ጠርቀም ያሉ ጥቅማጥቅሞችን መሻት፣ በቪዲዮም ሆነ በፎቶግራፍ ለመቀረጽ ፈቃደኛ ኣለመሆን፣ ለቃለመጠይቁም ቢሆን ኣፍ ከልብ ሆኖ ኣለመገኘት፣ ኣጥኚው ከፍተኛ ግምት ለሚሰጣቸው ጉዳዮች ከኣንዳንድ ሰዎች የሚሰጠው ምላሽ ዝቅተኛ መሆን እና የመሳሰሉ ችግሮች በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የእለት እለት ገጠመኞች በመሆናቸው እኔንም ተፈታትነውኛል:: ይሁንና የተጠቀሱት ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው ሀምሌ 1 እና 5 ቀናት 1999 ኣ.ም ከሰኣት በሁዋላ ያጋጠሙኝና ለኪሳራ የዳረጉኝ ችግሮች ግን በኣይነታቸው ለየት ስለሚሉ እጠቅሳቸዋለሁ::

እሁድ ሀምሌ 1 ቀን 1999 ኣ.ም የከሰኣት በሁዋላ ቀጠሮዬ ወደ ኣንዲት የኣቴቴን ስርኣታዊ ክዋኔ ልታከናውንልኝ (ልታስተናግድልኝ) ወደምትችል የኦሮሞ ሴት የሚወስደኝ ነበር:: ቀደም ሲል በተነጋገርነው መሰረት «በቪዲዮ እና በቴጵ እንዳታነሳኝ» ብላኛለችና የፎቶግራፍ ካሜራዬንና የግል ማስታወሻዬን ብቻ ይዤ ነበር የተገኘሁት:: ለክዋኔው ኣስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ኣስቀድሞ መዘጋጀት እንዳለባቸውም ተማምነን ለጠጅ ሳር፣ ጤና ኣዳም፣ ኮሰረት፣ የቀጤማ ጉዝጓዝ፣ ስንደል፣ እጣን፣ የቅንጨ እህል፣ ወተት፣ ቡና፣ ቅቤ፣ ቅመማ ቅመሞችና የመሳሰሉትን ገዝታ እንድታዘጋጅ ብር 100 ሰጥቻታለሁ:: በሌላ በኩል ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ጨሌዎች እንዲሁም ኣልባሳት እኔ ፈልጌ ማዘጋጀት እንዳለብኝ ተነግሮኛል:: ከኣልባሳቱ ውስጥ ከወገብ በላይ የሚለበሰው «የኣቴቴ ጥብቆ» በኦሮሞዎች ኣጠራር «ቆሎ» እና የራስ መሸፈኛ ሻሽ «ጉፍታ» ቢኖሯትም ጨሌዎቿን ግን ልጇ በብር 35 የሸጠባት መሆኑን ስለነገረችኝ ነበር የመፈለጉ ኣደራ በእኔ ላይ የወደቀው:: ስለሆነም እሁድ ከሰኣት በፊት ተፈላጊዎቹን ቁሳቁሶች ባስረከብኳት ወቅት ዝግጅቷን ማጠናቀቋንም ለማረጋገጥ ችያለሁ::

ከሰኣት በሁዋላ ብቻዬንም ከምሄድ፣ የሴት ስራ በይበልጥ በሴት ተጓዳኝነት ይሰምራል ብዬ በማሰብ፣ ቀደም ሲልም ስለሚተዋወቁ ከባለቤቴ ጋር ነበር በ8 ሰኣት የደረስነው:: ከፊል የቤቱን ወለል የሞላው ጉዝጓዝ ኣሮጌውን ቤት ኣድምቆታል፣ በረከቦቱ ላይ የጠጅ

ሳር እና የሳር ጉዝጓዝ ተነስንሶበት ስኒዎች በስርኣት ተደርድረዋል፣ ቅንጨሙ ተቀንጭቶ ሳር በተጎዘጎዘበት ማቶት ላይ በእግራም ሳህን ተሰይሟል። በፋመው ከሰል ላይ የተጣደው ጀበና የመፍላቱን ብስራት በኣፉና በጡቱ በሚያትጎለጉለው እንፋሎት ያበስራል። በኣጠቃላይ ኣብዛኛው ጉዳይ ስርኣት የያዘ ቢሆንም ያለመጫሚያ ያለችው፣ የኣቴቴውን ስርኣታዊ ልብስ የለበሰችውና ጨሌዎቿን በኣንገቷ ያጠለቀችው ወይዘሮ የሺ ግን በግንባሯ ተደፍታለች። በግንባሯ መሬት ትያዝ እንጂ ስትቆጣ ወይም ለጸብ ስትዘጋጅ ትከሻዋን እንደምታሳብጥ ድመት መቀመጫዋን ኣሳብጣ የምትታየው የቤቱ ባለቤት የምትሰግድ መስላ ብትታይም በፊቷ ላይ የሚነበበው የጭንቀትና የመከሳተር ስሜት ኣንዳች ጥርጣሬ ኣጫረብኝ። ምን ኣጋጠማት ይሆን?

በቤቱ ውስጥ ሁለት ሴቶች ቁጭ ብለው በዝምታ ያስተውሏታል። ከሁለቱ ሴቶች ጎን በቅርብ ርቀት ኣገጫቸውን ሸበቶ ጸጉር ያለበሰው ኣዛውንት የተቀዳላቸውን የመለኪያ ኣረቄ ትካዜ ባጠላበት ስሜት እያዩ ቁጭ ብለዋል። ሁሉም ጸጥ፣ ረጭ ባሉበት ሰኣት ኣዛውንቱ በግንባሯ ወደ ተደፋችው የሺ ቀና በማለት «የመጣሁት ላጫውትሽ ነበር ግን ይኸው ታመሻል እንግዴህ ልሂድ» ካሉ በሁዋላ ኣረቄያቸውን ፉት ኣሉለት።

ለመሆኑ ምን ሆና ነው? ኣልኳቸው። የኣዛውንቱ መልስ «የደም ግፊቷ ተነስቶባት ነው» የሚል ነበር። ሁለቱ ሴቶች ብቻ በከንፈር መጠጣ የታጀበ ጉርምርምታ ከማሰማት ውጭ ምንም ኣይናገሩም። ወይዘሮ የሺ ተረፈ የምታሳድጋት የ10 ኣመት ሴት ልጅ ግን ኣይኖቿ በኣሳዳጊ እናቷ ላይ እንደተተከሉ ናቸው። ባለቤቴም ግራ ተጋብታ የራሷን ቁዘማ ይዛለች። ብዙ የተደከመበት ጉዳይ እንደዋዛ መበላሸቱ ውስጥ ውስጡን ቢያሳስበኝም ወደ ሀኪም ዘንድ እንውሰዳት የሚል ሀሳብ ሰነዘርኩ።

ከሴቶቹ ኣንዷ «የለም ለዚህ ሀኪም ሳይሆን መድሀኒቱ መለማመን ነው» በማለቷ ጥርጣሬዬ «የደም ግፊቷ ተነስቶባት ነው» ከሚለው «የቤት ጸብ ነው» ወደሚለው መራኝ። ወዲያው ሴቶቹ ወደ ረከቦቱ እና ወደ እርሷ ቀረብ ብለው «ኣቴቴ ግምቢ፣ ኣቴቴ ዱላ እባክሽ ታረቂያት እባክሽ ተለመኛት» ማለት ሲጀምሩ እኔም ከእነሱ የሰማሁትን መልሼ እያስተጋባሁ «እባክሽ ታረቂያት፣ እባክሽ ተለመኛት፣ እባክሽ የዛሬን ይቅር በያት» ማለት ጀመርኩ። በመካከሉ ሽማግሌው የቀረቻቸውን ኣረቄ ኣንጠፍጥፈው ሄዱ። የሴቶቹም ሆነ የእኔ ልመና ወይዘሮ የሺን ከተደፋችበት ኣላቃናትም። ሴቶቹ የተመካከሩ ይመስል በኣንድነት «ኣንዳንድ ኣቴቴ ወንድ ኣትወድምና እስቲ ወጣ ብለህ ተዘዋወር» ኣሉኝ። ትእዛዛቸውንም ተቀብዬ ወጣሁ። ከ15 ደቂቃ በሁዋላ በህጻኗ ልጅ ተጠርቼ ስገባ ወ/ሮ የሺ ተረፈ ተነስታ በረከቦቱ ኣጠገብ እግሮቿን ዘርግታና የቅንጨውን ሳህን በጭኗ ላይ ኣድርጋ ሁሉም ነገር ሰክኖ በማየቴ ተገረምኩ። ኣሁን እሷ «ጎንደሮ ሲፋ» ስትል ሴቶቹም «እልልል! - እልልል!» ሲሉ ነገሩ ስርኣት የያዘ መሰለ። ይሁን እንጂ በእኔ ውስጥ ጥያቄ እንደተወ ነበርና በሁዋላ ከባለቤቴ እንደተነገረኝ በሽታዋ የደም ግፊት ሳይሆን ለብዙ ጊዜ ኣቴቴ ባለማድረጓ የተነሳ ከኣቴቴዋ የተሰነዘረባት ጸብ ነበር።



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ምንም እንኳን የተወሰነ የጊዜ ኪሳራ ቢያጋጥመኝምና የሺ በተዳከመ ስሜት ላይ ብትሆንም መክኖ የነበረው ፕሮግራም ነፍስ ዘርቶ እኔም ፎቶግራፉን ለማንሳት በቃሁ፡፡ በዚህ አይነት የእኔም ተሳትፎ የታከለበት የአቴቴ ስርአታዊ ክዋኔ በዚህ መልኩ ተጠናቀቀ፡፡ የተከሰተው ሁኔታ ግን ሌላ ራሱን የቻለ ጥናት ቢያስፈልገውም ከዚህ ጥናት አላማ ውጭ በመሆኑ በዚሁ ላብቃና ወደ ሀምሌ 5ቱ ውሎ ላምራ፡፡

የሀምሌ 5 ቀን 1999 ኢ.ም ቀጠሮዬ ወደ ፋሲል ሰራ የገበሬዎች መንደር የወሰደኝ ሲሆን በተለይ ደግሞ ጥናቱ በሸክላ ሰሪዎች ዙሪያ የሚከናወን ነው፡፡ ፕሮግራሙን የያዝኩት ከቁሳዊ ባህል አንዱ የሆነውን የሸክላ ቁሳቁስ አሰራር በቪዲዮ ለመቅረጽ ነበር፡፡ የቀጠሮውንም ቀን የመረጡትና ከሰአት በሁዋላ እንዲሆን የወሰኑት ከሸክላ ሰሪዎቹ አንዱ የሆኑት አቶ በቀለ ገባቦ ነበሩ፡፡ በዚሁ መሰረት ብር 200 ልከፍለው የተዋዋልኩትን ወጣት ቪዲዮ ቀራጭ ይገሩ የ5 ኪ.ሜ. የገ-ዞ ርቀቱን በእግር ተያያዝነው፡፡ ወቅቱ ክረምት ስለነበርና መኪናም ሆነ ጋሪ የማይጓዝበት በመሆኑ የጭቃውና የመንገዱ ርቀት የፈጠሩት ተጽእኖ የቪዲዮ ቀራጩን እረፍት የሚነሳ ጭቅጭቅ ቢያስነሳብኝም ጉዟችን ቀጥሏል፡፡ በሸክላ ሰሪዎቹ ሰፈር ስንደርስ ግን የቀጠሩኝ ግለሰብ አልነበሩም፡፡ የሄድኩበት አላማና የወጣው ገንዘብ በከንቱ መቅረት ስለሌለበት ሌላ ሸክላ ሰሪ በአይናችን ስናማትር በርቀት የእሳት ጭስ በማየታችን ወደዚያው አመራን፡፡ ወይዘሮ ብዙነሽ ገነሞ በአብዛኛው የሸክላ ምጣዶች ያሉባቸውን ድስቶች እና ማሰሮዎች በእሳት እያበሰሉ ነበር፡፡ የመጣንበትንና ያጋጠመንን ሁኔታ ስገልጽላቸው አንገታቸውን ደፋ አድርገው «አይሄ! ዛሬ እኮ ሀምሌ 5 የአመቱ አቦ ናቸው በዚህ ጊዜ ሁሉም ወደ ጠበል ጥሪ ይሄዳል እንጂ መቼ ይቀመጣል፤ መቼም እናንት የከተማ ሰዎች እንዲህ አይነቱን ነገር ከጉዳይም አትጥፉት፣ እንግዲያስ በዛሬው ቀን ቀጠሮ ይያዛል?» በማለት በጥያቄ አይን አዩን፡፡

ከወይዘሮ ብዙነሽ ገነሞ ጋር ሀሳብ እያንሸራሸርን ባለንበት ሰአት አንዲት ሴት በድንገት መጥታ ባጠገቧ ያገኘችውን ምጣድ በራሷ ላይ በማድረግ «እኔንም ፎቶ አንሳኝ» አለችው ቪዲዮ ቀራጩን፡፡ ሴትየዋ በስካር መንፈስ ውስጥ ስለነበረች ለማስመሰል ያህል እንደተቀረጸች (ፎቶ እንደተነሳች) ብንነግራትም በዚህ አልበቃ ብሏት አንድ ጊዜ ማሰሮዎችን በዙሪያዋ እየደረደረች፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የአካባቢውን ህጻናት እየጠራች «ፎቶ አንሱኝ» ማለቷን በመቀጠሏ፣ ይልቁንም ሁኔታዋን እያዩ በሚያውካኩ ህጻናት አካባቢው በመረበሹ ስራችንን መግታት ግድ ሆነብን፡፡ ከሴትየዋ ለመገላገል ያህል ወደ መንደሩ ሌላ አቅጣጫ አመራን፡፡ ህጻናቱ ከሁዋላ ከሁዋላችን መከተላቸውን ባያቆሙም ሰካራሟን ሴትዮ ግን ተገላግለናት ነበር፡፡

በደረስንበት የመንደሩ አንድ ክፍል ደቅቆ በአንድ ቦታ የተከመረ የሸክላ አፈር አየንና ትኩረታችንን ሳበው፡፡ በአፈሩ አቅራቢያ አንዲት ወጣት ከኮረት ያጣራችውን ደቃቅ አፈር እያቦካች በተነጠፈ ጨርቅ ላይ የሸክላ ምጣድ ቅርጽ ባቦካችው ጭቃ ትሰራለች፡፡ ገና ለመቅረጽ በመዘጋጀት ላይ እንዳለን ከወደ ደቡብ አቅጣጫ አንድ ሰው መጥቶ በአፈሩ


ኣቅራቢያ የተቀመጠች ህጻን ኣንስቶ በተከመረው ኣፈር ላይ ኣስቀመጣት። ህጻኗ በተወጣጡ ቁርጥራጭ ጨርቆች ተጣጥፎ የተሰፋ ጥብቆ ከወገቧ በላይ ከመልበሷ በስተቀር የተቀረው የሰውነቷ ክፍል ኣልተሸፈነም። ሰውየው ኣላማው ምን እንደሆነ ለጊዜው ባይገባንም በተሰባበሩ ቃላት «የማህበሩ ኣባል ነችና ፎቶ ኣንሷት፣ መንግስትም ይወቅ» በማለት ይናገራል። ግለሰቡ ይህን ሁሉ የሚያደርገው በስካር ስሜት ውስጥ መሆኑን ሲራመድ በመንገዳገዱና ሲናገርም ቅጥ የለሽ በመሆኑ ማወቅ ይቻላል። ኣላማችንና የመጣንበትንም ምክንያት ለማስረዳት ያደረግነው ጥረት ካለመሳካቱም በላይ በሰውየው ድርጊት የተነሳ በዙሪያችን ያሉት ህጻናት የሚያሳዩት ማውካካት ተዳምሮ መልካሙን ድባብ ስላጠፋብን ለሁለተኛ ጊዜ ቦታውን ለመልቀቅ ተገደናል።

ስካር የውስጥ ገበናን ማሳየት ብቻ ሳይሆን የራስንም ፍላጎት ያንጸባርቃልና ኣላማችንን ባልተረዱ እና በዚያ ቅጽበት ሊገነዘቡልን ባልቻሉ ሰካራሞች እንዲሁም ቀደም ሲል የተሰጠኝ ቀጠሮ ባለመከበሩ የተነሳ የጊዜ እና የገንዘብ ኪሳራ ተቀብዬ ለመመለስ የበቃሁበት ሀምሌ 5 ቀን 1999 ኣ.ም ምንም እንኳን ቀደም ሲል በትምህርት ቆይታዬ ወደመስክ ሄዶ ጥናትና ምርምር ለማድረግ ምን ኣይነት ቀንና ሰኣት መምረጥ እንዳለብኝ የተገነዘብኩ ቢሆንም ሽክላ ሰሪው ኣቶ በቀለ ገባቦ ስለቀጠሩኝና ምርጫውም የእሳቸው ስለነበር ደፍሬ መጋፋቱን ከነበረኝ ጉጉት ኣኳያ ኣላጤንኩትም። ስለሆነም ያልተጠበቀው ተከሰተ። ይሁንና ይህ መጥፎ ኣጋጣሚ ለእንዲህ ኣይነቱ የመስክ ጥናት ምን ኣይነት ቀንና ሰኣት መምረጥ እንዳለብኝ ተጨማሪ ትምህርት ሰጥቶኝ ኣልፏል።

በኣጠቃላይ በክፍል ኣንድ ከጥናታዊ ጽሁፉ ኣጠቃላይ መግለጫ በመነሳት ጥናቱን ለማካሄድ ለምን ኣስፈላጊ እንደሆነ ተዘርዝሯል። በዚህም መሰረት ኣላማው፣ ሰበበ ጥናቱ፣ የሚሰጠው ጠቀሜታና የኣጠናን ዘዴውን ለማየት ተችሏል። ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ በጥናቱ ሂደትና መጨረሻ ላይ ምን-ምን ጥያቄዎች መመለስ እንዳለባቸው፣ የጥናቱ ወሰን እስከ ምን ድረስ እንደሆነ፣ የጥናቱስ የመጨረሻ ግብ ምን መሆን እንዳለበትና ያጋጠሙ ችግሮች ተጠቅሰዋል። ጥናቱ ከየት ተነስቶ በምን በኩል ተጉዞ የሚደርስበትን ግብ የጠቆመውን ምእራፍ ኣንድ በዚህ ካካተትን፣ በማስከተል የተዛማጅ ጽሁፎችን ቅኝት ወደሚመለከተው ምእራፍ ሁለት እናልፋለን።

## 2. ትውራዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ

በዚህ ምእራፍ ከዚህ በታች በአራት ማእዘናት ውስጥ የተዘረዘሩትን አንድ በአንድ አቀርባለሁ፡፡




ይህ ሁለተኛው የጥናታዊ ጽሁፉ ምእራፍ «ትውራዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ» የሚል ርእስ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ የብሄረሰቦችን ታሪክ ከመሰረቱ ለማወቅ የተጻፈን ታሪክ ብቻ ማንበብ በቂ በማይሆንበት ጊዜ የህዝቡን ትውፊት እና ቅርሶቹን ማየትና መፈተሽ ሊታለፍ የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የጥናታዊ ጽሁፉ ሁለተኛው ምእራፍ ስለ ቅርስና ትውፊታዊ ፋይዳ «ትውራዊ ዳራ» በሚል ርእስ የተካተተ ሀሳብ በማቅረብ መጠነኛ ግንዛቤ ካስጨበጠ በሁዋላ፣ ጥናቱ በቁሳዊ ባህል ላይ የሚያተኩር በመሆኑና ቁሳዊ ባህል ደግሞ የባህል አንድ አካል ስለሆነ ከምንጩ ለመቅዳት ሲባል በተከታዩ የጽሁፉ ክፍል «ባህል ምንድነው?» በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍ ይነበባል፡፡ በማስከተልም ራሳቸውን የቻሉ፣ ግን ደግሞ አንዱ የአንዱ መሰረትና አንዱ የሌላው አጎላማሽ በሆኑት ቁሳዊ እና መንፈሳዊ የባህል ክፍሎች ላይ ስለአንድነታቸውና ልዩነታቸው መጠነኛ ሀሳብ ያስተላልፋል፡፡

ቁሳዊ እና መንፈሳዊ የባህል ክፍሎች የህዝቦች የዘመናት ያልተቋረጠ ፍላጎትና የስራ ውጤት ያስገኛቸው ቅርሶች ናቸው፡፡ ቅርሶች ደግሞ ታሪክን ለመመርመርና

ስለማንኛውም ህዝብ ኣንድ ኣይነት መረጃ ለመስጠት የሚጫወቱት ሚና ቀላል ኣይደለም። ስለሆነም «ቅርስ እና የቅርስ ኣስፈላጊነት» የሚለው ጽሁፍም የጥናቱ ሌላው ኣካል ነው። በማከልም «በጎባ ወረዳ የቅርሶች ኣጠባበቅና ይዞታ» በሚል ርእስ እየታዩ ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለመቃኘት የሞከረ ምጥን ጽሁፍ ቀርቧል። በተከታይነት የመመገቢያ ቁሳቁስ ከፎክሎር ጋር ያላቸውን ተዛምዶ የሚያስቃኘን «ፎክሎርና የመመገቢያ ቁሳቁስ» የሚል ርእስ ይነበባል። በመቀጠልም «ፎክሎርና ትእምርታዊ ፋይዳው» እና «የመመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ ከጥንት እስከዛሬ» የሚሉ ኣርእስት በዚህ ክፍል የሚቀርቡ ናቸው። እያንዳንዱ ርእስ እጅግ ሰፊ የሆኑ ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘ ይሁን እንጂ በዚህ ጽሁፍ የሚቀርበው ግን በተመጠን መልኩ ነው። በመጨረሻም ከዚህ ስራ ጋር ቅርበት ይኖራቸዋል የተባሉ ሶስት ኣገራዊ ጥናቶች ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ይመረመራል።

## 2.1. ትውራዊ ዳራ

የኣንድን ብሄረሰብ ማንነት ለማወቅ፣ ባህልና ወጉን፣ ታሪኩንና ልማዱን ለመተንተን ወደ ሁዋላ መለስ ብሎ የታሪክ ድርሳናትን ማገላበጥ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ጥፋት ወይም የጽሁፍ ቅርስ ሳይኖር ይቀርና ወይም ይታጣና ታሪኩን በውል ለማወቅ የሚደረገውን ጥረት ያደበዝዘዋል። በዚህ ጊዜ ታዲያ ሌሎች ኣማራጮች መፈለግ የግድ ነው። ከብዙዎች ኣማራጮች ኣንዱ ደግሞ ህዝባዊ ትውፊትን መመርመር፣ ቁሳዊ ቅርሶችን መመልከት ሊሆን ይችላል።

> *«..... ከጽሁፍና ከትውፊት ማስረጃዎች ሌላ ጥንታዊ ገንዘቦችና የህንጻ ፍርስራሾች፣ በጥርብ ድንጋይ የተቀረጹ ጽሁፎች፣ ኣጽሞች፣ የሸክላ ስብርባሪዎች፣ የስነጥበብ ውጤቶችና የስነልሳን ማስረጃዎች የታሪክ ምንጭ ናቸው» (ኦ.ባ.ቱ.ኮ.[1] 1996፣ 6)።*

ትውፊትን በተመለከተ የሰው ልጅ «የትመጣውን (his origin) የተመለከተበት፣ ነገውን ያውጠነጠነበት፣ ዛሬውን ያተኮረበት፣ እውነትና ሀሰትን የመረመረበት፣ የብዙ ዘመን እውቀትና ልምዱን ያመቀበት ኣንደኛው የቅርሱ ምንጭ ትውፊት ነው።» የሚሉት ፈቃደ ኣዘዘ ትውፊት፣ ታሪክንና ባህልን ወዘተ. ጠቃሚ መሆኑን በኣጽንኦት ሲገልጹም፣

> *የኣንድ ነገድ፣ ብሄረሰብ ወይም ብሄር ህዝብ ሀይማኖት ምንድነው? ምንድንስ ነበር? ፍልስፍናው ምንድነው? ታሪኩስ? ማህበረሰባዊ ድርጅቶቹ ምን ይመስላሉ? ማህበረሰባዊ ህይወትን የሚመሩና ስርኣት የሚያስይዙ እሴቶች ምን ምን ነበሩ? ምን ምን ናቸው? የሚሉትንና እነርሱን መሰል ጥያቄዎች ለመመለስ፣ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኣገሮች ባብዛኛው ፊታችንን የምንመልሰው ወደ ትውፊት ነው (1986፣ 5) በማለት ኣስምረውበታል።*

[1] ኦ.ባ.ቱ.ኮ፡- ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን

ሰዎች ሲገለገሉባቸው የቆዩ ነባር ቁሳቁስ፣ የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች፣ ታሪካቸውን ለመመርመር፣ ማንነታቸውን ለማወቅ ብሎም በዚያ ላይ ተመስርቶ የባህል እቃዎቻቸውንና አልባሳቶቻቸውን ምንነት ለመገመትና ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት አንድ እርምጃ ወደፊት ያራምዳሉ:: በላይነህ አሰጉ በመስከረም የርእዮተ አለም መጽሄት «ስለ ቅርሳ ቅርስ አንዳንድ ነጥቦች» በሚለው መጣጥፋቸው «የጥንት ሰዎችን ኣኗኗር፣ ተግባር፣ እምነት፣ እውቀትና ስልጣኔ በተጨባጭ የምናውቀው ትተውት ባለፉት ቅርስ ኣማካኝነት ነው» (1981፣ 7) በማለት የገለጹት ከዚሁ እውነታ በመነሳት ይመስላል::

የየትኛውም ትውልድ የታሪክ መሰረት ያለፈው ትውልድ ያቆየው ቁሳዊ ባህልና ቅርስ ነው:: ቅርሶቹ በከርሰ ምድር ይሁኑ በመሬት ላይ፣ በየብስ ላይም ይሁኑ በውሀ ውስጥ፣ ተንቀሳቃሽም ይሁኑ የማይንቀሳቀሱ፣ ሁሉም ስለኣለፈው ትውልድ የሚጠቁሙት ኣንድ ነገር (ታሪክ፣ ባህል፣ ወግ፣ ወዘተ.) ይኖራቸዋል:: ቁሳዊ ባህሎች በእቃነታቸው ብቻ የሚታዩ ሳይሆኑ ከእነሱ ጋር ኣፈታሪኮች፣ ግጥሞች፣ ሚቶች፣ ተረቶችና የዘር ኣመጣጥ ታሪኮችና የመሳሰሉት ሁሉ ኣሉ:: «ብሄራዊ ቅርስ በእርግጥ ቁሳዊ ነገሮችን ብቻ የያዘ ሳይሆን በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ትውፊትን ፣ ሚቶችን፣ ኣፈታሪኮችን፣ ግጥሞችንና የዘር ኣመጣጥ ታሪኮችን ጭምር ይዟል» ሆናስኪ ኤስ (Chojnacki. S.) (1971፣ 9):: ይህንኑ ሀሳብ ለማጠናከር ሆናስኪ ኤስ (Chojnacki. S.) በምሳሌ የጠቀሱትን ማቅረቡ ለመረዳት ቀላል ይሆናል::

> *... በተመሳሳይ በሺህ የሚቆጠሩ የፍቅር ታሪኮችን ያነበበ ሰው ከኣንዳቸውም ጋር ተሞክሮ እስከሌለው ድረስ በእርግጥ ስለፍቅር ያውቃል ለማለት ኣያስደፍርም:: ከተፈጥሮ ጋር ሳይቀራረቡ ስለ ተፈጥሮ እውነተኛ ግንዛቤ አለኝ ብሎ ማሰብ፣ ወይም የጥበብ ስራዎችን ሳይመለከቱ ሰነ ውበትን ኣደንቃለሁ ማለት፣ ወይም ለኣንድ ሀገር የቀደምት ተሞክሮዎች ወይም ግኝቶች ዋጋ ሳይሰጡ ሀገሪቱን ኣደንቃለሁ ማለት የማይታሰብ ነው:: (1971፣ 9)::*

ስለ ቁሳዊ ባህል ኣስፈላጊነት በማያሻማ መልኩ ብዙ ተብሏል:: ከፎክሎር ዘርፎች ኣንዱ የሆነው ቁሳዊ ባህል፣ ባህል ከሚያቅፋቸው ኣያሌ ነጥቦች ውስጥ ኣንዱ ነው:: ለመሆኑ ባህል ራሱ ምንድነው? ጽንሰ ሀሳቡ የሚያስተላልፈው ነገርስ እስከምን ይዘልቃል? ቀጥሎ ይህንን በተካተተ መልኩ እናየዋለን::

### 2.1.1. ባህል ምንድነው?

ባህል የሰው ልጅ በረጅም የታሪክ ዘመኑ የፈጠረው፣ ቀስ በቀስም ያደራጀው የተግባሩና የጥረቱ ውጤት ነው:: በመሆኑም የባህል ፈጣሪው ሰው ነውና፣ ባህል ያለ ሰው ህልውና የለውም:: በእርግጥም ለኣንድ ህብረተሰብ መሰረቱ ቤተሰብ የመሆኑን ያህል የባህል መሰረቱም ህብረተሰቡ ነው::

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ሰው በዚህ ዓለም ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ተፈላጊዎቹን መሰረታዊ ነገሮች ለማግኘት ከተፈጥሮ ጋር ያደረገው ግብ ግብ ቀላል አልነበረም:: ኣይሊሲ ኤሪክ (AYLSI, ERIC) An Introduction to the Study of African Culture በተባለው መጽሀፋቸው «የሰዎች ባህል የሚባለው የቁሳዊ እና ኣእምሮኣዊ ኣጠቃላይ ትጥቅ የሆነውንና ስነህይወታዊ እና ማህበራዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት ከኣካባቢያቸው ጋር የሚፈጥሩት መስተጋብር ነው» (1972፣ 1) ያሉት እዚህ ላይ እውነታውን ያጎላዋል::

ባህል ውስብስብ ነው፤ ከዚህም ኣንጻር ከእውቀት፣ ከእምነት፣ ከጥበብ፣ ከህግ፣ ከሞራል፣ ከልዩ ልዩ ልማድ እና በኣጠቃላይ ሰው እንደማህበራዊ ኣባልነቱ በልምድ እና በልማድ የሚተገብራቸውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው:: Culture and Identity በሚል ርእስ በጻፉት መጽሀፍ ኪድ (Kidd) ተከታዩን ጠቁመዋል:: «የህብረተሰብ ጥናት ኣጥኚዎች ባህልን የሰዎች (የቡድኖች) የኣኗኗር መንገድ ነው:: የኣንድ ሰው መለያው (መታወቂያው) እና የዛ ሰው ማንነት መገለጫው ነው» (2002፣ 2)::

ባህል የትውልድን ታሪክ ይዞ መቆየት ብቻ ሳይሆን ነጋሪም ኣስተላላፊም ነውና በሰዎች የተግባር ውጤት የሚገለጽ የሰዎች ቅርስ ነው:: «የሰዎች የስራ ውጤትና ከሌሎች እንስሳት የሚለዩበት መደበኛና ኣይነተኛ ምልክታቸው፣ የየወቅቱ ኣኗኗራቸው ነጸብራቅ፣ ድምራዊ የይዘት ክምችት፣ ያለው ክስተት ነው» (ፋሲል ተፈራና ሌሎችም፣ 1975፣ 55):: በተያያዘ ሁኔታ ቢልስ እና ሀሪ ሆጀር (Beals and Harry Hoijer 1953፣ 210) «ባህል በህብረተሰቡ መካከል መስተጋብራዊ ሁኔታን ፈጣሪ፣ የኣኗኗራቸው ዘይቤና ፈሊጥ ሁሉ ድምር ነው» ሲሉ በኣጽንኦት ገልጸዋል::

ከዚህ በላይ በጥቅሉ እንደተቀመጠው ባህል ሁለት፣ ነገር ግን የማይነጣጠሉ የቁሳዊ እና መንፈሳዊ ባህል ውጤትም ነው:: ምንም ይሁን ምን፣ ይስፋም ይጥበብም እንጂ ባህል የሌለው የህብረተሰብ ክፍል ስለሌለ ሁለቱም (ቁሳዊና መንፈሳዊ) የባህል ክስተቶች ይታያሉ:: እነዚህም በልዩ ልዩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ወቅት ይከሰታሉ:: ይሁንና ቁሳዊ ባህል የምንለው ምንድነው? መንፈሳዊ ባህልስ? ሁለቱን በየተራ ኣጠር ባለ ሁኔታ እንመለከታለን::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

### 2.1.2. ቁሳዊ ባህል

የሰው ልጅ ቁሳቁስን የፈጠረው እለታዊ ፍላጎቱንና የዘለቄታ ግቡን ለማሳካት ካለው ጽኑ ኣላማ ተነስቶ ነው:: በተፈጥሮ ያገኘውን እየለቃቀመ ከሚበላበት ወጥቶ በስራው የድንጋይ መሳሪያ ኣውሬ ማደን ሲጀምር የተሻለ ምግብ ኣገኘ:: እሳትን ከፈጠረም በሁዋላ ስጋውን በጥሬው ይበላ የነበረውን እየጠበሰ መብላት ሲጀምር የበለጠ ረካ:: እነዚህ ቀስ በቀስ የፈጠራቸው ቁሳዊ ባህሎች መንፈሱን እያረኩትና እያዝናኑት የበለጠ እንዲሰራ፣

እንዲፈጥር በር ከፍተውለታል፤ እዚህ ላይ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ባህሎች እየተደጋገፉ እንደመጡ ልብ ይሏል::

የሰው የተግባሩ ውጤት የሆነ ቁሳቁስ፣ ተጨባጭና በየግዜውም በአዳዲስ ፈጠራ የሚለዋወጡና በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የስራ መሳሪያዎች፣ ስራን ለማከናወን የሚረዱ የእደ ጥበብና የፋብሪካ ውጤቶች ሁሉ ከቁሳዊ ባህል ይመደባሉ:: በዚህም የሰው ልጅ በጥረቱ ያስገኛቸውና ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚያውላቸው ቁሳቁስ የተግባሩ ውጤት ናቸው ማለት ይቻላል:: በተጓዳኝም ቁሳቁስ የህብረተሰብ ታሪክ ነጋሪዎች ናቸው፤ ምክንያቱም የተሰሩበትና የተፈበረኩበት ዘመን ሲነሳ የህዝቡም ታሪክ አብሮ ይነሳልና ነው:: ለምሳሌ በተለያዩ ክፍላተ አህጉራትና አገራት በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ የምናገኛቸው ቁሳቁስ የጥንቱን ሰው ባህልና ታሪክ የሚያንጸባርቁ ናቸው:: ፍላጎትን ለማርካትና ኣላማን ስኬታማ ለማድረግ የሚመረቱ ቁሳቁስ - የተግባር መገልገያዎች፣ ህንጻዎች፣ በልዩ ልዩ ቅርጽ የሚሰሩ ቤቶች፣ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች፣ ወፍጮዎች ወዘተ. ሁሉ ከቁሳዊ ባህል ውስጥ ይመደባሉ:: በተጨማሪም ቁሳዊ ባህል የሚባሉት የህብረተሰብን ወይም የኣንድን ቡድን እምነት፣ ዘመኑ የደረሰበትን ሁኔታና ትጋት ወይም ግለሰቦች የደረሱበትን የእድገትና የእውቀት ደረጃ የሚያሳዩ ናቸው::

ለቁሳዊ ባህል መዳበርና መፈብረክ የእሳት መገኘት ጥንታዊውን ሰው በከፍተኛ ደረጃ ለውጦታል:: እሳት ምግቡን ኣብስሎ ለመመገብ ብቻ ሳይሆን ራሱን ከኣውሬዎች ጥቃት እንዲከላከል ኣስችሎታል:: Man's Unwritten Past በሚለው መጽሀፋቸው ፕላንት ቢ.ኤ. ኤድዝ (Plant, B.A. Edith) እንደጠቀሱት «የእሳት መገኘት ምናልባትም የሰው ልጅ ቀዳሚ መሳሪያ፣ የሁሉም ነገር ማከናወኛ የመጀመሪያው ደረጃ ሳይሆን ኣልቀረም» (1042፣ 23)::

ስልጣኔ እንደዛሬው በሁለት እግሩ ባልሄደበት በዚያ ጥንታዊ ዘመን የነበረውን ሰብኣዊ ፍጡር ትተን በዚህ ዘመን ላይ ሆነን ዘመነኛውን ሰው እንኳን ብናስተውል ብረትን ለማቅለጥ፣ ሸክላን ለማጠንከር እና ለልዩ ልዩ ተግባራት እሳት በመጫወት ላይ ያለው ሚና በቀላሉ የሚገመት ኣይደለም:: «ምትሀተኛው መሳሪያ» በማለት የእሳትን ጠቃሚነት ያስረገጡት ኦክሌይ (Oakley) እና ማን (Mann) ገለጻቸውን ሲቀጥሉ «እሳት የስራ መሳሪያዎችን በቀላሉ ለመስራት ኣስችሏል፤ ሰው የመፍጠርና የመፈብረክ ፍላጎት እንዲኖረው ብርታትን ሰጥቶታል» ኦክሌይ (1961፣ 181) እና ማን (1973፣ 23) በማለት ጠቃሚነቱን ያስረዳሉ::

ቁሳዊ ባህል የእድገትና የስልጣኔ ቅድመ መነሻና መሰረት መሆኑን በመጠኑ ተመልክተናል:: ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል እንደማይለያዩ እና የኣንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውንም በትንሹ ተረድተናል:: ቀጥሎ ደግሞ መንፈሳዊ ባህል ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንሞክር::

### 2.1.3. መንፈሳዊ ባህል

መንፈሳዊ ባህል የሚባለው የሰው ልጅ በንቃተ-ህሊናው የሚፈጥራቸው ልዩ ልዩ የእውቀት ዘርፎች፣ የኪነጥበብ ክፍሎች - ድራማ፣ ትያትር፣ ሙዚቃ ወዘተ. በተጨማሪም ፍልስፍናዎቹ፣ በሀይማኖታዊና እምነታዊ ስርአት ላይ ምህላና ምልጃ የማቅረቡ ሂደት፣ በአጠቃላይ በህሊናው እየፈጠረ የሚደሰትባቸውና ሀዘንና ስሜቱን የሚገልጽባቸው ክንውኖች ወዘተ. ያቀፋል:: መንፈሳዊ ባህል ከቁሳዊ ባህል ይመነጭና መልሶም ቁሳዊ ባህልን ያሳድጋል:: ይህ ተደጋጋፊነት፣ ሰው ቁሳዊ ባህልን ማዳበር ከጀመረበት ከጥንታዊው ዘመን ጀምሮ የኖረና እያደገ የመጣ ነው:: ኣያልነህ ሙላት «ባህልና ኣብዮታችን» በሚለው መጣጥፋቸው ቀጥሎ ያለውን ኣስፍረዋል::

> *ባህል ሁለት መልኮች ኣሉት:: እነሱም ቁሳዊ ባህልና ህሊናዊ ባህል ናቸው:: ቁሳዊ ባህል የምንለው ቁሳዊ ክንውንና ውጤቱን፣ ለምሳሌ የቴክኒክ መሳሪያዎች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ የቤት እቃዎች፣ የመገናኛ መሳሪያዎች እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: ህሊናዊ ባህል የሚባለው የንቃተ ህሊናንና የኣእምሮ ውጤቶችን የሚያጠቃልል ነው..... እውቀት፣ ትምህርት፣ ሳይንስ፣ ኪነጥበብ፣ ህግ፣ ፍልስፍና፣ ፖለቲካ፣ ሀይማኖት እና የመሳሰሉት የህሊና ክንውን ናቸው (1975፣ 81)::*

ከብዙ ጊዜ በሁዋላ ስልጣኔ የወለደው ሬዲዮ የቁሳዊ ባህል ውጤት ሲሆን በሬዲዮ ኣማካኝነት የሚቀርቡ ለምሳሌ እንደ ሙዚቃ፣ ድራማ፣ ስነጽሁፍና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች የህሊናዊ ባህል ውጤቶች ናቸው:: ሰው በሚሰራበት ጊዜ ኣንድ ቁስ ሲፈጥር ቁሳዊ ባህሉን ያዳብራል:: በፈጠረው ቁሳዊ ባህል እርካታ ሲያገኝ ደግሞ ህሊናዊ ባህሉን ያሰርጻል፣ በውስጡ በሰረጸው ህሊናዊ ባህል እርካታ ሲሰማው ሌላ ቁሳዊ ባህል ለመፍጠር ይተጋል፤ ይህንንም መጀመሪያ ስራ ቀጥሎ እርካታ፣ በማስከተልም እንደገና «ስራ» በማለት ማጠቃለል ይቻላል:: ስራ..... እርካታ ..... ስራ:: በዚህ ኡደትም ከተፈጥሮ ጋር እየታገለና ፍላጎቱን እያሟላ ይቀጥላል:: ተጨባጭ እና ረቂቅ፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ፣ ሰው ለዘመናት ለህልውናው ሲል የፈጠራቸው የባህሉ ውጤቶች፣ ራሱን ለውጦ ኣለማችንንም የለወጠባቸው ቅርሶቹ ሁሉም በቁሳዊ እና በመንፈሳዊ ባህሉ ውስጥ ኣሉ::

> *«ማንም የህብረተሰብ ክፍል የማምረቻ መሳሪያዎች፣ ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች መጠቀሚያ የሚሆኑ እቃዎች፣ የእምነቱ መገለጫዎች፣ ደስታውንም ሆነ ሀዘኑን የሚገልጽባቸው ዜማዎች፣ ኣባባሎች፣ ወጎች፣ ልማዶች ኣሉት:: ህይወትንና ተፈጥሮን የሚያደንቅበት ዘዴም ኣለው» (በላይነህ ኣሰጉ፣ 1981፣ 6)::*

ከዚህ በላይ በተገለጸው የበላይነህ ኣሰጉ ጽሁፍ ውስጥ ቁሳዊና ህሊናዊ ባህሎች ተንጸባርቀዋል:: ሁለቱም የሰው ልጅ ውጤቶች ናቸው፣ ሁለቱም ማንነቱን ይናገራሉ፣ ሁለቱም የሰው ልጅ ቅርሶች ናቸው:: እናም ቅርስ ምንድነው? ከጎባ ወረዳስ ኣኳያ እንዴት ይታያል? ተከታዩ ጽሁፍ በዚህ ላይ ጥቂት የሚለው ኣለው::

## 2.2. ቅርስና የቅርስ ኣስፈላጊነት

የሰው ልጅ በኣያሌ የታሪክ ዘመኑ የሰራቸውና ያካበታቸው ልዩ ልዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎቹ የዚያ ህብረተሰብ ቅርሶች ናቸው ማለት ይቻላል:: ቅርሶች የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ተብለው በሁለት ይከፈሉ እንጂ ሁሉም ያለፈውን ዘመን ትውልድ ማንነት፣ ልማድ፣ ትውፊትና ባህል በኣጠቃላይም ታሪኩን ሊነግሩት የሚችሉ ቋሚ ምስክሮች ናቸው:: ሰብኣዊ ፍጡራን ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ በጥረታቸው ያከናወኗቸው የእደጥበብ ውጤቶቻቸውም ሆኑ በልዩ ቴክኖሎጂ እገዛ የሰሯቸው የተግባር ግኝቶቻቸው ሁሉ ቅርሶቻቸው ናቸው::

የትናንት ማንነት በዛሬው ኣያያዛችን፣ የዛሬውም ማንነት ከትናንትናው መሰረታችን ጋር እርስ በእርስ እየተደጋገፈ ይገለጻል ስንል ትኩረታችን ኣፈታሪክ፣ ተረታ ተረት ወይም ትውፊት ላይ ብቻ ሳይሆን ከእነዚሁ ጎን ለጎን የቀደመው ትውልድ ትቷቸው ያለፋቸውን ቅርሶች በመመርመር ኣሰራራቸውንና፣ ጠቀሜታቸውን እንወቅ ከሚልም የሚመነጭ ነው:: በላይነህ ኣሰገ በመጣጥፋቸው ተከታዩን ሀሳብ ኣስፍረዋል::

> *«ቅርሶች በባህል፣ በስነውበት ይዘታቸው ተደናቂነት፣ ውበትና ታሪካዊነት ያላቸው ውርሶች ሆነው በተሰሩበት ዘመን ለተለያየ ኣይነት ኣገልግሎት ማለት ለሀይማኖት መገልገያ፣ ለንግድና ለልውውጥ፣ ለመከላከል፣ ለማህበራዊ ግንኙነት፣ ለቤት ኣገልግሎት፣ ለጌጥ፣ ለክብርና ለዝና ማትረፊያ ወዘተ. ታስበው የተሰሩ ናቸው» (1981፣8)::*

ህብረተሰቡ በእለት እለት እንቅስቃሴው በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ የሚገለገልባቸው ቁሳቁስ፣ የጦር መሳሪያዎች፣ ኣልባሳት፣ ልዩ ልዩ የወግ እቃዎች በኣጠቃላይ ሰዎች ያፈሯቸው መጠቀሚያዎች ውለው ባደሩ ቁጥር የታሪክ ማስረጃ የመሆናቸው ፋይዳ የጎላ ነው:: ቅርሶች ጥቅማቸው በዚህ ብቻ የሚገታ ሳይሆን ለኣንዳንድ የፈጠራ ስራዎችም ማበረታቻና ማነቃቂያም ይሆናሉ:: የቀድሞቹን ቅርሶች ኣይተን እኛም በዚያ ስራ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ የተሻለ ለመስራት ልንነሳሳ እንችላለን:: ያለፉትን ቅርሶች ስንመለከት ከምን እንደተሰሩ፣ ማን እንደሰራቸውና መቼ እንደተሰሩ፣ እንዴት እንደተሰሩ፣ እንመረምራለን በዚህም ውበትን እናደንቃለን፣ ያለፈውን ትውልድ ኣሰራር እናጠናለን ፣ በዚያም ላይ ተመስርተን የራሳችንን ፈጠራ በማከል ኣዲስ ነገር እናመነጫለን::

ቅርሶች በህዝቦች መካከል ያለውንም የባህል ትስስር ያሳውቁናል:: በኬንያውያንና በኢትዮጵያውያን፣ በኡጋንዳውያንና በኢትዮጵያውያን፣ በሌሎችም ኣገሮችና ህዝቦች መካከል በተለይ በእደጥበብ ውጤቶች ኣንጻር ብዙ መመሳሰል ይታያል:: ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያውያን ኦሮሞዎች የተሰሩ ምግብ መመገቢያ እቃዎች በኬንያና በኡጋንዳ የሚገኙ የተወሰኑ ጎሳዎች ከሰሯቸው ቁሳቁስ ጋር በኣሰራር፣ በእቃዎቹ ላይ በሚገኙት



ADDIS ... U.S LIBRARY

የጌጥ አጠቃቀሞች ተመሳስሎዎች ያጋጥማሉ:: ለምሳሌ በኬንያውያንና ኡጋንዳውያን የተወሰኑ ጎሳዎች ከስንደዶና ከዘንባባ ስፌት የተሰሩ የወተት ማለቢያ ጮጮዎችና የታበቱባቸው የጠፍር ጥብጣቦች (Straps) እንዲሁም የተዋቡባቸው ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ጨሌዎችና ነጭ ዛጎሎች፣ በሌላም በኩል ከእንጨት የሚሰሯቸው አንዳንድ የመመገቢያ ቁሳቁስ ቅርጽና የአሰራር ጥበብ ኢትዮጵያውያን ኦሮሞዎች ከሚሰሯቸው ጮጮዎችና የእንጨት ስራ ውጤት ከሆኑ አንዳንድ ቁሳቁስ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው:: ይህ ደግሞ ታሪክንና በህዝቦች መካከል የነበረውን የባህል መወራረስ ለማወቅ ለሚፈልግ ተመራማሪ አንድ የጥናት መስክ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል:: ሶምጂ ሱልጣን (Somjee Sultan 1993፣ 14፣44) እና ናዚታ (Nzita 1993፣ 12፣16፣104) በኬንያ እና በኡጋንዳ ላይ የጻፏቸውን መጻህፍት ልብ ይሏል::

በየስነቃል መምሪያ (1991፣ 50-52) መጽሀፋቸው ፈቃደ አዘዘ የስነቃል ጥናት ፋይዳ ከቅርስ አኳያ፣ ከስነልቦናና ከልማት አኳያ፣ ከትምህርት አኳያ እና ከስነጽሁፍ እድገትና ምንጭነት አኳያ ጠቃሚነቱን አጉልተው ያሳዩበት ግላጼ ሙሉ በሙሉ ለቁሳዊ ባህልም ያገለግላል:: ስለሆነም የቁሳዊ ባህል ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት አራት ነጥቦች እይታ አንጻር ጠቃሚነት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል::

ቅርሶች ከዚህ በላይ በገለጽናቸው እና እዚህ ላይ ባልተገለጹም ሌሎች አያሌ ጥቅሞቻቸው አስፈላጊነታቸውን ከተቀበልን መጠበቅ እንዳለባቸው ለማመን እርቀን አንሄድም:: ግን እንዴት ይጠበቁ? ያጠፋፋቸውን መንስኤ ማወቅ በጥንቃቄ ለመጠበቅ የሚያስችል ፍንጭ ሊሰጠን ይችላልና በመጀመሪያ ቅርሶች እንዴት ይጠፋሉ? ለሚለው ጥያቄ መልስ እናፈላልግ::

ቅርሳቅርሶች በሰው የስራ ውጤት እና በተፈጥሮ ተገኝተው መልሰው ሰብአዊ ፍጡራንን የሚያገለግሉ ቢሆንም በተፈጥሮ እና በሰው ስራሽ ልዩ ልዩ መንስኤዎች ጉዳትና ጥፋት ይደርስባቸዋል:: በርካታ ቅርሶች በግዴለሽነት፣ በከተሞችና በኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ በቴክኖሎጂ እድገት ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ወድመዋልም:: ከሁሉም በላይ ቅኝ ግዛት፣ ጦርነት፣ ወረራ፣ የባእድ አምልኮ እና የመሳሰሉት ሁሉ የቅርሶች ጠላት ናቸው::

የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ በአብዛኛው የጦርነት ታሪክ በመሆኑ በዚህ ሳቢያ አያሌ መተኪያ የሌላቸው ቅርሶች ወድመዋል፣ ተዘርፈዋል፣ ጠፍተዋልም:: ለዚህም ግራኝ መሀመድና የኢጣሊያ ተስፋፊዎች የአስነሷቸው ጦርነቶች ማስረጃዎች ናቸው:: ሌላው በተለይ ለአንዳንድ ቁሳዊ ባህል መጥፋትና መበላሸት በምክንያትነት የሚጠቀሰው ባህርና የብስ ተሻጋሪው የባህል ወረርሽኝ ነው:: አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ ቁሳቁስን ለእድገት አስፈላጊ እስከሆኑ ድረስ መቀበሉ ባይከፋም በአንጻሩ የራስን የትም ከመወርወር ይልቅ ቢያንስ ለዛሬው ስልጣኔ መሰረት ናቸውና በክብር ተመዝግበው

የሚጠበቁበት ቦታ ቢቀመጡ ይመረጣል። እንደ ኣልባሌ ነገር የትም ከተጣሉ የቤት ውስጥ መመገቢያ ቁሳቁሶች ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቢቻልም ከዚህ ጽሁፍ አቅም በላይ እንዳይሆን ኣንዱን ብቻ እንመለከታለን።

ባለፉት ዘመናት እግራም መሶብ በስንደዶ ሰበዝ እና በተለያዩ ቀለማት በተነከሩ ኣለላዎች ቀልብን በሚስብ ሁኔታ፣ ኣይንን በሚማርክ መልኩ እየተሰፉ በርከት ያሉ የኣንድ ቤተሰብ ኣባላት፣ ኣነስ ካሉም ባልና ሚስት ይመገቡበት ነበር። ያ እንጀራ ተነባብሮ ይቀርብበት የነበረ ባህላዊ እግራም መሶብ ከተወሰኑ ኣመታት ወዲህ በተለይም ዘመነኛው ትሪ መመገቢያ መሆን ሲጀምር የትሪ ማስቀመጫ ጠረጴዛ ሆነ። ጠረጴዛ ቦታውን ሲረከብ ደግሞ የትሪ ማቅረቢያነቱንም ተነፈገና ለእንጀራ ማቅረቢያነት እንዳልዋለ ሁሉ በጓዳ እንዲወሰን ከመደረጉም በላይ ኣንዳንድ ነገሮችን ለምሳሌ ሽንኩርት፣ ትርፍራፊ እንጀራ፣ ንፍሮ፣ ብጣሪ እህልና የመሳሰሉትን መያዣ ሆነ። ቀስ በቀስም ይህም ኣገልግሎቱ ተሸሮ ትንሽ ግንዛቤ የሰረጸላቸው ቤተሰቦች በየጓዳው እዚህም እዚያም ሲወረውሩት፣ ይህም ከነኣካቴው ያልታያቸው ደግሞ ከቤት ጓሮ በታዛ ስር በመስቀል የጸሀይና የንፋስ ሰለባ ኣደረጉት። ተፋራጅ ያጣው መሶብ በዚህ መልኩ ሲወገድ ከመሶብ ጋር የተያያዘው የህዝብም ታሪክ ኣብሮ ጠፋ።

በጎባ ወረዳ ኣንጻር ከተመለከትንም ይህ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ ቀስ በቀስ መወገድ በጎባ ኦሮሞዎችም ዘንድ ይታያል። ከእንጨት ተፈልፍለው እና ጌጥ ወጥቶላቸው ለገንፎ መመገቢያነት ያገለግሉ የነበሩ «ገበታዎች» እና «ቆሪዎች» ከውጭ በመጡ ሳህኖች ይሰጡ የነበሩትን ግልጋሎት ከተነጠቁ ወዲህ ኣንድም ለኣንዳንድ ነገሮች ማስቀመጫ ሆነዋል፤ ኣንድም በጓዳ ተወስነዋል ወይም ተጥለዋል። ይህ ኣይነቱ ሁኔታ ሀገርኛውን ቁሳዊ ባህል ከመድረክ ኣስወጣው። በየቦታው ያስተዋሉትን የቅርሶች መባከን ታዝበው ይመስላል «The Preservation of Ethipia's Cultural Heritage» በሚለው መጣጥፋቸው ሆናስኪ. ኤስ (Chojnacki S.)

> *«ዘወትራዊ ጠቀሜታ ያላቸው እንደ ልብስ፣ የጦር መሳሪያዎች፣ የሸክላ ስራ ውጤቶች፣ የእንጨት ስራዎች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች በጥቅሉ ዘመናዊ እውቀት በሌላቸው ሰዎች ይሰሩ የነበሩ የእደጥበብ እና የልዩ ልዩ ጥበብ ስራቶች ምንም ኣይነት ኣሻራ ሳይተው በመጥፋት ላይ ናቸው» (1971፣ 13) ያሉት።*

ኢትዮጵያ ቀደምት የሰው ዘር መገኛ ብቻ ሳትሆን ቀዳሚ የስልጣኔ ባለቤት እንደነበረች ኣያሌ ቅርሶቿ ዛሬም ይመሰክራሉ። እንደኣለመታደል ሆኖ ብዙዎቹ ቅርሶች በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ ጥፋት ቢወድሙም ዛሬም የኣንዳንዶቹ ኣሻራቸው ኣልጠፋም። ሪቻርድ ፓንክረስት (Richard Pankhrust) (1970፣ 23) «ኢኮኖሚክ ሂስትሪ ኦፍ ኢትዮጵያ» በሚል ርእስ የጻፉትን ኣቢይ እና ታመነ «ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለልማት» (1978፣ 11) በሚለው መጣጥፋቸው እንደሚከተለው ይጠቅሳሉ።

*ኢትዮጵያውያን ያማሩና የለሰለሰ (ቀጭን) ፈትሎችን ይፈትሉ እንደነበር፣ ከጥጥ እና ከሱፍ የሚሰሩ ልብሶችን፣ ከበሬ፣ ከበግ እንዲሁም ከልዩ ልዩ እንስሳት ቆዳዎች፣ ኮርቻዎች፣ ጋሻና የጎራዴ ሰገባዎችን፣ ኣንፋሮችንና ለምዶችን፣ የመጽሀፍ ሽፋኖችን፣ ከቀንድ መለኪያዎችን፣ ዋንጫዎችንና የምጥን መያዣ ድጉሶችን፣ ከብረታ ብረት የጦርና የእርሻ መሳሪያዎችን፣ ከወርቅና ከብር የተዋቡ የኣንገት፣ የጣትና የሽማ ጌጦችን ይሰሩ ነበር።*

ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት የቁሳዊ ባህል ክምችት ነበራቸው። በተለይ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች በእንጨትና በስፌት እደጥበቦች የቱን ያህል ምጡቅና የላቀ ድርሻ እንደነበራቸው በምልከታና በቃለመጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይሁን እንጂ ዛሬ-ዛሬ ለቀደምት ቁሳቁስ የተሟላ እንክብካቤ ሲደረግ ኣይታይም።

ለዘመናት ኣገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ እቃዎች ኣርጀት ካሉ ከጥገና ይልቅ እጣ ፈንታቸው መጣል ነው። የትም እንዳይጣሉና በሚገኙበት ሁኔታ በስርኣት እንዲቀመጡ የብሄረሰቡን ኣባላት ለማንቃትና ለማሳወቅ የሚደረገውም ጥረት ኣነስተኛ ነው። ቀጥሎ የጎባ ወረዳን በተመለከተ በመስክ ጥናት ወቅት የዚህ ጥናት ኣቅራቢ የታዘባቸውን ሁኔታዎች በተከታይነት እናነባለን።

## 2.3. በጎባ ወረዳ የቅርሶች ኣጠባበቅና ይዞታ

በጎባ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ብሄረሰቦች የልዩ ልዩ ቅርሶች ባለቤት ናቸው። ቅርሶቻቸው የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች፣ የእርሻ፣ የሙዚቃና የጦር መሳሪያዎች፣ ለሀዘንና ለደስታ ጊዜ የሚገለገሉባቸው ልዩ ልዩ ኣልባሳትና ቁሳቁሶች፣ ሀይማኖትንና ልማዳዊ እምነቶችን የሚያንጸባርቁባቸው እቃዎች፣ በኣጠቃላይ ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ የልዩ ልዩ እደጥበብ ስራቶች ወዘተ. ናቸው። ቅርሶቹ በልማዳዊ ኣሰራር እየተሰሩ የብሄረሰቡን ኣባላት ሲያገለግሉ የቆዩ ሲሆን ኣንዳንዶቹም እስከ ኣለንበት ዘመን የዘለቁ ናቸው። ይሁን እንጂ የወረዳው የቅርስ ይዞታ ሲገመገም ለታሪክ እና ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ፣ ለምርምርና ለጥናት በሚጠቅሙበት ሁኔታ ተማክለው የተቀመጡ ሳይሆን በኣንዳንድ ግለሰቦች ቤት ከሞላ ጎደል ለራስ ጠቀሜታ ብቻ ሲባል ብዙም እንክብካቤ በማይታይበት መልኩ የሚገኙ ናቸው። በዚህም የተነሳ ላለመጥፋታቸውና ላለመበላሸታቸው ምንም ኣይነት ዋስትና የላቸውም።

የዚህ ጥናት ኣቅራቢ በኣንዳንድ የገበሬ ቀበሌ መንደሮች ሲዘዋወር እንደተመለከተው ቆሪ (Qorii) እና ቁዲ (Quudii) የመሳሰሉ መመገቢያና የወተት ማስቀመጫ ቁሳቁስ እንዳላገለገሉ ሁሉ ትንሽ ኣርጀት ሲሉ በየቤቱ ታዛ ስር ወይም በኣጥር እንጨት ላይ እየተሰኩ የተጣሉ ሲሆን ኣንዳንዶቹም የህጻናት «እቃ-ቃ» መጫወቻዎች ሆነዋል። እቃዎቹ በዚህ ሁኔታ ለምን ተጣሉ? የሚል ጥያቄ ሲቀርብም የሚሰጡት መልሶች እንደየሰዎቹ ግንዛቤ የተለያየ ነው። ለምሳሌ የጎባ ወረዳ ቡርቂቱ ገበሬ ማህበር ነዋሪ



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

የሆኑት ወ/ሮ ሲይላ ኢብሮ አስተያየታቸውን ጠይቁ የሰጡኝ መልስ

> ቁዲ የወተት ማስቀመጫ ነው፣ ወተቱ ጥሩ መኣዛ እንዲኖረው ቁዲው በየጊዜው መቆራሸት አለበት፣ ለማቆራሸት ደግሞ የወይራ እንጨት ያስፈልጋል፤ ወይራ ውድ ከመሆኑም በላይ እንደልብ አይገኝም:: ከዚህም በላይ ቁዲውን ለማቆራሸት ጠዋትና ማታ የሚጠፋውም ጊዜ ቀላል አይደለም:: ቁዲው አርጀት ካለ የመጠገኛ ዘዴም ስለሌለን ይኸው እንደምታየው በየቤቱ ታዛ ስር እንጥለዋለን:: ስፌቱ ራሱ የተወሰነ የአገልግሎት ጊዜ ነው ያለው:: አገልግሎቱን ሲጨርስ ይሳሳል፤ ከሳሳ ደግሞ በሚቆራሽበት ጊዜ በቀላሉ ይቃጠላል:: ይህም እንዲሰነጠቅ ስለሚያደርገውና ማከሚያም ዘዴ ስለሌለን እንጥለዋለን::

የአንዳንዶቹም ሀሳብ እንደሚያረጋግጠው በአብዛኛው ቁዲን የመሳሰሉ ነባር እቃዎች ሲያረጁ ወይም በመሰንጠቅ ከአገልግሎት ውጭ ሲሆኑ ለመተካትም በገበያ ላይ ስለማይገኙ ዘመነኛዎቹን የላስቲክና ከብረት የተሰሩ እቃዎች መግዛት የተለመደ ነው:: ይሁን እንጂ በላስቲክ እቃ የሚቀመጠው ወተት በተቆራሸ ቁዲ ውስጥ እንደሚቀመጠው ወተት ጣእሙ አያረካም ይላሉ:: በአጠቃላይ መልሶቻቸው የተለያዩ ናቸው::

በጎባ ወረዳ ውስጥ ለቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ እንዳይደረግ ምክንያቶቹ ብዙ ቢሆኑም ዋናው ግን ከቅርሶች ጥበቃ ባለሙያና ከአስተባባሪም እጥረት ጋር የሚያያዝ ነው:: ሀላፊነትን ተቀብሎ በየገበሬ መንደሩ እየተዘዋወረ የብሄረሰቡን አባላት የሚያነቃ፣ የሚያስተምር አካል የለም:: የዚህ ጥናት አቅራቢ በጎባ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ኢ.ም ተገኝቶ የታዘበው እውነታ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: ሁለት ሰራተኞች 9 ካሬ ሜትር ስፋት ባላት አንዲት ክፍል ውስጥ አንድ አነስተኛ ጠረጴዛ እየተጋሩ የመስራታቸው ሁኔታ ችግሩ የቱን ያህል የገዘፈ መሆኑን ለመገንዘብ በቂ ነው:: ሰራተኞቹ እንደሚናገሩት የሰው ሀይል እና የበጀት እጥረት የተሟላ ክፍል ካለማግኘት ጋር ተዳምረው በየገጠሩ እንዳይዘዋወሩ እንቅፋት ሆኖባቸዋል:: በዚህም የተነሳ ምንም የተሟላ መረጃ የላቸውም:: በቃለ መጠይቁ ወቅት የተገኘውም ሌላው መረጃ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አሉታዊ ሁኔታ ስር የሰደደ መሆኑን የሚመሰክር ነው:: ሀጂ አብዱልጀዋድ አዲ የ88 አመት አዛውንት የሆኑ የላሽቆና ገበሬ ማህበር ነዋሪ ናቸው:: በወረዳው የኦሮሞ ባህል አለመጠናቱንና በብዙሀን ነዋሪዎች በተለይም በወጣቱና በጎልማሳው ዘንድ እንደማይታወቅ አስረግጠው ነው የሚናገሩት:: «እኛን ስለእቃዎቻችን፣ ስለአልባሳቶቻችን በአጠቃላይ ስለ ባህላችን የሚጠይቀን አላገኘንም፤ አንተ ግን ይህን ቃለ መጠይቅ ስለአደረክልን እናመሰግንሀለን:: የኦሮሞ ባህል ሰፊ ቢሆንም የሚጠይቀን አጥተን ያለንን ግንዛቤ ይዘን ልንሞት ነው:: ልጆቻችንም ባህላችንን ማስተላለፍም አልቻሉም፤ አሁን አናገርከን፣ ስለዚህ የምታመሰግነን አንተ ሳትሆን እኛ ነን......» በማለት በወረዳው የባህልና የቅርሶች ጥናት ባለመደረጉ የተሰማቸውን ቅሬታ ተናግረዋል:: በጎባ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ በቀለ ቱፋም የአንዳንድ ቁሳቁሶችን ያለጥንቃቄ መያዝና የትም መጣል፣ እንዲሁም በባለቤትነት የሚያሰባስባቸው አካል አለመኖር ያሳደረባቸውን ስጋት እንደሚከተለው ገልጸዋል::

> *ቆሪዎችም ሆኑ ሌሎች መሰል መመገቢያ እቃዎች ቤት ኣጣበቡ እየተባለ ላለመጣልም ትንሽ ያሳዘናቸው ይመስላል:: በማዳበሪያ፣ በምናምን ኣድርገው ከቤት ጓሮ ይጥሏቸዋል:: ይህ ነው ባህሉን እያጠፋው ያለው:: እኛም ልጆቻችንን ኣናስተምርም፤ኣናንቀን ነው የምንነግራቸው:: በማእከል ደረጃም ኣሰባሳቢ ይፈልጋሉ፣ እንጨቱም፣ የሸክላ ኣፈሩም ጠፉ፣ ችግሩንም ኣባባሰው:: በቂ ጥናት ተደርጎላቸው፣ የነበረው እውነተኛ ገጽታ ኣብሮ ተጽፎ ቢገኝ፣ ቢያዝ፣ ለዚህም ባለቤት ቢኖረው ጥሩ ነው ብዬ እገምታለሁ ብለዋል::*

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው እውነታ እንዳለ ይሁን እንጂ በጎባ ወረዳ የሚገኙ ኣንዳንድ ትምህርት ቤቶች ባህላዊ እቃዎችን ለማሰባሰብና ለህዝብ እይታ ለማብቃት የሚያደርጉት ጥረት ኣበረታች ነው:: በዚህ በኩል የባቱ ተራራ ኣጠቃላይ 2ኛ ደረጃ የመሰናዶ ትምህርት ቤት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው:: የዚህ ጥናት ኣቅራቢ በ27/8/99 ኣ.ም በቦታው ተገኝቶ እንዳረጋገጠው በተለይ የኦሮምኛ ቋንቋ የመሰናዶ ተማሪዎች በርእሰ መምህሩ በኣቶ ታምራት ስዩም እና የኦሮምኛ ቋንቋ መምህር በሆኑት በኣቶ ኣለሙ ወርቁ ኣስተባባሪነት እቃዎቹን ለማሰባሰብ እያደረጉ ያሉት ጥረት የሚመሰገን ነው:: ቁሳቁሶቹ በ «Gumii Afaan Oromoo» (ጉሚ ኣፋን ኦሮሞ) (የኦሮምኛ ቋንቋ ክበብ) ኣማካኝነት ተሰብስበው በተመደበላቸው ክፍል ውስጥ በመልክ በመልክ ተቀምጠዋል:: በ27/8/99 ኣ.ም በነበረው የክበቡ ኣመታዊ በኣል ላይ ከተለያዩ ቦታዎች የተጠሩ እንግዶች በተገኙበት የዚህ ጥናት ኣቅራቢ የተሳተፈባቸው ኣንዳንድ መርሃ ግብሮች ተከናውነዋል:: በወቅቱ ስለ ቁሳቁሶቹ ኣሰራርና ኣጠቃቀም ገለጻ በተሰጠበት ወቅት በቪዲዮ ከማስቀረጹም በላይ ስለ ቁሳዊ ባህል ኣስፈላጊነት፣ በተለይም ቁሳዊ ባህል የህዝብ ታሪክና ባህል ኣሳዋቂ መሆኑንና የማይናቅ ድርሻ እንዳለው በመጠቆም ኣሁን የተያዘው ቅርሶችን የማሰባሰብ ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፣ መልካም ኣጀማመሩም ከዳር እንዲደርስ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እጅና ጓንት ሆኖ መንቀሳቀስ እንደሚገባው የማስገንዘቢያ ንግግር ኣድርጓል::

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሰረት ለቅርሶች ኣጠባበቅና ይዞታ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ የግድ ነው:: ይህ ካልሆነ ግን ለዘመናት የተካበቱ ልዩ ልዩ ቅርሶች ሊጠፉ ይቻላሉ:: በውጤቱም የነበረው እንዳልነበረ ይሆንና የብሄረሰቦችን የታሪክ ኣሻራ ያወድማል:: ታሪኩ የወደመበት ብሄረሰብ ደግሞ ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ ለማወቅ ኣይቻልም:: እናም ምን መደረግ ኣለበት? የሚለው ኣቢይ ጥያቄ መልስ ማግኘት ይፈልጋል:: ጥናታዊ ጽሁፉ መልስ ሊሆኑ ይችላሉ የሚላቸውን ሀሳቦች በመደምደሚያው የጥናቱ ክፍል ያቀርባል::

## 2.4 ፎክሎርና የመመገቢያ ቁሳቁስ

ፎክሎር እጅግ በጣም ሰፊ ይዘትና ጽንሰሀሳቦችን የያዘ የጥናት መስክ ነው። በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በዚህ አጭር ጽሁፍ የፎክሎርን ምንነት መተንተን አይቻልም። በአጭሩ ፎክሎርን በውቅያኖስ ብንመስለው የመመገቢያ ቁሳቁሶች ደግሞ በጠብታ ውሀ ይወከላሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ በመጠኑ ለማየት ያህል ፎክሎር ምንድነው? ከመመገቢያ ቁሳቁስ ጋርስ እንዴት ይያያዛል? ለሚሉት ጥያቄዎች በወፍበረር ቅኝት በትንሹ ለማስጨበጥ እሞክራለሁ።

> *«ፎክሎር የየቡድኖች ጥበባዊ ግንኙነት ነው። ፎክሎር በተወሰኑ ቡድኖች ውስጥ ትርጉም ያለው ነገር እንደሚያጠና ሁሉ ለብዙሀን ባህላዊ ስነውበትም አድናቆትና ትርጉም ይሰጣል። የፎክሎር ዘርፎች በጊዜና በቦታ ውስጥ እንደሚሰራጩ ሁሉ በተጨማሪም በእይታ፣ በቃል፣ በአካል እንቅስቃሴ ፣ በቁሳዊ ተስተላልፎና በመሳሰሉትም ይገለጻሉ። በአጠቃላይ ፎክሎር ስርአታዊ የሆነ የብዙሀን የባህል ጥናት ነው» (http://www.elearn.arizonaedu/sfair).*

በመስኩ ላለፉት በርካታ ኣመታት ጥልቅ ጥናት ያደረጉት ፈቃደ ኣዘዘ ፎክሎር የሚለውን ቃል፣ ቃል በቃል ከመፍታት ይልቅ በውስጡ ከሚያቅፋቸው ዘርፎች ብንነሳ ይሻላል በማለት በተለይ የዶርሰንን (የDorsonንን) ሀሳብ መሰረት አድርገው በየስነቃል መምሪያ (1991፣11-15) እና በሰሚያጠ ድምጾች (1996፣ii-iv) መጻህፍቶቻቸው፣ ፎክሎር - ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል በሚባሉ አራት ዘርፎች መከፈሉን ገልጸው፣ በእያንዳንዳቸውም ላይ የይዘት ትንታኔ ሰጥተውባቸዋል።

ሰዎች የሚናገሩት ወይም የሚተገብሩት፣ በህይወት ዘመናቸው የሚሰሩትን ስራ ማጣፈጫ የሚያደርጉበት፣ ደስታ ሀዘናቸውን፣ እኩይ ሰናይ ድርጊታቸውን የሚገልጹበት፣ መልካምና መጥፎ ስሜታቸውን፣ ብሶትና ሀሴታቸውን የሚያመለክቱበት፣ የሚመርቁበትና የሚረግሙበት ወዘተ. ሁሉም በፎክሎር ውስጥ ያልፋል። ለምሳሌ የልዩ ልዩ ብሄረሰብ ኣባላት እንደ ሀይማኖታቸውና እምነታቸው በሀዘን ጊዜ ጥቁር መልበስ ወይም ነጭ ኮፍያ ማድረግ፣ የሀዘን እንጉርጉሮው፣ የደስታ ጭፈራው፣ ሲመርቁ ለምሳሌ የቤት በታች እርሻ፣ የጎረቤት ውሻ፣ የሚስት ኣርጣጣ[2] ይስጥህ የሚሉት፣ ሲረግሙም የእርሻ ጋራ ዞሮ፣ የጎረቤት ዶሮ፣ የሚስት ወይዘሮ ይዘዝብህ እያሉ የሚኮንኑት በቃልም ቢነገር በጽሁፍም ቢሰፍር ወዘተ. ሁሉም ፎክሎር ይመዘዝበታል፣ ይተገበርበታል። ፎክሎር በየሰው ኣእምሮ እየተረገዘ፣ በየሰው ድርጊትና ኣንደበት ይወለዳል። እናም ኣነሰም በዛ በሁሉም ዘንድ በሁሉም ቦታ ኣለ። ፎክሎር የማይገባበት የሰው ልጅ ገጠመኝ ኣለመኖሩን ፈቃደ ኣዘዘ (1996፣ v) «ፎክሎርን የሁሉት ክንዋኔዎች መግለጫ ኣድርገን ልንወስደው እንችላለን፤ ሰዎች በዘልማድ (በባህል)

[2] ኣርጣጣ፡- ጉልበቷን ለቤቷ የምታውል፣ ታማኝ ሚስት



A.A.U. LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሚናገሩት እና ሰዎች በዘልማድ (በባህል) የሚተገብሩት፡፡ የሰዎች መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህል ነው ማለት ይቻላል» በማለት የገለጹት፡፡

ጆርጅስ ሮበርት ኤ. እና ሚካኤል ኦውን ጆንስ (Georges Robert A. and Michael Owen Jones) የተባሉ ፎክሎሪኖች Fokloristics An Introduction በሚለው መጽሀፋቸው «The pervasiveness of Floklore» በሚል ርእስ (1995፣1) በሰጡት ሀሳብ «ፎክሎር ከእየቀኑ ህይወትና አኗኗራችን ጋር የተጠበቀ ግንኙነት ያለውና በጣም አስፈላጊም ነው» በማለት ገልጸዋል፡፡ በእርግጥም ፎክሎር በሰው ህይወት ውስጥ በየቀኑ ተከሳችና ከእየ እለቱ ህይወታችን ጋር መስተጋብራዊነት ያለው ነው፡፡ በአጭሩ የሰው ልጅ የሚተነፍሰውን አየር ያህል በፎክሎር ይገለገላል፡፡ ፎክሎር እያንዳንዳቸው በብዙ አይነት ሊከፈሉ የሚችሉ አራት ዘርፎች ይኑሩት እንጂ ፈቃደ እንደሚያስገነዝቡት አራቱም የፎክሎር ዘርፎች ግድግዳ ከልሏቸው፣ ድንበር ተበጅቶላቸው ሳይገናኙ የሚቀመጡ ሳይሆኑ በድርጊታዊ ሂደት ውስጥ ቅንጅት ሲፈጥሩ እናያቸዋለን፡፡ አንድን የኦሮሞ እስላም ባህላዊ ዝየራ ወይም የ«ባሮ»[3] ስነስርአት በምሳሌ ወስደን ብናይ አራቱ ዘርፎች እንዴት እንደሚጣመሩ ለማጤን እንችላለን፡፡

አንድ የኦሮሞ እስላም (ብዙውን ጊዜ የሚዘይሩት እስላሞቹ ናቸው፤ ከሀይማኖት ጋር ይያያዛልና) አቀንቃኝ (ዘያሪ) በባሌ ያለውን የድሬሼክ ሁሴንን (መንፈሳዊ ቦታ) እየጠራ በ«ባሮ» ማቀንቀኛ ስርአት (ዝየራ) የአዘያየር ስልት ቅዱስ የሆነውን ቦታና ብዙ አውሊያ (ገድል) እንደሰሩ የሚነገርላቸውን ሼኽ ሁሴንን እየጠቀሰ በዜማ ውዳሴና ምስጋና ለማቅረብ ሲዘጋጅ ወረጋውን (ሌጣውን) ሳይሆን በራሱ ላይ የሚጠመጥመው አማማ (Amaamaa) ጥምጥም፣ በእጁ የሚይዘው ባለ ባላ ዘንግ፣ የሚለብሰው ባህላዊ ልብስና አድማቂ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲሁም የሚያሰማው ግጥም ይኖረዋል፡፡ ንቅናቄውና ዝየራው የአወዳደሱን ስልት ተከትሎ ይካሄዳል፡፡ ይህ ሁሉ ክንውን ለየዋህ ተመልካች ዝየራ ብቻ ነው ተብሎ ይወሰድ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ላቅ ላለው ፎክሎረኛና ለፎክሎር ተማሪ ግን ቃል ግጥሙ ስነቃልን፣ ዝየራው ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን፣ የባሌውን የድሬ ሼክሁሴን እየጠራ ጆሮውን በአንድ እጁ ይዞ በባለ ባላው ዘንግ ደግሞ እሩቅ እያመለከተ ግጥሙን ሲደረድር ሀገረሰባዊ ልማድን፣ የታጀበባቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የለበሰው ባህላዊ ልብስና በራሱ ያሰረው ጥምጥም ከቁሳዊ ባህል ይመደባሉ፡፡

ይህ ጥናት ተተኳሪ ያደረገው የቁሳዊ ባህል አንድ አይነት (Genre) በሆነው የመመገቢያ ቁሳቁስ ላይ በመሆኑ ወደዚያው እናምራ፡፡ የመመገቢያ ቁሳቁስ የሚባሉት የሰው ልጅ ምግቡን አብስሎም ሆነ በጥሬው አቅርቦ የሚመገብባቸው ወይም የሚያበስልባቸውና

---

[3] ባሮ፡- በባሌው የድሬ ሼክ ሁሴን መንፈሳዊ ቦታ እምነታዊ በአላቸውን ለማክበር የሚሰባሰቡበት ምእመናን (የእምነቱ ተከታዮች) የድሬ ሼክ ሁሴንን ገድል እያሰቡ በዝየራ የሚያዜሙበት ስርአታዊ ክዋኔ ነው፡፡

የሚያስቀምጥባቸው ቁሳቁስ ናቸው። ይሁንና ቁሳቁስ ማለት ምን ማለት ነው? ቁሳቁስ የሚለው ቃል ሰፊ ይዘትና ጽንሰ ሀሳብ የያዘ ቢሆንም ኣጠር ኣድርጌ ለመግለጽ እሞክራለሁ።

የሰው ልጅ ከጥንታዊ ታሪኩ ጀምሮ በተፈጥሮ እያገኘ ለልዩ ልዩ ተግባሮች በግልጋሎት ላይ ሲያውላቸው የነበሩ እንደ ድንጋይ፣ እንጨት፣ ኣጥንት ወዘተ.፣ በሁዋላም ተፈጥሮን እየገራ ከልዩ ልዩ ጥሬ እቃዎች (እንጨት፣ ሸክላ፣ ቅል፣ ቀንድ፣ ብረት ወዘተ.) የሚያመርታቸው ልዩ ልዩ መሳሪያዎች፣ ከእንስሳትና እጽዋት ተዋጽኦ እየሰራ ሲገለገልባቸው የነበሩና ዛሬም የሚያገለግሉት የእደጥበብ ውጤቶች፣ ከኢንዱስትሪ ኣብዮት ወዲህም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የፈጠራቸው ለመመገቢያ፣ ለመተኛ፣ ለመጻፊያ፣ ልዩ ልዩ ነገሮችን ለማከናወኛ የፈበረካቸው እቃዎች ወዘተ. ሁሉ፣ በተጨማሪም ኣእምሮውን ሊያዝናኑለት የሚችሉትን እንደ ድራማ፣ ትያትርና ፊልም ለመስራት፣ መጽሀፍ ለመጻፍ ወዘተ. የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ እርቃኑን ለመሸፈን የሚገለገልባቸው ኣልባሳት፣ የመዋቢያ ጌጦች፣ ፍላጎቱን ለማሟላት፣ ሀዘንና ደስታውን ለመግለጽ እንዲያስችሉት ከተራ እደጥበብ ጀምሮ በጎጆ ኢንዱስትሪና በፋብሪካ ደረጃ የሚያመርታቸው መገልገያ መሳሪያዎች ሁሉ በድምሩ ቁሳቁስ በመባል ይታወቃሉ።

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት መመገቢያ እቃዎችም የቁሳቁስ ኣንድ ክፍል ናቸው። ከቁሳዊ ባህል፣ ብሎም ከፎክሎር ጋር የጠበቀ ቁርኝትም ኣላቸው። ግን እንዴት ይዛመዳሉ? ኣንድ ባህላዊ የኦሮሞ መገልገያ ቁስን ወስደን ተዛምዷቸውን እናጢን።

«ቆሪ» (Qoorii) የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ባህላዊ መመገቢያ እቃ ነው። በሰርግ ወይም በተለያዩ የሀይማኖትና የእምነት በኣላት ወይም በተለይ ኦሮሞዎችን በሚመለከቱ ልዩ ልዩ በኣላት ወቅት ዘፈን ሲዘፍኑ፣ ጭፈራ ሲያሳዩ ባህላቸውን ለማንጸባረቅ ይዘውት ወዲህና ወዲያ እየተዘዋወሩ ወይም እየዘለሉ በሚዘፍኑበት ጊዜ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ማሳያ ይሆናል፤ ኣባወራው በ«ቆሪ» ገንፎ ቀርቦለት ማባያ ቅቤው ካነሰው ባለቤቱን (ሚስቱን) በቀጥታ ሳይሆን በፈሊጣዊ ኣነጋገር «ማል ሀጳ ኤበሉ ቆሪን ጎግዴ» «Maal Hadhaa Ebaluu Qooriin Gogide» (የእገሌ እናት ምነው ቆሪዋ ለምን ደረቀች) ሲል ስነቃልን ተግባራዊ ያደርጋል። በልዩ ልዩ ሀይማኖታዊ እምነታዊ ስርኣት (በመውሊድ ወይም በኣቴቴና በረንቲቻ) ወቅት በማሰሮ የተገነፋው ገንፎ በ«ቆሪ» ሲቀርብ ሀገረሰባዊ ልማድን ያስታውሳል። «ቆሪ»ው በራሱ የሰው ልጅ የፈጠረው የእደጥበብ ውጤቱና መገልገያ እቃው ስለሆነ ደግሞ ቁሳዊ ባህል ውስጥ ይመደባል።

ቁሳቁስ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ እና ከፎክሎር ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተሞክሯል። ምንም እንኳን የመመገቢያ ቁሳቁስ ከጠቅላላው ቁሳዊ ባህል ኣንጻር ሲታይ የጠብታ ያህል ቢሆንም መልእክትን፣ ባህልና ወግን፣ ልማድንና የሰው ልጅ ያለፈበትን የታሪክ ጉዞ በትንሹ ሊያስተዋውቅ ይችላል

የሚል እሳቤ ኣለ። ፎክሎር ከቁሳዊ ባህልና ብሎም ከቁሳቁስ ጋር ካለው የጠበቀ ግንኙነት የተነሳ ትእምርታዊ ፋይዳውም የጎላ ነው። ይህንን ሀሳብ ለማብራራት ተከታዩ ርእስ የሚነግረን ኣለው።

## 2.5 ፎክሎርና ትእምርታዊ ፋይዳው

ትእምርት የሚለው ቃል ምልክት የሚለውን ፍች የያዘ ነው። ምልክት ደግሞ ማሳወቂያ ኣንድን ነገር ከሌላው መለያ ነው። የኣንድ ሰው ሀሳብ፣ ኣላማ ወዘተ. የእዚያ ሰው መለያውና ምልክቱ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ኣንጻር እንደ ኣሻራ፣ መታወቂያ፣ ፓስፖርት እና ቋንቋ ሁሉ፣ የፎክሎር ትእምርታዊ ፋይዳ ኣንድን ሰው ወይም ብሄረሰብ ከሌላው ሰውና ብሄረሰብ ለመለየት ያገለግላል። በዚሁ መሰረት ቀጥሎ የፎክሎርን ትእምርታዊ ፋይዳ እንመለከታለን።

ሰዎች እንደየባህላቸው ዘፈን ይዘፍናሉ፣ ጭፈራ ይጨፍራሉ፣ ዳንስ ይደንሳሉ ወዘተ. ዘፈኑ፣ ጭፈራው፣ ዳንሱ፣ እስክስታው ወዘተ. ኣንዱን ብሄረሰብ ወይም ግለሰብ ከሌላው ብሄረሰብና ግለሰብ ይለየዋል። በጭፈራውና በዘፈኑ ውስጥ ከዚህም ጋር የሚከናወኑ ልዩ ልዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ግለሰቡን ከሌሎች የሚለዩት ትእምርቶች ናቸው። በምሳሌ እናጢን።

ሰሜን ኢትዮጵያ (የትግራይ ብሄረሰብ) እስክስታ ይበልጡኑ ኣንገትን ከመስበቅ ጋር ይያያዛል፤ ወደ ጎጃምና ጎንደር ወረድ ስንል የዘፈኑ ኣድማቂ የሆነው ንቅናቄ በትግራይ ከኣየነው የኣንገት እንቅስቃሴ ይልቅ ወረድ ብሎ ለትከሻ ከፍተኛውን ሚና ይሰጣል። ጉዟችንን ቀጥለን ወደ ደቡብ እንሂድና የወላይታ ብሄረሰብን ለኣብነት እንጥቀስ። በወላይታ የብሄረሰቡ ኣባላት እግርን በሀይል ከፍ እያደረጉና እንጣጥ በማለት፣ መቀመጫን በማወዛወዝ፣ ሽንጥን በመስበቅ፣ ዳሌን በመወዝወዝ (በተለይ ሴቶቹ) የሚጫወቱት ጨዋታ ከሌሎች ልዩ የሚያደርጋቸው ትእምርታቸው ነው። ወደ ኦሮሞዎች ኣጨፋፈር ስንመጣም ረገዳው፣ ፎሌው ወዘተ. እግርን በመጠኑ ከማንሳት፣ ወገብና ትከሻን በተዋሀደ ስልት ከመስበቅ ጋር ተቀናጅቶ የሚፈጥረው ድባብ የብሄረሰቡ ትእምርት ነው። በተጨማሪም ጭፈራው፣ ዘፈኑ፣ እስክስታውና ውዝዋዜው ወዘተ. ከተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና ኣልባሳት ጋር ሲቀርብ የሚከሰተው ድባብ ትእምርትነቱን የጎላ ያደርገዋል። የየብሄረሰቦችን ቡድን ያካተተ ኣንድ የሙዚቃ ትርኢት (Musical Concert) ቢዘጋጅ፣ የየብሄረሰቦቹን የሙዚቃ ኣከዋወን ቀደም ብሎ የሚያውቅ ግለሰብ በሙዚቃው ብቻ ተመስጦ ጠለቅ ብሎ ከማስተዋል ካልታቀበ በስተቀር ይህ የእገሌ፣ ይህ ደግሞ የእገሌ ብሄረሰብ ሙዚቃ ነው ማለት ኣይገደውም። ብዙ ብሄረሰቦች ያሏትን ኢትዮጵያ በዚህ ኣነስተኛ ጽሁፍ ለመግለጽ መሞከር «ኣባይን በጭልፋ» ነውና እንዲያው በኣጭሩ የልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ጭፈራና የኣዘፋፈን ስልት የየራሳቸው ትእምርትና መለያ ነው ብለን እናብቃ።

ዋናው ጉዳያችን ወደሆነው መመገቢያ ቁሳቁስ የፎክሎር ትእምርታዊ ፋይዳ ስንመጣም ከዚህ በላይ ከተገለጸው የተለየ ኣይሆንም። ምክንያቱም የመመገቢያ ቁሳቁሶችም ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉበት ትእምርታዊነት (Sybmolical) ሚና ኣላቸውና። ይህን ጉዳይ ግልጽ ለማድረግ በኦሮሞ ባህል ተተኳሪነት ሁለት ምሳሌዎችን ልጥቀስ።

ከኦሮሞች ባህላዊ መመገቢያ እቃዎች ኣንዱ «ገበታ» (Gabataa) ነው። «ገበታ» በባሌም ሆነ በወለጋ ስያሜው ኣንድ ነው። ይሁን እንጂ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች የሚጠቀሙበት «ገበታ» እና በወለጋ ያለው «ገበታ» በተለይ የመመገቢያ ክፍሉ (እንጀራ ወይም ገንፎ ወይም «ቡራቶ» የሚቀመጥበት ለማለት ነው) ይዘትና ቅርጹ ልዩነት ኣለው። በሁለቱም ዞኖች ውስጥ የሚገኙት ገበታዎች ከእግራቸው ረዣዥሞችና እንደ ገበታው የኣሰራር መጠን እስከ 50 ሳንቲ ሜትር የሚደርሱ ናቸው። ከመሬት ጋር የሚገናኘው ዋናው መቆሚያቸውም ዘርጠጥ ያለ ነው። የሁለቱ ገበታዎች ዋናው ልዩነት በምግብ ማስቀመጫው የገበታው ክፍል ላይ በመሆኑ የጎባው ገበታ የጎረጎደ ሲሆን የወለጋው ግን ዝርግ እና ሰፊም ነው። ይሁን እንጂ የሁለቱም ዞኖች ገበታዎች ከኣንድ እንጨት ተፈልፍለው የሚሰሩ ባህላዊ መመገቢያ እቃዎች ናቸው።

የጎባው «ገበታ» ጎርጓዳ በመሆኑ «ቡራቶ» የተባለውን ባህላዊ ምግብ እዚያው ውስጥ ያሹበታል። «ቡራቶ» የበሶ ዱቄትና ቅቤ ብቻ በውህደት የሚሰሩት ምግብ ነው። በገበታው ውስጥ «ቡራቶ»ውን የማዘጋጀቱ ተግባር ሁልጊዜም ባይሆን ገበታው ኣጎራጎዱ ሰፊ ከሆነና ግራና ቀኝ ደግፈው የሚይዙ ወንዶች ካሉ ዱቄቱንና ቅቤውን ያዋህዱበታል። በአንጻሩ የወለጋው ገበታ ብዙ እንጀራ እንዲይዝ ታስቦ የሚሰራ በመሆኑ ዝርግ እና ሰፊ ነው። ስለዚህ የጎረጎደው ገበታ ለጎባ ወረዳ ኦሮሞ ትእምርታዊ ፋይዳ ሲኖረው ዝርጉና ሰፊው ገበታ ደግሞ ትእምርታዊ ፋይዳነቱ ለወለጋ ኦሮሞዎች ነው። በዚህም የተነሳ ለኣንድ ባህሉን ለሚያውቅ ሰው ሁለቱን ገበታዎች ቢያቀርቡለት በየኣድራሻቸው ይልካቸዋል፤ ምክንያቱም በኣንድ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ ለሚገኙት የሁለቱ ዞኖች (ወለጋና ባሌ) ባህላዊ የመመገቢያ ገበታ የሆነው ቁስ ቅርጽና ኣጠቃቀም በእየዞኖቹ ለሚገኙት የኦሮሞ ብሄረሰቦች ልዩ መለያና መታወቂያ ምልክት (ትእምርት) ነውና።

ወደ ጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ልመልከትና ሌላ ኣንድ ምሳሌ ላክል። «ኤለምቱ» (Elemtuu) ማለቢያ ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ጨሌዎችና ነጫጭ ዛጎሎች ትሽለማለች፤ በጠፍር ጥብጣቦች (Straps) ተውባ ትታያለች። ተምሳሌትነቷም የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች በተለይም የሴቶቹ እንደሆነች መገመት ይቻል ይሆናል። ምክንቱም ሴቶቹ ራሳቸውን የሚያስውቡትና የሚያጌጡበት መዋቢያ ለማለቢያዋ ከሚጠቀሙበት መዋቢያ ቁሳቁስ ጋር ኣንድ ነውና። በኣጠቃላይ የፎክሎር ትእምርታዊ ፋይዳ በፎክሎር ዘርፎች ሁሉ በየኣህጉሩ፣ በየኣገሩ፣ በየክልሉ፣ በየዞኑና በየወረዳው ወዘተ. የሚገኙ ህዝቦችንና ብሄረሰቦችን ማንነት ኣጉልቶ የሚያመለክት ነው። ጆርጅስ ሮበርት ኤ እና ሚካኤል

ኦውን ጆንስ (Georges Robert A and Michael Owen Jones) «Introduction: Folklore and its study» በሚለው ጽሁፋቸው የፎክሎርን ተምሳሌታዊነት እንደሚከተለው ገልጸውታል፡

> *እርስ በእርሳችን ተገናኝተን በየቀኑ በሚገጥመን መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ስንነጋገር ወይም የምናውቀውን፣ የምናስበውን፣ የምናምንበትንና የሚሰማንን ጉዳይ ስንናገር በአብዛኛው ተምሳሌታዊ በሆነና ራሳችንን ከሌላው በቀላሉ መለየት በሚያስችል ሁኔታ እንገልጻለን:: ይህም ለምሳሌ በማዜም፣ ሙዚቃ በመጫወት፣ በምሳሌያዊ አነጋገራችን፣ በዳንስ አደናነሳችንና አንዳንድ ነገሮችን በመፍጠርም ሊሆን ይችላል (1995፣1)::*

ቁሳቁሶች ፎክሎራዊ የሆነ ትእምርታዊ ፋይዳ እንዳላቸው ከዚህ በላይ በትንሹ በቀረበው ምሳሌ ጥቂት ግንዛቤ ሳንጨብጥ አልቀረንም:: በሌላ በኩል ነገሮች በልዩ ልዩ ምክንያቶችና መነሻዎች በየጊዜው ሲለዋወጡ እናያለን:: ለውጡ በመመገቢያ ቁሳቁሶችም ላይ ይከሰታል:: ዋናው ምክንያት ከባህል መለዋወጥ ጋር የሚመጣ ነው:: ለምሳሌ የባህል መወራረስ፣ የፋብሪካ ምርቶች በአዳዲስ አይነት፣ መጠንና ቅርጽ መፈብረክ ወዘተ. ናቸው:: ቀጥሎ የመመገቢያ ቁሳቁስን በተመለከተ ያለውን ለውጥ ለማሳየት ጥቂት ነገሮችን ልበል::

## 2.6 የመመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ ከጥንት እስከ ዛሬ

የሰው ልጅ ፍላጎት በማያቋርጥ ሂደት ላይ እስከአለ ድረስ የለውጥ እንቅስቃሴ ይኖራል:: ምክንያቱም ለውጡ የማያቋርጠው የሰው ልጅ ፍላጎት ነጻብራቅ ስለሆነ ነው:: እዚህ ላይ የሁሉንም አይነት መመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ ለማየት አንዳዳም:: ምክንያቱም በዚህ አጭር ጽሁፍ የሁሉንም አይነት መመገቢያ ቁሳቁስ ማየት ካለመቻሉም በላይ ከተነሳንበት አላማም ስለሚያርቀን ነው::

ቀደም ሲል ወደዚህ ጽሁፍ በሚያስገባን መንደርደሪያ ሀሳብ ላይ ለለውጥ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን በመጠኑ ጠቅሰናል:: ምክንያቶቹ ግን ከዚያም በላይ ይርቃሉ:: ለምሳሌ አንዳንድ ቁሳቁስ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን ብቻ የማስተናገድ አቅም ይኖራቸውና በልዩ ልዩ በአላት፣ በሰርግና በሀዘን፣ በደቦ ስራ ወዘተ. ወቅት በርከት ያሉ ተጋባዥ እድምተኞችን የማስተናገድ አቅም አይኖራቸውም:: ስለዚህ ሌላ ብዙ ሰዎችን የሚያስተናግድ እቃ ሊያስፈልግ ነው:: በሌላ በኩል ለአንድ አይነት ቁስ የመስሪያ ጥሬ እቃ ሲታጣ በሌላ መቀየር አስፈላጊ የሚሆንበትም ጊዜ ይኖራል:: በጦርነት፣ በስደት፣ በድርቅና በመሳሰሉት ህዝብ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ሲፈልስ ቀድሞ የነበረውን ባህል ይተውና የአዲሱን አካባቢ ህዝቦች ባህል ሊወርስ ይችላል፤ ሌላው ደግሞ አዳዲስ ቴክኖሎጂን ከመከተል አኳያ ወዘተ. ይከሰታል:: በዚህ ላይ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ወስደን እንመልከት::

«ቆሪ» (Qorii) ባህላዊ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች መመገቢያ እቃ ነው፡፡ እንደ ኣቶ በቀለ ቱፋ አገላለጽ ለወረዳው ኦሮሞ ብሄረሰቦች መመገቢያ እቃ ቆሪ መሰረት ጣይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቆሪ የተወሰኑ ተመጋቢዎችን ብቻ የሚያስተናግድ በመሆኑ በሰርግ፣ በደቦ ስራ፣ በልዩ ልዩ ክብረ በኣላት ወዘተ. ላይ ለሚቀርቡ ተጋባዥ እንግዶች እየከፋፈሉ በየቦታው ከመጋበዝ በኣንድ «ገበታ» መገላገሉን የመረጡት የብሄረሰቡ ኣባላት የሁዋላ ሁዋላ «ገበታ»ን ፈጠሩ፡፡ ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን ቆሪዎች ከኣገልግሎት መስመር ወጥተዋል ማለት ኣይደለም፡፡ ብዙ ሰዎችን በኣንድ ጊዜ ኣያስተናግዱ እንጂ ለቤተሰብ ኣባላት የሚሰለፉት፣ ለደራሽ እንግዳ ገንፎ ማቅረቢያ የሚሆኑት፣ ዘመድ ለመጠየቅ ቅቤ የጠገበ ገንፎ ተይዞ የሚወሰድባቸው ናቸው፡፡ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ደግሞ በጀበና ላይ የተከሰተውን ለውጥ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

ጥንታዊው የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ጀበና ቅርጹ እንደ ገንፎ ማገንፊያ ኦኮቴ (Okkotee) ማሰሮ የሚመስል ሆኖ ከገንፎ ማገንፊያው ማሰሮ የሚለየው ከወደ ኣፉ ሾጠጥ ማለቱ እና ቡናውን ለመቅዳት የሚያስችል ቅርጽ መያዙ ነው፡፡ ከዚህም በስተቀር ሁሉም ጀበናዎች ባይሆኑም ኣንዳንዶቹ የመያዣ ጆሮ ኣላቸው፡፡ የፈላውን ቡና ለመቅዳት ሲፈለግ የጀበናውን ጆሮ መያዝ ወይም ሲሊንደር ቅርጽ ያለውን ኣንገቱን መጨበጥ የተለመደ ነው፡፡ ከዚህም በላይ እንደ ዘመናዊው ጀበና ቡናው የሚወርድበት ጡት ስላልነበረው የሚቀዳው በኣፉ በኩል ነበር፡፡ ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የጥንታዊውን የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ጀበና የሚመለከት ሲሆን በኣሁኑ ጊዜ ግን የጥንቱ ጀበና የለም ወይም በኣንዳንድ እድሜ-ጠገብ ሰዎች ቤት ተወስኗል፡፡

ኣሁን ኣሁን ኦሮሞዎቹም ይሁኑ ሌላው ብሄረሰብ በስፋት የሚጠቀምበት ጀበና የመያዣ ጆሮና የመቅጃ ጡት ያለው፣ ኣንገቱ እስከ ጆሮው መጋጠሚያና እስከዋናው ኣካሉ ድረስ በሲሊንደር ቅርጽ ወይም በብርሌ ኣንገት ቅርጽ የተሰራ ነው፡፡ እንደ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ከሆነ ይህ ኣይነቱ ጀበና ከኣማራ መምጣት ጋር ኣብሮ ብቅ ያለ እና በኦሮሞዎች ቤት፣ ቤተኛ ሆኖ የቀረ ነው፡፡

በዚህ ኣይነት በመመገቢያ ቁሳቁስ ላይ ብዙ ኣይነት መለዋወጦች ተደርገዋል እየተደረጉም ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ ያለውን ለውጥ ስናጤን ደግሞ ለውጡ ምን ያህል ስርነቀል እንደሆነ ለማወቅ ብዙ ኣንመራመርም፡፡ ምክንያቱም የሰው ፍላጎት የወለደው የቴክኖሎጂ ለውጥ ኣለና፡፡ ዘመን ዘመንን በተካ ቁጥር፣ የነበረው ቁሳዊ ባህል ለኣዳዲስ ቁሳዊ ባህል ቦታውን ሲለቅ፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የቀድሞውን ቁሳዊ ባህል ኣውልቀው ኣዳዲስ ቁሳዊ ባህል ሲለብሱ፣ ኣብሮ በመኖር ሳቢያ የኣንዱ ባህል በሌላው ላይ ሲነግስ ወዘተ. እዚህ ተደርሷል፡፡ ይህ ዛሬ የምናየው የለውጥ እንቅስቃሴ ለመቆሙ ዋስትና የለምና ሂደቱ ይቀጥላል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የመመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ ከዚህ በላይ በተገለጹ ምክንያቶች ክሱት ይሁን እንጂ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ወደፊት እንደምናየው ከሸክላና ከስንደዶ ስራቶች በስተቀር ከሌሎች ጥሬ እቃዎች (ከቅል፣ ከቀንድ፣ ከእንጨት፣ ከቆዳ) ይሰሩ የነበሩ ቁሳቁስ አሁን አሁን ግን ሲሰሩ አይታይም:: የማይሰሩበትን ምክንያት አንጥሮ ለማውጣት ራሱን የቻለ ሰፊ የጥናት መስክ የሚጠይቅ ቢሆንም የዚህ ጥናት አቅራቢ ተዘዋውሮ ያገኘውን መረጃ ጭምቅ ሀሳብ በተከታይነት ያቀርባል::

1. በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገራት በፋብሪካ ደረጃ እየተሰሩ የሚወጡ ቁሳቁስ እንደ አሸን በመብዛታቸው የተነሳ የብሄረሰቡ አባላት የፋብሪካ ውጤት ወደሆኑ ቁሳቁስ በማዘንበላቸው::
2. በየጊዜው በሚከሰተው የደን መመናመን የተነሳ ነባር ቁሳቁሶችን እንደልብ ለመስራት የሚያስችል እንጨት ባለመኖሩ::
3. በተፈጥሮ የሚገኘውን የመስሪያ ጥሬ እቃ ወደ ቁሳዊ ባህል ይለውጡ የነበሩ ሙያተኞች አብዛኞቹ በሞት ስለተለዩ፣ ወይም አካባቢውን ስለለቀቁ፣ አልፎ አልፎ ቢኖሩም እንኳን የመስራት ፍላጎት ስለሌላቸው::
4. አልፎ አልፎ የደን ውጤት የሆኑ ዛፎችን ራቅ ካሉ ቦታዎች ለማምጣት ቢቻልም እንኳ ባህላዊ እቃዎቹን ሰርቶ የሚገኘው ጥቅም ግንዱን ለእንጨት ሞተር ቤቶች በመሸጥ የሚካበተውን ዳጎስ ያለ ገንዘብ የሚያካክሰው ባለመሆኑ::
5. የባህል እቃዎቹን ለመስራት የሚፈጀው ጊዜና ገንዘብ እቃዎቹ ተሸጠውም ሆነ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ የሚገኘውን ጥቅም የሚካክሰው ባለመሆኑ ::
6. ባህላዊ እቃዎቹ በገበያ ላይ ያላቸው ተፈላጊነት ከቀን ወደ ቀን እየቀነሰ ከመምጣቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ያሉትን ጥቂት ሙያተኞች የመስራት ስሜት እያዳከመው በመምጣቱ::
7. የደን ውጤቶች የሆኑትን ዛፎች ራቅ ካሉ ገደላማ ቦታዎች ቆርጦ ለማምጣት ያለው ውጣውረድ መገልገያ ቁሳቁሶቹን ሰርቶ ከሚገኘው ጥቅም ጋር ሲመዛዘን በጣም ከፍ ያለ መሆኑ::
8. የቀድሞቹ ነባር ቁሳቁስ የሁዋላ ቀርነት ምልክት ናቸው ተብሎ መታሰቡ::
9. ጥንታውያን የእደጥበብ ሙያተኞች ሙያቸውን ለልጆቻቸው ለማስተላለፍ ፍላጎት ያላቸው ሆነው አለመገኘት::
10. ዘመነኛው ወጣት ባህላዊ እቃዎቹን ለመስራትም ሆነ በአገልግሎት ላይ ለማዋል ፍላጎት ያለው ባለመሆኑ::
11. በጥቅሉ የባለሙያ፣ የመስሪያ ጥሬ እቃዎች አቅርቦት እየቀነሰ በመምጣቱ ናቸው::

## 2.7 በጥናታዊ ጽሁፉ ዙሪያ የተከናወኑ አገራዊ ስራዎች ክለሳ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ይዞት በተነሳው ርእስና በተተኳሪው ወረዳ ላይ በቀጥታ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች እንዳላጋጠሙኝ ቀደም ሲል በገጽ አንድ ላይ ጠቅሻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ቁሳዊ ባህልን መሰረት አድርገው የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች የጻፉ አንዳንድ ግለሰቦች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከዚህኛው ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር የበለጠ ቅርበት ይኖራቸዋል ያልኳቸውን ሶስቱን ብቻ በመውሰድ ከእኔ ስራ ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

«በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ የቤት እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች መዘርዝር ከነአገልግሎታቸው» (1986) በሚል የቀረበው የአሰገደች አወቀ ጥናት በአላማው ማሳየት የፈለገው የቤት እቃዎቹንና የእርሻ መሳሪያዎቹን ከማህበራዊ ስነልሳን ገጽታዎች ምልከታ አንጻር ማየት፣ ሌሎች ተመራማሪዎችን ለተመሳሳይ ጥናት ማነሳሳት ወዘተ. ነው፡፡ የአሰገደች ጥናታዊ ጽሁፍ በኦሮሞ ብሄረሰቦች ላይ በማተኮሩና የቤት ቁሳቁስን የተመለከተ በመሆኑ ከዚህኛው ጥናት ጋር የበለጠ የሚቀራረብ ይሁን እንጂ የመመገቢያ ቁሳቁሶችን አሰራር፣ አገልግሎት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ከሚተነትነው ከዚህኛው ጥናት ጋር የአቀራረብ ልዩነት አለው፤ ምክንያቱም የአሰገደች ጥናታዊ ጽሁፍ የቁሳቁሶችን ስም ከአጫጭር መግለጫዎቻቸው ጋር ከማስተዋወቅ ባሻገር ስለአሰራራቸው፣ አገልግሎታቸውና ባህላዊ ፋይዳቸው በትንተና የሚያቀረበው ነገር ስለሌለ ነው፡፡ በተጨማሪም ያተኮረችባቸውን የቁሳቁስ ስእሎች በአባሪነት ያስቀመጠች በመሆኗ የመመገቢያ ቁሳቁሶቹን ፎቶግራፎች ጎን ለጎን እያስተያየ ገለጻውን ከሚጽፈው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ (1993)፤ «የባህላዊ የቤት እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሀዲያ ብሄረሰብ» የሚል ሲሆን በጥናቱ ትኩረት የሰጠው የእቃዎቹን የነበረ ጠቀሜታ ማስተዋወቅ፣ የብሄረሰቡን ቋንቋ፣ ባህላዊና ፎክሎራዊ ይዞታ ማሳየት ነው፡፡ ምንም እንኳን የተሾመ እና ይህኛው ስራ በቁሳዊ ባህል ላይ ያነጣጠሩም ቢሆን በተተኳሪ ቦታ፣ በአቀራረብና በይዘት ልዩነት አላቸው፡፡

በ1995 ኣ.ም «የቤት ውስጥ እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሰሜን ወሎ በላስታ አካባቢ በግዳን ወረዳ» የሚል ርእስ በመስጠት ጥናት ያቀረበችው ጸጋ መለሰ በቁሳዊ ባህል ላይ አተኩራለች፡፡ አላማዬ ነው ያለችውን ስትገልጽ የጥናቷ ትኩረት አካባቢ ነዋሪ ቁሳዊ ሀብቱ ቢጠና ታሪኩን፣ ባህሉንና ቋንቋውን ለማጥናት ስለሚረዳ ይህንኑ በጽሁፍ መዝግቦ ለማቆየት መሆኑን ጠቁማለች፡፡ ዋናው ትኩረቷ ስያሜ ላይ እንጂ በእቃዎቹ አሰራር፣ ግልጋሎትና ባህላዊ ፋይዳ ላይ ባለመሆኑ ከዚህኛው ጥናት ይለያል፡፡ ከአላማ አኳያ ሁለቱም ጥናቶች የተወሰኑ መመሳሰሎች ቢኖሯቸውም በይዘት ግን ይለያያሉ፡፡

በጥቅሉ፣ ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ይዞት ከተነሳው ተተኳሪ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የተመሳሰለ፣ በተለይ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት አላጋጠመኝም:: በተለይ ደግሞ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት ያደረገበት የባሌ መስተዳድር ዞን ወይም በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰቦች ላይ የተሰራ ይህን መሰል ጥናት አላጋጠመኝም:: በዚህ የተነሳም ምናልባት ለዞኑ በተለይም ለጎባ ወረዳ ይህ ጥናት የመጀመሪያው ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ::

የዚህ ጥናት ሁለተኛ ምእራፍ የሆነውና ከዚህ በላይ የቀረበው ጽሁፍ «ትውፊታዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ»ን በስፋት የተመለከተ ነው:: በዚህም የአንድን ህዝብ ታሪክ ለመመርመር ትውፊታዊ ማስረጃዎች እና ባህላዊ ቅርሶች የቱን ያህል ጠቀሜታ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ተሞክሯል:: በተከታይነትም «ባህል ምንድን ነው?» የሚለው ርእስ መጠነኛ ሀሳብ ከተሰጠበት በሁዋላ ስለ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል የሚናገር ሀሳብ ቀርቧል:: ሌላውና የዚህ ምእራፍ አካል «ቅርስና የቅርስ አስፈላጊነት» የሚለው ርእስ ነው:: ተከታዩ ጽሁፍ «በጎባ ወረዳ የቅርሶች አጠባበቅና ይዞታ» የሚለው ነው::

ሌላው የጽሁፉ ይዘት «ፎክሎርና የመመገቢያ ቁሳቁስ» በሚል ንኡስ ርእስ የቀረበው ሲሆን በዚህም የመመገቢያ ቁሳቁስ ያላቸውን ፎክሎራዊ ገጽታ ለማሳየት ተሞክሯል:: በተጨማሪም የፎክሎርን ትእምርታዊ ፋይዳ የሚያስቀኘው ርእስ «ፎክሎርና ትእምርታዊ ፋይዳው» በሚል ቀርቧል::

የምእራፍ ሁለት ሌላው ይዘት «የመመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ ከጥንት እስከዛሬ» የሚለው ሲሆን በዚህም የሰው ልጅ ቁሳዊ ባህል በየጊዜው ለውጥ እያሳየ መምጣቱ ተመልክቷል:: በመጨረሻም ሶስት ቀደምት የዲግሪ ማሟያ ስራዎች በ«ጥናታዊ ጽሁፉ ዙሪያ የተከናወኑ አገራዊ ስራዎች ክለሳ» በሚል ርእስ ተቃኝተዋል:: በዚህም ይህን ምእራፍ በማብቃት ወደ ምእራፍ ሶስት እንተላለፍ::

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

# 3. የጎባ ወረዳ ማስተዋወቂያ

ይህኛው ምእራፍ ከዚህ በታች በሶስት ማእዘናት ውስጥ የተዘረዘሩትን ኣንኳር-ኣንኳር ኣርእስት የሚመለከት በመሆኑ ኣንድ በኣንድ ኣቀርባለሁ::

መግቢያ

32-34

የጎባ ወረዳ

34-45

ሀይማኖትና ልዩ ልዩ እምነቶች

45-47

የጎባ ወረዳ ርእሰ ከተማ ስም የትመጣ (Origin)

47-49

በባሌ መስተዳድር ዞን የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብን ቁሳዊ ባህል ተተኳሪ ያደረገው ይህ ጥናት ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳይ ከመግባቱ በፊት በምእራፍ ሶስት ላይ የማስተዋወቂያ ጽሁፍ ለማቅረብ ይሞክራል:: በዚህም መሰረት «የጎባ ወረዳ ማስተዋወቂያ» በሚል ኣቢይ ርእስ መነሻነት ሌሎች ንኡሳን ኣርእስት የተካተቱበት ጽሁፍ በዝርዝር ይቀርባል:: ይህ ምእራፍ በዝርዝር የቀረበበት ምክንያት የጥናታዊ ርእሱ ተተኳሪ ወረዳ በመሆኑ ነው:: ስለዚህም መልከኣ ምድራዊ ኣቀማመጡ፣ በወረዳው መስህብነት ስላላቸው ቦታዎች፣ የነዋሪው ብዛት፣ የብሄረሰቦች እና የቋንቋ ስብጥር፣ የኣየር ጠባይ፣ የህዝቡ የኑሮ መሰረት፣ ሀይማኖትና ልዩ ልዩ እምነቶች፣ የጎባ ወረዳ ርእሰ ከተማ «ጎባ» ለመባል የበቃበት ኣፈታሪካዊ ትንተናዎች በስፋት ተዳስሰዋል:: እነዚህ ዝርዝር ንኡሳን ኣርእስት በዚህ መልኩ እንዲቀርቡ የተደረገው ከጥናታዊ ርእሱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገናኙ በመሆናቸው ነው:: በዚህም መሰረት ከልዩ ልዩ ጸሀፍት የተገኙትንና ኣገሬውስ ምን ይላል? በሚል ጥያቄ መነሻነት የተዳሰሱትን መልሶች ሰንጠረዣዊ መግለጫዎችን ካካተተ ትንተና ጋር ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል::

ይሁንና የጥናታዊ ጽሁፉ ርእስ «በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ የምግብ ቁሳቁስ ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና» የሚል ሆኖ ሳለ ስለ ጎባ ወረዳ ማተቱ ለምን ኣስፈለገ? ከዋናው የጥናቱ ርእስ ጋርስ ያለው ፋይዳ ምንድነው? የሚሉ እና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ:: ጥያቄዎቹ ተገቢ እንደመሆናቸው ኣጠር ያለ መልስ መስጠቱም ኣስፈላጊ ነው::

ሁሉም ነገር በጊዜና በቦታ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ኣንድ ነገር በኣንድ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ይቆያል:: በዚህም መሰረት ስለኣንድ ብሄረሰብ ቁሳዊ ባህል ስንናገር የእዚያን ብሄረሰብ

መኖሪያ ክልሉን፣ መመገቢያ ቁሳቁሶቹም የሚሰሩበትንና የሚገኙበትን ቦታ መጥቀስ ተገቢም፣ አስፈላጊም ነው። በተጨማሪም የብሄረሰቡን ብዛት፣ የቋንቋና የብሄር ስብጥሩን ማሳወቅ ታሪካዊ ፋይዳም ይኖረዋል። ምክንያቱም የብሄረሰቦቹ መኖሪያ የት ነው? ምን አይነት ቁሳቁስ ይሰሩና ይጠቀሙ ነበር? ቁሳዊ ባህላቸውስ ምን ይመስላል? ቋንቋቸው፣ ሀይማኖታቸው ወይም በልማድ የሚተገብሯቸው ልዩ ልዩ እምነቶች ምን-ምን ነበሩ? ወዘተ. ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የምናገኘው የመኖሪያ ቦታዎቻቸውንና ቁሳቁሶቻቸውን ስንመረምር ነው። ባሳለፍናቸው ዘመናት «ድንቅነሽ» (ሉሲ) እና «ሰላም» የተባሉ የጥንታዊ ሰው ቅሪት አካላት የተገኙት በቁፋሮ ነው። ቅሪት አካላቱ የተገኙትም ጥንት ሰዎች ይኖሩበት ይሆናል ተብሎ ከሚገመት ቦታ ነው። ቅሪት አካላቱ የታሪክ መረጃ ሆነው ስለሚጠቀሱ የእነሱ ስም ሲነሳ የተገኙበት ቦታም አብሮ ይጠራል። በዛሬ ላይ ሆነን የትናንቱን እናጥና ስንል መሰረታችን የሚሆነው አገሩ፣ ቦታው፣ ነዋሪዎቹ፣ ቁሳዊ ባህላቸውና የመሳሰሉት መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል።

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የምንናገርላቸው ቁሳቁሶች ከምንም አይነት ጥሬ እቃዎች (ከእንጨት፣ ከሸክላ አፈር፣ ከቀንድ፣ ከቆዳ ወዘተ. ይሰሩ)፣ የት ቦታ ነው የተሰሩት? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ከዚህ በተጓዳኝ ስለብሄረሰቦች ባህላዊ ምግብ ስንናገር ምግቦቹ የተዘጋጁበት የእህል አይነት የበቀለው የት ነው? ምን አይነት የአየር ጠባይስ አለው? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። የእነዚህና መሰል ጥያቄዎች መልስ የሚገኘው ደግሞ በስርኣት ከተጻፈ የሰነድ ማስረጃ ነው። ስለ ነዋሪዎቹ ሀይማኖትና እምነት ስናወሳም ብሄረሰቦቹ የነበሩበት ቦታ ለሚከተሉት ሀይማኖትና እምነት ምን ያህል ተጽእኖ ያደርግ እንደነበር መጠየቃችን አይቀርም። በአጠቃላይ የነዋሪዎቹ ቋንቋ፣ ልማድ፣ ባህል ወዘተ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚኖሩበት የመኖሪያ ቦታ ጋር ስለሚያያዝ በአንድ ጥናት ውስጥ መጠቀሱ አግባብነት ይኖረዋል። አንድን ቦታ ነዋሪዎቹ ከሚጠቀሙበት ቁሳቁስ ጋር አጣምሮ ማስተዋወቁ ብሄረሰቡን ታሪኩንና ባህሉን ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች አንትሮፖሎጂስቶች አገሩንና ቁሳቁሶቹን በአንድ ከማየት አኳያ መንታ ጥቅም አለው።

«የጎባ ወረዳ ማስተዋወቂያ» በሚል ርእስ በተመለከተው በዚህ ጽሁፍ፣ የወረዳው ኦሮሞ ብሄረሰቦች የምግቦቻቸው ምንጭ ወተት እና ከወተት ተዋጽኦዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። ወተት የሚያገኙት ደግሞ ከሚያረቧቸው እንስሳት ነው። «ቡራቶ» እና «ገንፎ» የመሳሰሉት ባህላዊ ምግቦቻቸው ከገብስና ከስንዴ እንደሚዘጋጁ ተነግሯል። እንስሳቱም ሆኑ አዝርእቱ ከሚገኙበትና ከበቀሉበት ቦታ የአየር ጠባይ ጋር ግንኙነት አላቸው። ስለዚህ ነዋሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁስ፣ አልባሳትና ምግቦቻቸው ወዘተ. ሲጠቀሱ የአካባቢውን መልክአምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ጠባዩን ወዘተ. ማንሳት ታሪክንና ባህልን ከማሳወቅ አኳያ ሲታይ ፋይዳው የጎላ ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የሰዎች አኗኗር፣ አመጋገብ፣ አለባበስ ወዘተ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ

በኣካባቢው መልከኣምድርና የኣየር ጠባይ ተጽእኖ ስር ስለሚወድቅ ነው። ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ የታሪካቸውንና የባህላቸውን የትመጣ (Origin) ይነግረናልናም ነው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ካሉት 257 ወረዳዎች እና በባሌ መስተዳድር ዞን ከሚገኙት 19 ወረዳዎች ኣንዱ ስለሆነው የጎባ ወረዳን ወደሚያስቃኘን ጽሁፍ እናምራ።

## 3.1. የጎባ ወረዳ

በዚህ «የጎባ ወረዳ» በሚለው ኣቢይ ርእስ - የወረዳው መልክኣ ምድራዊ ኣቀማመጥ፣ መስህብነት ያላቸው ቦታዎች፣ የህዝብ ብዛት፣ የብሄረሰብ ስብጥር፣ የቋንቋ ስብጥር፣ የኣየር ጠባይና የህዝቡ የኑሮ መሰረት በሚሉ ንኡሳን ኣርእስት የተካተቱ ጽሁፎች ይቀርባሉ።

### 3.1.1. መልክኣ ምድራዊ ኣቀማመጥ

የባሌ ዞን መስተዳድር ካሉኣት ወረዳዎች ኣንዱ የሆነው የጎባ ወረዳ ርእስ ከተማ ጎባ ሲሆን ከኣዲስ ኣበባ በ445 ኪ.ሎ ሜትር ላይ በደቡባዊ ምስራቅ ኣቅጣጫ ይገኛል። እንደ Goba "AANAA" Administration Office (2005 እ.ኤ.ኣ.) ያልታተመ መረጃ፣ የጎባ ወረዳ በሰሜን ከሲናና ዲንሾ፣ በደቡብ ከመና ኣንጌቱ፣ በምስራቅ ከኣዳባ፣ በምእራብ ከጎሮ እና በርበሬ ወረዳዎች ይዋሰናል።

ከወረዳው እና ከጎባ ከተማ ኣስተዳደር በተገኘው መረጃ መሰረት የወረዳው ኣጠቃላይ የቆዳ ስፋት 1799.8 ካሬ ኪ.ሜ. ነው። ከደቡብ ኣቅጣጫ የሚታየው የወረዳው የመሬት ኣቀማመጥ ተራራማ፣ ዳገታማ፣ ኣባጣ ጎባጣ፣ ቁልቁለትና ገደላ ገደል ሲሆን ከወደ ሰሜናዊ ምእራብ ደን ለበስ፣ ዳገትና ሜዳን ኣጣምረው የያዙ ቦታዎች ኣሉት። ከምስራቅ እና ከሰሜን ኣቅጣጫ ሲታይ ደግሞ ሜዳማ የሆነ ክፍል ይበዛበታል። ጠቅለል ባለ ሁኔታ፣ ካለው የቆዳ ስፋት 35% ኣባጣ ጎባጣ፣ ገዳላ ገደልና ቁልቁለት ሲሆን የቀረው 50% ተራራማ፣ 15% ደግሞ ሜዳማ ነው (2005፣1)። ወረዳው ለኣስተዳደር በሚያመች መልክ በ15 የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ቢዋቀርም የጎባ ከተማን ሳይጨምር 23 የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ኣሉት።

ከጎባ ከተማ ወደ ደቡብ ኣቅጣጫ ሲኬድ የመሬቱ ኣቀማመጥ ከፍታ እስከ ሪራ መዳረሻ እየጨመረ ይሄዳል። ይህም ቀን ቀን ሞቃት፣ ከሰኣት በሁዋላ ጀምሮ ደግሞ እጅግ በጣም ቀዝቃዛ እስከሆነው የሳነቴ ኣምባ መጨረሻ ድረስ ይዘልቃል። «ትውውቅ» በሚል ርእስ የታተመ መጽሄት፣ ኣንድ የቢ.ቢ.ሲ. (BBC) ዘጋቢ ስለ ሳነቴ ኣምባ የተናገረውን ሲጠቅስ «በኣየር ላይ ያለ ደሴት» (An island in the air) ካለው በሁዋላ በሰራው ዶክመንተሪ



AAU LIBRARY (stamp)

ፊልም «ቀን ቀን ሳሀራ ማታ ማታ ሳይቤሪያ» ((ገጽ 35) በማለት ዘግቧል:: በሳሀራ እና በሳይቤሪያ መመሰሉ መሬቱ ከፍታ ስላለውና ለጸሀይ ጨረር ቅርብ ስለሆነ ቀን ቀን በጣም በመሞቁና ማታ ማታ ደግሞ ከፍተኛ ውርጭ ያለበት በመሆኑ ነው:: ይህ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን ቀይ ቀበሮ እና ጸጉራማ አይጠ መጎጦችን የያዘው የሳነቴ አምባ፣ በኢትዮጵያ 2ኛ የሆነውንና 4377 ሜትር ከፍታ ያለውን የቱሉዲምቱን እንዲሁም በሶስተኛ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነውንና 4297 ሜትር ከፍታ ያለውን የባቱ ተራሮችን ይዟል:: ከዚሁ ጎን ለጎን በጣም ዝቅተኛ የሆነው ቦታም የሚገኘው በዚሁ በጎባ ወረዳ ሲሆን ከባህር ጠለል በላይ 1500 ሜትር ከፍታ ያለው በወቾ ሚሽርጌ ገበሬ ቀበሌ ማህበር አካባቢ ያለው ቦታ ነው (2005፣1)::

## ሰንጠረዥ 1፡ በጎባ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ዝርዝር

| ተ.ቁ | የገበሬ ማህበራት እና የከተማ ቀበሌ ስሞች | የማህበረሰቡ /መንደሩ/ መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1 | ወልታኢ ቶሻ | ሲንጃ |
| | | ቡርቂቱ |
| 2 | ኢቲቱ ሱራ | ሺፋሪዮ |
| | | ላሽቆና |
| | | ጋማ ጣጃ |
| 3 | ፋሲል ሀንጋሶ | ፋሲል ሀንገሶ |
| 4 | አሎሼ ጢሎ | ፋሲል ጢሎ |
| | | አሎሼ |
| 5 | ወልታኢ አዚራ | ወልታኢ አዚራ |
| 6 | ሪራ | ሪራ |
| 7 | ወልታኢ ማጊዳ | ሚስራ |
| | | ዳዊ |
| 8 | አሹታ | አሹታ |
| 9 | ኢላሳ | ኢላሳ |
| | | አዋሻ ሀጋላ |
| 10 | ወልታኢ ቁብሳ | ከዱ |
| | | መቻመና |
| 11 | ወቾ ሚሺሪጌ | ወቾ ሚሺሪጌ |
| 12 | ወልታኢ ወቾ | ቡካ |
| | | ሶጊዶ |
| 13 | ሸደም | ሸደም |
| 14 | ኣዳባ ገፈጫ | ኣዳባ ገፈጫ |
| 15 | ዋጂቱ ሻቤ | ዋጂቱ ሻቤ |
| | አጠቃላይ | 23 |

*ምንጭ፡ ጎባ ወረዳ የገጠር ልማት ጽ/ቤት፣ 2005 ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ በሚያመች መልኩ የተወሰደ::*

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው አንዳንዶቹ የገበሬ መንደሮች ለአስተዳደር በሚያመች መልኩ እና ከቅርበታቸው አኳያ በአንድ ቀበሌ እንዲጠቃለሉ ተደርገዋል። ለምሳሌ ኢቲቱ ሱራ በስሩ ሶስት መንደሮችን ማለትም ሽፋሪዮን፣ ላሽቆናንና ጋማ ጣጃን ይዟል። አንዳንድ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ደግሞ ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ ናቸው፤ ለምሳሌ በተራ ቁጥር 3, 5, 6 ወዘተ. የተጠቀሱትን ማየት ይቻላል።

### 3.1.2. መስህብነት ያላቸው ቦታዎች

በኢትዮጵያ በከፍታቸው ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ተራሮች በጎባ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ቀደም ሲል በዚሁ ክፍል ተጠቅሷል። ከእነዚህ በስተቀር በባሌ ለቱሪስቶችም ይሁን ለሌላ የአይን ማረፊያ ከሆኑት የተፈጥሮ ስጦታዎች አንዱ የባሌ ተራራት ብሄራዊ ፓርክ ነው። ፓርኩ ካለው የቆዳ ስፋት አኳያ ከሚገኝባቸው ወረዳዎች አንዱ ደግሞ የጎባ ወረዳ ነው። (ሰንጠረዥ ሁለትን ይመልከቱ)። በፓርኩ ውስጥ በሌላው አለም የማይገኙ ቀይ ቀበሮ፣ ኒያላ፣ የምኒልክ ድኩላ፣ ትላልቅ ጸጉራማ አይጠመጎጦች ይገኛሉ። (ትውውቅ ገጽ 35)። መስከረም 22 ቀን 1999 ኢ.ም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን «ሀገሬ» ፕሮግራም በተላለፈው መሰረት ይህ ከባህር ጠለል በላይ 2500 ሜትር ከፍታ ያለው ብሄራዊ ፓርክ በውስጡ ካሉት ከ200 በላይ አእዋፋት 16ቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትንም ይዟል። <u>Atlas of Bale Zone</u> መጽሀፍ እንዳረጋገጠው የባሌ ብሄራዊ ፓርክ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት 52% ያህሉን አጥቢ እንስሳት እና 60 ያህል የወፍ ዝርያዎችን ይዟል።

መስከረም 5 ቀን 1999 ኢ.ም የኢትዮጵያ ሬዲዮ «ኢትዮጵያን እንቃኛት» ሳምንታዊ ፕሮግራም መስከረም 22 ቀን 1999 ኢ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን «ሀገሬ» በሚለው የማስተዋወቂያ ፕሮግራም ስለባሌ መስተዳድር ዞን መስህብ ስፍራዎች በተለይ በጎባ ወረዳ ላይ ያተኮረውን እንደሚከተለው አስቀምጠውታል።

> *በሀዋ ላይ የሚገኝ ምድር (An island in the air) የሚባለው፣ ከጎባ በስተደቡብ የሚገኘው የሳነቴ አምባ 695 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው። ይህም ከ3800 - 4377 ሜትር ከፍታ ያለው ነው። በአፍሪካ ከሚገኘው ውርጭ 80% በኢትዮጵያ የሚገኝ ሲሆን ከዚህ አህዝ የሳነቴ አምባ 64% ይዟል። የሳነቴ አምባ ከባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ 31.6% የቆዳ ስፋት ይጋራል። በዚሁ አምባ ትልቁን ፍልፈል ጨምሮ 8ቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ 13 የአይጥ ዝርያዎች አሉት። ለባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ መጠሪያ የሆኑት በኢትዮጵያ 2ኛ ደረጃ ከፍታ ያለውና 4377 ሜትር ርዝማኔ ያለው የቱሉዲምቱ፣ ከቱሉ ዲምቱ ቀጥሎ 4297 ሜትር ከፍታ ያለው የባቱ ተራራ፣ ከባቱ ተራራ ቀጥሎ 4205 ሜትር ከፍታ ያለው የቀራሪማ ተራራ እና ሌሎችም ኮንቴ፣ ዋረቡና ዋሳማና የተባሉ ተራሮች ናቸው።*

ሰንጠረዥ 2: የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች

| ተ.ቁ | የመስህቡ ቦታ ስም | የሚገኝበት ወረዳ | የሚገኝበት ርቀት | | በቦታው ላይ የሚታዩ ልዩ ልዩ አዳዲስ ነገሮች | አሁን የሚገኝበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከፊንፊኔ | ከሮቤ | | |
| 1 | የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ* | ሲናና ዲንሾ፣ ጎባ፣ ኣዳባና መና ኣንጌቱ፣ የፓርኩ ጽ/ቤት በዲንሾ ከተማ ይገኛል | 400 | 30 | የኣፍሪካ ከፍተኛ የተፈጥሮ ቦታዎችና ምህዳር ነው:: በሌላው ኣለም የማይገኙ እጽዋትና እንስሳትን ይዟል | በፓርኩ ክልል የሰዎች መስፈር ተጽእኖ ይታይበታል |
| 2 | የሶፍ ኡመር ዋሻ | ጎሮ የወይብ ወንዝ ከሚያልፍበት ላይ | 530 | 100 | ኣስደናቂ የተፈጥሮ ዋሻ | እስከ ዋሻው መዳረሻ መንገድ ተሰርቶለታል |
| 3 | ድሬሼክ ሁሴን | ጎሎልቻ | 600 | 170 | የእስላሞች መንፈሳዊ ገዞ | እስከ ጃራ ከተማ በቀላሉ ያስኬዳል |
| 4 | መዳ የተፈጥሮ ምንጭ | መዳ ወላቡ | 662 | 232 | የተፈጥሮ ምንጭ፣ ኣስራ ኣንድ ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰፋፊ ዛፎች | ከፍተኛ ደረጃ የመንገድ ችግር ኣለበት |

*ምንጭ: የባሌ ዞን ኣትላስ፣ የኣርሲ ባሌ የገጠር እድገት ፕሮጀክት (ጁላይ፣ 2004)*

* በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ሁሉም የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች በባሌ መስተዳድር ዞን የሚገኙ ሲሆን በተለይ በተራ ቁጥር ኣንድ ላይ የተጠቀሰው የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ግን ከቆዳ ስፋቱ የተወሰነው ክፍል በጎባ ወረዳ ውስጥ ይገኛል::

### 3.1.3. የህዝብ ብዛት

በ1994 እ.ኤ.አ. በተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ስታትስቲካዊ መረጃ መሰረት የጎባ ወረዳ ህዝብ ብዛት 59,028 እንደሆነ ተዘግቧል:: ከዚህ ኣሀዝ የወንዶች ቁጥር 28,362 ሲሆን፣ የሴቶቹ ደግሞ 30,666 ነው:: በከተማ ከሚገኘው 28,358 ነዋሪ ውስጥ የወንዶች ብዛት 13,155 ሲሆን የተቀሩት 15,203 ሴቶች ናቸው::

የገጠሩን ነዋሪ በተመለከተ እ.ኤ.አ. የ1994 ቆጠራ እንደሚያመለክተው፣ ከጠቅላላው 30,670 የገጠር ነዋሪ ውስጥ ወንዶቹ 15,207 ሲሆኑ፣ 15,463ቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው:: ከተሰጠው መረጃ ተነስተን ያለውን የህዝብ ብዛት በደረጃ ብናስቀምጥ ካሉት የዞኑ ወረዳዎች የጎባ ወረዳ የ11ኛ ደረጃን ይዟል::

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የህዝብ ቁጥር ከ1996 እና 1997 ኣ.ም ወዲህ ያሻቀበ ይመስላል:: የጎባ ወረዳ ኣስተዳደር ጽ/ቤት (Goba Aana Administration Office 2005፣ V) መረጃ እንደሚያመለክተው የጎባ ከተማን ሳይጨምር በ23ቱ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ያለው ህዝብ 41,091 ሲሆን፣ ወንዶቹ 20,244፣ ሴቶቹ ደግሞ 20,847 ናቸው:: በሌላ በኩል ከጎባ ከተማ የህዝብ ኣደረጃጀት ጽ/ቤት በ1999 ኣ.ም ያልታተመ ኣመታዊ መጽሄት መሰረት የጎባ ከተማ የህዝብ ብዛት 48,326 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ወንዶቹ 23,138፣ ሴቶቹ 25,188 ናቸው:: በዚህም መሰረት የወረዳው ህዝብ ኣጠቃላይ ድምር 89,417 መሆኑ ነው:: ይህም እ.ኤ.አ. በ1994 ከህዝብና ቤት ቆጠራ ከተገኘው ኣሀዛዊ መረጃ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ልዩነት ታይቷል:: የከተማው ነዋሪ በገጠር ካለው ህዝብ ይልቅ ቁጥሩ ኣመዝኖ የሚታየው በየጊዜው ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባው የህዝብ ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመምጣቱ ነው::

**ሰንጠረዥ 3: በባሌ ዞን፣ በጎባ ወረዳ የገጠርና ከተማ ነዋሪዎች በቆጠራና በግምት የተገኘ የህዝብ ብዛት በጾታ (እ.ኤ.አ. 1994)**

| | ሁለቱም ጾታዎች | ከተማና ገጠር | | ከተማ | | | ገጠር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት |
| ባሌ ዞን | 1,217,864 | 603,895 | 613,969 | 130,307 | 62,976 | 67,331 | 1,087,557 | 540,919 | 546,638 |
| ጎባ ወረዳ | 59,028 | 28,362 | 30,666 | 28,358 | 13,155 | 15,203 | 30,670 | 15,207 | 15,463 |

*ምንጭ: የማእከላዊ እስታትስቲካል ባለስልጣን የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን (እ.ኤ.ኣ፣ 1994)*

* *ከዚህ በላይ የቀረበው ኣመልካች ሰንጠረዥ ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ብቻ ኣስፈላጊ ነው ተብሎ የተወሰደ በመሆኑ በሰንጠረዡ የነበሩትን ሌሎች የባሌ ዞን ወረዳዎችን ኣላካተተም::*

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

### 3.1.4. የብሄረሰብ ስብጥር

በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል እንደሚስተዋለው ቁጥራቸው ይነስም ይብዛ፣ በጎባ ወረዳ ውስጥ በርካታ ብሄረሰቦች አሉ። የኢትዮጵያን ማእከላዊ እስታትስቲክስ ባለስልጣን (CSA[4] 1994, GC) እንደሚያመለክተው በጎባ ወረዳ ከነበሩት 59028 ነዋሪዎች ውስጥ ኦሮሞዎች 37267፣ አማራዎች 19655፣ ቤተጉራጌዎች 772፣ ወላይታዎች 456፣ ትግሬዎች 425፣ ዶርዜዎች 189፣ ወርጂዎች 72፣ ጋሞዎች 38፣ ጎፋዎች 2፣ ሌሎች በጥቅሉ 352 ነበሩ። ከዚህ ትንታኔ እንደታየው የኦሮሞዎች ብዛት ከፍተኛውን ቁጥር ይዟል። ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያም አንጻር ሲታይ እውነታን ያዘለ ነው። ምክንያቱም በህዝብና ቤት ቆጠራ (1994፣ 40 ቅጽ ሁለት ላይ) የብሄረሰቦችን ስብጥር አስመልክቶ ከአገሪቱ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ኦሮሞዎች 32.1 ፐርሰንት፣ አማራዎች 30.1 ፐርሰንት እንደሆኑ ይጠቁመናልና ነው። ይህንን ነጥብ በዞን ደረጃም ብናየው እርግጠኝነቱ በጉልህ ይንጸባረቃል። የቆጠራው ውጤት፣ የባሌን መስተዳድር ዞን ጠቅሶ እንዳረጋገጠው «ከእያንዳንዱ 1000 ሰዎች ውስጥ ኦሮሞዎች 88.93 ፐርሰንት፣ አማራዎች 7.65 ፐርሰንት ሲሆኑ የቀሩት የልዩ ልዩ ስብጥር ብሄረሰቦች ናቸው» (1994፣ 39)።

የብሄረሰቦች ስብጥርን በተመለከተ በተለይ ኦሮሞዎች እና አማራዎች ላይ በማተኮር የጎባ ወረዳን ስንቃኝ ከከተማ ይልቅ በገጠሩ የኦሮሞ ነዋሪዎች ቁጥር ያመዝናል። በከተሞች አካባቢ ደግሞ ቁጥራቸው በመመጣጠን ወይም አማራዎች በመጠኑ በለጥ ብለው የሚታዩበት ሁኔታ አለ። ለዚህ የጎባ ከተማን እንደማስረጃ መጥቀስ ይቻላል። በ(CSA 1994, GC) ስታትስቲካዊ መረጃ በጎባ ከተማ 57.7% የሚሆኑት አማራዎች ሲሆኑ የተቀሩት 42.3% የሚሆኑት ኦሮሞዎችና ልዩ ልዩ አናሳ ቁጥር ያላቸው ብሄረሰቦች ናቸው። በአጠቃላይ በጎባ ወረዳ ውስጥም ሆነ በባሌ ዞን ከፍተኛውን ቁጥር 3/5 ወይም 62.1 ፐርሰንት በላይ የሆነውን አህዝ የያዙት ኦሮሞዎች ናቸው (1984 እ.ኤ.አ፣ 38)።

### 3.1.5. የቋንቋ ስብጥር

በጎባ ወረዳ ውስጥ የተለያዩ በርካታ ብሄረሰቦች እንደመኖራቸው የተለያዩ ቋንቋዎችም ይነገራሉ። በወረዳው በብዛት የሚገኙት ኦሮሞዎች ስለሆኑ በገጠሩ አካባቢ በስፋት የሚነገረውም የኦሮምኛ ቋንቋ ነው። በተለይ የኦሮምኛ ቋንቋ የክልሉ የስራ ቋንቋ ከሆነ ወዲህ በከተሞችም የቋንቋው የስርጭት አድማስ ሰፍቷል። በእርግጥም ይህ ሁኔታ በ1984 እ.ኤ.አ. ከህዝብና ቤቶች ቆጠራ ከተገኘው እስታትስቲካዊ ዳታ በጣም የተለወጠ ይመስላል። ምክንያቱም ከ23 አመታት በፊት በጎባ ከተማ የአማርኛ ቋንቋ 86.5% ይነገር

[4] CSA:- Central Statistical Authority

የነበረው አሁን በእጅጉ አሽቆልቁሏል:: ለዚህ ለውጥ መከሰት ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል:: እነዚህም:-

1. የኦሮምኛ ቋንቋ የክልሉ ብሎም የዞኑ የስራ ቋንቋ በመሆኑ፣
2. የኦሮሞ ተወላጆች ከገጠር ወደ ከተማ በብዛት እየገቡ በመሆናቸው፣
3. የሌሎች ብሄረሰብ ህዝቦች ደግሞ አካባቢውን እየለቀቁ ወደ አዲስ አበባ እና ወደ ሌሎች ከተሞች የመሄዳቸው ውጤት ነው::

ቀደም ባሉት አመታት የነበረውን፣ በተለይ ማእከላዊ ስታትስቲክስ (1994 እ.ኤ.አ.) እንደሚያረጋግጠው ኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች 56.3%፣ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች 42.4%፣ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች 0.416%፣ የሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች በጥቅሉ 0.884% ነበሩ::

### 3.1.6. የአየር ጠባይ

የአንድ አካባቢ የአየር ጠባይ የሰዎችን አኗኗር ይወስናል:: ይህም በመጠለያቸው፣ በአለባበሳቸውና በአመጋገባቸው ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም:: በዚህም መሰረት ወደፊት በተለይ የአካባቢውን ቁሳዊ ባህል ስንመለከት ከአየር ጠባዩ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ጉዳዮች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ እዚህ ላይ ወረዳው ምን አይነት የአየር ጠባይ እንዳለው ማንሳቱና ማስተዋወቁ ተገቢ ይመስለኛል::

የጎባ ወረዳ ከጥቂት ወይናደጋነት ከሚታይባቸው አንዳንድ የገበሬ ቀበሌ መንደሮች በስተቀር በአብዛኛው የደጋነት የአየር ጠባይ ያይልበታል:: ይህ ደግሞ ከመሬት ገጽታው አኳያ የሚገመገም ነው:: በትክክል እንደሚታየው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሲታይ ሜዳማ ቦታዎች ይኑሩ እንጂ የተቀረው ዳገታማና ተራራማ አካባቢ ይበዛዋል:: ይህም ከጎባ ከተማ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲኬድ በብዛት የሚያጋጥም ነው::

«የጎባ ወረዳ የአየር ሙቀት በአማካይ ከፍተኛው 18°C ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 5°C ነው» Goba “AANAA” Administration Office (2005፣1):: የጥቅምት እና የግንቦት ወራት ቀዝቃዛና ሞቃታማ እንደሆኑ ይታወቃል:: የ«ትውውቅ» መጽሄት እንደዘገበው «ከመጋቢት እስከ ጥቅምት ወር መግቢያ ድረስ በክረምትነት ይታወቃል፤ አልፎ አልፎ የጥቅምት ወር በቅዝቃዜ ወይም በዝናባማነት የሚያልፍበት ሁኔታ ይከሰታል:: ከህዳር እስከ የካቲት ለአራት ወራት በጋ የአየር ንብረት ይንጸባረቅበታል» (ገጽ 35)::

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

የወረዳው የአየር ጠባይ በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚታየው ሁሉ ሁልጊዜ በየአመቱ አንድ አይነት (Constant) እንደሆነ የሚቀጥል አይደለም:: ይህንን መሰረት አድርጎ የጎባ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት እንደጠቆመው «ወረዳው በአመት ሁለት ጊዜ ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን ከፍተኛው የዝናብ መጠን ከሰኔ እስከ ጥቅምት መግቢያ ድረስ ክረምት የሚባለውን ወቅት ሲይዝ መካከለኛው የዝናባማ ወቅት ደግሞ ከመጋቢት እስከ ሚያዚያ መጨረሻ ድረስ ይዘልቃል፤ ከፍተኛው የወረዳው የዝናብ መጠንም 1300 ሚሊ ሜትር ነው» (2005፣2):: የወረዳው ጠቅለል ያለ የአየር ጠባይ ይህንን ከመሰለ በዚህ ላይ የተመሰረተው የህዝቡ ኑሮስ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ እንፈልግ::

## 3.2 የህዝቡ የኑሮ መሰረት

የሰው ልጅ የኑሮ መሰረት ለመብላት፣ ለመጠጣት፣ ለመልበስ፣ የራሱን መጠለያ ለማዘጋጀትና በአጠቃላይም ፍላጎቱን ለማሟላት ከተፈጥሮ ጋር ከሚያደርገው ትግል ይመነጫል:: በዚህም መሰረት የጎባ ወረዳ ህዝብ የኑሮ መሰረት በተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ የተመሰረተ ነው:: ነዋሪው እንደፍላጎቱ እና እንደገጠመኙ የሚያከናውናቸው በርካታ የስራ መስኮች - የመንግስት ስራ፣ ሽመና፣ የሸክላ ስራ፣ ንግድ ወዘተ. ተግባራት ቢኖሩም አብዛኛው ነዋሪ የሚሳተፍባቸውን የግብርናን እና ከእሱ ጋር የሚጣመረውን የከብት ማርባት ስራዎችን ብቻ እንመለከታለን::

### 3.2.1 የግብርና ስራ

አብዛኛው የወረዳው ህዝብ ኑሮው የተመሰረተው በግብርና እና በተጓዳኝነት በሚከናወኑ ከብት ማርባት፣ ንብ ማነብ እና የመሳሰሉትን በመስራት ነው:: የGoba "AANAA" Administration Office መግለጫ «የባሌ ዞን በአጠቃላይ እና በተለይ ደግሞ የጎባ ወረዳ የኢኮኖሚ መሰረት ግብርና ነው» (2005፣8):: የወረዳው ህዝብ የገቢ ምንጭ በአመዛኙ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከግብርና የሚገኝ ነው:: በወረዳው ውስጥ ያለው ተስማሚ የአየር ጠባይ የተለያዩ አይነት ሰብሎችን ለማምረት እገዛ አድርጓል:: ከእነዚህም:- ገብስ፣ ስንዴና አጃ ግንባር ቀደም ተመራች ሲሆኑ በተከታይነት የቅባት እህሎች ይገኛሉ:: ለእርሻ ስራ በጥቅም ላይ ከዋለው መሬት የጥራጥሬ እህሎች 90 በመቶውን ሲይዙ የቅባት እህሎች ደግሞ 8 ከመቶ ናቸው:: «በ2003 እ.ኤ.አ. የእርሻ ናሙና ቆጠራ ተወስዶ በተደረገው ጥናት መሰረት አንድ የገጠር ቤተሰብ በአማካይ 0.48 ሄክታር ይዞታ እንደነበረው ያሳያል» (2005፣9)::

ሰንጠረዥ 4፡ በጎባ ወረዳ በሁለቱም የምርት ወቅቶች የግል ገበሬዎች ግምታዊ የእርሻ ይዞታና ወቅታዊ የሰብል ውጤት

| የሰብል ኣይነት | የይዞታ መጠን | ስፋት | የተመረተው መጠን | የተገኘው ምርት |
|---|---|---|---|---|
| | | በሄክታር | በኩንታል | የኩንታል መጠን በሄክታር |
| ወቅታዊ ሰብሎች | 7620 | 15,755.74 | 186,714.13 | |
| እህል | 7,397 | 15,493.52 | 164,114.86 | |
| የኣገዳ እህሎች | 7,323 | 14,115.78 | 153,815.13 | |
| ጤፍ | 109 | 33.60 | 72.15 | 2.15 |
| ገብስ | 6,764 | 7,284.97 | 72,190.82 | 9.91 |
| ስንዴ | 4,722 | 4,932.24 | 63,490.08 | 12.87 |
| በቆሎ | 799 | 72.60 | 1,022.29 | 14.08 |
| ኣጃ | 4,260 | 1,789.36 | 17.020.71 | 9.51 |
| ጥራጥሬ | 3,558 | 1,208.80 | 9,247.18 | |
| ባቄላ | 1,932 | 420.11 | 6,357.31 | 15.13 |
| ኣተር | 2,190 | 639.07 | 2,441.99 | 3.82 |
| ሽንብራ | 109 | 8.97 | 133.78 | 14.91 |
| ኣብሽ | 428 | 30.13 | 85.29 | 2.83 |
| የቅባት እህሎች | 478 | 168.94 | 1,052.31 | |
| ተልባ | 394 | 166.32 | 1,046.00 | 6.29 |
| ኣትክልቶች | 993 | 27.05 | 1,942.22 | |
| ጥቅል ጎመን | 169 | 4.76 | | |
| የኣበሻ ጎመን | 702 | 19.79 | 1,367.78 | 69.11 |
| ቃሪያ | 197 | | | |
| የስራ ስር ተክሎች | 3272 | 235.16 | 20,667.66 | |
| ቀይ ስር | 95 | 0.52 | 61.16 | 117.62 |
| ሽንኩርት | 4760 | 315.29 | 30,574.43 | 96.97 |
| ድንች | 1780 | 102.29 | | |
| ነጭ ሽንኩርት | 359 | 5.82 | 463.13 | 79.58 |

*ምንጭ፡ ማእከላዊ የእርሻ ምርምር ኮሚሽን ፣ የኢትዮጵያ የእርሻ ምርት ዝርዝር ናሙና (እ.ኤ.ኣ. 2001/2002)*

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ወረዳው በሰብል ምርቶች በከፍተኛ ደረጃ ጥራጥሬዎችን፣ ገብስና ስንዴን የሚያመርት ሲሆን ከኣትክልቶች ደግሞ ሽንኩርትና ድንች የላቀ ስፍራ ኣላቸው።

የሰው ልጅ ከዝቅተኛ የኣሰራር ደረጃ ተነስቶ ቀስ በቀስ የእርሻን ሙያ እያጠናከረ እንደመጣ የተለያዩ ጸሀፍት ያረጋግጣሉ። የእርሻ ስራ ጥንታዊነት ኣለው። ሰዎችን ወደ ልዩ ልዩ የተግባር መገልገያ እቃዎች ስራ ከመራቸውም ኣንዱ የእርሻ ተግባር እንቅስቃሴ የመጀመራቸው ሁኔታ ነው። ምክንያቱም ልዩ ልዩ ምርቶችን ለማምረት የሚያገለግሉትን የስራ መሳሪያዎች እንደ ማጭድ፣ ማረሻ፣ መጥረቢያና ፋስ ወዘተ. በኣጠቃላይ የምርት ማከማቻ ቁሳቁስን በእደ ጥበብም ሆነ በፋብሪካ ደረጃ ማመረት ነበረባቸውና ነው። «የተሻሻሉ የእርሻ ዘዴዎች፣ የሰው ልጅ ዘላቂ የመኖሪያ ቤቶች እንዲያንጽና የቤት እቃዎችም እንዲሰራ፣ እንዲኖሩትም ኣድርጎታል» (ሲዶኖቭ ማርቲን ገጽ 47)።

በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ ነዋሪዎችም የእርሻን ስራ በመጀመሪያ ቀስ በቀስ በእጅ ተይዘው በሚሰሩ መቆፈሪያዎች፣ በገሶዎችና በመኮትኮቻዎች ጀምረው ዛሬ ሞፈርና ቀንበርን በማዋደድ በበሬ እስከማረስ የደረሱት በሂደት ነው። ይሁን እንጂ ከ13ኛው እና ከ7ኛው ሺ. ኣመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት በመካከለኛው የድንጋይ ዘመን እንደተጀመረ የታሪክ ድርሳናት ያረጋገጡት የእርሻ ስራ ዛሬም ምንም ያህል የኣሰራር ጥበቡ ሳይለወጥ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ዘንድ ጥንታዊነቱን የሙጥኝ እንዳለ በመሰራት ላይ ነው።

### 3.2.2. ከብት እርባታ

የኣፋርና የሱማሌ ብሄረሰብ ኣባላት ለግመሎቻቸው የተለየ ክብር የሚሰጡትን ያህል ኦሮሞዎች ለከብቶቻቸው የሚሰጡት ኣለኝታነት ከግምት በላይ ነው። ምክንያቱም ከብቶች በኦሮሞዎች ባህል ልብስም፣ ጉርስም፣ ገንዘብም በኣጠቃላይ ሁሉም ነገር ናቸውና። የኦሮሞዎች ጥንተ-ታሪክ ከብትን እንደ ልጅ ከማየትና ከመንከባከብ የመነጨ በመሆኑ ኣብዛኛው የጦርነት ታሪካቸው ለከብቶቻቸው የተሻለ የግጦሽ ቦታ ከመፈለግ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም የተነሳ ለከብቶቻቸው ያላቸውን ፍቅር በተመለከተ ብዙ ማለት ይቻላል። ኦ.ባ.ቱ.ኮ. <u>የኦሮሞ ታሪክ እስከ ኣስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን</u> በሚለው መጽሀፉ ጥንት፣ ኦሮሞዎች ከሚኖሩባቸው በርካታ ቦታዎች ኣንዱ «ፉጉግ» የተባለው እንደሆነ ጠቁሞ ገለጻውን ሲቀጥል «ፉጉግ ለሰውም ሆነ ለከብት እርቢ ኣመቺ ከመሆኑ የተነሳ ኦሮሞዎች ለበርካታ ዘመናት ሰፍረው የኖሩበት የደጋ መሬት ሳይሆን ኣይቀርም» (1996፣ 69) ይላል።

የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ከብቶችንና ከእነሱ የሚያገኙትን ተዋጽኦ ለብዙ ኣላማ ያውሉታል። ለሰርግ ሆነ ለሀዘን ከብቶች ለመስዋእትነት የማይቀርብበት የኦሮሞ ባህል የለም ማለት ያስደፍራል። ከዚህም በላይ ከቀላል ጸብ እስከ ከፍተኛ መገዳደል ለሚኖረው ኣለመግባባት የእርቅ ኣውርድ ስጦታዎች፣ የጉማ (ካሳ) ተከፋይ በመሆን ያበጠውን የሚያስተነፍሱ፣ የተወጠረውን የሚያረግቡ ከብቶች ናቸው። ለታጨች ጉብል ቤተሰቦች

ለጥሎሽ የሚቀርቡ፣ ከተገባች በሁዋላም በስጦታ መልክ የሚበረከቱ፣ ሁሉንም ኣይነት ለሁሉም የሚሆኑ ናቸው ከብቶች:: የቆየ ኣፈ-ታሪክ ሲጠቀስ ደግሞ መገበያያ እና መለዋወጫ እንደነበሩ ይነገራል:: በኣጠቃላይ ከብቶች በኦሮሞዎች ዘንድ የኑሮኣቸው መሰረት፣ ዋልታና ማገር ወዘተ. ናቸው:: ከታሪክም ኣኳያ ሲታይ የኦሮሞ ባህልና ኣጭር ታሪክ በሚለው መጽሀፋቸው ጀቤሳ ኤጄታ «ሴቶቻቸው የሚያጌጡበት የቆዳ ልብስ ከሚመረጥ ጌጥ ኣንዱ ነው፤ .... ይህ የቆዳ ልብስ በልዩ ኣዋቂዎች የሚሰራ በጣም የሚያምር ስለሆነ ..... ከ40 እስከ 60 ጊደር ያወጣል» (1989፣230) በማለት ያረጋግጣሉ::

በጎባ ወረዳ ያሉ ኦሮሞዎች ከብቶቻቸውን የጨው ውሀ (ሆራ) በማጠጣት፣ ቦጂ (ጨውነት ያለው ኣፈር) በማብላት እና ወደ ተሻለ የግጦሽ ሳር በመውሰድ ይንከባከባሉ:: ለህጻናት ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ ኣብረዋቸው የሚያድጉ ጊደሮች ይሰጧቸዋል:: ይህ ኣይነቱ ኣሰጣጥ «ጉቱ ቡሳ» (ቁንጮ ማውረድ) በሚል ባህላዊ ኣጠራር ጊደር ተሰጥቶት ጸጉሩን ይላጫል» (1989፣44) በማለት ጀቤሳ ከጸሩት ጋር ይመሳሰላል::

ኦሮሞዎች በእርጥብ ነገር ይመሰጣሉ:: እርጥብ ሳር፣ ውሀ፣ ወተት እና የወተት ተዋጽኦዎች የኑሮኣችን ምንጭ፣ የእኛነታችን መለያ ነው የሚል የቆየ ኣባባል ኣላቸው:: «በኦሮሞ ፍልስፍና ህይወት ሆነ ማንኛውም ተፈጥሮ የሚመነጨው .... ከእርጥብ ነገር ነው የሚል እምነት ኣለ» (ኦ.ባ.ቱ.ኮ፣ 1996፣111):: ይህ እውነታ ቅቤ በመቀባት፣ ለተጋቢዎች ወተት በማጠጣት፣ እርጥብ ሳር በወተት ውስጥ እየነከሩ በመርጨት፣ ወተትን በኣፍ ተጎንጭቶ በመርጨት (እንትፍትፍ በማለት ወዘተ.) ይገለጻል:: ከህይማኖት እና እምነት ጋር በተያያዘ መልኩ በከብቶች ኣማካኝነት የሚፈጽሙኣቸው ስርኣቶች በቦረንትቻ፣ በመስቀልና በመሳሰሉት በኣላት ላይ ይንጸባረቃሉ:: «የኣባት እናት ኣያና ይከበራል፤ ይዘከራል:: ስለመጪው ዘመን ኣዋቂዎች ቃሉ[5] ይጠየቃል፣ ከብት ታርዶ ስለመጪው ሁኔታ ሞራ ይነበባል» (1996፣38)::

በከብቶቻቸውና ከእነሱ በሚገኘው ተዋጽኦ ላይ ጠንካራ እምነት ያላቸው የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት ባህላዊ ምግቦቻቸው ገንፎ፣ ጨኮ፣ ቡራቶ፣ ጨጨብሳና የመሳሰሉት ሁሉ የሚቀርቡባቸው ቁሳቁሶች በክብር ይሰራሉ፣ በክብር ይያዛሉ፣ በጌጣጌጦች ይሸለማሉ፣ የተለያዩ ለኣይን ማረፊያ የሆኑ ቅርጾችም ይወጣላቸዋል:: ለኣባወራው በተለይ የሚቀመጠው ቀዝቃዛ ወተት በደንብ በተዘጋጀችና፣ በተቆራሸች ባለማንጠልጠያ ጡንጦ በራስጌው ይቀመጣል ወይም በግድግዳ ይሰቀላል:: «ጽዳቱ በተጠበቀና በተቆራሸ ወይም በወይራ እንጨት በታጠነና በተወለወለ ጡንጦ የታለበው ትኩስ ወተት (ሚኢ) «Mi'ii» ተከድኖ ቅዝቃዜ በሚሰማው ቦታ ወይም በኣባወራው ኣልጋ በስተራስጌ ይሰቀላል» (መሀመድ ከዲር፣ 1988፣ 13):: ሲልቨር ማን ራይሞንድ (SILVER MAN, RAYMOND-) ETHIOPIA: TRADITIONS OF CREATVITY በሚል ርእስ ባዘጋጁት የልዩ ልዩ ጽሁፎች መድብል “Every Woman is an Artist:

[5] በገዳ ስርኣት ውስጥ የኦሮሞን የህይማኖት ተቋማት የሚመራ ግለሰብ



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

The milk containers of Elema Boru." በሚለው ንኡስ ርእስ ማርኮስ ባሲ (Marcos Bassi) ሲጽፉ «ጥገቶች ከመታለባቸው በፊት የወተት ማለቢያው ጥሩ መኣዛ ባለው የወይራ ማእጠንት (ቆራሱማ) ይቆራሻል:: ይህ ሳይደረግ በነባር ወተት ላይ አዲስ የታለበ ወተት አይጨመርም::» ካሉ በሁዋላ በመቀጠልም «የቆራስማው አሰራርና አጠቃቀም የወተቱን ጮጮ የውስጠኛ ክፍል ስለሚለበልበው ጥቁር፣ ጥቅጥቅ፣ ለስላሳና ጥሩ መኣዛ እንዲኖረው ያደርጋል:: አከዋወኑ የወተት እቃውን በተሟላ ሁኔታ ንጹህ ሲያደርገው ለወተቱም ጥሩ መኣዛን ይሰጠዋል .....» (1999፣ 84) በማለት ኦሮሞዎች ለወተት እቃዎቻቸው ያላቸውን ከበሬታ መስክረዋል::

ይህ እስከ ኣሁን የተገለጸው ኦሮሞዎች ስለ ከብቶች፣ ስለቁሳቁስ እና ምግቦች ያላቸው ኣመለካከት በጎባ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ኦሮሞዎችም ዘንድ ይንጸባረቃል:: የጎባ ወረዳ ደጋማ እና በከፊልም ወይና ደጋነት ያለው የኣየር ጠባይ ስለሚታይበት በኣካባቢው የቀንድ እና የጋማ እንስሳት በስፋት ይረቡበታል:: ከዚህ በተጨማሪም በጎች ደጋማውን የኣየር ጠባይ ስለሚቋቋሙ ገበሬው በብዛት ያረባል:: ከዚህ ጎን የፍየሎችም የእርባታ ሁኔታ የሚናቅ ኣይደለም:: ይህ ከእርሻው ጎን ለጎን የሚከናወነው እንስሳትን የማርባት ተግባር ንብን በማነብ እና ከንብ የሚገኘውን የማር ተዋጽኦ በመጠቀም ረገድም የማይናቅ ስራ እየተሰራ ነው:: በኣጠቃላይ በወረዳው ውስጥ የሚከናወነውን የእንስሳት እርባታ በተመለከተ የGoba Ana Administration Office ባልታተመ ኣንድ መጽሄት ላይ ያወጣው ጽሁፍ የሚከተለው ነው:: «ከሰብል ምርት ቀጥሎ ለወረዳው የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የእንስሳት እርባታ ነው:: በ(2003 እ.ኤ.አ.) በተደረገ ግምገማ በወረዳው 52,210 የቀንድ ከብቶች፣ 26,908 በጎች፣ 2,685 ፍየሎች፣ 9,935 ፈረሶች እና 1,045 በቅሎዎች እንዳሉ ታውቋል:: ከእነዚህም በተጨማሪ 24,038 ዶሮ፣ ቆቅ እና ጅግራ የመሳሰሉ የኣእዋፍ ዘሮች እና 3031 የንብ ቀፎዎች ነበሩ» (2005፣9)::

## 3.3 ሀይማኖትና ልዩ ልዩ እምነቶች

ኣንድ ህዝብ በሚከተለው ሀይማኖት እና ልዩ ልዩ እምነቶች ሳቢያ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ባህሉ ይገለጻል:: በሀይማኖት እና በእምነት ምክንያት የሚጠቀሙባቸው ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች፣ የማንነታቸው ማንጸባረቂያ የታሪካቸው ዱካ የመሆናቸው ጉዳይ ኣሌ ኣይባልም:: ኣንድ ተመራማሪም የታሪካቸውን ፈር እየቀደደ የመጨረሻው ግብ ላይ የሚደርሰው በሀይማኖት እና እምነት ሳቢያ የሚጠቀሙባቸውን መመገቢያ እቃዎች እየመረመረ መሆኑ እሙን ነው:: ከዚህም ኣንጻር ነው ይህን ጉዳይ እዚህ ላይ ማንሳት ኣስፈላጊ የሆነው::

የኦሮሞ ብሄረሰቦች የእስልምና እና ክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ናቸው:: ከዚሁ ጋር የፕሮቴስታንት፣ የካቶሊክ፣ የወንጌላዊ ኣማኞች ወዘተ. እንዳሉም ኣይታበልም::

ከሀይማኖት ጎን ለጎን ከኣምላክ (ዋቅ) ጋር ያገናኛሉ ተብለው የሚታመንባቸው እንደ ኢሬቻ፣ በረንትቻ፣ ኣቴቴ፣ ውቃቢና ኣውሊያ የመሳሰሉትም በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ይተገበራሉ:: እነዚህም ልዩ ልዩ እምነቶች በመጀመሪያ በኦሮሞዎች ዘንድ በስፋት ይንጸባረቁ እንጂ ኣብሮ መኖር በፈጠረው የባህል መወራረስ ምክንያት ኣማራዎች እና ሌሎች ብሄረሰቦችም ተግባራዊ እያደረጓቸው ነው:: ፍቅሬ ቶሎሳ (Fikre Tolossa) «Oromo Contribution to Ethiopian Civilization» በሚለው መጣጥፋቸው የሚከተለውን ጠቁመዋል:: «ኦሮሞዎች ለኣማራዎች ካበረከቷቸው መንፈሳዊ ኣስተዋጽኦዎች እሬቻ፣ ኣቴቴ፣ ኣውሊያ እና ውቃቢ የመሳሰሉትን እና እንስሳትን ለመስዋእትነት ማቅረብ የሚጠቀሱ ናቸው» (እ.ኤ.ኣ. 1993፣ 24)::

ኦሮሞዎች ዋቅ (ኣምላክ) እያሉ የማመናቸው ጉዳይ ጥንታዊነት ያለው ነው:: በምድር ላይ ልዩ ልዩ ጥፋት ዳግም እንዳይመጣ ለኣምላካቸው ምህላና ጸሎት ያቀርባሉ:: «....ጎፍታ መጬ ሰገሊ ኡማ ኡማሞታ ሁንዱማ (እግዚኣብሔር የሰራዊት ጌታ የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪ) እያሉ በመጸለይና በመለማመን ኖረዋል ኣሁንም ያምናሉ» (ጀቤሳ ኤጀታ፣ 1989፣17):: በጎባ ወረዳ ውስጥ ያሉ ኦሮሞዎችም እስላሞቹ «ኣላህ» ሲሉ ክርስቲያኖቹ «ዋቅ» የሚሉት ከዚህ ከቆየው ሀይማኖታቸው ተነስተው ነው:: «ኦሮሞዎች በሰፈሩበት ኣካባቢ ሁሉ.... ባህልና የግብርና ተግባር በመማር እንዲሁም የእስልምናና የክርስትና ሀይማኖቶችንና ስርኣቶችን ተቀበሉ» (ላጵሶ ጌ.ድሌቦ፣ 1982፣174)::

በጎባ ወረዳ የሚገኙ የኦሮሞ ክርስትና ኣማኞች ዋቅ (እግዚኣብሔር) ለሚሉት ኣምላካቸው የሚያደርጉት ስነ ስርኣት በገና፣ በመስቀል፣ በፋሲካ ጾም ፍች እና በመሳሰሉት በኣላት ይተገበራል:: በዚህም ጊዜ የበኣሉ ስርኣት የሚጠይቀውን ለማሟላት ዝግጅታቸውን በተለያዩ ቁሳቁስ በማጀብ ያከብራሉ:: ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ የሚታየው የልዩ ልዩ እምነት ጉዳይ ነው:: ይህ ደግሞ በሁሉም ብሄረሰቦች ዘንድ እየተተገበረ ያለ ጉዳይ ነው:: ኣንዱ የሚያምንበት መንገድ ስሙ ይቀየር እንጂ ሌላውም በተመሳሳይ ያምንበታል ወይም ለሀይማኖቱ መረማመጃ፣ ከኣምላኩ ጋር መገናኛ መንገድ ያደርገዋል:: ይህንን ነጥብ ፍቅሬ «ኦሮሞዎች በሰብኣዊ ፍጡራን ዘንድ 44 ኣውሊያዎች ወይም መንፈሶች ኣሉ ብለው ያምናሉ፣ ይህ ደግሞ 44 ታቦቶች ወይም 44 ቅዱሳን ኣሉ ብለው ከሚያምኑት ኣማራዎች ጋር ይመሳሰላል» (1993፣27) ብለውታል::

...S LIBRARY ...ABA UNIVERSITY

ይህ እንግዲህ ክርስቲያን ኦሮሞዎችና ኣማራዎች በእምነት ዙሪያ በተመሳሰሎ የሚያራምዱት የቆየ ልማድ የባህል መወራረስ የፈጠረው ጉዳይ ነው:: ምንም እንኳን የዚህ ጽሁፍ ኣላማ ቁሳዊ ባህል ላይ የሚያነጣጥር ቢሆንም ከሀይማኖት ወይም ከእምነት ጋር የሚሄድበት ኣጋጣሚ የሰፋ ስለሆነ ኣንዳንድ ምሳሌዎችን ማንሳት ተገቢ ነው:: ከእምነት ኣንጻር በኦሮሞውም ሆነ በኣማራው በስፋት የምትታወቀው «ኣቴቴ» ኣከዋወኗ በልዩ ልዩ ቁሳቁስ እና ኣልባሳት የተከበበ ነው:: በዚህም መሰረት ኦሮሞዎች ከጥንታዊ

ልማዳቸው ተነስተው በተለየ መንፈስ ያከብሯታል:: «ኣቴቴ የሴት መንፈስ ነች:: ኣንድ ኣይነት ጠባቂ መልኣክም እንደሆነች ይቆጠራል:: በሶስት መንገድም ትገለጣለች:: እነዚህም ኣቴቴ ግንቢ (ተከላካይ ኣምላክ)፣ ኣቴቴ ሀራ (የውሀ መንፈስ) እና ኣቴቴ ዱላ (የጦርነት ተከላካይ ወይም መልኣክ) በማለት ነው» (ፍቅሬ ቶሎሳ፣ እ.ኤ.ኣ. 1993፣28)::

በኣጠቃላይ በሌላው የኣለም ክፍልም ሆነ በኢትዮጵያ ሁለቱ፣ ክርስትናና እስልምና በእጅጉ የተስፋፉ ሆነው በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት ይሰጣቸው እንጂ በጎባ ወረዳ ኦሮሞች ዘንድ የፕሮቴስታንት፣ የካቶሊክ፣ የወንጌል ኣማኞች እና ሌሎችም የሀይማኖት እና የእምነት ዘርፎች እንዳሉ ይታወቃል::

## 3.4. የጎባ ወረዳ ርእሰ ከተማ ስም የትመጣ (Origin)

የጎባ ወረዳ መስተዳድር ርእሰ ከተማ የሆነችው ጎባ ይህን ስሟን ከመያዟ በፊት «ከርማሚዳ» በመባል ነበር የምትታወቀው:: ይሁን እንጂ «ጎባ» የሚለው ስያሜ ከየት ተገኘ? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመፈለግ ኣፈ-ታሪክን መመርመር ግድ ይላል:: ምክንያቱም «ኣፈ-ታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በኣብዛኛው በኣንድ በተወሰነ ኣካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ ኣንድ ገጽታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው» (ዘሪሁን ኣስፋው 1992፣31):: የብዙ ጊዜ የኣካባቢው ነዋሪ የሆኑት ሀጂ ፊቂ ሀሰኖ «'ከርማሚዳ' ተብላ ነበር የምትታወቀው» ይላሉ:: «'ከርማሚዳ' በኣካባቢው የነበሩ የስድስት ጎሳዎች መጠሪያ ነበር፤ እነዚህ ጎሳዎች በጥቅሉ 'ከርማሚዳ' ይባሉ ስለነበር ነዋሪዎቹ የእነሱን ስም ለቦታው ሰጡትና 'ከርማሚዳ' እየተባለች መጠራት ጀመረች» በማለት ከቆየ ትዝታቸው ይጠቅሳሉ::

በ1884 ኣ.ም እንደተቆረቆረች የሚነገርላት የጎባ ከተማ ኣሁን ያላትን ሰው ሰራሽ ውበት ከመያዟ በፊት የተለያዩ የዱር ኣራዊቶች የመሸጉበትን ደን ለብሳ እንደነበር በሰፊው ይነገራል:: «ለጎባ ከተማ መቆርቆር መነሻው የዳግማዊ ምኒልክ የመስፋፋትና ኣገርን የማቅናት እንቅስቃሴ ነው» (እንግዳየሁ ለገሰ እና ይልማ ጥበቡ 1979፣6-7)::

ለጎባ ከተማ «ጎባ» መባል የተለያዩ ኣፈ-ታሪኮች ያሉ ቢሆንም ለኣሳማኝነት ቀረቤ የሆኑትን በተከታይነት እጠቅሳለሁ:: የጎባ እና ኣካባቢው የመሬት ገጽታ ዳገታማ ነው:: መጀመሪያውኑ ጎባ ከተማን ለመመስረት ያበቃት ከጠላት ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል ዳገታማ ቦታ ላይ መሆኗ፣ የማገዶ እንጨት እና ከኣምስት ያላነሱ ወንዞችን የመያዟ ሁኔታ ነው:: የመልክኣምድሩን ኣቀማመጥ መነሻ ኣድርገው የኣካባቢው ነዋሪና የ89 ኣመት ኣዛውንት የሆኑት ኣቶ ኣበበ ወልደጻዲቅ የተናገሩትን (ኣበበ፣ 1995፣ 29) ጠቅሶ የጻፈው ተከታዩ ነው::

*ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በራስ ዳርጌ (አንዳንዶቹም ራስ ናደው ይላሉ) የሚመራ ሰራዊት መላካቸውንና ራስ ዳርጌም ከልጃቸው ከደጃዝማች አስፋው ዳርጌ ጋር አርሲን አቅንተው ወደ ባሌ እንደመጡ እና ጋሰራ ወረዳ በተለይ «ጉራንዳ» ከተባለው ቦታ ላይ እንደሰፈሩ ይነገራል:: የጉራንዳ አካባቢ ገደላ ገደል ከመሆኑም በላይ ውሀና የማገዶ እንጨት እንደልብ የማይገኝበት ስለነበር ሌላ የተሻለ ቦታ እንዲፈልጉ አሳሾችን ሲልኩ፣ የተላኩት አሳሾች በዚያን ጊዜ «ከርማሚዳ» ትባል የነበረችውና በዛሬዋ ጎባ አካባቢ እንደደረሱ በቦታው በነበሩ የጎሳ አባላት ይገደላሉ:: ይህንን የሰሙት ራስ ዳርጌ «ክተት ሰራዊት» ብለው አካባቢውን ይቆጣጠራሉ፡ አገሩንም ካረጋጉ በሁዋላ የቅርቡን እየተዘዋወሩ፣ የሩቁን ደግሞ በአጉሊ መነጽር ሲመለከቱ ወንዞችና የማገዶ እንጨትም እንደልብ ያለው ከመሆኑም በላይ ተራራማና ዳገታማነቱ ጠላትን ለመከላከል እንደሚያስችላቸው ይገነዘቡና «አገር ማለት አንቺ ነሽ እንዲህ ጉብ ያልሽው ለዚህ ኖሯል! አይ ጉብታ!» ማለታቸው ይነገራል::*

የቦታውን ጉብታማነት መሰረት አድርገውም ተከታዮቻቸው «እዚያ ጉብ ወዳለው ቦታ እንሂድ» እያሉ ሲናገሩ የሰማ ሁሉ የሁዋላ ሁዋላ «ጉብ» የሚለውን ወደ «ጎባ» እንደቀየረውና መጠሪያ ሆኖ እንደኖረ ያመለክታል::

ሌላው የተነገረው አፈ-ታሪክም ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ጋር ይዛመዳል:: መሰረት የሚያደርገውም የመልክአምድሩን አቀማመጥ ነው:: በጎባና አካባቢው አማራዎችና ኦሮሞዎች በስብጥር ይኖሩ ነበር:: አማራዎቹ በአብዛኛው በጉብታማው አካባቢ ነበር የሰፈሩት:: ኦሮሞዎቹ ታዲያ አማራዎቹ ያሉበትን ቦታ ለማመልከት እርስ በእርሳቸው ሲነጋገሩ «አማሮኒን ኤሳ ጅርቲ?» (አማሮች የት ናቸው?) ብለው ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚሰጡት መልስ «ከን ጉባራ ጅርቲ» (ከፍ ካለው ቦታ ላይ ናቸው) የሚል ነበር:: በኦሮምኛ ቋንቋ «ጉባ» ('ባ' ይጠብቃል) ማለት ከፍ ያለ ማለት ነው:: ይሁንና በሂደት ተለውጦ «ጉባ» የሚለው ወደ «ጎባ» ቢቀየርም መነሻው የኦሮምኛ ቃል «ጉባ» የሚለው ነው ይላሉ:: ሌላው አፈ-ታሪክ የሚጠቅሰው ደግሞ «ጎባው» የሚባሉ አጋፋሪ ነበሩ በማለት ነው:: እናም የ«ጎባው» የበላይ ገገር የነበሩት አስተዳዳሪ መልእክተኞችን ሲልኩ «ወደ 'ጎባው' ሂዱ» ይሉ ስለነበር የአጋፋሪ «ጎባው»ን ስም መነሻ በማድረግ «ጎባ» ተባለ የሚሉም አሉ::

«'ጎባ' በሚል ስያሜ በመጠራት ላይ የሚገኘው አካባቢ ጥንት 'ከርማሚዳ' ይባል ነበር» ይሉና ሀጂ ፈቂ ሀሰኖ ከአፈ ታሪክ ያገኙትን መረጃ ጠቅሰው ገለጻቸውን ሲቀጥሉ

*'ከርማሚዳ የሰው ስም ሲሆን የመጀመሪያ መጠሪያው 'ሼህ አህሚድ' የሚል ነው:: ይህም ሰው፣ ግራኝ መሀመድ በጦርነት ይዞ ካመጣቸው ሰዎች አንዱ ነበር:: 'ሼህ አህሚድ' ጎባ አካባቢ ተቀምጦ ስድስት ልጆች ወለደ፤ እነዚያ ተራብተው ብዙ ሆኑ:: የሰውየው ስም ቃሉ አረብኛ ስለሆነ ኦሮሞዎች ደግሞ አረብኛ ስለማያውቁ 'ሼህ አህሚድ' የሚለውን 'ከርማሚዳ አሉት:: በዚያው ለዛሬዋ 'ጎባ' መጠሪያ ሆኖ ቆየ:: አማራ ለማቅናት ሲመጣ ግን በአካባቢው የነበረውን ጉብታ አይቶ 'ጎባ' ብሎ ጠራው:: 'ጎባ' ከአማራ መምጣት ጋር የመጣ ስም ነው ብለዋል::*

የዛሬዋ የጎባ ከተማ ኣሰያየም ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሲመስል «ጎባ» እስከ ደርግ ኣገዛዝ ፍጻሜ እና እስከ ኢህኣዲግ (የኢትዮጵያ ህዝባዊ ኣብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር) የመጀመሪያዎቹ ሁለት ኣመታት ድረስ የባሌ ዞን ርእሰ ከተማ ነበረች፡፡ የዞን ርእሰ ከተማነቱን ሮቤ ከተረከበች በሁዋላ ግን ጎባ በወረዳ ደረጃ ተወስና በ23 ገበሬ ቀበሌ መንደር ተዋቅራለች፡፡ የጎባ ከተማ ግን ለብቻዋ በኣንድ የከተማ ምክር ቤት በመመራት ላይ ትገኛለች፡፡

በዚህ ምእራፍ የጥናታዊ ጽሁፉ ተተኳሪ የሆነውን፣ ጎባ ወረዳን በዝርዝር ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፡፡ በዝርዝሩ የተመለከትናቸው በተለይ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ተጓዳኝነት ይኖራቸዋል ተብለው የታሰቡትን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጎባ ወረዳን ለማስተዋወቅ በተደረገው ሙከራ መልክኣምድሩን፣ መስህብነት ስላላቸው ቦታዎች፣ የህዝቡን ብዛት፣ የቋንቋና የብሄረሰቦች ስብጥሩን፣ የኣየር ጠባዩን፣ የህዝቡ የኑሮ መሰረት በምን ላይ ያተኮረ እንደሆነ፣ ሀይማኖትና ልዩ ልዩ እምነቶችን በተመለከተና ልዩ ልዩ መረጃዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ በሰንጠረዥ የተደገፈ መረጃ ካቀረበ በሁዋላ በመጨረሻ ስለ ጎባ ከተማ «ጎባ» መባል የተነገሩትን ኣፈታሪኮች ጠቅሶ ጽሁፉ ያበቃል፡፡ በዚህም ዋናውና የጥናቱን ተተኳሪ ርእስ ወደያዘው ምእራፍ ኣራት እንሻገራለን፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ... ILS LIBRARY

## 4. የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያና የመጠጫ ቁሳቁስ

በዚህ ምእራፍ ከዚህ በታች በኣራት ማእዘናት ውስጥ የተዘረዘሩትን ኣርእስት የሚመለከቱ ዝርዝር ሀሳቦች በተጻፉበት ቅድመ ተከተል መሰረት አንድ በአንድ ኣቀርባለሁ፡፡


መግቢያ<br>
50-51<br>
ከእንጨት የሚሰሩ ቁሳቁስ<br>
ትውፊዊ ዳራ<br>
52-79<br>
ከሸክላ የሚሰሩ መመገቢያ እቃዎች<br>
79-106<br>
ከቅል የሚሰሩ ቁሳቁስ<br>
106-114<br>
የስፌት እቃዎች<br>
114-137<br>
ከቆዳ የሚሰሩ እቃዎች<br>
137-142<br>
ከቀንድ የሚሰሩ እቃዎች<br>
142-148


ይህ ክፍል የጥናቱ ዋና ኣላማ የሚተገበርበት በመሆኑ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች የመመገቢያና መጠጫ ቁሳቁስ ኣሰራር፣ ኣገልግሎትና ባህላዊ የኣንዳንዶቹንም ማህበራዊ ፋይዳን ይመለከታል፡፡ በዚህም መሰረት ከምግብ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ የመመገቢያ ቁሳቁሶችን በፎቶግራፍ ከተደገፉ ገለጻዎች ጋር ይቃኛል፡፡

ተተኳሪዎቹ ቁሳቁሶች በጥቅሉ ሲታዩ የእደጥበብ ውጤትና ስሪታቸውም ከእንስሳት፣ ከእጽዋትና ከሸክላ ኣፈር ነው፡፡ በዝርዝር ሲታኙ ደግሞ ከእንጨት፣ ከሸክላ፣ ከቅል፣ ከስንደዶ (ከዘንባባ፣ከሀረግ)፣ ከቆዳና ከቀንድ የተሰሩ ናቸው፡፡ የኣገላለጽ ሂደቱም አሰራራቸውን፣ ኣገልግሎታቸውንና ባህላዊ፣ የኣንዳንዶቹንም ማህበራዊ ፋይዳቸውን የሚከተል በመሆኑ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሰረት ይቀርባሉ፡፡

ኣንዳንድ ቁሳቁስ በቅርጽና በመጠን ቢለያዩም የኣሰራር ጥበባቸው ኣንድ ኣይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ከኣንድ ኣይነት ጥሬ እቃዎች የሚሰሩ ቁሳቁስ የኣሰራር ጥበባቸው ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ በኣንዱ ላይ ገለጻ ከተሰጠ ላለመደጋገም ሲባል ተመሳሳዩ ቁስ ሊዘለል ይችላል፡፡ ከእንደነዚህ ኣይነት ቁሳቁስ ውስጥ «ጃዩ» እና «ጡዌ» ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ኣንዳንድ እቃዎች ደግሞ የተወሰነ ኣገልግሎት እንዲሰጡ (እንደ ጮጮ እና

ማለቢያ የመሳሰሉት) ታስበው ቢሰሩም ሁለገብ አገልግሎት ሲሰጡ ይታያል። በመሆኑም የሚያበረክቱትን አገልግሎት ሁሉ መግለጹ የሌላውን ቦታ ስለሚይዝ በሁለገብነታቸው የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ቢጠቀሱም አንዱን የአገልግሎት ዘርፍ ግን በዋናነት በመውሰድ በዚያው ላይ ብቻ ሰፋ ያለ ገለጻ ይሰጣል።

በሌላ በኩል ምንም እንኳን ጥናታዊ ጽሁፉ የእቃዎቹን ባህላዊ ፋይዳ መግለጽ ኣላማው ቢሆንም ኣንዳንድ ቁሳቁስ ከሚያበረክቱት አገልግሎት ባሻገር የተለየ ባህላዊ ፋይዳ ላይኖራቸው ይችላል። ስለዚህም በልዩ ኣጋጣሚ - በሰርግ፣ በሀዘን፣ በደቦ ስራ፣ በሀይማኖታዊና እምነታዊ ስርኣቶች ወዘተ. ላይ ለየት ባለ ሁኔታ የብሄረሰቡን ባህላዊ ፋይዳ የሚያንጸባርቁ ሆነው የተገኙትን ቁሳቁስ ባህሉን በሚያሳዩበት ሁኔታ ብቻ ይገለጻሉ።

የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ከሸክላ እና ከስፌት ስራቶች ውጭ ከሌሎች ጥሬ እቃዎች የሚሰሩትን ቁሳቁስ ከሞላ ጎደል ቢገለገሉባቸውም የእቃዎቹ ምንጭ ራሳቸው ተገልጋዮቹ ሳይሆኑ ኣንድም ከቀደምት ዘመናት የተወረሱ በመሆናቸው፣ ኣንድም ራቅ ካሉ ቆላማ ኣካባቢዎች በግዥም ሆነ በስጦታ ያገኙኣቸው በመሆናቸውና በጎባ ወረዳ ውስጥ ስለማይሰሩ ስለ እነሱ መረጃውን ያገኘሁት ጥንት እቃዎቹ በሚሰሩበት ዘመን የነበሩ ሰዎች የተመለከቱትንና የሰሙትን ከነገሩኝ ግለሰቦች ነው። በዚህም መሰረት በ«ነበር» የተነገረኝን ከመቀበል በስተቀር ለጊዜው ሌላ ኣማራጭ ኣላገኘሁም። በዚህ ጉዳይ ላይ ሀጂ ከዱ ጎበና የቀንድ ስራ በጥንታዊነቱ ብቻ የሚታሰብ መሆኑን የጠቀሱትን ሀሳብ እዚህ ላይ ማንሳቱ ነገሩን ግልጽ ሳያደርገው ኣይቀርም።

የቀንድ ውጤት የሆኑት ቁሳቁስ ዱሮ ኣውሬ እንደልብ በሚታደንበት እና ከብቶችም እርካሽ በነበሩበት ዘመን ይሰሩ ነበር። ኣሁን ግን የቀንድ ዋንጫዎቹና መለኪያዎቹ «የክብር እቃ ለተከበሩ ሰዎች» ከሚባልላቸው ዘመን ያለፉ በመሆናቸውና ተፈላጊነታቸው እየቀዘቀዘ፣ ከባለሙያ መታጣት ጋር ተጨማምሮ ከገበያ ስላስወጣቸው፣ በቀንድ ቁሳቁስ ላይ ያለውም መረጃ «ነበር» ከሚል የመነጨ ነው።

በሌላ በኩል የሸክላና የስንደዶ ስፌት ውጤቶችን በተመለከተ ግን በጎባ ወረዳ ውስጥ በብዛት የሚሰራባቸው የስራ መስኮች በመሆናቸው እቃዎቹ ሲሰሩ እና በጥቅም ላይ ሲውሉ ለማየት እድል ኣግኝቻለሁ። «ማየት ማመን» ነውና። «ኣይኖች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ብቻ ሳይሆን መረጃዎቹንም ለመተንተን እንደመሳሪያ የማገልገላቸው ፋይዳ ጠቃሚ ነው» ሶምጂ ሱልጣን (Somjee Sultan 1999፣1)። እኔ ያየሁዋቸውን፣ ሌሎችም እንዲያጤኗቸው በ«ነበር»ም የተነገሩትን ይሁን በተጨባጭ በማየት ያገኘሁዋቸውን መረጃዎች እንደቅደም ተከተላቸው የዚህ ምእራፍ ኣካል ኣድርጌኣቸዋለሁ።

## 4.1 ከእንጨት የሚሰሩ ቁሳቁስ

በዚህ ክፍል የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ባህላዊ መመገቢያ ቁሳቁስ የሆኑትን «ገበታ»ን፣ «ቆሬ»ን፣ «ቁዲ ሶረታ»ን፣ «ኦኮሌ»ን፣ «ኪላ»ን፣ «ቁሉሙካ ሰላታ»ን እና «ቦቤ»ን እንመለከታለን::

## 4.2 ትውራዊ ዳራ

በታሪክ የመጀመሪያው የሰው ልጅ ደኖችን በተፈጥሮ እንዳሉ መጠቀም ከጀመረበት የዝቅተኛው የኑሮ ደረጃ (Savagery) ጀምሮ ኣሁን እስከኣለበት ደረጃ የደረሰው ቀስ በቀስ ነው:: <u>ABC of Dialectical and Historical Materialism</u>. «የመጀመሪያው ስራ ተጀመረ ተብሎ የሚታሰበው ጥንታዊው ሰብኣዊ ፍጡር ከእንጨት፣ ከድንጋይና ከኣጥንት ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማምረት ሲጀምር ነው» (ገጽ 115) ይላል:: ሮበርትስ (Roberts) በበኩላቸው ከሌሎች ቁሳቁስ ይልቅ እንጨት በሰው ልጅ የእድገት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ያበረከተ እንደነበር ሲገልጹ «እንጨት የሰው ልጅ መጠቀሚያ እንደነበር ይነገራል:: እስከ ሀያኛው ክፍለ-ዘመን መግቢያ የወጥ ቤት እቃዎች፣ የማእድ ቤት ውስጥ መጠቀሚያ ሆኑ መያገርዎች፣ ልዩ ልዩ ክፍሎች ይሰሩ የነበረው ከሸክላ ወይም ከብረት ሳይሆን ከእንጨት ነበር» (1972፣ 243) ይላሉ::

እንጨትና የእንጨት ተዋጽኦን በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠቀሙ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ብሄረሰቦች ኣንዱ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ነው:: በዚህም የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ተፈጥሮን ወደ ባህል ለውጠዋል:: በሰሯቸው ቁሳቁሶች እየተደሰቱና እየተገለገሉም ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ባህላቸውን ኣሳድገዋል:: በዚህም እንደሌሎች ህዝቦችና ብሄረሰቦች ሁሉ የታሪካቸውንና የባህላቸውን መረጃ ከቁሳዊ ባህላቸው መምዘዝ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል::

የደን መኖር ከእንጨት ለሚሰሩ ቁሳቁስ መሰረት ነው:: ከዚህ ኣኳያ የጎባ ወረዳ ሰፊ የሆነ የደን ይዞታ ባለቤት እንደነበር መረጃዎችና ኣፈታሪኮች ይጠቁማሉ:: የባሌ መስተዳድር ዞን «ባሌ» የሚለውን ስም ለማግኘት ከበቃችባቸው ምክንያቶች ኣንዱ ጥቅጥቅ የነበረው የደን ይዞታዋ ነው:: የጎባ ወረዳ የረዥም ጊዜ ነዋሪ የነበሩት የ89 ኣመቱ ኣዛውንት ኣቶ ኣበበ ወልደጻዲቅ በ1995 ኣ.ም ለዚህ ጥናት ኣቀራቢ ተከታዩን ኣፈታሪክ ነግረውታል::

> *ጥንታዊው የባሌ ጠቅላይ ግዛት ተፈጥሮኣዊ ኣቀማመጥ በጣም ደስ የሚል ደን ለበስ ነበር:: በደኑ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ብርቅዬ የዱር ኣራዊት ታይተው የማይጠገቡ እንደነበር ይነገራል:: ከመልክኣምድሩ ኣቀማመጥ ጋር የሚታዩት እጽዋት ኣይንን የመሳብ ኣቅም ነበራቸው:: ታዲያ በኣንድ*

UNIVERSITY ... LIBRARY

*ወቅት ያንን አካባቢ በሲናር በቅሎ ተቀምጣና አገልጋዮች አስከትላ ትዘዋወር የነበረች የወቅቱ ባላባት ሚስት አካባቢውን ዞራ ካየች በሁዋላ በደኑ ውበት ከመመሰጧ የተነሳ ይህንንስ ለ«ባሌ» ነበር ብላ በመናገሯ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ «ባሌ» እየተባለ መጠራት ጀመረ ይላሉ።*

በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ-መንግስት ለጎባ ከተማ መቆርቆር ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ምክንያት የሆነው አሁን «ጎባ» በሚል ስያሜ ይጠራ የነበረው ቦታና አካባቢ ሰፊ የሆነ የደን ዞታ ያለው ስለነበርና የማገዶ እንጨት እንደልብ የመገኘቱ ሁኔታ ነበር። ይህንንም ከኣፈታሪክ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል። በዚህ ጉዳይ ላይ የተጠቀሰውን አፈታሪክ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ «የጎባ ወረዳ ርእሰ-ከተማ ስም የትመጣ (Origin)» በሚል የተጻፈውን ይመልከቱ። በማስረጃ የተደገፈው ደግሞ ተከታዩ ነው።

መስከረም 22 ቀን 1999 ኣ.ም በ«ሀገሬ» የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንን ሳምንታዊ ፕሮግራም ላይ እንደተላለፈው አፍሪካ ካሏት ጥቅጥቅ ደኖች አንዱ ነው ተብሎ የሚታወቀው የሀረና ጥቅጥቅ ደን ከጎባ ከተማ 50 ኪሎ ሜትር ጀምሮ ወደ ደቡብ አቅጣጫ እስከ ደሎመና ከተማ መዳረሻ ይዘልቃል። የሀረና ጥቅጥቅ ደን ከባህር ጠለል በላይ ከ1500-3400 ሜትር ከፍታ ያላቸው የተለያዩ የመሬት አቀማመጦች ስላሉት ለልዩ ልዩ እጽዋት መብቀል ምቹ ሆኗል። ስለሆነም 30 ሜትር ርዝማኔ ያላቸው ቅርንጫፍ አልባ ወይም መጠነኛ ቅርንጫፎች ያላቸውን ዛፎች ጨምሮ እንደ ኮሶ፣ ቀረሮ፣ ዋንዛ፣ ብሳና፣ ግራር፣ ቀርከሀና የመሳሰሉ እጽዋትን ይዟል። በኣጠቃላይ በጣም ረጃጅም፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ቁመት ያላቸው ልዩ ልዩ የዛፍ ዝርያዎች ከሀረግና ከቁጥቋጦች ጋር በህብር የበቀሉበት ሰፊ ቦታ ነው የሀረና ጥቅጥቅ ደን።

በባሌ ውስጥ የሚገኘው ደን ከቅርብ ኣመታት ወዲህ በእርሻ ይዞታ መስፋፋት እና በተለይም በ1992 ኣ.ም በተከሰተ የሰደድ እሳት ክፉኛ ቢጎዳም ዛሬም አሻራው ጨርሶ አልጠፋምና የደኑ ይዞታ ምን ያህል የተጠናከረ እንደነበር ከሀረና ጥቅጥቅ ደን ይዞታ ማወቅ ይቻላል።

ምንም እንኳን የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ቁሳቁስን ከእንጨት መስራት መቼ ጀመሩ? እንዴት ጀመሩ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ባላገኝም ብዙዎች ሰዎች በጎባ ከተማና ኣካባቢዋ በቅርብ ርቀት የደን መኖር የብሄረሰቡን ኣባላት ቁሳቁሶችን በእንጨት ወደመስራት ሳይመራቸው እንዳልቀረ ይገምታሉ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

### 4.2.1 ገበታ (GABATAA)

በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ከእንጨት ከሚሰሩ የመመገቢያ እቃዎች አንዱና ትልቁ «ገበታ» ነው። ኣቶ በቀለ ቱፋ «ገበታ ማለት ከኣጠቃላይ ይዘቱ ኣንጻር ውስጡ ባዶ የሆነ ኣፈሰፊ ማለት ነው። ገበታ ለሚለው ቃል ‘ገበቴ’ የሚለው ቃል ነው መነሻው። ኦሮሞዎች የገበታን ስርወቃል ‘ገበቴ’ እንደሆነ ኣድርገው ነው የሚወስዱት» ይላሉ።

የጎባ ወረዳ የረዥም ጊዜ ነዋሪ የሆኑት የ88 ኣመቱ ኣዛውንት ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ «ለእኛ ገበታ የመመገቢያ እቃዎቻችን ሁሉ ቁንጮ ነው።» ካሉ በሁዋላ ሀሳባቸውን እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> *«ይህን የምንለውም በሶስት ምክንያቶች ነው፤ እነዚህም ብዙ ሰዎችን በኣንድ ጊዜ ሊያሳትፍ የሚችል ማእድ በመሆኑ፣ የእኛነታችን ምልክት፣ የባህላችን መገለጫ ኣርማችንና መታወቂያችን በመሆኑና ምርጥ የሆነውን ባህላዊ የኦሮሞ ምግብ በብዛት የምናዘጋጅበት ስለሆነ ነው» በማለት ያስረዳሉ።*

«ገበታ» (Gabataa) በጣም ትልቅ፣ መካከለኛና ኣነስተኛ መጠን ኣለው። የሁሉም ኣይነት ኣሰራር ኣንድ ኣይነት ሲሆን ልዩነቱ የሚታየው ገበታውን ለመስራት በሚፈጀው ጊዜ ነው። ይሁንና ገበታ እንዴት ይሰራል?

***የ«ገበታ» (Gabataa) ኣሰራር፡-*** ስለ «ገበታ» ኣሰራር ኣቶ ኣለሙ ወርቁ የነገሩኝ ተከታዩ ነው።

> *ገበታ (Gabataa) የሚሰራው ከእንጨት ነው። የመስሪያው እንጨት ግንድ የሚገኘው ቆላ ቀመስ በሆነ ኣካባቢ ነው። ግንዱ ጸሀይንና ንፋስን ሊቋቋም የሚችል፣ በቀላሉ የማይሰነጠቅ መሆን ኣለበት። ዋንዛና የኮሶ እንጨት ለገበታ ስራ ተመራጮች ናቸው። ይሁን እንጂ የዝግባ እንጨትም ከተገኘ ኣይጠላም። ገበታውን የሚሰራው ማንኛውም ሰው ሳይሆን ለስራው ብቃት ያለው ሙያተኛ ነው። እንጨቱ በባለሙያ ከተመረጠ በሁዋላ ከወፍራሙ በኩል ተመርጦ ይቆረጥና ቅርፊቱና የማያስፈልጉ ነገሮች በስለታም መጥረቢያ በስልት ይጠረባሉ። ተከታዩ ስራ ዋናውን የምግብ መያዣውን የገበታ ኣካል በመሮና በመጥረቢያ እየቦረቦሩ እስከሚፈለገው ደረጃ ድረስ ማጎርጎድ ነው። በጣም ትልቁ ገበታ የ«ደሂ ገበታ» (Gabataa dahii) የሚባለው ሲሆን የእግሩ ርዝማኔ ከ50 እስከ 70 ሳንቲሜትር ይደርሳል። በመካከለኛና በኣነስተኛ መጠን ላይ ያሉት ከ30 እስከ 40 ሳንቲሜትር ሊሆኑ ይችላሉ። ዋናውና ምግብ መያዣው ክፍል በሚበቃ ሁኔታ ከተቦረቦረ በሁዋላ የማለስለሱ ስራ በሱፋጭና[6] ስለት ባላት ኣነስተኛ መጥረቢያ ይከናወናል። እየለሰለሰ ባለበት ሂደትም የእግሩን ቅርጽ የማውጣቱ ስራ ይከናወናል። የገበታው እግር ወጣ ገባ እንዳይሆን መጀመሪያውኑ የሚመረጠው ቀጥ ያለ ግንድ ነው። ዘንግ የሚመስለው የእግሩ ክፍል መጠነ ዙሪያው ሳይበላለጥ እየተጠረበ ይስተካከላል። መሬት የሚይዘው ኣካሉ ግን ዘርጠጥ ማለት ኣለበት። ይህም ክብ ቅርጽ እንዲኖረው ያደርጋል። የመጨረሻው የእግሩ ኣካል ክብ መሆኑም ተደላድሎ እንዲቆም ያስችለዋል። የገበታው እግርም ሆነ ዋናው ኣካሉ የተቀጣጠሉ ሳይሆኑ ከኣንድ ግንድ ወጥ በሆነ መልኩ ነው የሚሰሩት። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ገበታው ከተሰራ በሁዋላ የማለስለሱ ስራ ይከናወናል። ገበታን ኣልፎ ኣልፎ ካልሆነ እንደሌሎች ከእንጨት የሚሰሩ መመገቢያ እቃዎች በተለያዩ ቅርጾች (ክብ፣ ኣራት ማእዘን፣ ሶስት ማእዘን....) የሚነደፉ ሸንትሮችን ኣያወጡለትም። ልሙጥ እንደሆነ ይተውታል። በኣንዳንድ ገበታ ላይ የመያዣ ጆሮ ከዚያው ከኣካሉ በግራና በቀኝ ያወጡለታል። ጆሮው እንደ እንስራ ጆሮ ሰፊ ቀዳዳ ያለው ሳይሆን በመጠኑ ወጣ ወጣ ያለ ነው። «ቡራቶ» የተባለውን የኦሮሞዎች ባህላዊ ምግብ የተሞላ ትልቅ ገበታ ለማንሳት ከሁለት ያላነሱ ጠንካራ*

---

[6] *ሱፋጭ፡- ስለታም ድንጋይ*

*ሰዎች ያስፈልጋሉ። በገበታ የአሰራር ሂደት በመጀመሪያ የሚሰራው የመመገቢያ ክፍሉ ወይም አካሉ ነው። መመገቢያውን ቦርቡረው ከሰሩ በሁዋላ ወደ እግሩ ስራ ይመለሳሉ። ገበታውን የመቦርቦሩ፣ የማስተካከሉና የመላጉ ስራ ከተጠናቀቀ በሁዋላ በንፋስና በጸሀይ በቀላሉ እንዳይሰነጠቅ በፍግ ውስጥ ከ5 እስከ 7 ቀናት ያቆዩታል። የፍግ ውስጥ ቆይታውን እንደጨረሰም ታጥቦ ከጸዳ በሁዋላ በጉሎ፣ በሞራና በቅቤ በተደጋጋሚ ይሟሻል። ይህን የሚያደርጉት ምግብ በሚሰሩበት ጊዜ የመስሪያውን ቅቤ እንዳይጠጣባቸውና እንዲደረጅ ነው። በዚህ ሁኔታ ከደረጀ በሁዋላ ነው አገልግሎት ለመስጠት የሚበቃው። አንድን የገበታ ስራ አንድ ሙያተኛ ጠዋት ወደ ሌላ ስራ ከመሰማራቱና ማታ ማታም ከሌላ ስራ ከተላቀቀ በሁዋላ እስከሚመሽ ድረስ ብቻ ባሉት ሰኣቶች የሚሰራው ከሆነ ለማጠናቀቅ አንድ ወርና ከዚያም በላይ ይወስድበታል። ቀኑን ሙሉ ስራዬ ብሎ ከሰራው ግን በ5 ቀናት ውስጥ ሊጨርሰው ይችላል። እነዚህ ቀናት የፍግ ውስጥ ቆይታውን ኣያካትቱም። የገበታው የልስላሴ ብቃት የሚለካው በእጅ በመዳሰስ ነው። የቀድሞው የገበታ ኣሰራር ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት ነው። በዚህ በእኛ ዘመን ግን ሙያተኛውም፣ እንጨቱም ስለሌሉና የብሄረሰቡ ኣባላት በዘመን ኣመጣሽ እቃዎች መጠቀም ስለጀመሩ የገበታ ስራ ኣይኑር እንጂ ኣልፎ ኣልፎ በጥቅም ላይ ሲውል ግን ይታያል በማለት ኣጠናቀዋል።*

«ገበታ» ስለሚሰራበት የእንጨት ኣይነት የተናገሩት ኣቶ በቀለ ቱፋ በበኩላቸው «እንጨቱ በቀላሉ ኣፈር የማይበላው፣ የማይሰነጠቅ፣ ክብደት የሌለውና ጠንካራ ከሆነ ተመራጭ ነው» በማለት ገልጸዋል።

ገበታ በጣም ትልቅ፣ መካከለኛና ኣነስተኛ ተብሎ እንደሚሰጠው ኣገልግሎት ይሰራል። በጎባ ወረዳ በጣም ትልቅ የተባለውን ገበታ ባላገኝም መካከለኛውንና ኣነስተኛውን ለማግኘት ችያለሁ። መካከለኛው ገበታ መሬት ከሚነካው የእግሩ ጠርዝ እስከ ዋናው የገበታ ኣካል ጫፍ ድረስ ያለው ርዝመት 75 ሳንቲሜትር ነው። ምግቡ የሚቀመጥበት የዋናው ኣካሉ መጠነ ዙሪያ 105 ሳንቲሜትር ሲሆን የእግሩ መጠነ ዙሪያም 55 ሳንቲሜትር መሆኑን ኣረጋግጫለሁ። ከዚህም በስተቀር ክብ ቅርጽ የያዘውና መሬቱን የሚቆነጥጠው (መሬት ላይ የሚቆመው የእግሩ ኣካል) መጠነ ዙሪያ 40 ሳንቲሜትር ሲሆን በእግሩ የመጨረሻ ጠርዝ እና በመሬት መቆሚያው መካከል ያለው ርዝመት 23 ሳንቲሜትር ነው።

በኣንጻሩ ኣነስተኛ የተባለው ገበታ ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለው ርዝመት 45 ሳንቲሜትር ነው። ምግቡን የሚይዘው የዋናው ኣካሉ መጠነ ዙሪያ ደግሞ 94 ሳንቲሜትር ሲሆን የእግሩ (የዘንጉ እግር ውፍረት ወይም መጠነ ዙሪያ) 45 ሳንቲሜትር ነው። መሬት የሚይዘው ክብ ቅርጽ መጠነ ዙሪያ ደግሞ 30 ሳንቲሜትር ሲሆን መሬት ላይ የሚቆመው የእግሩ ኣካል ክብ ቅርጽ ነው። ይህ ክብ ቅርጽ ደግሞ እግሩ ከተገጠመበት የመጨረሻ መጋጠሚያ እስከ ጠርዙ ያለው ርዝመት 20 ሳንቲሜትር ነው። ከዚህ በላይ ከተገለጸው ኣሀዛዊ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የእግሩ ዘንግ መጠነ ዙሪያ ከዋናው የመመገቢያ ኣካሉ መጠነ ዙሪያ በግማሽ ያህል የሚቀንስ መሆኑን ነው። በተጨማሪም

[LS LIBRARY ... VERSITY]

ከታች ያለው ክብ መቆሚያ (መሬት ቆንጣጩ ኣካል) ጠቅላላውን ገበታ ሊያቆም በሚችል መልኩ ተመጣጥኖ እንደሚሰራ መገንዘብ ይቻላል:: በጥቅሉ የገበታው ኣሰራርና ቅርጽ የሚወሰነው ጠቅላላ ገበታውን እንዲሸከም ተደርጎ ነው:: በኣጠቃላይ ምንም እንኳን በልማዳዊ ኣሰራር የሚሰራም ቢሆን ሙያተኞቹ የእቃውን ቅርጽና ኣሰራር ከተሸካሚ ኣካሉ ጋር የተመጣጠነ በማድረግ ምን ያህል ጥረት ያደርጉ እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል:: ሁለቱን ገበታዎች ከፎቶግራፍ 1 ላይ ማየት ይቻላል::



*ፎቶግራፍ 1:- በተለያዩ መጠኖች የተሰሩ ገበታዎች ከስፌት መክደኛዎቻቸው ጋር::*

ገበታ ክዳን ያለው ባህላዊ የመመገቢያ እቃ ነው:: ቀደም ባሉት ኣመታት ገበታም ሆነ ክዳኑ ሁለቱም ከእንጨት ነበር የሚሰሩት:: ይሁን እንጂ ከጊዜ ብዛት ክዳኑ ከኣገልግሎት ውጭ ቢሆን እንጨት እንደልብ ካለማግኘት ጋር ተያይዞ የሁዋላ ሁዋላ ክዳኑን ከስንደዶ ስፌት መስራት ተጀመረ:: ይህም ቀስ በቀስ የወንዶቹን ተሳትፎ ብቻ የሚጠይቀው የገበታ ስራ ወደ ሴቶቹም ተሸጋገረ:: ይህን በተመለከተ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ «ዱሮ ክዳኑንም ሆነ ዋናውን መመገቢያ ገበታ ለመስራት የሚሳተፈው ወንድ ብቻ ነበር:: ኣሁን ኣሁን እንጨቱም እንደልብ ባለመገኘቱ ክዳኑን በተለይ ከስንደዶና ከዘንባባ መስፋት የግድ ሆነ:: ለዚህ ስራ የሚሳተፉት ደግሞ ሴቶች ናቸው» በማለት ያስረዳሉ::

*የገበታ ክዳን ኣሰራር:-* የ«ገበታ» ክዳን እንደገበታው መጠን ተለክቶ የሚሰራ ነው:: የመስሪያ ቁሳቁሶቹም ስንደዶ፣ የተለያየ ቀለም ንክር የሆኑ ኣለላዎች፣ ኣክርማ፣ ከላላ (ሀረግ) ወስፌ እንደሁም እጅን የማርጠቢያ ውሀ ናቸው:: የክዳኑ ቅርጽ ከስንደዶ በመስፋት የምንጠቀምበትን የድስት እፊያ ይመስላል::

ኣሰራሩን በተመለከተ ሁለት ወይም ሶስት ሰበዞች ቆለፍለፍ ተደርገው በክብ ቅርጽ ይገመዱና ኣክርማ ይዞርባቸዋል:: በዚህ ኣይነትም የስፌቱ ስራ ይጀመራል:: ይህም

ጅምር (wiixnii) ይባላል። የገበታውን ክዳን ለመስፋት የሚጀመረው ከእጀታው ወይም ከመያዣው ነው። የእጅ መያዣው ቁመቱ ከ2 እስከ 4 ሳንቲሜትር ይረዝማል። ከእጅ መያዣው እስከ ጠርዙ መጨረሻ ያለው የክዳኑ ርዝመት እንደ ገበታው አፍ ስፋትና ጥበት ከ27-30 ሳንቲሜትር ይሆናል። በቀለም የተነከረው ኣለላ ኣልፎ ኣልፎ ጌጥ እንዲሆን በተለያዩ ቅርጾች (ክብ፣ ሶስት፣ ኣራት ማእዘን) እየሆነ ይሰፋበታል። ከዚህም በተጨማሪ ለማስዋብና ኣይን እንዲስብ ለማድረግ በገበታው እጀታ (መያዣው) ላይ ኣልፎ ኣልፎ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ጨሌዎች ይታበቱበታል። የሚታበቱትም በቀጫጭን ጠፍሮች (Straps) ላይ ነው። ኣሰራሩም መጀመሪያ ጠፍሩ በመክደኛው የእጀታ ኣናት ክቡ ቅርጽ ላይ ዙሪያውን ይሰፋና፣ በተሰፋው ጠፍር ላይ ደግሞ እንደክር በቀጠኑ የጠፍር ጥብጣቦች (እንዲሁም የተገመደ ክር ወይም ቺንጊያ ሊሆን ይችላል) ጨሌዎቹ እንዲያያዙ ይደረጋል። የክዳኑ የእጅ መያዣ ኣናት ኣንዳንድ ጊዜ ዝርግ እና የሰፌድ ቅርጽ ያላት ኣነስተኛ ስፌት የተገጠመለት ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ ድቡልቡል ቅርጽ እንዲኖረው ይደረጋል። ይህም በጣት ለመያዝ እንዲያመች ነው። ኣልፎ ኣልፎ እንደሚሰፋውና እዚህም በፎቶግራፉ ላይ እንደሚታየው የዋናው ገበታ ክዳን መጋጠሚያና በእጀታው ኣናት ላይ ያለው የትንሽ ሰፌድ (ክብ) ቅርጽ ያለው ስፌት የሲሊንደር ቅርጽ ካለው ቀንድ ጋር ይያያዛል። ይህ ደግሞ የመክደኛውን የመጨረሻ ጫፍ በጣት ከመያዝ ይልቅ በእጅ ጨብጦ ለመያዝ ያመቻል። እዚህ ባለው ፎቶግራፍ ላይ በተለይ በቀኝ በኩል ያለውን እንደሲሊንደር ቅርጽ ካለው ቀንድ ጋር የተያያዘውን እና በግራ በኩል በስንደዶ ስፌት ብቻ የተገጠመውን ክዳን ማየት ይቻላል።

*የገበታ ኣገልግሎት*:- በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህል የገበታ ኣገልግሎት «ቡራቶ» (Burattoo) እና «ገንፎ» «መርቃ» (Marqaa) ከተባሉ ባህላዊ ምግቦቻቸው ጋር የተያያዘ ነው። ገበታው በኣብዛኛው ኣገልግሎት የሚሰጠው በሰርግ፣ በደቦ ስራ፣ በሀይማኖታዊና ህዝባዊ ክብረ በኣላት ላይ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ብዙ እድምተኞችን በኣንድ ጊዜ የሚያስተናግድ ስለሆነ ነው። የዚህ ጥናት ኣቅራቢ በ21/8/99 በሮቤ ከተማ በነበረው የሚሌኒየም ዋዜማ በኣል ላይ በኣዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ለነበሩ እንግዶች በገበታ የተዘጋጀ «ቡራቶ» ተቆራርሶ ሲሰጣቸው ተመልክቷል። ኣቶ ኣለሙ ወርቁ ስለ ገበታ ኣገልግሎት የተናገሩት ተከታዩ ነው።

> *በሙሽሪት እናት ቤት ሰርገኞች በብዛት ይመጣሉ። ሰርገኞችም ብቻ ሳይሆኑ ትልቁ ኣማችም ይመጣል። ኣጃቢዎቹም ከ80 እስከ 100 ኣንዳንዴም ከዚህ ቁጥር በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም እንዲህ ብዛት ያለውን እድምተኛ ለመጋበዝ ትልቁ ገበታ (ገበታ ደሂ) ያስፈልጋል። በሰርጉ ቤት እንኳን ባይኖር ከሌላ ቦታ ተፈልጎ ይመጣል። የገንፎው ዱቄት የሚመጣው ከእየዘመድ ኣዝማዱ ቤት ቢሆንም ለሙሽራውና ለኣጃቢዎቹ የሚዘጋጀው ገንፎ የሚገነፋውና ቅቤው የሙሽሪት እናት ዱቄትና ቅቤ ነው። ከሌላ የመጣ ዱቄትና ገንፎ ኣይቀላቀልበትም። በሁለት ወይም በኣራት «ወሻ» (ኣፈሰፊ እንስራ) ተገንፍቶ ትልቁን ገበታ (ገበታ ደሂውን) መሙላት ኣለበት። ገንፎ ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ*

> *የተዘጋጀ ቡራቶም በዚሁ መልክ ሊቀርብበት ይችላል:: በጣም ትልቁ ገበታ «ገበታ ደሂ» (Gabataa dahii) ይባላል:: ገበታው በኣንድ ጊዜ እስከ 20 ሰዎችን የማስተናገድ ኣቅም ኣለው:: ኦሮሞዎች እንዲህ ኣይነቱን ገበታ የሚገለገሉበት ኣንዲት እናት ሴት ልጇን በዳረች ጊዜ ልጅቷን ለመውሰድ ለሚመጡ በርካታ ሰርገኞች እንዲያስተናግድላት ነው:: ልብ በል ይህ በወንዱ ቤት ሳይሆን በልጅቷ እናት ቤት የሚደረግ መስተንግዶ ነው:: ምክንያቱም ልጅቱን ለመውሰድ የሚመጡ በርካታ እንግዶች (እድምተኞች) ስለሚኖሩ ነው:: የመጡትን በርካታ ሰርገኞች በኣንድ ወይም በሁለት ትላልቅ ገበታዎች ማስተናገድ ይመረጣል::*

ሌላው የገበታ ኣገልግሎት በራሱ በገበታው «ቡራቶ» ለመስራት ማስቻሉ ነው:: ከዚህ ኣንጻር የገበታው ዋናው ምግብ መያዣ ኣካሉና የእግሩ መርዘምም ኣስተዋጽኦ ኣላቸው:: ይህንንም የባህሉ ባለቤት የሆኑት ኣቶ በቀለ ቱፋ እንደሚከተለው ያስረዳሉ::

> *በኣንድ ጊዜ ከ15 -20 የሚደርሱ ሰዎችን የሚያስተናግድ በመሆኑ በገበታው ኣጠገብ ያሉት ሰዎች ቁጭ ብለውና ተንበርክከውም ለመመገብ ሲችሉ ከእነሱ ጀርባ ያሉት ሌሎች ተመጋቢዎች ደግሞ ተንጠራርተው ለመመገብ የሚችሉት የእግሩ መርዘም በፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ነው:: በተጨማሪም «ቡራቶ» ሲዘጋጅ የበሶውን ዱቄትና ቅቤውን ለማዋሀድ ሲባል በጣም ስለሚሰበቅና በተሰበቀ ቁጥርም እየጋለ ስለሚሄድ ምግቡ የሚቀመጥበትን ቦታ በእጅ ደግፎ መያዝ ኣይቻልም፤ መያዝ የሚቻለው እግሩን እና በትክሻም ዋናውን ኣካሉን በመደገፍ ብቻ በመሆኑ ከዚህ ኣንጻርም ጥቅም ኣለው የእግሩ መርዘም::*

የገበታው ኣገልግሎትና ኣሰራሩ ተደጋጋፊዎች ናቸው:: ለምሳሌ ዋናውና ምግብ መያዣው የገበታ ኣካል በጣም ሰፊ በመሆኑ በኣንድ ጊዜ ብዙ የበሶ ዱቄትና ቅቤ ይይዛል:: የእግሩ መርዘምም ለመያዝ ቀላል እንዲሆንና ሲመገቡም እንዳያጎነብሱ ይረዳል:: ዱቄቱና ቅቤው በገበታው ውስጥ እንዲዋሀዱ በሚደረግበት ወቅት፤ ገበታው እንዳይወድቅ ሁለት ጠንካራ ወንዶች በግራና በቀኝ ኣቅፈውና ደግፈው ይይዙታል:: ኣሰራሩም ተደግፎ እንዲያዝ የሚረዳ በመሆኑ በእጃቸው እግሮቹን በትከሻቸው ደግሞ ዋናውን ኣካሉን ይይዛሉ:: የገበታ ሌላው ኣገልግሎቱ የተዘጋጀውን ምግብ ጣእሙ ሳይቀነስ ለረዥምም ጊዜ ይዞ ለማቆየት መቻሉና በቶሎ እንዲቀዘቅዝ ኣለማድረጉም ነው:: ኣቶ በቀለ ቱፋ በዚህም ላይ የሚሉት ኣላቸው::

> *በ'ገበታ' መመገብ የለመዱ ኣንዳንድ ሰዎች በሳህን ቢቀርብላቸው ግድ ካልሆነባቸው በስተቀር ኣይለምዱም:: በሳህን የቀረበ ገንፎ ከሁለት ሰኣት በሁዋላ ሲቀዘቅዝ በገበታ የቀረበው ግን ሳይቀዘቅዝ ሊቆይ ይችላል:: ጠዋት የተሰራውን ገንፎ በገበታው ኣስቀምጦ ማታ መመገብ ይቻላል:: በተጨማሪም ገበታው ራሱ ለምግቡ የሚመች ጥሩ ጠረን የመፍጠርና እንዲቆይ የማድረግ ሁኔታ ስላለው ለመመገቢያነት ኣገልግሎቱ ተመራጭ ነው:: ቡራቶውንም ቢሆን ኣያሻግተውም:: ቡራቶው ቅቤ ጠጥቷልና ለብዙ ጊዜ ይቆያል:: ከዚህም በላይ ገበታው ራሱ በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ የሚያስችል ነው::*

***የገበታ ባህላዊ ፋይዳ፡-*** ባህላዊ ፋይዳ ስንል ኣንድ የመመገቢያ ቁስ ከተራ ኣገልግሎቱ በተጨማሪ የብሄረሰቡን ባህል እንዴትና መቼ-መቼ ሊገልጽ እንደሚችል የምናጤንበት

በመሆኑ በዚህ ጽሁፍ ደግሞ የገበታን ባህላዊ ፋይዳ ለማመልከት ጥረት ይደረጋል:: በዚሁ መሰረት ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ የገበታን ባህላዊ ፋይዳ ከገለጹበት ሀሳብ እንነሳ::

*ገበታ በህዝባዊና ሀይማኖታዊ በኣላት ላይ «ቡራቶ» ወይም «ገንፎ» ሰንቆ የሚቀርብ ባህላዊ የመመገቢያ እቃ ነው:: በተለይ ብዙ እድምተኞች በሚኖሩበት እንደ ሰርግ (Ciidaa)፣ ተስካር (Sadaqaa)፣ የገና በኣል (Moyaliida)፣ በደቦ (Jigii) እና በትላልቅ የድግስ ወቅት በርካታ ሰዎችን እንዲያስተናግድ ታስቦ የሚቀርብ የክብርና የወግ እቃ ነው:: በተለይ ትልቁ ገበታ ሴት ልጇን በምትድር እናት ቤት ባህላዊው ምግብ ተዘጋጅቶበት በኣንድ ጊዜ ብዙ እድምተኞችን ለማስተናገድ ማስቻሉ የባህላዊ ፋይዳው መገለጫ ነው::*

ኣቶ ኣለሙ ወርቁ በበኩላቸው የገበታን ባህላዊ ፋይዳ እንደሚከተለው ያስቀምጡታል::


*በሰርግ ስርኣት ወቅት ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው ገበታ ደሂ «Gabataa dahii» (ትልቁ ገበታ) ሙሽሪትን ሊወስዱ የሚመጡ እድምተኞችን ሁሉ እንዲጋብዝ ተደርጎ ሙሽራው በተቀመጠበት ኣካባቢ ይሰየማል:: ተጋባገርችም እንደ እድሜ ተዋረድ በገበታው ኣቅራቢያ ይቀመጣሉ:: ቀጥሎ ያለው ስርኣት በርከት ባሉ ቁዲዎችና ጡንጦዎች ወተት ኣብሮ መቅረቡን ካረጋገጡ በሁዋላ ሽማግሌዎች ምርቃት ይጀምራሉ:: የምርቃቱ ስነስርኣት እንዳበቃ በኣስተናጋጅ ሽማግሌዎች ኣማካኝነት በመጀመሪያ ከሁሉም ተጋባገርች በእድሜ የሚበልጡትን የተወሰኑ ሰዎችና ሙሽራውን እንዲመገቡ ይጋብዟቸዋል:: በዚህ ኣይነት እንደየእድሜ እርከናቸው በየተራ ወደ ገበታው እየቀረቡ እንዲመገቡ ከተደረገ በሁዋላ የማብቂያው የምርቃት ስርኣት ይከናወናል:: በየመካከሉ ቅቤ ሲያንስ እየተከታተሉ የሚያቀርቡ ሰዎች ራቅ ብለው ይቆጣጠራሉ:: ቅቤው ያነሰ መስሎ ሲታያቸውም ጃዩ በተባለ የቅቤ መያገሪ እቃ የያዙትን ቅቤ በገበታው ላይ ያፈሱታል:: ከገበታው ጋር ወተት የያዙ ቁዲዎች ወይም ጮጮዎች ይሰለፋሉ:: ኣንድ ቁዲ ወተት ለ3 ወይም ለ4 ሰዎች እየተሰጠ በወተቱ እያማጉ ይመገባሉ:: ይህ ሁሉ ስርኣት በኣንድ ትልቅ ገበታ የሚከናወን ቢሆንም ምናልባት ገበታው የሚያንስ መስሎ ከታየ ገንፎ ወይም «ቡራቶ» የያዙ ቆሪዎች በተጠባባቂነት ይቀመጣሉ:: ገበታው ከተሰየመበት ቦታ የሚነሳው፣ ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ከወጣ በሁዋላ ነው:: እስከዚያው ግን እድምተኛው ሁሉም በልቶ እንኳን ቢያበቃ ገበታው ከቦታው ኣይንቀሳቀስም:: የዚህ ኣይነት ኣቅርቦት ባህላዊ ፋይዳን ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ፋይዳንም ያጎለብታል:: ምክንያቱም እድምተኞቹ በየእድሜ እርከናቸው በሚመገቡበት ጊዜ የየራሳቸውን ጫወታ፣ ወግና ንግግር ያደርጋሉና::*

«ቡራቶ» (Buratoo) የተባለው የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህላዊ ምግብ በገበታው ዋና ኣካል ውስጥ መዘጋጀቱም ሌላው ባህላዊ ፋይዳው የሚገለጽበት መስክ ነው:: ስመሆኑ «ቡራቶ» እንዴት ይሰራል? ገበታና ቡራቶ ስለማይለያዩ ኣዘገጃጀቱን ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል::

ILS LIBRARY UNIVERSITY

«ቡራቶ» የበሶ ዱቄትና በርካታ ቅቤ ፍጹም ተዋህደው የሚፈጥሩት ባህላዊ ምግብ ነው:: ባህላዊው ምግብ በገበታ ውስጥ ወይም በሌላ እቃ ሊዘጋጅ ይችላል:: በገበታው የሚዘጋጀው ገበታው ሰፊ (ትልቅ) ሲሆንና ተመጣጣኝ እድሜ እና ኣቅም ያላቸው፣ ገበታውን ደግፈው የሚይዙ ወንዶች ሲኖሩ ነው:: ኣቅማቸው ተመጣጣኝ መሆን

ያለበትም በሶውንና ቅቤውን በሀይል እየሰበቁ ለማዋሀድ በሚደረግበት ጊዜ ወደ ኣንደኛው ወገን እንዳያጋድል ነው። ኣሁን ወደ «ቡራቶ»ው ኣዘገጃጀት እናምራ። የቡራቶውን ኣዘገጃጀት ከፎቶ ሁለት መመልከት ይቻላል። ቡራቶው የሚዘጋጀው በገበታ ሳይሆን በሌላ እቃ ነው። ምክንያቱም ገበታው ኣነስተኛ ነውና። ተዘጋጅቶ ያበቃለትን «ቡራቶ» ግን የሚያስቀምጡት በገበታው ነው።



ፎቶግራፍ 2፡- የ«ቡራቶ» ዝግጅትና ገበታ አይለያዩም። የ«ቡራቶ» ዝግጅት በህብረት

«ቡራቶ»ን ለመስራት ወንዶቹ ገበታውን የመያዝና በሶውንና ቅቤውን የማዋሀድ የስራ ድርሻ ቢኖራቸውም ትልቁን ሚና የሚጫወቱት ሴቶቹ ናቸው። ሴቶቹ እጃቸውን በውሀ ንጹህ ካደረጉ በሁዋላ መድረቅ ኣለበት። ምክንያቱም ትንሽ የውሀ ጠብታ ከቀን ብዛት የቡራቶውን ጣእም ሊለውጠው ይችላልና። እጃቸውን ካደረቁ በሁዋላ በመጀመሪያ ትንሽ ትንሽ ቅቤ እየጨመሩ በእጃቸው ያሻሉ። ከዚያ በሁዋላ ቅቤ በብዛት እየተጨመረ በጠፍጣፋ ማማሰያ በሀይል ይሰበቃል። የማማሰያው ጠፍጣፋ መሆን ቅቤውና ዱቄቱ

እንዲዋሀዱ ኣስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ሴቶቹ በሀይል ስለሚሰብቁት መዛልና መድከማቸው ባይቀርም ሌሎች እየተተኩ በሚገባ ያዋህዱታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ቅቤ የጠገበው የበሶ ዱቄት በመጀመሪያ ላይ ልል ይሆንና እንደገበቴ ውሀ በዚያው በተዋሀደበት እቃ ላይ ይዋልላል፡፡ ከጊዜ ብዛት ግን ይደርቅና ይደድራል፡፡ ውሎ ባደረ ቁጥር በእጅ ስለማይቆረስም ስለታም ሰንጢ ኣስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም «ቡራቶ» ውሎ ሲያድር ጠንካራ ከመሆኑ ጋር በተፈጥሮ ምራቅ ብቻ ለውሶና ኣጣጥሞ ወደ ጉሮሮ መላኩ ይከብዳል፤ ይተናነቃልና፡፡ የዚህ መፍትሄው ደግሞ በእነሱው፣ በኦሮሞዎቹ እጅ ነው፡፡ ኣቅም እስከፈቀደ ድረስ በጡንጦ ወይም በጮጮ የሚያዝ የማወራረጃ ወተት እና «ቡራቶ» ተለያይተው ኣያውቁም፡፡ ፎቶ ሶስት ይህንኑ የሚያሳይ ሲሆን ፣ በዚህ ፎቶግራፍ ሲቁኣቸውን (ዘንጋቸውን) በግራ፣ በጌጥ የተሸለሙ የወተት መያዣ ጡንጧቸውን በቀኝ እጃቸው ይዘው የተዘጋጀውን የ«ቡራቶ» ምግብ ማእድ ለመክፈት የተዘጋጁ ሴቶች ይታያሉ፡፡



*ፎቶግራፍ 3፡- የገበታ «ቡራቶ» በጡንጦ ከተያዘው የማወራረጃ ወተት ጋር፡፡*

ሌላው የገበታ ባህላዊ ፋይዳ የሚረጋገጥበት ክዋኔ ደግሞ ተከታዩ ነው፡፡ «ቡራቶ» እና ወተት እንደማይለያዩ ቀደም ባሉት ገጾች ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ባህላዊ ስርኣታዊ ክዋኔው እንደሚያረጋግጠው በኣንድ የገበታ ማእድ ላይ ምንም እንኳን ከ«ቡራቶ» ጋር ወተት የመቅረቡ ሁኔታ የታመነም ቢሆን የቀረበው የገበታ ማእድ ከመበላቱ በፊት የኣገር ሽማግሌዎች ከገበታው ጋር ሁሉም ነገር መሟላቱን ለማረጋገጥ ይጠይቃሉ፡፡

ይህንን በተመለከተ ኣቶ በቀለ ቱፋ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *ገበታ፣ ባለድግሱ (የድግሱ ኣዘጋጅ) የሚያዘጋጀው ምግብ ሲቀርብበትና የደጋሹ ዘመድ ከሌላ ቦታ ኣዘጋጅቶበት ወደ ዋናው ደጋሽ ቤት የሚቀርብበት ስርኣታዊ ክዋኔ ይለያያል፡፡ በደጋሹ ቤት የደጋሹን ምግብ ይዞ የሚቀርበው ገበታ የራሱ ክብር፣ ዝናና ማእረግ ኣለው፡ ተጋባዦቹም በሽማግሌዎች ኣማካኝነት የገበታውን ባህላዊ ኣቀራረብ ተመርኩዘው የሚጠይቁት ባህላዊ የምቾት ጥያቄ ኣላቸው፡፡ ለምሳሌ ሽማግሌዎችና ተለቅ ተለቅ ያሉት ወይም በተለየ ምክንያት (በገዳይነት፣ በኣስተዳዳሪነትና በሽምግልና፣ በጦረኛነት ወዘተ.) ታዋቂ የሆኑት የተለየ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ የማወራረጃ ወተት ኣብሮ መቅረቡም ይጠየቃል፡፡ የተጠየቁት ነገሮች መሟላታቸው ሲረጋገጥም ኣፍን በምግብ ከማሟሸት በፊት የምርቃት ስርኣት ይከናወናል፡፡ በዚህም መሰረት ገበታ ኣቅራቢዎቹ «የገበታው ክብር የእኔ ክብር ነው» የሚል ኣባባል ስላላቸው ተጨንቀውና ተጠበው ያዘጋጁታል፤ ይመገቡበታልም፡፡ ባህላዊ ፋይዳውም ጎልቶ የሚወጣው ከሚሰጠው ይህን ከመሰለ ግልጋሎት ኣንጻር ነው፡፡*

ገበታ ከሚያበረክተው ባህላዊ ፋይዳ በተጨማሪ ትእምርታዊነትም ኣለው፡፡ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች በሰርግም ይሁን በትላልቅ በኣላት፣ በተስካርና በገና በኣል ወዘተ. ለተጋባዥ እንግዶቻቸው ገበታ ከሌላቸው በቆሪ ምግቡን ያቀርባሉ፡፡ ኣንድ ቆሪ ደግሞ በኣንድ ጊዜ ከ3-5 ሰዎችን ነው ማስተናገድ የሚችለው፡፡ በዚህ ሁኔታ ብዙ እድምተኞች ባሉበት ክዋኔ ላይ ብዙ ቆሪዎች ሊያስፈልጉ ነው፡፡ ይህን ኣይነት ጫና ለማስቀረት ሲባል «ገበታ» ያስፈልጋል፡፡ በርካታ ሰዎች በሚስተናገዱበት ዝግጅት ላይ የገበታው መቅረብ የጌትነትና የሀብታምነት ማመልከቻም ሆኖ ስለሚወሰድ ትእምርትነቱ የጎላ ነው፡፡ በቡድን ቀርቦ በኣንድነት መመገቡ የገበታ ማህበራዊ ፋይዳ መገለጫ ኣንዱ መንገድ ነው፡፡

በተጨማሪም ገበታ ማህበራዊ ፋይዳን ያጎለምሳል፡፡ ይህ ደግሞ በኣንድ ጊዜ ከየቦታው የተጠሩ ተጋባዦችን በማስተናገድ ይገለጻል፡፡ የማይተዋወቁ ቢሆኑም እንኳን በኣንድ ማእድ ላይ በመቅረባቸው ምክንያት ብዙ የሀሳብ መንሸራሸሮች ሊደረጉ፣ ለወደፊቱም ሊተዋወቁ ይችላሉና የሚያበረክተው ማህበራዊ ፋይዳ ትልቅ ግምት ይሰጠዋል፡፡ ሌላ ጊዜም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲፈላለጉና እንዲወያዩ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም የግንኙነቱ መሰረት በትልቁ ገበታ እስከ 20 ሰዎች፣ በመካከለኛው እስከ 15 ሰዎች፣ በትንሹ ደግሞ ከ10-12 ሰዎች የመመገብ እድል ስለሚሰጥ ነው፡፡

ገበታ በርካታ ኣስተዋጽኦ ያለው መሆኑን የሚገልጹት ኣቶ በቀለ ቱፋ በኣንድ በኩልም ያላቸውን ቅሬታም እንደሚከተለው ይናገራሉ፡፡

> *ታሪክ የኣንድ ህዝብ ያለፈው፣ የዛሬውና የመጪው ጊዜ ቅርሱ ነው፡፡ የገበታ እቃም የኦሮሞ ህዝብ የማንነቱ መግለጫ ነው፡፡ የዱሮ ኣባቶቻችን የሀብታምነታቸው ማረጋገጫ ነው፡፡ ምክንያቱም ቡራቶውና ገንፎው ከመጠን ያለፈ ቅቤ የነበረው ከመሆኑም በላይ ክብር በሚያጎናጽፈው የገበታ እቃ ይቀርብ ነበርና፡፡ ጥንት ቅቤውን ብቻ ላለመጠጣት ሲባል ትንሽ ምግብ፣ በቆሎ ነገር ነበር የሚቀርበው፡፡ በኣሁኑ ጊዜ ግን ቅቤ ማባያ ነው እንጂ በቅቤ መች ይበላል፡፡ ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው፤ ከእህሉና ከቅቤው መጥፋት ጋር በገበታ መመገብም እየቀረ ነው፡፡*

በማለት ኣድናቆትና ቅሬታቸውን ከገለጹ በሁዋላ ወደ ጥንቱ ዘመን ተመልሰው ኣንድ የቀድሞ ሽማግሌ «ጥንት ልጆቻችን ይዋኙ የነበረው በትልቅ ገንዳ በተሞላ ወተት ውስጥ ነበር» በማለት የነገሯቸውን ያስታውሳሉ። ይህን ክፍል ከመዝጋቴ በፊት ለኣቶ በቀለ ቱፋ ያነሳሁላቸውን ጥያቄና የሰጡትን መልስ ላክል። ጥያቄው፣ ለመሆኑ በዘመናችን ገበታ በስፋት በጥቅም ላይ የማይውልበት ምክንያቱ ምንድነው? የሚል ነበር። የባህሉ ባለቤት የሆኑት ኣቶ በቀለ ቱፋ መልሱን በምሳሌ ነበር ያስደገፉት።

*«'እርጎው የለም እንጂ ዳቦው ቢኖር ኖሮ ኣምጌ እበላ ነበር' የተባለውን ምሳሌ ኣስታወሰኸኝ፤ ዛሬማ ገበታውን ሰሪ ባለሙያ፣ እንጨቱ፣ ቅቤውና እህሉስ መቼ ተገኝተው። የገበታ ነገር ታሪክ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው። ኣንዳንድ ጊዜ ለበኣል ሲፈለግ እንኳን የሚገኘው በየግለሰቦች ቤት በማጠያየቅ ነው።»*

## 4.2.2 ቆሪ (QORII)

የእንጨት ስራ ውጤት ከሆኑት የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ መመገቢያ ቁሳቁስ ኣንዱ ቆሪ «Qorii» ነው። ኣቶ በቀለ ቱፋ «ቆሪ ማለት የጎረጎደ፣ ጎርጓዳ ማለት ነው፤ ኣሰራሩ ከእንጨት ሆኖ ተቦርቡሮ (ጎድጓዳ ሆኖ) የተዘጋጀ መመገቢያ እቃ ነው» በማለት ይገልጹታል። ቆሪ ከገበታ ጋር ሲነጻጸር የገበታ ታናሽ (ትንሹ) የመመገቢያ እቃ ነው።

***ኣሰራር፡-*** ቆሪ ለንፋስና ለጸሀይ በቀላሉ በማይበገሩ የኮሶ እና ዋንዛ እንጨቶች ይሰራል። የቆሪን ኣሰራር በተመለከተ ሀጂ ኣብጄልጀዋድ ኣዲ ቀጥሎ ያለውን ሀሳብ ሰጥተውኛል።

*«ቆሪ» የእንጨት ስራ ውጤት ነው፤ እንጨቶቹ በወይና ደጋም በቆላም ሊበቅሉ የሚችሉ የኮሶ እና የዋንዛ ግንዶች ናቸው። እንደ ኮሶ እና ዋንዛ የመሳሰሉ እንጨቶች የጸሀይንና የንፋስን ጥቃት ሊቋቋሙ ስለሚችሉና በቀላሉ ስለማይሰነጠቁ ለቆሪ ኣይነት ስራ ተመራጭ ናቸው። ኣሰራሩ ቅርጽ ከማውጣት ክዳኑን ሙሉ በሙሉ የእንጨት ውጤት ከማድረግና ኣነስተኛ በመሆኑ ለመስራት ከሚወስደው መጠነኛ ጊዜ በስተቀር ከገበታ ኣሰራር ጋር ተመሳሳይ ነው። የሚገኝ ከሆነ ከኮሶ እንጨት ይልቅ የዋንዛ እንጨት «ሙካ ወዴሳ» (Muka Waddeessa) ይመረጣል። የዋንዛ ወፍራሙ ወገን ይቆረጥና ኣላስፈላጊው ቅርፊት ከተነሳለት በሁዋላ የተፈለገው መጠን ላይ እስከሚደርስ ድረስ እየተጠረበ ይዘጋጃል። የመጥረቡ ተግባር እንዳበቃ የተፈለገውን ግንድ ለማግኘት የመቦርቦሩ ተግባር በኣነስተኛ መጥረቢያና መሮ ይከናወናል። እተፈለገው መጠን ድረስ ከተቦረቦረ በሁዋላ በሱፋጭ፣ በብርጭቆ ስባሪ ያለሰልሱታል። የማለስለሱ ስራ ካበቃ በሁዋላ ፍግ ከተገኘ በፍግ ውስጥ፣ ፍግ ካልተገኘም በእበት ይለቀለቅና በጥላ ውስጥ ቅጠል ተሸፍኖ ይቀመጣል። የቆይታው ጊዜ ከ5-6 ቀናት ይወስዳል። ከዚያ በሁዋላ ቅርጽ የማውጣቱ ስራ ይከናወናል። ቅርጽ የሚያወጡለትም በወስፌ (ሙታ) «Mutaa» ወይም ሹል ጫፍ ባለው ሰንጢ ሊሆን ይችላል። ቆሪን ለመስራት በፍግ ውስጥ ወይም በእበት ተለቅልቆ የሚቆይበትን ጊዜ ሳያካትት በ10 ቀናት ውስጥ ሊያልቅ ይችላል። ይህ ግን እንደመጠኑ ትልቅነትና ትንሽነት የሚወሰን ነው።*

የቆሪ ስራ በይበልጥ ወንዶችን የሚመለከት ቢሆንም የሴቶችም ተሳትፎ ኣለበት:: ወንዶች እንጨቱን ጠርበውና በወስፌና በሰንጢ የተለያየ ቅርጽ ያላቸውን ጌጣጌጦች ካወጡለት በሁዋላ የማሚሸቱ ስራ የሴቶቹ ነው:: ክዳኑ የስፌት ከሆነም የሚመለከተው ሴቶቹን ነው::

የሪራ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም በቆሪ ላይ ያለውን ጌጥ እንዴት ትሰሩታላችሁ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት መልስ ተከታዩ ነው::

> *ቆሪን የምናስውበው በዋናው ቆሪ እና በክዳኑ ላይ በጠፍር «»ቴጳ» (teephaa) እናብተዋለን:: የቆሪው ክዳን ከዋናው እናት ቆሪ እንዳይለያይና በቀላሉ እንዳይከፈት ከታች ከእግሩ እና ከዋናው ቆሪ መጋጠሚያ ጀምሮ «ሳምሳ» የሚባል የጠፍር ማሰሪያ እናብታለን:: የማበቱ ስራ በመጠላለፍና በክዳኑ ቀዳዳ ኣልፎ ከክዳኑ በላይ እስከሚወጣ ድረስ በሶስት ኣቅጣጫ ወደ ላይ እንዲወጣ ኣድርገን እናስራለን:: ጠፍሩን ካሰርን በሁዋላ ይበልጥ ለማሳመር ጨሌዎችንና ዛጎሎችን በጠፍሩ ጥብጣብ ላይ እናያይዛለን:: የሚያያዙት በጣም ቀጫጭን በሆኑ ሌሎች ጠፍሮች ወይም በችንጊያ ሊሆን ይችላል:: የጨሌዎችና ዛጎሎች ኣደራደር ወደታች ወይም ወደ ጎን ሊሆን ይችላል:: ጨሌዎቹ በኣንድ መደዳ፣ ዛጎሎቹም እንዲሁ በኣንድ መደዳ ይደረደራሉ:: መጀመሪያውኑ ክዳኑ ሲሰራ በእጅ መያዣው ላይ ሶስት ወይም ሁለት ቀዳዳዎች እንዲኖሩት ይደረጋል:: እነዚህ ቀዳዳዎች ከታች የመጣውን ጠፍር በውስጣቸው በማሾለክ ወደ ላይ ለማንጠልጠያ እስከሚተርፍ ድረስ እንዲዘልቅ ያደርጉታል:: ይህ ጠፍር በማንጠልጠያነት ከማገልገሉ በተጨማሪ ክዳኑም እንዳይወድቅ ኣፍኖ ይይዝልናል::*

በፎቶ 4 ላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂምን ሀሳብ የሚያጠናክር ቆሪ ማየት ይቻላል:: ቆሪው በኣረንጓዴ ጨሌዎች የተሸለመ ነው:: ልጅቱም የምታስተዋውቀው የቆሪ እቃን ነው::



*ፎቶግራፍ 4:- የቆሪን አገልግሎት በማስተዋወቅ ላይ::*

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የዚህ ጥናት ኣቅራቢ ኣይቶ እንዳረጋገጠው ቆሪ የሚቦረቦረው እንደየባለቤቶቹ ፍላጎት ሰፋ ወይም ጠበብ ተደርጎ ሲሆን የእግሩ ኣለመርዘምም ሆነ የመጠኑ ማነስ ከሚሰጠው ኣገልገሎት ኣንጻር በመሆኑ ከገበታ በእጅጉ ይለያል። በዋናው እናት ቆሪም ሆነ በክዳኑ ላይ የሚሰሩ የጌጥ መስመሮች ቅርጻቸው ይለያያል። በመሆኑም ትይዩ መስመሮች (parallel)፣ ባለ ሶስት ቅርጽ (Triangle)፣ በኣግድም የተጋደሙ መስመሮች (horizontal lines) ወይም ጥልፍልፍ ዲያመንድ መስመሮች (entanglement diamond lines) ዚግዛግ ወይም ክብነት ያላቸው ሽንትሮች (Zigzag or Circle Grooves) እና የመሳሰሉት ይኖሩባቸዋል። የቆሪ ክዳን ኣሰራርም እንደየፍላጎት ይለያያል። ኣንዳንድ ክዳን ወጣ ያለ ጉልላት የመሰለ መያዣ ይቀረጽለታል፣ ሌላው ጣቶችን ሊያስገቡ የሚችሉ ቀዳዳዎች ይበጁለታል። ፎቶግራፍ 5ን መመልከት ነገሩን ግልጽ ያደርገዋል።




*ፎቶግራፍ 5፡- በተለያየ ቅርጽና መጠን ከእንጨት የተሰሩ ቆሪዎች።*

«ቆሪ» እግር ያለውና የሌለው ተብሎ ሊከፈል ይችላል። እግር ያለው ቆሪ የእግሩ (መቆሚያው) ርዝመት ከ3-5 ሳንቲሜትር ቁመት ሊኖረው ይችላል። እግሩ ተቀጥላ ሳይሆን ከዚያው ከዋናው እንጨት የሚዘጋጅ ነው። እግሩ (መቆሚያው) በግልጽ የማይታይ ቆሪ ደግሞ ከወደ መቀመጫው ጠፍጣፋ ሆኖ ይቀረጻል። ቆሪ እንዲደረጅ በጉሎ፣ በሞራና በቅቤ እንቃሪ (ኣተላ) ይታሻል። ኣንዳንድ የቆሪው ተንከባካቢዎች የቅቤውን እንቃሪ (ቅቤ ከተነጠረ በሁዋላ የሚቀረው ዝቃጩ ነው) በውስጡ ያደርጉና

ለተወሰኑ ቀናት ከድነው ያስቀምጡታል:: የቆሪ ክዳን በአብዛኛው 99% የሚዘጋጀው ከእንጨት ሲሆን አዘገጃጀቱ የድስት እፊያ የመሰለ ቅርጹን ከመጠበቅ ውጭ የሚሰራለት የሽንትር ጌጥም ሆነ የአሰራር ቅደም ተከተሉ ለእናት ቆሪው የተጠቀሙበት አሰራር ነው:: አልፎ አልፎ ሙያተኛ ሲጠፉ እና በተለያዩ ምክንያቶች (ጊዜ ሲያጥር፣ እንጨት እንደልብ ሳይገኝ ወዘተ.) ሳያመች ሲቀር ከስንደዶ ስፌት ይዘጋጃል:: የስንደዶው ስፌት አዘገጃጀት በገበታ ክዳን አሰራር ላይ ከጠቀስነው የተለየ አይደለም::

በ«ቆሪ» ላይ በተለያዩ ቅርጾች የሚሰሩት ሽንትሮች (እንደንቅሳት ያሉት) ለማስጌጥ ሲባል በጥንቃቄ የሚሰሩ ባለሙያው የሚፈተንባቸው ናቸው:: እንደ አቶ በቀለ ቱፋ ሽንትር-ሽንትር ማጋጌጫ ንቅሳቶች በኦሮምኛ «በበሬሱ» «Babarreessuu» ይሉታል:: «ጥበብን መስራት፣ ጥበብን ማሳየት ማለት ነው» ሲሉ ያረጋግጣሉ::

ቆሪዎች በተለያየ መጠን ይሰራሉ:: በጎባ ወረዳ በዚህ ጥናት ላይ ያገኘሁኣቸውን የትልቅና የትንሽ ቆሪ መጠን ምን እንደሚመስል ልዩነታቸውን ለማጤን ያህል እንመልከት:: የትልቁ ቆሪ ቁመት ከእግሩ እስከ ክዳኑ መያዣ 33 ሳንቲሜትር የእግሩ መጠነ ዙሪያ 13 ሳንቲሜትር ነው:: ቆሪ በተፈጥሮው (በአሰራሩ) ከታች እና ከላይ ጠበብ እያለ ይመጣና ከክዳኑ መጋጠሚያ ላይ አፈ ሰፊ ይሆናል:: በዚህም መሰረት ትልቁ ቆሪ የክዳኑና የዋናው ቆሪ መጋጠሚያ (መዝጊያ) ላይ መጠነ ዙሪያው 59 ሳንቲሜትር መሆኑን አረጋግጫለሁ:: በክዳኑ ኣናት ላይ ያለው መያዣ ደግሞ መጠነ ዙሪያው 9 ሳንቲሜትር ነው::

የትንሹ ቆሪ (ይህ በተለይ እግር የሌለው ነው) ቁመቱ 28 ሳንቲሜትር ሲሆን የመቀመጫው መጠነ ዙሪያ ደግሞ 12 ሳንቲሜትር ነው:: ከመክደኛው መጋጠሚያ ጀምሮ መሬት ላይ እስከሚቀመጠው ኣካሉ ድረስ ቁመቱ 14 ሳንቲሜትር ነው:: መክደኛውና ዋናው ቆሪ የሚጋጠሙበት ቦታ ዙሪያውን ሲለካ 17 ሳንቲሜትር መሆኑን ኣይቻለሁ:: ከዚህ በላይ ያስቀመጥኩት በምልከታ ያገኘሁዋቸው ሲሆኑ የትንሽና የትልቅ ቆሪን የመጠን ልዩነት ለማስገንዘብ ያህል ነው እንጂ የተገለጹት መጠኖች ቋሚ ናቸው ማለት አይደለም፤ እንደሰሪዎቹ ይለያያሉና::

*ኣገልግሎት፡-* ቆሪ በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ በዋነኝነት የገንፎ እና የበሶ ምግቦች ማቅረቢያና መመገቢያ ነው:: በሰርግ፣ በደቦ ወይም በበኣላት የተሻሉና ውብ ቆሪዎችን መጠቀም የተለመደ ነው:: በዚህም የተነሳ የቆሪው ውበትና ጥበባዊ ጌጥ የኣዘጋጅዋ ሴት ሙያዊ ብቃት የሚፈተንበት ነው::

ብዙውን ጊዜ በኣላትን ምክንያት በማድረግ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች እርስ በእርስ ሲጠያየቁም ሆነ ወደ ሌሎች የብሄረሰብ ኣባላት የ«እንኳን ኣደረሳችሁ» መልእክት

ለማስተላለፍ ባዶ እጃቸውን ኣይሄዱም፤ ቅቤ የጠገበ ገንፎ በቆሪ ሞልተው፣ በኣንዱ ጎናቸው ኣቀፍ ኣድርገውና ነጠላቸውን በቆሪው ላይ ጣል ኣድርገው ይሄዳሉ እንጂ።

በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀውን ገንፎ በመሀሉ ትልቅ ጉድጓድ (ቅቤ የሚጨመርበት) ይሰራለትና በርከት ያለ ቅቤ ይደረግበታል። ቅቤው የገንፎ ልባስ ስለሚደረግለት ኣይታይም። ይህ በመንገድ ላይ እንዳይፈስም ይረዳል። ገንፎውን የለበሰው ቅቤ ሽፋኑ የሚነሳለት ለመበላት ሲቀርብ ነው። ገለጥለጥ ሲደረግም የነጠረው ቅቤ ለኣይን ይከሰታል። ቆሪ ከገበታ ኣንጻር ሲታይ ኣነስተኛ እንደመሆኑ መጠን የኣንድ ቤተሰብ ኣባላት ሊመገቡበት ይችላሉ። በዚህም ቤተሰባዊ ፍቅርን ያደራጃል። ሌላው የቆሪ ኣገልግሎት «ገበና ከታች የምስጢር ጓዳ መሆኗ ነው» ይሉና ኣቶ በቀለ ቱፋ የ«ቆሪ»ን ባህላዊ ፋይዳ እና ከ«ቆሪ» ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮችን ይዘረዝራሉ።

*«ቆሪ» ከ«ገበታ» በፊት የመጣች ለ«ገበታ» መሰረት የሆነች፣ በጎባ ዙሪያ ፈሳሽ ላልሆኑ ምግቦች - ቡራቶ፣ በሶ፣ ጨጨብሳ ወዘተ. መመገቢያ የሆነች፣ ከ2 እስከ 3 ሰዎችን ማስተናገድ የምትችል እቃ ነች። «ገበታ» እንደልብ ስለማይገኝ እንደ እድምተኛው ብዛት ከ5 እስከ 6 ወይም ከዚህም ቁጥር በላይ የሆኑ ቆሪዎች በማእድነት ይቀርባሉ። «ቆሪ» ነባር እቃ በመሆኗ እድሜ ለጠገቡ ሰዎች ትዝታቸው ነች። እንደ ኦሮሞ ኣጠቃላይ ህዝብ ስንወስዳት ደግሞ ታሪካዊ እሴት ነች። ከዚህም በላይ «ቆሪ» የጓዳ ምስጢር፣ የባለቤቶቿ ገበና ከታች ነች። ምክንያቱም «ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ ኣያድርም» እንላለንና ገንፎው ቅቤ ባይኖረው ወተት ተጨምሮበት፣ በሶውም ያለ ቅቤ በደረቁ የቤተሰቡ ኣባላት ስለሚመገቡት ነው ገበና ደባቂ መባሏ። በመሆኑም ትዝታ ከመሆኗና ከታሪክ ነጋሪነቷ ባሻገር የቤትን ገበና ስለማታጋልጥ ፋይዳዋ የላቀ ነው።*

*«በተጨማሪም» ይላሉ ኣቶ በቀለ በተጨማሪም የ«ገበታ»ው ክብር የደጋሹ ወይም የባለሙያዋ ሴት የመሆኑን ያህል የ«ቆሪ» ክብር ደግሞ የኣባወራው ነው። «ሀጰ ወራዋ» ሚስቱ ለ«ኣባ ወራዋ» ለባለቤቷ ክብር የምትገልጽበት ነው። ምክንያቱም በወረዳው የኦሮሞ ባህል ለኣባወራው ምግብ የሚቀርበው በጥንቃቄ በተያዘች ቆሪ ነውና። ይህች ቆሪ በጌጥም የተሸለመች ነች። ቆሪዋ የተንገላታች ከሆነ አባወራው ግምት ይወስዳል። ስለዚህ በጥንቃቄ ትያዛለች።*

***የቆሪ ባህላዊ ፋይዳ*** : «ቆሪ» ከተዳረች ልጅ ጋር ዘማች በመሆኑ ባህላዊ ፋይዳው ጎልቶ ከሚወጣበት መድረክ ኣንዱ የሰርግ ስርኣታዊ ክዋኔ ነው። በዚህ ረገድ ያለው ባህላዊ ፋይዳ የተዳረች ሴት ልጅ ድንግልና እንደኣላትና እንደሌላት ለመግለጽ የመልእክት ማስተላለፊያ ሆኖ ከማገልገሉ የሚመነጭ ነው። ይህም በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ ሲተገበር እንደቆየ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ

*«ከእናቷ ቤት የተላከውን ቆሪ ሙሉ ገንፎ የልጁ (የኣግቢው) ቤተሰቦች ሙሉ በሙሉ ከበሉ በሁዋላ ገንዘብ ጨምረው የሚልኩበት ስርኣት በድንግልናዋ እንደተገኘች ሲያረጋግጥ በሌላ ወገን ገንፎውን ሳይበሉ መልሰው ከላኩት ግን ድንግልና ያልነበራት መሆኑን መጠቆሚያ ነው» በማለት ያረጋግጣሉ።*

ይህ ስርኣታዊ ክዋኔ በሀረርጌ ክፍለ ሀገር በጨርጨር ኣውራጃ ይሰራበት እንደነበር በኣንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ተረጋግጧል። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ኦሮሞዎች ተመሳሳይ ባህል እንደሚያንጸባርቁ ይገመታል። ሀረርጌና ባሌ ደግሞ ጎረቤታሞች ከመሆናቸውም በላይ ባሌ «እ.ኤ.ኣ. ከ1942 ጀምሮ የሀረር ጠቅላይ ግዛት ወረዳ፣ ከ1946 ጀምሮ ደግሞ የሀረር ኣውራጃ በመሆን ከቆየች በሁዋላ በ1960 ሙሉ ጠቅላይ ግዛት ሆነች» (Mindaye Abebe፣ እ.ኤ.ኣ. 2005፣15) የሚለውን ስናጤን በሁለቱ ዞኖች፣ በቆሪ ኣማካኝነት የሚታየው ባህላዊ ፋይዳ ኣንዱ ከሌላው የወሰደው ይሆናል የሚል ግምት ያሳድራል። የ«ቆሪ»ውን ባህላዊ ፋይዳ በተመለከተ የሽመልስ እጅጉ ጥናታዊ ጽሁፍ ተከታዩን ኣስፍሯል።

> *በቀነ ጫጉላዋ ማግስት ክብረ ንጽህናዋ ቀድሞ ያልተደፈረ ከሆነ የምስራች፣ ቀድሞ የተደፈረ ከሆነ ደግሞ መርዶ ማርጃ የሚሆን ከእናቷ ቤት «ቆሪ ሀጳ» «Qorii Hadhaa» (የእናት ቆሪ) በመባል የሚታወቅ ገንፎ በቅቤ ተደርጎ በቆሪ ይመጣል። ሙሽሪት ከነክብሯ ከተገኘች የልጁ ቤተሰቦች ገንፎውን ጥርግ ኣድርገው ከበሉ በሁዋላ በቆሪው ውስጥ የደስታ መግለጫ ገንዘብ በመጨመር በልጅቱ ሚዜዎች በኩል ቆሪውን መልሰው ይልካሉ። ....ነገር ግን ሙሽሪት ክብረንጽህና ከሌላት ገንፎውን በትንሹ በስተው በማውጣት ቀሪው እንዳለ ሳይነካ ለወላጆቿ ይላካል (1981፣23)።*

ቆሪ የነገር ማጣፈጫና የነገር ማለዘቢያ በመሆንም ያገለግላል። «ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ» እንዲሉ በኦሮሞ ባህል ነገርን፣ ውይይትን በምሳሌ ኣስደግፎ መናገር የተለመደ ነው። ነገርን በደረቁና በፊት ለፊት ከመናገር ይልቅ ወዝ ኣላብሶ፣ ሰዎችን እንዲያስፈግግ ኣርቅቆ መናገር በኦሮሞዎች ይዘወተራል። ፍካሬያዊ ኣነጋገር በእማሬ ተላብሶ ነገርን ለማዋዛት በሚቀርብበት ጊዜ መልእክቱን ኣንጥሮ የተፈለገው ነጥብ ላይ ለመድረስ የኣድማጩን ብስለት ይጠይቃል። ይህ ደግሞ በኦሮሞዎች የተለመደ ነው። «ነገር በምሳሌን ....... በተመለከተ በቆሪ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ኣንድ ኣባባል ኣለ» ኣሉና ኣቶ በቀለ ቱፋ ኣይናቸውን ቦዘዝ ኣድርገው ኣንዴ ወደቤታቸው ጣራ ሌላ ጊዜ ወደ ግድግዳው ከወረወሩ በሁዋላ በትዝታ የሚያስታውሱትን እንደሚከተለው ኣወጉኝ።

> *ብዙውን ጊዜ በኦሮሞ የኣመጋገብ ባህል ኣባወራው የሚመገበው በቤቱ በኣንደኛው ክፍል ነው። ባለቤቱ (ሚስቱ) (ሀጳ ወራዋ) ደግሞ በሌላው የቤቱ ክፍል ትቀመጣለች ወይም ጉድጉድ ትላለች። በዚህን ጊዜ በ«ቆሪ» የቀረበለትን ምግብ በመመገብ ላይ ያለው ባለቤቷ «ማል ሀጳ ኤበሉ ቆሪን ጎግዴ» «Maal Hadhaa Ebaluu Qooriin Gogide» (የእግሌ እናት ምነው ቆሪዋ ለምን ደረቀች) ይላታል። ኣነጋገሩ በቀጥተኛ ፍችው ከሚያስተላልፈው ይልቅ ዋናው መልእክቱ ያቀረብሽልኝ ምግብ ቅባት (ቅቤ) ጎድሎታል ወይም ኣልጣመኝም የሚል ነው። ደራሽ እንግዳም መጥቶ በመመገብ ላይ እያለ ኣባወራው መልእክቱን የሚያስተላልፈው በዚሁ ኣይነት በመሆኑ ሚስቱን እያስገነዘበ በኣንጻሩ እንግዳውንም ያስፈግጋል። ነገሩ ፈሊጣዊ ኣነጋገር ነውና።*

*ታሪካዊ ፋይዳ፡* ታሪካዊ ፋይዳ ስንል ቁሳቁስ በእደጥበብ የተገኙበት ወይም በፋብሪካ የተፈበረኩበት ዘመን ሲጠና የህዝቦች፣ የብሄረሰቦች ወዘተ. ታሪክም አብሮ ይጠናል ማለታችን ነው። ታሪክን ስንጠቅስ የድንጋይ ዘመን፣ አጥንት ግልጋሎት የሰጠበት ዘመን፣ የሰው ልጅ በእንጨት መገልገል የጀመረበት ዘመን፣ የብረትና የሸክላ ዘመን ወዘተ. ስንል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለ ህዝቦች ታሪክ መናገራችን ነው። ከዚህ አንጻር ቀደም ሲል በአቶ በቀለ ቱፋ እንደተገለጸው ቆሪ ከገበታ በፊት በግልጋሎት ላይ የዋለ እቃ ነው። ምንም እንኳ የዚህ ጥናት ኣላማ ባይሆንም በሌሎች ተመራማሪዎች የቆሪ ኣገልግሎት መቼ ተጀመረ? መቼስ ለገበታ ቦታውን ለቀቀ? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ የህዝብን ታሪክ ለማወቅ ይቻላል። ቆሪ በዚህ ረገድ አንድ ሚና ሳይኖረው ኣይቀርም። እዚህ ላይ የቆሪ ታሪካዊ ፋይዳ ስንል ቆሪ ከገበታ በፊት የተገኘ ባህላዊ እቃ እንደነበር ለመጠቆምና በዚያ ሳቢያ የህዝብን ታሪክ ለሚመረምሩ ግለሰቦች ፍንጭ ለመስጠት ነው።

እንደ ገበታው ሁሉ ቆሪም ከእንጨት በመሰራቱ እና የባለሙያው መታጣት፣ ዘመነኛ የሆኑ ልዩ ልዩ እቃዎች እንደ ኣሸን መፍላት ኣገልግሎቱን እየቀነሰው መጥቷል። ኦሮሞዎቹ ግን የእንጨቱ እና የሰሪው ኣለመኖር እንጂ በላስቲክ ሳህን መመገቡን የሚፈልጉት ኣይመስልም። ገንፎውን ያቀዘቅዝብናል እያሉ በተለይ የላስቲኩን፣ ዘመን ወለድ እቃ ሲኮንኑ ይሰማሉ።

### 4.2.3 ቁዲ ሶረታ (QUUDII SOORATAA)

ቁዲ «Quudii» ከእንጨት ከሚሰሩ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ባህላዊ መመገቢያ ቁሳቁስ ውስጥ ኣንዱ ነው። «ቁዲ ሶረታ» ማለት ምን ማለት ነው? ብዬ ላቀረብኩላቸው ኣቶ በቀለ ቱፋ ሲመልሱ

> *«ሶረታ (Soorataa) ማለት ምግብ ማለት ነው፤ ከዚህ ተነስተን 'ቁዲ ሶረታ' የሚለውን የምግብ መያዣ ቁዲ ልንለው እንችላለን። በ'ቁዲ ሶረታ' የሚቀመጡ ምግቦች ቆይተው የሚበሉ ወይም ለደራሽ እንግዳ የሚቀመጡ እንደ ጭኮና ጨጨብሳ የመሳሰሉ ከእህልና ከቅቤ ብቻ የሚዘጋጁ የምግብ ኣይነቶች ናቸው» ብለዋል።*

የእቃው ስያሜ ከኣገልግሎቱ ጋር የቀረበ ነው። በዚሁ መሰረት እንደ ኣቶ በቀለ ቱፋ ከሆነ ለወተት ማስቀመጫ የሚሆነውን (Quudii Aannanii) «ቁዲ ኣነኒ» የወተት ቁዲ ይሉታል። ቁዲ ኣፈ-ጠባብ ከመሆኑ ጋር ለወተት ማለቢያ ወይም ማጠራቀሚያ እንጂ እንዴት ለምግብ ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ ሲመልሱም «ጠባብ ቢሆንም የቀንድ ማንኪያ ስላላቸው ምግቡን በማንኪያ ያወጡና በሌላ እቃ ላይ አድርገው ይመገቡታል» በማለት መልስ ሰጥተዋል።

*ኣሰራር፡* - በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ ከእንጨት የሚሰሩ መመገቢያ እቃዎች ኣሰራር ከጥቂት ጥበባዊ ልዩነቶች በስተቀር በኣብዛኛው ተመሳሳይ ነው፡፡ ተመሳስሎውን ለማጤንም ቁዲንና ቆሪን መመልከት ይቻላል፡፡ ፎቶግራፍ 5ን እና 6ን ያጢኑ፡፡ ለቁዲ መስሪያ የሚሆነው እንጨት ቀላል ግን ደግሞ ጸሀይና ንፋስን ሊቋቋም የሚችል ነው፡፡ ተመራጮቹ እንጨቶችም የኮሶ፣ የዝግባ ወይም የዋንዛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የተፈለገው የቁዲ መጠን ውስጡ በመሮ ወይም ቀጠን ባለች ስለታም መጥረቢያ ይጠረባል፡፡ ከእቃው ትንሽነት አኳያ በኣጭር ጊዜ ውስጥ ከመጠናቀቁ በስተቀር የኣሰራር ቅደም ተከተሉ በገበታ ላይ ያየነውን በመሆኑ እዚህ ላይ መድገሙ ኣያስፈልግም፡፡

የቁዲዎች መቀመጫ ጠፍጣፋና ክብ ወይም ሞላላ ቅርጽ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ ጠፍጣፋ በመሆኑም ቁዲው መሬት ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ ተረጋግቶ ሊቆም ይችላል፡፡ ቁዲ ከመቆሚያው መጋጠሚያ ከላይ ክዳኑ እስከሚገጥምበት ድረስ ያለው የውፍረት መጠን ኣንድ ኣይነት ነው፡፡ ይህ እንደሰሪዎቹ ቢለያይም ከግማሽ እስከ 1 ሳንቲሜትር ይደርሳል፡፡ ውፍረቱ ቀጠን ብሎ የሚታየው የቁዲው ኩሬ (ክዳን) ከእናት ቁዲው ጋር በሚገጥምበት ኣካባቢ ላይ ነው፡፡ የግጣሙ ኣካባቢ በጣም ለስላሳና ቀጠን ያለ ነው፡፡ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ እንደሚሉት ቀጠን ማለቱ ክዳኑ ግጥም ብሎ እንዲዘጋ ያደርጋል፡፡



*ፎቶግራፍ 6፡- በተለያየ መጠን ከእንጨት የተሰሩ ቁዲዎች፡፡*

በቁዲ ግራና ቀኝ ባሉት የወገቡ ኣካባቢዎች ሁለት ጆሮዎች ተቀጥላ ሳይሆኑ ከዚያው ከቁዲው ኣካል ተፈልፍለው ይሰሩለታል፡፡ ይህ በሁሉም ቁዲዎች ላይ ተግባራዊ የሚሆነው የጆሮ ኣወጣጥ እንደ እንስራ ጆሮ ሰፊ ቀዳዳ ያላቸው ሳይሆኑ ማንጠልጠያ

የሚሆነውን የጠፍር ጥብጣብ ወይም ቀጭን የገመድ ማንገቻ ሊያስገባ የሚችል መጠነኛ ቀዳዳ ብቻ ነው የሚኖራቸው:: በጆሮዎቹ ላይ የሚታበተው ጠፍር ወይም ገመድ ከቤት ውጭ ወተት ይዘውበት በሚሄዱ ጊዜ ማንጠልጠያ በመሆን፣ በቤት ውስጥም መስቀያ በመሆን ያገለግላል:: ቁዲዎች ኣልፎ ኣልፎ እንደ ሰንጢ፣ መሮ፣ ወስፌ ወዘተ. በመሳሰሉ ስለታም መሳሪያዎች ጌጥ ይወጣላቸዋል:: ጌጦቹ በተለያየ ቅርጽ (ሶስት፣ ኣራት ማእዘን) የሚነደፉ ናቸው:: ይህም እቃውን ለማስጌጥ ሲባል የሚሰራ ንቅሳት ነው:: ከዚህ ውጭ የጨሌ ወይም የዛጎል ጌጥ ሲደረግባቸው ኣይታይም:: ቁዲዎች በመጠን የተለያዩ ሆነው ይሰራሉ:: የዚህ ጥናት ኣቅራቢ ትልቁን፣ መካከለኛውንና ትንሹን እንዲሁም እግር ያላቸውንና የሌላቸውን ቁዲዎች ለማየት ችሏል:: በምልከታውም መሰረት ባለእግሩሙ ረጅሙ ቁዲ ቁመቱ 29፣ በዋናው ቁዲ እና በክዳኑ መጋጠሚያ ላይ ያለው መጠነ ዙሪያ 30፣ የእግሩ መጠነ ዙሪያ 10፣ በክዳኑ ላይ ያለው የእጅ መያዣ ርዝመት 7 ሳንቲሜትር እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል:: የመካከለኛው ቁዲ ርዝመት 23፣ የክዳኑና የዋናው ቁዲ መጋጠሚያ መጠነ ዙሪያ 32፣ የእግሩ መጠነ ዙሪያ 8 ሳንቲሜትር ነው:: ትንሹ ቁዲ ግን ከሁለቱ ኣንጻር ሲታይ በመጠን የሚያንስ በመሆኑ ቁመቱ 18፣ የክዳኑና የኣፉ መጋጠሚያ ዙሪያ 27፣ የእግሩ መጠነ ዙሪያ 7.5፣ የክዳኑ መያዣ 6 ሳንቲሜትር ነው:: እግር የሌለው ቁዲም ቁመቱ 30፣ የክዳኑና ዋናው ቁዲ መጋጠሚያ መጠነ ዙሪያ 32፣ መሬት ላይ የሚቆመው ጠፍጣፋው ክፍል መጠነ ዙሪያው 9፣ የመክደኛው ኣናት በእጅ የሚያዘው ደግሞ 7 ሳንቲሜትር እንደሆነ በምልከታ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል (የአሀዞቹ መስፈርያ ሳንቲሜትር ነው::) ከዚህ በላይ እንደተመለከተው በቁዲዎች መካከል የመጠን ልዩነት ይታያል:: ሌላው ቀርቶ ትልቅ በሚባሉ ቁዲዎች መካከል እንኳን ልዩነት ኣለ:: ይህም «እህሉ ኣንድ ሴቱ ኣስራ ሁለት» እንደሚባለው የተለያዩ ሙያተኞች እንደየግንዛቤያቸው ይሰሩታል ማለት ነው:: በኣጠቃላይ እዚህ ላይ ተለክተው እንደማስረጃ ከተጠቀሱት ቁዲዎች በለጥ ያሉ ወይም ያነሱም ሊሰሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል::

***የቁዲ ክዳን ኣሰራር፡-*** የቁዲ ክዳን ለክዳንነቱ ብቻ ሳይሆን መጠጫም ሆኖ ስለሚያገለግል መጠኑ ትልቅ ነው:: ከእጅ መያዣው ጫፍ ጀምሮ ከዋናው ቁዲ ጋር እስከሚጋጠምበት ድረስ የተለያየ ቅርጽና የውፍረት መጠን ይኖረዋል:: ፎቶግራፍ 6 ላይ እንደሚስተዋለው የቁዲዎች ክዳን ኣሰራር 3 ደረጃች ኣሉት:: ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ይህንኑ ሲገልጹ

> *የመጀመሪያው በእጅ በደንብ ለመያዝ የሚያስችል ቅርጽ ያለው ሆኖ ከስረኛው የክዳኑ ኣካል ተረፍ (ወጣ) ተደርጎ ከስርም በስልት የተከረከመውና ኣናቱ ዝርግ የሆነው ክፍል ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በድርብ ቅርጽ መጥቶ፣ ሽንትሮች እንደንቅሳት ጌጥ የወጡለት ወደ ዋናው የቁዲ ኣፍ በሚገጥመው ላይ ተደርቦ የሚታየው ነው:: ሶስተኛውም ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር ቀጠን ያለውና ከዋናው ቁዲ ኣፍ ጋር በመክደን (በመግጠም) የሚገናኘው የመክደኛው የመጨረሻ ግጣም ነው ብለዋል::*

ቁዲ ግልጋሎት ላይ ከመዋሉ በፊት በሚገባ ይቆራሻል:: ለቆራስማ የሚሆነው እንጨት ጥሩ መኣዛ ያለው የወይራ እንጨት ነው:: መጠኑ ትንንሽ የሆነ የወይራ ጉማጅ በእሳት ውስጥ ይገባና በመንደድ ላይ እያለ ሙያተኛዋ ሴት ያንን የሚነደውን የወይራ እንጨት እያነሳች በቁዲ ውስጥ ትጨምርና ክዳኑን ግጥም አድርጋ ዘግታ ትንጠዋለች:: በዚህ ኣይነት ተደጋጋሚ ስራ፣ ውሀ በመጠኑ እያርከፈከፈች ካከናወነች በሁዋላ በንጹህ ጨርቅ ውስጡ ይጠረጋል:: በዚህ የታለበ ወተትም ጣእሙ ያረካል:: ስለዚህ ይህንን የማትጠቀም የኦሮሞ ሴት እንደ ገልቱ ስለምትቆጠር ለቁዲ እቃዎቿ ጥንቃቄ ታደርጋለች:: በተለይ ለቡና ወተት የሚቀመጥበት ቁዲ በዚህ መልኩ ካልተዘጋጀ ወተቱ ሊረጋ ስለሚችል ቆራስማ መጠቀሙ ዋና ተግባር ነው::

***የቁዲ ኣገልግሎት፡*** የቁዲዎች ዋና ኣገልግሎት ለወተት ማለቢያ፣ ለእርጎ ማስቀመጫና በተለይ በሚገባ የተቆራሸ በመሆኑና ጥሩ መኣዛ ስለሚኖረው ለቡና የሚሆነውን ወተት ማቆያ በማድረግ ይገለገሉበታል:: ከዚህም በስተቀር እንደ ጭኮና ጨጨብሳ ያሉ ምግቦችን ያቆዩበታል::

***የቁዲ ባህላዊ ፋይዳ*** በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ሴት ልጅ ስትዳር የጎጆ መውጫ ተብለው ከሚበረከቱ እቃዎች ኣንዱ ቁዲ ነው:: ከዚህ ጎን የኦሮሞ ኮረዳ በምታገባበት ጊዜ እርጎ፣ ጨጨብሳ፣ ጭኮ የመሳሰሉ ምግቦች በቁዲ ውስጥ ተደርጎላት ትሸኛለች:: በመልስ ወቅት ወደ ቤተሰቦቿ ስትመጣ ተመሳሳዮቹን ምግቦች ይዛበት ትመጣለች:: ዘመዶቿ ምግቡን ከተመገቡና እርጎውንም ከጠጡ በሁዋላ በምላሹ ፍራንክ ወይም የቡና ቅሽር ሞልተው ይመልሱላታል:: ከዚህ በተጨማሪም በሰርጉ እለት ቤተ ዘመዶች ልዩ ልዩ የምግብ ኣይነቶች «ቡራቶ»፣ ጨጨብሳ፣ እርጎ የመሳሰሉትን ይዘውበት ይመጣሉ:: እንደሀጂ ኣብዱልጀዋድ ገለጻ የሰርጉ እድምተኞች በቁዲ የቀረበውን ምግብ ከተመገቡ በሁዋላ ቤተዘመዶችና ታዋቂ የኣካባቢው ሽማግሌዎች ይቀራሉ:: እነዚህ ወደሁዋላ የቀሩ ቤተዘመዶችና ሽማግሌዎች በቁዲዎቹ ውስጥ ያለውን ምግብ እየበሉ እና እርጎውንም እየጠጡ ሙሽሮቹን ይመርቃሉ፣ ስጦታም ያበረክቱላቸዋል:: ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ስርኣታዊ ክዋኔ የቁዲ ባህላዊ ፋይዳ ይረጋገጣል:: የቁዲዎች መነሻ የኦሮሞ ቁሳዊ ባህል እንደሆነ ይገመት እንጂ በሌሎች ብሄረሰቦችም ዘንድ በተለይ ማለቢያና የወተት ማቆያ በመሆን ግልጋሎት ይሰጣሉ::

***ማህበራዊ ፋይዳ፡*** ቁዲዎች ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በተለይ በሰርግ፣ በደቦ ስራ እና በኣንዳንድ በኣላት ላይ ቤተዘመድ ምግብና እርጎ ይዞባቸው የሚመጣ በመሆኑ ያቀራርባሉ፣ ያገናኛሉ:: በዚህም መሰረት በቤተዘመዳሞች እና በኣካባቢው የብሄረሰቡ ኣባላት መካከል የሚፈጥሩት ማህበራዊ ፋይዳ የጎላ ነው::

### 4.2.4 ኦኮሌ (OKOLEE)

ከእንጨት የሚሰራውም ሆነ ከቆዳ የሚዘጋጀው የማር መያዣ እቃ «ኦኮሌ» (Okolee) በሚል ስያሜ ይታወቃል:: በዚህ ክፍል የምንመለከተው ግን ከእንጨት የሚሰራውን «ኦኮሌ» ነው::

***አሰራር:-*** የኦኮሌን አሰራር ሀጂ አብዱልጀዋድ ኣዲ ኣጠር ኣድርገው እንደሚከተለው ይገልጹታል::

> *የእንጨቱ ኦኮሌ ከኮሶ ወይም ከዝግባ እንጨት ይዘጋጃል:: ተፈላጊው እንጨት በባለሙያ ይቆረጥና ለተወሰነ ጊዜ በውስጡ ያለውን ርጥበት እንዲመጥና መሰንጠቁ እስኪወጣለት ይቀመጣል:: ቀጥሎም እንጨቱ እየተጠረበና እየተቦረቦረ ተፈላጊውን መጠን እስከሚይዝ ድረስ ስራው ይቀጥላል:: የእንጨቱ ኦኮሌ በኣካሉ ግራና ቀኝ ትናንሽ ቀዳዳ ያላቸው መያዣዎች እየተሰረሰሩ ከሌላው ኣካሉ ፈጠው ይወጣሉ:: በተበሱት ቀዳዳዎች ከጠንካራ የቀንድ ከብት ቆዳ የተዘጋጀ የጠፍር ጥብጣብ ይታበትበታል:: ይህ የታበተ ጠፍር እቃውን (ኦኮሌውን) ይዞ ለመሄድና በቤት ውስጥ ለማስቀመጥ ሲፈለግ ማንጠልጠያ ሆኖ ያገለግላል::*

የእንጨቱ ኦኮሌ ከ4 እስከ 6 ሳንቲሜትር የሚረዝም ክብ ቅርጽ እግር ይኖረዋል:: የኦኮሌው እግር ተቀጥላ ሳይሆን ከዋናው ኣካሉ ተቦርቡሮ የተሰራ ነው:: የኦኮሌ ቅርጽ ብዙውን ጊዜ ሞላላ ነው:: ኣሰራርና ቅርጹ ሞላላ ከመሆኑ በስተቀር ቁዱን ይመስላል:: ከኣፉ የመጨረሻ ጠርዝ ወደታች ሰበር ብሎ የሆዱ ዋና ክፍል የሆነው እስከሚጀመርበት ድረስ ያለው ርዝመት ከ3 እስከ 4 ሳንቲሜትር ነው:: ዋናው ኣካሉ፣ እግሩ (መቆሚያው) ኣጠፍ ተደርጎ እስከሚሰራበት ድረስ 25 ሳንቲሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን በኣንድ ኣይነት የውፍረት መጠን ነው የሚሰራው ወይም ኣንዱ ቦታ ሳሳ ሌላ ቦታ ደግሞ ወፈር ኣይልም:: የኣፉ ኣካባቢ ግን ከዋናው ኣካሉ ጋር ሲመጣጠን ስስ እና ክብ ቅርጽ ያለው ነው:: የዚህ ጥናት ኣቅራቢ ያጋጠመው ኦኮሌ ከኣፉ ጠርዝ እስከ እግሩ የመጨረሻ ጠርዝ ድረስ ያለው ርዝመት 30 ሳንቲሜትር ነው:: የዋናውና ወፍራም የሆነው ኣካሉ መጠነ ዙሪያ 34 ሳንቲሜትር ነው:: ስስ የሆነውና ክብ ቅርጽ ያለው የኣፉ ኣካባቢ መጠነ ዙሪያ 15 ሳንቲሜትር ነው:: ከዚህ ኣንጻር የዋናው ኣካሉ መጠነ ዙሪያ ከኣፉ መጠነ ዙሪያ ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ ይጨምራል ማለት ነው:: ዋናው መቆሚያው እግር ርዝመቱ 2 ሳንቲሜትር ሲሆን ይህም እንደዋናው ኣካሉ ኣይወፍርም፤ በኣፉ ኣካባቢ እንዳለው ኣካሉ ስስ ነው:: ከእግሩ መታጠፊያ እስከላይኛው የኣፉ ኣካባቢ መታጠፊያ ድረስ ሞላላ ቅርጹ እንደተጠበቀ ይሰራና የኣፉ ኣካባቢ ያለውና ክብ ቅርጽ የሆነው መክደኛውን ሊቀበል በሚችል መልኩ የሚሰራ ነው::

የእንጨቱ ኦኮሌ ከእንጨት የሚዘጋጅ መክደኛ ኣለው:: መክደኛው ቀዳዳ ያለው ወይም ከወደ ኣናቱ ደቦልቦል ያለ ወይም ሲሊንደር ቅርጽ ያለው መያዣ ኣለው:: የመክደኛው የላይኛው ኣካሉ ወፍራም ሲሆን ወደ ዋናው ኦኮሌ የሚገባው (የሚገጥመው)

የመክደኛው ኣካል ግን ሳሳ ያለ እና በቀላሉ ከዋናው ኦኮሌ ኣፍ ጋር ሊገጥም የሚችል ነው፡፡ የኦኮሌ ስራ የሚከናወነው በወንዶች ነው፡፡ የኦኮሌን ቅርጽ ለማየት ፎቶግራፍ 7ን በግራ ጠርዝ ይመልከቱ፡፡



*ፎቶግራፍ 7፡- የእንጨትና የቆዳ ኦኮሌ፡፡*

*ኣገልግሎት፡-* ብዙውን ጊዜ የእንጨቱን ኦኮሌ ማር ይይዙበታል፡፡ ያስቀምጡበታልም፡፡ በኣንዳንድ ኣካባቢ ደግሞ በደንብ እያቀራሹ ወተት ያልቡበታል፡፡ ማር መያዣ ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ኣልፎ ኣልፎ በኣንድነት በመሰብሰብ በእጃቸው ወይም በማንኪያ እያወጡ ይመገባሉ፡፡ ተመጋቢቹ በቡድን ወይም የኣንድ ቤተሰብ ኣባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ ማህበራዊ ፋይዳውን ያንጸባርቃል፡፡ ምክንያቱም የቡድን አባላትን በኣንድ ማእድ ኣቀራርቦ ያቋድሳልና በማለት ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ የሚያስታውሱትን ይናገራሉ፡፡

### 4.2.5 ኪላ (KILLA)

ኪላ ትንሽቱ ቆሪ ልትባል ትችላለች፡፡ ከትንሽነቷ፣ ለውበት ሲባል ከሚታበትባት የጠፍር ጥብጣብና ከማስጌጫዎቿ ጨሌዎችና ዛጎሎች በስተቀር ቅርጿና ጥበባዊ ኣሰራርዋ ቆሪን ትመስላለች፡፡ ፎቶግራፍ 8ን ልብ ይበሉ፡፡ ኪላዎች ከስንደዶ ይሰፋሉ፣ ወይም ከእንጨት ይሰራሉ፡፡ ከዚህ ላይ የምንመለከተው ግን የእንጨት ውጤት የሆኑትን ኪላዎች ነው፡፡

*ኣሰራር፡-* ስለ ኪላ ኣሰራር ኣቶ ኣለሙ ወርቁ እና ኣቶ ኣደም ቃሲም ቀደም ባሉት ጊዜያት ሲሰራ ያዩትን እንደሚከተለው ያስታውሳሉ፡፡

*ኪላዎች የወንዶችንና የሴቶችን የስራ ተሳትፎ የሚጠይቁ የእንጨት ስራ ውጤቶች ናቸው:: እንጨቱ ኮሶ፣ ዝግባ ወይም ዋንዛ ሊሆን ይችላል:: የኪላዎች መጠን በቁመትም በስፋትም ከቆሪዎች ጋር ሲነጻጸር ኣነስተኛ እንደመሆናቸው መጠን እንደገበታ መስሪያ ወፍራም ግንድ ኣያስፈልጋቸውም:: ቢሆንም ግንዱ በሰል ያለ እና በቀላሉ የማይሰነጣጠቅ መሆን ኣለበት:: ሰሪዎቹ ሙያተኞች ይሆናል ያሉትን ግንድ ከቆረጡ በሁዋላ ቅርፊቱን ያነሱና ለተፈለገው የኪላ መጠን ቅርጽ ማውጣት ይጀምራሉ:: መጠኑ የሚወሰነው በኣይነ ግምት ሲሆን በመጀመሪያ የምግብ ማስቀመጫውን ክፍል እየቦረቦሩ እስከሚፈልጉበት ደረጃ ድረስ ያጎረጉዱታል:: ብዙውን ጊዜ ተለቅ የምትለዋ ኪላ ከ25 እስከ 28 ሳንቲሜትር ቁመት (ርዝመት) ኣላት:: የእግሯ ርዝመትም እስከ 7 ሳንቲሜትር ይሆናል:: ግንዱ ተጠርቦና በተፈለገው መጠን ከተቦረቦረ በሁዋላ እያስተካከሉ የመጥረቡና የማለስለሱ ተግባር ይቀጥላል:: ይህ ከዚህ በላይ የገለጽኩልህ በተለይ ኪላዎቹን ለመስራት የወንዶቹን ተሳትፎ ነው:: ቀጥሎ ያለው ተግባር ደግሞ ሴቶቹን የሚመለከት ነው:: ወንዶቹ ጠርበውና ኣለስልሰው ያዘጋጁትን ኪላ ሴቶቹ ዙሪያዋን በእበት ይለቀልቁና ለ15 ቀናት ያህል ጸሀይና ንፋስ በማይበረታበት ቦታ ያስቀምጧታል:: የእበት ውስጥ የቆይታ ጊዜዋን ከጨረሰች በሁዋላ ያጻዱዱና በሞራና በቅቤ ኣተላ (እንቃሪ) በተደጋጋሚ ያሟሿታል:: በተለይ የቅቤውን እንቃሪ በውስጧ በማድረግ ወይም በርከት ባለ የቅቤ ዝቃጭ ውስጥ በመንከር ለብዙ ጊዜ ያቆዩኣታል:: ይህም በኣገልግሎት ላይ በምትውልበት ጊዜ መጠቀሚያ ተብሎ የሚቀመጥባትን ቅቤ እንዳትጠጣ ነው:: የሚቀጥለው ተግባር ኪላዋን ማስዋብ ነው:: ለማስዋብ ደግሞ የሚያስፈጉት ሰንጢ፣ ወስፌና የመሳሰሉት መሰርሰሪያዎች ናቸው:: በመሰርሰሪያዎቹ ኣማካኝነት ልዩ ልዩ ሽንትሮች (ንቅሳቶች) ይቀርጹባታል:: ቅርጾቹ ኣግድማዊ፣ ቁልቁል ወይም ክብና የዲያመንድ ሊሆኑ ይችላሉ:: ሌላው ኪላዎችን የማስዋቢያ ቁሳቁስ ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ጨሌዎችና ነጫጭ ቀለም ያላቸው ዛጎሎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ዘርፍ ዘርፍ ያላቸው «ሳምሳዎች» የጠፍር ጥብጣቦች ኣስፈላጊ ናቸው:: ጨሌዎችና ዛጎሎች ከመደረጋቸው በፊት የጠፍር ጥብጣቦቹ በኪላዋ ኣካል ላይ እየተጠላለፉ ይታበታሉ:: ኣንዳንዶቹ የጠፍር ጥብጣቦች በዋናዋ ኪላ እና በእግሯ መለያያ ወይም 8 ቁጥር ቅርጽ ከተሰራባት ይጀምርና በሁለት ወይም በሶስት ኣቅጣጫ ይመጣና በክዳኑ ቀዳዳ ለማንጠልጠያነት እስከሚተርፍ ድረስ ይታበታል:: ሌላው ኣይነት ኣጠላለፍ ደግሞ ከወገብ ጀምሮ እስከ ክዳኗ ድረስ መንታ ቅርጽ ወይም ሶስት ሆኖ ወደላይ ይወጣል:: ከወገብ የሚጀምረው ጠፍር ሁለትና ሶስት ዘርፎች እንዲኖሩት በቀጭኑ እየተተለተለ መሬት እስከሚነካ ድረስ ረዝሞ ይታያል:: የጠፍር ጥብጣቡ መሬት የሚነካው ኪላዋ መሬት ላይ በምትቀመጥበት ጊዜ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ ያለው ጌጥ በጨሌና በዛጎል የሚከናወነው ነው:: ጨሌዎቹንና ዛጎሎቹን በ«ሳምሳው» (በጠፍሩ ላይ) ለመስፋት ቺንጊያ ወይም በጣም ቀጭን የሆነ ጠፍር ያስፈልጋል:: ከዚህ በሁዋላ ጨሌዎቹና ዛጎሎቹ ሳይደባለቁ (ሳይሰባጠሩ) በየራስ በእየራሳቸው ቁልቁል መስመር ይዘው በተዘጋጀው ቺንጊያ ወይም ጠፍር ኣማካኝነት መጀመሪያ በታበቱት ጠፍሮች «ሳምሳ» ላይ ይሰፋሉ:: የጨሌና ዛጎሎቹ ድርደራ እስከ ኪላዋ ወገብ ወይም ከወገቧም ትንሽ ዝቅ እስከሚል ይሰፋሉ:: የብዙዎቹ ኪላዎች ክዳን ከእንጨት የሚሰራ ሲሆን ኣልፎ ኣልፎ ከስንደዶም ይሰፋል:: ከእንጨት የሚሰራው ክዳን እጀታው ላይ ጠፍሩን «ሳምሳውን» የሚያሾልኩ ከ2 እስከ 3 የሚሆኑ ቀዳዳዎች ይኖሩታል:: የጠፍሩ በክዳኑ እጀታ ውስጥ ማለፍ ኪላዋን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ክዳኑ እንዳይወድቅ እና እንደተገጠመ እንዲቆይ ያደርገዋል::*

ከዚህ በላይ ስለኪላዎች የኣሰራር ጥበብ ኣቶ ኣለሙ ወርቁና ኣቶ ኣደም ቃሲም የሰጡት ገለጻ ሲሆን የተሰጠውን ገለጻ ከኪላዎቹ ቅርጽ እና ከሚታየው ውበታቸው ጋር

ለማጣጣም ፎቶግራፍ 8ን ይመልከቱ::



*ፎቶግራፍ 8:- በልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ያሸበረቁና የተለያየ መጠን ያላቸው ከእንጨት የተሰሩ ኪላዎች::*

***አገልግሎት:-*** በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ ኪላ ቅቤ ማስቀመጫ ነች:: ኪላዋ በደንብ የተቀራሸች ከሆነ ደግሞ ለደራሽ እንግዳ እና ለቡና የሚሆን ወተት ያኖሩባታል:: በቤት ውስጥም በምሰሶ (ወጋግራ) እና በየግድግዳ ላይ እየሰቀሉ ማስጌጫ፣ ቤት ማድመቂያ ያደርጓታል:: ወደ መንገድ ሲሄዱም ቅቤ ይይዙባታል፣ በኣቧራ እንዳትጎሳቀልም በዳንቴል ይሸፍኗታል:: በፎቶግራፍ 9 ኪላዋ በኣገልግሎት ላይ መሆኗን ይመልከቱ::

***ባህላዊ ፋይዳ:-*** የኪላዎች ባህላዊ ፋይዳ በይበልጥ የሚንጸባረቀው ኣንዲት እናት የዳረቻትን ልጇን ለመጠየቅ ስትሄድ ወተት ወይም ቅቤ ሞልታባት ከእጇ የማትለያት ሲሆን ነው:: ከፎቶ 9 ያጤኗል:: አቶ ኣደም ቃሲም እንደሚያረጋግጡት በተለይ በሰርግ ጊዜ ኪላና ጮጮ ኣይነጣጠሉም:: ቤተዘመዳሞች በኪላ ቅቤ በጮጮ ደግሞ ወተት ይዘው ይመጣሉ:: በኦሮሞ ባህል ወተት በጮጮ ሳይያዝ ቅቤ ብቻ በኪላ መያዙ ከስድብ ይቆጠራል:: ስለዚህ ኪላና ጮጮ ወደ ሰርግ ቤት ኣብሮ ዘማች ናቸው::



ፎቶግራፍ 9፡- ቂቤ በኪሳ ዘመድ ጥየቃ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## 4.2.6 ቁሉ ሙከ ሰላታ (Quluu Muka Salaataa) ከእንጨት የተሰራ የሰላታ (የስግደት) ውሀ መያዣ

*ኣሰራር፡-* «ቁሉ ሙከ ሰላታ» የኮሶ እንጨት ተቦርቡሮ የተለያዩ የጌጥ ቅርጾች እየተበጁለት የሚሰራ ነው፡፡ ቅርጹ ሞላላ ወይም ክብ ሊሆን ይችላል፡፡ ሞላላ ቅርጽ ያለው «ቁሉ ሙከ ሰላታ» ሰፊ ቀዳዳ ያለው መያዣ ጆሮ ከዚያው ከኣካሉ ተሰርስሮ ይሰራለታል፡፡ ፈሳሽን ወደ ውስጥ ለማንቆርቆርና ከውስጡ ለመቅዳት የሚረዳ መጠነኛ ቀዳዳ ይሰራለታል፡፡ የ«ቁሉ ሙከ ሰላታ» የውስጠኛ ኣካሉ የሚቦረቦረውና ክፍት እንዲሆን የሚደረገው በመቀመጫው በኩል ባለው ሰፋ ያለ ቀዳዳ በመሰርሰሪያ መሮ ወይም በቀጭን ስለታም መጥረቢያ ነው፡፡ ውስጣዊ ኣካሉ ተቦርቡሮ ካበቃ በሁዋላ ቀዳዳው በልኩ ተቆርጦና ተከርክሞ በተዘጋጀ መሰል ግጣም ይገጠማል፡፡ ግጣሙ በደንብ እንዲገጥም ኣንዳንድ ጊዜ ሙሻዙር ይቀርጹለታል፡፡ ከመቀመጫው በኩል ክፍቱን ቀዳዳ የሚገጥመው ግጣም በልክ ከተቆረጠ በሁዋላ በሀይል እየተመታ እንዲገጥም ነው የሚደገረው፡፡ ይህም ግጥም ብሎ ይይዛል ከሚል እሳቤ ነው፡፡ የመቀመጫው ቅርጽ ሞላላ ወይም ክብ ሊሆን ይችላል፡፡ በፎቶግራፍ 10 በቀኝ በኩል ሁለቱን ይመልከቱ፡፡



*ፎቶግራፍ 10፡- የቅልና እንጨት ስሪት የሆኑ ባህላዊ የውሃ መያዣ እቃዎች፡፡*

የ«ቁሉ ሙከ ሰላታ» እግር ኣንድ ወጥ ከሆነው ከዋናው እቃ ተረፍ ብሎ መሬት እንዲይዝ ታስቦ የሚሰራ ነው፡፡ የእግሩ ቅርጽ የዋናውን እቃ ቅርጽ ነው የሚይዘው፡፡ በዚህም መሰረት «ቁሉ ሙከ ሰላታ»ው ሞላላ ከሆን ሞላላ ቅርጽ ሲኖረው ክብ ከሆነም ክብ ቅርጽ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ የ«ቁሉ ሙከ ሰላታ» የውጨኛው ኣካሉ ከላይ እስከ እግሩ መጨረሻ ድረስ እንደኣስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ቅርጽ (ኣራት፣ ሰስት ጎን ፣ ዲያመንድ፣ ባለ መስመርና ክብ ወዘተ.) የሆኑ ሽንትር-ሽንትር ቅርጾች ወይም ንቅሳት በሰንጢ፣ በወስፌና በመሮ እየታገዙ ያወጡለታል፡፡ የተሰሩለት ሽንትር ሽንትር ንቅሳቶች ለኣይን ደስ እንዲል ያደርጉታል፡፡ «ቁሉ ሙከ ሰላታ» ከኮሶ ብቻ ሳይሆን ውስጡን በመቦርቦርና ለኣያያዝ ቀላል ከሆነው የኮርች እንጨትም ይዘጋጃል፡፡ ይህ ከኮርች የሚዘጋጀው ግን ቤትን ለማስጌጥ ካልሆነ ፈሳሽ ለመያዝ ኣይገለገሉበትም፡፡ ፎቶግራፍ 10ን ይመልከቱ፡፡

በፎቶው ፤ ከሚታዩት ባለ ኣንገታሙ የኣንገቱ ርዝመት 7፣ የመቀመጫው መጠነ ዙሪያ 45፣ ከኣንገቱ መጨረሻ እስከ መቀመጫው ያለው ርዝመት 14፣ የኣንገቱ ጫፍ መጠነዙሪያ 7፣ ውሀን ለማንቆርቆር የሚረዳው የቀዳዳው መጠነ ዙሪያ 1.5 ሳንቲሜትር ነው፡፡ ባለጆሮኣሙ ደግሞ የኣፉ መጠነ ዙሪያ 2፣ የዋናው ኣካሉ መጠነ ዙሪያ 43.5፣ ቁመት 28.5፣ ፈሳሽ የሚንቆረቆርበት መጠነ ዙሪያ 1.5 የመቀመጫው ግጣም መጠነ ዙሪያ 6.5 ሳንቲሜትር ነው፡፡ ከዚህ በላይ የቀረቡት ኣሀዞች ሁሉም በሳንቲሜትር ነው

የተሰፈሩት:: መረጃዎቹም የተገኙት በምልከታ ከተገኙት ሁለቱ እቃዎች ነው:: የአሀዞቹ መረጃ የእቃዎቹ የኣሰራር መጠን በተለወጠ ቁጥር እንደሚለዋወጥ ማጤን ይገባል::

***ኣገልግሎት:-*** «ቁሉ ሙከ ሰላታ» ኣሁን-ኣሁን ከላስቲክ በተሰሩ ውሀ መያዣዎች ኣገልግሎቱን እየለቀቀ መጣ እንጂ ቀደም ባሉት ዘመናት በቆላማው የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ የውሀ ስንቅ ይዘውበት ይጓዛሉ:: ሲጠማቸው ውሀውን ይጠጡታል:: በስግደትም ወቅት ንጽህናቸውን ይጠብቁበታል ሲሉ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ተናግረዋል::

### 4.2.7. ቦቤ (BOOBEE)

«ቦቤ» የእንጨት ውጤት ከሆኑ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ እቃዎች ኣንዱ ነው:: ኣቶ በቀለ ቱፋ «ኦሮሞዎች ለእያንዳንዱ ጉዳይ እቃ ኣላቸው- ለዱቄት ቡሬ፣ ለገንፎ ቆሪ፣ ለቅቤ ጡዌ፣ ለወተት ጡንጦ፣ ለማር ደግሞ ቦቤ» ካሉኝ በሁዋላ የ«ቦቤ»ን ኣሰራር እንደሚከተለው ነግረውኛል::

***ኣሰራር:-*** የቦቤ ኣሰራር ሌሎች የእንጨት ውጤት የሆኑ እቃዎች በሚሰሩበት ቅደም ተከተል መሰረት የሚሰራ ነው:: የመስሪያው እንጨት ዝግባ፣ ዋንዛ ወይም ኮሶ ሊሆን ይችላል:: ከትልቅ ዛፍ ተፈልፍሎና ተቦርቡሮ የሚሰራ ሲሆን ከሌሎች የእንጨት ውጤት እቃዎች የሚለየው ለጥንካሬ ሲባል እንደከበሮ በውጭ በኩል ዙሪያውን በቆዳ መለበጡ ነው:: በቆዳ ከመለበጡ በስተቀር ቅርጽና ኣሰራሩ እንደ ቁዲ (Qudii) ነው::

***ኣገልግሎት:-*** ቦቤ ማር መያዣ ነው:: ሰዎች ከጫካ የሚቆርጡትን ማር ያስቀምጡበታል:: ከዚህም በላይ ሌላ የመመገቢያ እቃ ሳያስፈልጋቸው በቀንድ ወይም በዘመናዊ ማንኪያም ሊሆን ይችላል ወይም በጣታቸው ከውስጡ እየጨለፉ ይመገቡበታል:: በሌላ በኩል ጥንት ለእጅ መንሽያ እየተባለ ለባላባት ወይም ለጉልተኛ ማር ይወሰድበት እንደነበር ከኣባቴ የተነገረኝ ነው በማለት ኣቶ በቀለ ቱፋ ያስታውሳሉ::

## 4.3. ከሸክላ የሚሰሩ መመገቢያ እቃዎች

«ኦኮቴ»፣ «ጢሊቴ»፣«ጡዌ»፣«ጃዩ»፣ «ወሸ» የተባሉትን እቃዎች ኣንድ በኣንድ እና የቡና ስርኣት ማከናወኛ ቁሳቁስን ደግሞ በጥቅሉ በዚህ ክፍል የሚተኮርባቸው መመገቢያና መጠጫ ባህላዊ እቃዎች ናቸው::

### 4.3.1. ትውፊታዊ ዳራ

ሸክላ በጎባ ወረዳ ውስጥ መሰራት ከተጀመረ ብዙ ኣመታትን ኣስቆጥሯል:: በእድሜ የመሸበቱን ያህል ግን ጥበባዊ ኣሰራሩ የላቀ ደረጃ ላይ ኣልደረሰም:: ለዚህ ኣያሌ

ምክንያቶችን ማስቀመጥ ቢቻልም የዚህ ጥናታዊ ትኩረት ባለመሆኑ አልፈዋለሁ:: የሸክላ ስራ በብዛት የሚሰሩት ጥንት ከሌላ አገር የመጡ ወላይታዎች፣ እነሱንም ቱክተው ያሉት ልጆቻቸው፣ አማራዎች እና ብዙም ባይሆኑ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች አሉ:: ከጎባ ደቡባዊ አቅጣጫ የሚገኙት ፋሲል ሰራና ፋሲል ሀንገሶ የመሳሰሉት የገበሬ መንደሮች የያዙት አፈር ለስራው ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ይመስላል:: ስለሆነም ከጥንት ጀምሮ የሚታወቅ «የሸክላ ሰሪዎች ሰፈር» የሚባል አለ:: ግን እንዴት ሰፈሩ?

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆን የታሪክ ማስረጃ ላላጋጠመኝም፤ ይሁንና ስለ ሸክላ ሰሪዎች አሰፋፈር አቶ አበበ ወልደጻዲቅ ለዚህ ጥናት አቅራቢ በ1995 ኣ.ም የነገሩት ተከታዩ አፈ-ታሪክ ነው::

> *ከመቶ ኣመታት ቀደም ብሎ ባሌን በገዥነት ተሾመው ይመጡ የነበሩ ገዥዎች (አስተዳዳሪዎች) ከነተከታዮቻቸው በዚያን ጊዜ ኣጠራር «የጎባ ጋራ» በኣሁኑ «የሚካኤል ጋራ» በሚባለው ኣካባቢ ይሰፍሩ (ይቀመጡ) ነበር:: ይህ ኣካባቢ የሸክላ ሰሪዎች ኣሁን ከሚገኙበት ኩታገጠም[7] ነው:: የገዥው መደብ ኣባላት ልዩ ልዩ በኣላትን ለምሳሌ የንግስ፣ የዘመን መለወጫ፣ የስልጣን ሹመት ወዘተ. ሲከበር ለመኳንንቱና ለመሳፍንቱ በኣጠቃላይ ለተከታዮቻቸው ግብር ያበሉ ነበር:: ለግብሩውም ጠጅና ጠላ በትላልቅ ጋኖች መሸም የተለመደ ነው:: ለሚሰራውም የኣይነት ወጥ በገ-ፈጅ (ትልቅ ሰታቴ ድስት) ያስፈልግ ነበር:: ይሁንና ለየበኣሉ ወቅት እቃዎቹን በየጊዜው ከሌላ ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን የተገኙትንም ማጓጓዝ የበለጠ ኣዳጋች ሆኖ ቆይቷል:: ስለዚህ ሹማምንቱ ዘዴ መቀየስ ግድ ሆነባቸው:: በምክክሩም መሰረት፣ በየጊዜው የሸክላ እቃ እየለመኑ ከሩቅ ከማጓጓዝ ሸክላ ሰሪዎቹን ራሳቸውን ለምን ኣናመጣም? የሚለው ሀሳብ ተነስቶ በማምጣቱ ስለተስማሙ በኣገሪቱ ቅርብ እና ሩቅ ያሉ ሸክላ ሰሪዎች እየተፈለጉ በውድም በግድም እንዲመጡ ሆነ:: ከጎባ በስተደቡብ ያለው የፋሲል ሰራ የሸክላ ኣፈር እንደልብ የሚገኝበት በመሆኑ በዚያው እንዲሰፍሩ ተደረገ:: ቀደም ሲል ኣካባቢው «የሸክላ ሰሪዎች ሰፈር» የሚለውን መጠሪያ እስካገኝ ድረስ «የፋጋ ሰፈር» በመባል ነበር የሚታወቀው:: ከብዙ ኣመታት በፊት መጥተው የነበሩት በሞት እና ኣካባቢውን በመልቀቅ ቢለዩም ልጆቻቸው ሙያውን እየወረሱ ዛሬም በብዛት በማምረት በጎባ እና ሮቤ ከተሞች ምርቶቻቸውን ያቀርባሉ (ኣበበ 1995፣46-47)::*

ምንም እንኳን በወረዳው በርካታ ሸክላ ሰሪዎች ቢኖሩም በኣፈ-ታሪክ እንደተነገረው ከሌሎች የኣገሪቱ ክፍሎች የመጡ እና እዚያው እየተዋለዱ ሙያቸውን ለልጆቻቸው ያስተላለፉ ናቸው:: ሸክላን በመስራት የኦሮሞዎቹ ተሳትፎ ብዙ የሚባልለት ኣይደለም:: በስራው ላይ ያሉት ግን የኦሮምኛ ቋንቋውንም ሆነ ባህሉን ወርሰዋል:: ኦሮሞዎቹም ቢሆኑ በተለይ ሰላሌዎች በስፋት ኣይሁን እንጂ ልዩ ልዩ የሸክላ ውጤት የሆኑ ቁሳቁስ ይሰራሉ:: በዚህም መሰረት ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር የጋራ መጠቀሚያ ናቸው

---

[7] *ኩታገጠም - ድንበረተኛ ወሰነተኛ*

የተባሉትን እቃዎች ትቼ የኦሮሞዎችን ባህል ብቻ በጉልህ የሚያመለክቱትን ቁሶች እንደሚከተለው ኣቀርባቸዋለሁ። ከዚያ በፊት ግን የሸክላን ኣሰራር ኣጠቃላይ ዳራዊ እይታ እናንብ።

ከጥንቱ የተለየ የኣሰራር ጥበብ ብዙም ሳይታከልበት እስካለንበት ዘመን እያዘገመ ያለ እደ ጥበብ ነው - የሸክላ ስራ በጎባ ወረዳ። በነባሩ የኣሰራር ልማድ እየተጓዙም በመሆናቸው ስራው ኣድካሚ ብቻም ሳይሆን ኣሰልቺነትም እንዳለው የሙያው ሰዎች ይናገራሉ። ይህን እደጥበብ ሴቶችም ወንዶችም ይተግብሩት እንጂ በተጨባጭ ያለው ሁኔታ ሲታይ የሴቶቹ ስራ ያመዝናል። ኣንዳንድ ጊዜም ስራውን በጋሪዮሽ ያከናውናሉ።

የሸክላው ኣሰራር በሚፈለገው የእቃ ኣይነት መጠኑና ቅርጹ ይለያይ እንጂ የኣሰራሩ ሂደት ተመሳሳይ ነው። ተፈላጊውን ኣፈር ካለበት ቦታ ያመጡታል። የመጣውን ኣፈር እንዲደርቅ ከተደረገ በሁዋላ በዱላ በመቀጥቀጥ ያደቁታል። የደቀቀውን ኣፈር ይነፉና ኣንኳር እና የማያስፈልገውን ከውስጡ ካወጡ በሁዋላ ደቃቁን በውሀ ይለውሱና በሚገባ እያሹ ያቦኩታል። በዚህ የማብኳት ስራ ላይ የሴቶቹ ሚና የላቀ ሲሆን ኣፈሩን በማጓጓዝ ተግባር ላይ ግን ወንዶቹ ናቸው ስራውን በኣብዛኛው የሚወጡት።

ኣፈሩ በጣም ደቃቅ ከሆነ በሁዋላ በሴቶቹ እንዲቦካ ይደረጋል። ከዚህ በሁዋላ የሚፈለገውን የእቃ ኣይነት ቅርጽ (Form) እያወጡ እና እጃቸውን በውሀ ራስ እያደረጉ ስራውን ያቀላጥፋሉ። «ባህላዊ ሸክላ በእጅ ኣማካኝነት ቅርጽ እየወጣለት ከመሬት ኣፈር ይሰራል» ግላሲ (Glassie፣ 1999፣ 174)። በዚህ ሁኔታ በእጅ እየተለካ ኣስፈላጊውን ቅርጽ ከያዘ በሁዋላ በእሳት ለማቃጠል ብዙ የሸክላ እቃዎች መጠራቀም ኣለባቸው። ይህም የእንጨት፣ የጊዜ፣ የገለባ ወጪን ይቀንሳልና ነው። ወደ ገበያም በኣንድ ጊዜ ለመውሰድ ብዙ እቃዎች በተመሳሳይ ጊዜ መጠራቀም ኣለባቸው። የማቃጠሉ ተግባር የእቃው ጥንካሬ ኣይነተኛ ተጠሪ ነው። በማቃጠልም ሆነ ደርቆ ከወጣለት በሁዋላ እቃው ስንጥቅ ካለውና ለኣይን ጎላ ካላለ ቀይ ኣፈር በመጠቀም እንዲደፈን ያደርጉታል። ወይም በስንጥቁ ላይ የቁልቋል ውሀ ያፈሱና ከቀይ ኣፈር ጋር ያሹታል፣ ቢሆንም ለመሸወድ ካልሆነ በስተቀር ኣተኩሮ ላስተዋለው ስንጥቁ ይታወቃል። ስንጥቁ ከባድ ሆኖ ዋጋ የማያወጣ ከሆነ ግን ይሰባበርና ለተከታዩ የሸክላ ስራ ከተዘጋጀው ኣፈር ጋር ይደባለቃል። ይህ የኣሰራር ኡደት ነው ስሁልጊዜውም የሚከናወነው።

ሸክላው ተቃጥሎ መብሰሉ ከተረጋገጠ በሁዋላ ከእሳት ውስጥ የማውጣቱ ተግባር የወንዶችን እገዛ በጣም ይሻል (ይፈልጋል)። በዚህ ላይ ኣባወራው የእርሻ፣ የንግድ ወይም ሌላ ስራ ቢኖርበትም ሸክላዎቹ ተቃጥለው ካበቁ በሁዋላ በማውጣቱ ስራ መተባበር ግዴታው ነው። በዚህም መሰረት ቢሰበሩ ከፍተኛ ኪሳራን ያስከትላሉ ለሚባሉ እቃዎች ቅድሚያ በመስጠት የማውጣቱ ስራ ይከናወናል። በኣጋጣሚ ኣባወራው ወይም

የደረሰ ልጅ እንኳን ባይኖር ጎረቤታሞቹ ሸክላ ሰሪዎች የመረዳዳት ባህል እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ የሸክላ ስራ የአንድን ቤተሰብ ወይም ጎረቤታሞችን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንም ያቀራኛል፡፡ ከመሬት አፈሩ ከወንዝ ውሀው ይገናኛሉና፡፡ ይህም ባይሆን እሳቱ ጨርሶ እስኪከስም ይጠብቁና ያወጡታል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ዝናብ ቢጥል እንኳን በቅጠልም ሆነ በገለባ ባገኙት ነገር ይሸፍኑታል እንጂ ለኪሳራ አይተውትም፡፡ ለዚህ ደግሞ የጎባ አካባቢ የባህር ዛፍ ቅጠልና የእህል ገለባ እንደልብ ስለሚገኝበት ጥሩ አጋጣሚ ነው፡፡ ከዚህ በላይ በጥቅሉ የቀረበውን ሀሳብ በተመለከተ ሙያተኞቹን አነጋግሬ ያገኘሁትን ዝርዝር የሸክላ አሰራር ጥበብና ከዚሁ ስራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ቀጥሎ በስፋት እንመለከታለን፡፡

የሸክላ ስራ ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ አቶ በቀለ ገባቦ እና አቶ ጥላሁን ጥሩነህ «የሸክላ ስራ ከእደጥበባት ስራዎች አንዱ ሲሆን ወንዶችና ሴቶች ተባብረው የሚሰሩት፣ የሸክላ አፈርና ውሀ ተዋህደው የሚያስገኙት፣ የረጅም ጊዜ እድሜ ያለው የሰዎች የተግባር ውጤት ነው» በማለት መልሰዋል፡፡ ቀጥሎም የሸክላ ቁሳቁስ አሰራር ሂደት ምን እንደሚመስል ተከታዩን ሀሳብ ሰጥተዋል፡:

*ወንዶች ከ8 እስከ 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ወደሚገኘው «ፋሲል ሀንገሶ» ወደተባለው ቦታ በመሄድ የሸክላውን አፈር ቆፍረው፣ በአህያ ጭነው ያመጣሉ፡፡ የመጣው አፈር በጸሀይ እንዲደርቅ ከተደረገ በሁዋላ እንዲደቅ በዱላ ይወቃል፡፡ ተከታዩ ስራ የደቀቀውን አፈር በወንፊት እየነፉ አንኳሩንና አላስፈላጊ የሆኑ ሳርና ጓል የመሳሰሉትን መለየት ነው፡፡ የተነፋው ልም አፈር በውሀ ከተቦካ በሁዋላ ለአንድ ቀን በቤት ውስጥ እንዲያድር ይደረጋል፡፡ ይህም እንዲብላላ ለማድረግ ነው፡፡ በማግስቱ እንደገና በደንብ ያሹታል፡፡ ቀጥሎ ያለው ተግባር አሮጌና ሰፊ የሆነ ጨርቅ በመሬት (በሸክላ ስራ ውድማ) ላይ ይነጠፍና በደንብ የታሸውንና የተቦካውን አፈር በጨርቁ ላይ የተፈለገውን የሸክላ እቃ ቅርጽ ያወጡበታል፡፡ ቅርጹ በጨርቅ ላይ የሚሰራው የሸክላው አፈር ከሌላ ባእድ (ደባል) አፈርና ሳር ወይም ሌላ ነገር ጋር እንዳይደባለቅ ነው፡፡ ቅርጽ የማውጣቱና የማለስለሱ ተግባር በጨርቅ፣ በፌስታል ወይም በማዳበሪያ ከረጢት ቅዳጅ ይከናወናል፡፡ ከማለስለሱ ተግባር በሁዋላ ከ2 እስከ 3 ቀናት ቆይቶ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ ውሀውን ከመጠጠና ከደረቀ በሁዋላ በቦንዳ እየፋቁ የማለስለሱ ስራ ይቀጥላል፡፡ ይህም እንዳበቃ ጥላማ ቦታ እየተፈለገ በየአጥር እና በቤት ታዛ ስር እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ይህ ደግሞ በንፋስ እንዲደርቅ ለማድረግ ይረዳል፡፡ መድረቁ ከተረጋገጠ በሁዋላ በለስላሳ አሎሎ ድንጋይ ይወለወላል፡፡ አሎሎው የሚሻክረውን ከማስወገዱም በላይ እንዲያብረቀርቅም ይረዳዋል፡፡ ተከታዩ ተግባር በጨርቅ እየጠረጉ ማለስለስ ነው፡፡ ቀጥሎም ለአንድ ቀን እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው የአሰራር ሂደት እንዳለ ሆኖ ለመተኮሻ የሚሆን እንጨት ተሰነጣጥቆ ከገለባ ጋር ይዘጋጃል፡፡ ሸክላዎቹ በሚተኮሱበት መሬት (አውድማ) ላይ አመድ ይነሰነስና የተሰነጣጠቀው እንጨት ይነጠፍበታል፡፡ እንጨቱ በእሳት ቢቀጣጠልም የተዘጋጁት ሸክላዎች ሙሉ በሙሉ ከመቃጠላቸው በፊት በምድጃው ዳር በተተከሉ እንጨቶች ወይም የሸክላ ስብርባሪዎች ድጋፍ እንዲቆሙ ይደረጉና በእሳቱ ይንቃቃሉ፡፡ ይህ በእሳት የማንቃቃት ተግባር «ኡሬ» ይሉታል፡፡ «ኡሬ» የሚለው ቃል ወላይትኛ ሲሆን የሸክላውን እቃ በእሳት ማለማመድ ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከ1 እስከ 2 ቀናት ከቆዩ በሁዋላ መብሰላቸውን ለማረጋገጥ በእጅ መታ፣ መታ ማድረግ ነው፡፡ በእጅ ሲመቱ ቋ! ቋ! ቋ! የሚል ድምጽ ከሰጡ በትክክል በስለዋል ማለት ነው፡፡ ጓ! ጓ! ጓ! የሚል ድምጽ ከሰጡ ግን እንደገና*

*እንዲንቃቁ ይተዋሉ:: ከዚህ ሁሉ በሁዋላ የማጠቃለያው ስራ ተፈላጊውንና እስከ ኣሁን የተደከመባቸውን ሸክላዎች በእንስራ ወይም በድስት እና በመሳሰሉ ሰባራ እቃዎች ላይ በማድረግ ከስር እንጨት ከበላያቸው ደግሞ ገለባ እያነደዱ ማቃጠል ነው:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በማቃጠያው ውድማ ላይ ኣመድ የሚነሰነሰው ከመሬት የሚነሳው እንፋሎት ሸክላውን እንዳይጎዳውና እንዳይሰነጠቅም ለማድረግ ነው:: በማቃጠሉ ተግባር ላይ ሸክላዎቹ እየጋሙ፣ ወደቀይነት እየተለወጡ ይሄዳሉ:: እሳቱ የተፈለገውን ያህል ነዶ ሲያበቃ እቃዎቹ እዚያው ኣመዱ ውስጥ ታፍነው ይቆያሉ:: በመጨረሻም በራሱ ጊዜ ከቀዘቀዘው ኣመድ ውስጥ በጨርቅ እየያዙ በማውጣት ወደገበያ እስከሚወሰዱ ድረስ በቤት ውስጥ ማቆየት ነው:: በኣንድ ጊዜ የሚቃጠሉት በርከት ያሉ የሸክላ እቃዎች ናቸው:: ይህም ጊዜን፣ እንጨትና ገለባን ለመቆጠብና ወደገበያም ለመውሰድ ይረዳል::*

ኣቶ በቀለ ገባቦ የስራውን ክብደት ሲገልጹም

*«ከሁሉም ከሁሉም አፈሩን መቆፈር ይከብዳል:: ወደታች ሁለት ሜትር ከቆፈርን በሁዋላ ወደ ጎን እስከ 12 ሜትር ልንቆፍር እንችላለን:: በዚህ ጊዜ ታዲያ በካስማ ያልተያዘው ኣፈር እየተናደ ጉዳት ያደርሳል:: በዚህም የተነሳ የኣካል ጉዳተኛ የሆኑና ህይወታቸውንም ያጡ ሙያተኞች አሉ»*

ሲሉ ከቆየ ትዝታቸው ከጠቀሱ በሁዋላ የመፍትሄውንም ሀሳብ ሲጠቁሙ «መንግስት ከላይ ያለውን አፈር በግሬደር ቢያነሳልን እኛ ደግሞ ተፈላጊውንና ከስር ያለውን የሸክላ አፈር መቆፈር ላይከብደን ይችላል» በማለት አጠቃለዋል::

ሸክላው በእሳት በመንቃቃት ላይ እያለ ወይም ከስራው ፍጻሜ በሁዋላ ስንጥቅ ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጉታላችሁ? ለሚለውም ጥያቄ ኣቶ በቀለ ገባቦ ተከታዩን መልስ ሰጥተውናል::

*ስንጣቂው ኣነስተኛና በቀጭኑ ከሆነ ወይም ስፋት ከሌለው ለመሸወድ ያህል ቀይ ልም ኣፈር ተፈልጎ በስንጣቂው ላይ እናሸዋለን:: ይህ ካላረካን ቁልቋል እናደማና በስንጥቁ ላይ ካፈሰስን በሁዋላ ደቃቁን ቀይ ኣፈር እናደርግበትና እናሸዋለን ወይም እንደመድመዋለን:: ይሁን እንጂ እየፈገፈግን ምልክቱን ለማጥፋት የምናደርገው ጥረት ብዙውን ጊዜ ይታወቅብናል:: ኣንዳንድ ጊዜም ገዥዎቹ «እናንተው ደህናውን ምረጡልን» ስለሚሉን ደንበኛ ላለማስቀየምና ላለማጣት ስንል እውነቱን ነግረንና ከመደበኛ ዋጋው ቀንሰን እንሸጥላቸዋለን:: የሸክላው ስንጥቅ ከፍተኛ ከሆነ ግን እንሰባብረውና ለተከታይ የሸክላ ስራ ከተዘጋጀ ኣፈር ጋር ቀላቅለን እናቦካዋለን::*

እንደ ባለሙያተኞቹ ኣነጋገር በክረምት ወቅት ኣንድን የሸክላ እቃ ሰርቶ ለኣገልግሎት ለማብቃት በኣማካይ ከ10 እስከ 12 ቀናት ሲወስድ ብበጋ ጊዜ ግን ከ7 እስከ 8 ቀናት ይፈጃል:: በሸክላ እደጥበብ ተግባር ላይ ወንዶችም ሴቶችም በህብረት የሚሰሩ ቢሆንም የሴቶቹ ስራ እንደሚያመዝን ግን ወንዶቹ በማረጋገጥ መስክረውላቸዋል:: በዚህም መሰረት ኣፈሩን ማድረቅ፣ መውቃት፣ መንፋትና በውሀ እያቦኩ ማሸትና በተነጠፈ ጨርቅ ላይ ቅርጽ ማውጣት ከሴቶቹ የሚጠበቅ ስራ ነው:: በተጨማሪም በጨርቅ፣ በፌስታል ወዘተ. እና በለስላሳ የኣሎሎ ድንጋይ መወልወልና ማለስለስም የሴቶቹ ተግባር

ነው:: የቀረው ስራ - ኣፈር ማምጣቱ፣ በእሳት ማንቃቃቱና መተኮሱ የወንዶቹ ቢሆንም በኣጠቃላይ ግን መረዳዳት የሰፈነበት ተግባር ይስተዋላል::

ሸክላን በእሳት የማብሰል ክዋኔ ከቤት ይልቅ በውጭ የሚተገበር በመሆኑ ዝናብ ሲዘንብ እንዴት ታደርጋላችሁ? ለሚለው ጥያቄ ኣቶ ሹንካ ገርማሞ እና ኣቶ በቀለ ገባቦ «ዝናቡ መለስተኛ ከሆነ በገለባ እናፍነዋለን፤ ዝናቡ ሀይለኛ ከሆነ ግን በጨርቅ እየያዝን በማውጣት ወደ ቤት እናስገባዋለን» በማለት መልሰዋል::

ኢትዮጵያ ቀደምት የስልጣኔ እፍታ ከቀመሱ ኣገሮች ተርታ ተሰልፋ የነበረ ቢሆንም በተለይ የእደጥበባት ስራን በተመለከተ ጥቂት የማይባሉ የህዝብ ወገኖች ከነበራቸው ዝቅተኛ ኣመለካከት የተነሳ መናናቅ በመንገሱ የጥንታዊነቱን ያህል ኣመርቂ ውጤት ሊታይበት ኣልተቻለም:: መናናቁና ማኮሰሱ ኣንገት የሚያስደፋ ነበርና የተረገዘው የህሊና ቁስል በእደ ጥበቡ የላቀ ደረጃ ላይ ኣለመድረስን ወልዷል:: በተለይ የንቃተህሊና ማነስ የፈጠረው ኣሉታዊ ኣመለካከት የሸመና፣ የቆዳ፣ የሸክላ ሰራተኛ ወዘተ. ሙያተኞችን የተለያዩ ተቀጥላ ስሞች እየሰጡ ማጥላላትና ማግለል የተለመደ ነበርና ኣሁን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? ብዬ ላነሳሁት ጥያቄ ኣቶ በቀለ ገባቦ ተከታዩን መልሰዋል::

> *በእርግጥ እኔ ብሄረሰቤ በኣባቴ የዚሁ የወላይታ፣ በእናቴ ደግሞ የኦሮሞ ብሄረሰብ ወለጋ ነኝ:: ባለው በጊዜው ተጽእኖ ፍጹም የወላይታ ብሄረሰብ ነው እንድባል ኣልፈልግም ነበር:: ምክንያቱም ስድብ ኣለ:: እሱ የወላይታ ብሄረሰብ ሰርቶ ባቀረበው ምጣድ፣ እንስራ፣ ጋን እየተጠቀመ ኣንዳንድ ኣስተሳሰብን በደንብ ያላሟላ፣ ሁሉም ሰው ማለት ኣይደለም፣ የተወሰነ ሰው በጥላቻ ሲናገር እሰማለሁ:: ወላይታ የተባለው ብሄረሰብ ሊከበር የቻለው ደርግና ኢህኣዴግ ከመጡ ወደዚህ ነው:: ቀደም ባለው ጊዜ የሚሰጠው ስም በጣም የሚያሳዝን ነው:: ከኣዳምና ከሄዋን እንደተፈጠረ እንኳን የማይናገር ነበር:: ኣውሮፓውያን እንኳን ከእኛ የሚለዩት ደግሞ ምናልባት በቆዳ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር ከእኛ ጋር ኣንድ ናቸው:: ይህ ከግንዛቤ ሳይወሰድ የወላይታን ብሄረሰብ ቆዳን የሚፍቅ ፋቂ፣ ብረት ቀጥቅጦ ማረሻ የሚሰራውን ቀጥቃጭ፣ በተለይ ሸክላ ሰሪውን ደስ የማይል ስድብ ኣለ «ፉጎች ሰፈር» የሚል:: «ሰራተኛ ሰፈር» መባል ሲገባው «ፉጎች ሰፈር» መባሉ በጣም የሚያሳዝን ነው:: መንግስት በዚህ በኩል ትኩረት ሰጥቷል:: ዛሬ ይህን ቃላት የሚናገር ኣለ ብዬ ኣልገምትም:: ኣልፎ ኣልፎ ቢኖርም ተስተካክሏል:: ህብረተሰቡ ጠንክሮ እየሰራ ነው:: ለሰዎች ግልጽ ባይሆንም ዛሬ የእኛ ሰዎች በሬ ገዝተው እያረሱ ነው:: መኪና ባይገዙም በበሬ ራሳቸውን ያስቻላቸው ይህ ኣፈር ነው:: ለተጠቃሚውም የማይናቅ ኣስተዋጽኦ እያደረገ ነውና ዛሬ በዚህ በኩል ችግር የለብንም:: «ሸክላ ሰራተኞች» የምንባል እንጂ «ፉጎች ሰፈር» የምንባል ኣይደለንም:: ይህ መናቅ የማይገባው ስራ ነው::*

ሰዎች ለማህበራዊ ኑሮኣቸው ኣውታር የሚሆኑ ልዩ ልዩ ግንኙነቶችን ይመሰርታሉ:: ከዚህ ኣልፎም በጋብቻ ይተሳሰራሉ:: ይህ ኣይነት ትስስር ደግሞ ከተራ ግንኙነት ይወጣና የዝምድና ሀረግ ያስመዝዛል:: በሌላ በኩል በሚኖሩበት ኣካባቢ በእቁብ፣ በእድር፣ በሰንበቴ፣ በማህበርና በመሳሰሉት ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ:: ይህ ሁኔታ ደግሞ

በኢትዮጵያ የተለመደ ነው። ሓዎንታዊ ጎኑ የመጠንከሩን ያህል የተወሰኑ የህዝብ ኣባላት በተለይ የእደጥበብ ሰራተኞችን የሙያ ውጤት እየተጠቀሙ ሙያተኞቹን ግን ሲጋብቻ፣ ለኣብልጅነት ወዘተ. ያገልሉኣቸው እንደነበር ትዝታው ገና ጨርሶ ኣልመከነም። ሙያተኞቹ በእቁብ፣ በእድርና በመሳሰሉትም ቢሆን የጎላ ተሳትፎ እንዳልነበራቸው እማኝ መቁጠር ኣያሻም። ያ የነበረው ኣሉታዊ ሁኔታ በኣሁኑ ጊዜ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ለሚለው ጥያቄ

> *«ኣይ ያ ዱሮ የነበረ ነው፤ በተለይ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ጊዜ በጣም ከፍተኛ ጥላቻ ነበር። እኔ ራሴ ከራሴ ዘመዶች ርቁ ነበር ባለው ተጽእኖ ወላይታ መባልን ኣልፈልግም ነበርና። ዛሬ እኔ ከፈለግሁኝ ለልጄ የማንም ልጅ ትሁን ዳሩልኝ ብል የሚከለክለኝ የለም። እኔም ከብዙዎቹ ጋር ተጋብቻለሁ፣ የኔንም ልጅ ይጠይቃሉ፣ እኔም የፈለግሁትን ጠይቁና ኣስጠይቁ ልጄን ኣጋባለሁ። ኣሁን እንኳን የዚህ ኣይነት ተጽእኖ የለብንም» ብለዋል ኣቶ በቀለ ገባቦ።*

ቀደም ሲል ከኣፈታሪክ የተገኘው መረጃ እንደጠቆመው የመጀመሪያዎቹ ሸክላ ሰሪዎች ከሌላ ቦታ በውድም፣ በግድም መጥተው ሙያቸውን ለልጆቻቸው እያስተላለፉ ስራውን ሰንሰለታማ እያደረጉት ባልተቋረጠ ሁኔታ እስከ ዘመናችን ዘልቀዋል። ይህ ሀቅ እንዳለ በመሆኑ ለመሆኑ ከእርስዎ ልጆች ይህን የሸክላ ስራ የለመደና የሚሰራ ኣለ? በማለት ለኣቶ በቀለ ገባቦ ጥያቄ ሰነዘርኩ።

> *«ልጆቼ ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ ቢሆንም ቋንቋ ኣትችሉም (ኦሮምኛን ማለታቸው ነው) ሲባሉና ስራ ሲያጡ ግዴታ በዚህ ላይ ተሰማርተው ይሰራሉ። ትንሺን ልጅ ማስተማር ባለመቻሌ በሸክላ ስራ ላይ ተሰማርታለች። ትልቁም ትምህርቱን ከጨረሰ በሁዋላ (የ12ኛን ክፍል ማለታቸው ነው) ትዳር መስርቶ ይህንኑ ስራ ይሰራል። በዚህ ኣካባቢ ያሉ ልጆች ሌላ ስራ መንግስታዊ ስራ እንዳይሰሩ ብዙ ምክንያቶች ኣሉ። ቋንቋውን ያለመጠቀም፣ ይህን ሲያሟሉ ባለመቻላቸው ወደ ጉልበትና እርሻ ይሰማራሉ» በማለት ኣጠቃለዋል።*

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርኳቸው ሴት ሸክላ ሰሪዎች ከወንዶቹ ሀሳብ የተለየ የተናገሩት ባይኖርም ዛሬ ሙያቸው እንደተከበረላቸውና ኣንገት የሚያስደፋ ነገር እንደሌለባቸው ነገር ግን ሙያው በዘመናዊ የኣሰራር ጥበብ የታገዘ ባለመሆኑ ልፋትና ድካም እንደሚበረታባቸው በተለይ ወ/ሮ ቡዙነሽ ገነሞ የበኩላቸውን ሰንዝረዋል።

### 4.3.2. ኦኮቴ (OKKOTEE) ማሰሮ

ቀደም ሲል የእንጨት ውጤት በሆኑ መመገቢያ ቁሳቁስ ኣሰራር ላይ እንደተጠቀሰው የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ከእንጨት ለሚሰራው «ገበታ» ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጡ ሁሉ ከሸክላ ኣፈር ከሚሰሩ እቃዎች ኣንዱ ለሆነው ለ«ኦኮቴ» (ማሰሮ) ትልቅ ክበሬታ ኣላቸው። ምክንያቱም «ኦኮቴ» በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ ባህላዊ ምግባቸው የሆነውን ገንፎ ማገንፊያ ነውና። ይሁንና እንዴት ይሰራል?

ብዙነሽ ገነሞ ይባላሉ:: ነዋሪነታቸው ለጎባ ከተማ እና ለፋሲል ሱራ የገበሬዎች ክልል ኣዋሳኝ ላይ በገበሬ ክልሉ ውስጥ ነው:: የሸክላ ስራ ሙያውን የወረሱት ጥንት በዚሁ ሙያ ይተዳደሩ ከነበሩት እናታቸው መሆኑን የሚናገሩት ብዙነሽ ገነሞ በዚሁ ሙያ የ30 ኣመት ልምድ እንዳላቸው ጠቁመዋል:: የሸክላ ሙያ ይስማማል ወይ? ኣልኳቸው «እግዜር ይመስገን ጥሩ ነው» በማለት ጀመሩ::

ወይዘሮ ብዙነሽ ገነሞ በመቅረጸ ድምጽ መቀረጹንና ፎቶግራፍ መነሳቱን ባይፈልጉትም ኣንደበታቸውን ኣልነፈጉኝም ነበርና የሸክላውን ያሰራር ሂደት ኣንድ የማሰሮ ኣሰራርን እንደምሳሌ ውሰዱና ኣስረዱኝ? ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን መልስ ሰጡኝ::

*(ይህ የምታየው ኣፈር» በማለት ጀመሩ ወደ ኣፈሩ በእጃቸው እያመለከቱ ይህ የምታየው ኣፈር ፋሲል ሀንገሶ ከሚባል ቦታ ልጆቼ ቆፍረው፣ በኣህያ ጭነው ያመጡት ነው:: ኣፈሩ ከመጣ በሁዋላ እዚህ ቦታ ላይ ለጸሀይ ይሰጣል፣ ርጥበቱ ሲመጥና እየደረቀ ሲመጣ በዱላ ይወቃል፣ እንዲደቅም እናደርገዋለን:: በማድቀቁ ተግባር ልጆቼም ይረዱኛል:: ከዚህም ኣንኳር-ኣንኳሩን ለመለየት በወንፊት እነፋዋለሁ፣ ቀጥሎም በደንብ እያሸሁ ኣቦካዋለሁ:: የማሰሮን ስራ ከልጅነቴ ነው የማውቀው፣ ለምን መሰለህ እናቶቻችን ምጣድና ጋን ሲሰሩ እኛ በትንንሽ ማሰሮ እስር እስራቸው እየሄድን እንለምዳለን፣ እነሱም ያበረታቱናል (እየሳቁ) ኣሁን ለምሳሌ ኣንድ ትንሽ ማሰሮ ለመስራት የተቦካውን ጭቃ በመጀመሪያ ደቦልቦል ኣደርግና በጨርቅ ላይ ካስቀመጥኩት በሁዋላ እጄን በውሀ እያራስኩ መሀሉ ክፍት እስኪሆን ድረስ ጭቃውን ወደ ዳርና ዳር እየገፋሁ ከታች ያለውን የሆዱን ክፍል ማለት ነው ቅርጽ እንዲይዝ ኣደርገዋለሁ:: ከዚያም ወደ ላይ እየላግሁት ወደ ጉሮሮው ስደርስ ሰበር እንዲል ኣደርግና ክብ የሆነውን ቅርጹን ትንሽ ካወጣሁለት በሁዋላ የከንፈሩን ኣካባቢ ወደ ውጭ ለጠጥ እንዲል ኣደርገዋለሁ:: ኣሁን እንግዲህ የማሰሮ ቅርጽ ያዘ ማለት ነው፤ ስራው ግን ገና ኣያበቃም፣ እጄን ውሀ እያራስኩ ከውስጥ ያልተስተካከለ ነገር ካለ እየቧጠጥኩም በእጄ እየላግሁም እሰራዋለሁ:: ቀጥሎም ቁራጭ ጨርቅ፣ ወይም የማዳበሪያ ቅዳጅ ኣመጣና በእሱ እያስተካከልኩ ቅርጹን በደንብ እንዲሆን ኣደርጋለሁ:: በተለይ የከንፈሩ ኣካባቢ እንዳይወፍርም በጣምም እንዳይቀጥንም ከውጭ በኩል ጠፍጣፋ መደገፊያ (እንጨትም ሊሆን ይችላል ወይም ቅል፣ ወይም ለስላሳና ጠፍጣፋ ኣጥንት ብቻ ያመቸውንና የተገኘውን) ኣስደግፌ ደግሞ በያዝኩት ጨርቅ ቅርጹን ኣሳምራለሁ፣ እየላግሁም ኣስተካክለዋለሁ:: በዚህ ሁኔታ ከሰራሁ በሁዋላ ለ2 ወይም ለ3 ቀናት እንዲደርቅ እተወዋለሁ:: ውሀውን መምጠጡን ካረጋገጥኩ በሁዋላ በእጄ ስነካው ሻካራ በሚመስለኝ ቦታ ላይ ሁሉ በቦንዳ እየፋቅሁ ኣስተካክላለሁ:: ቀጥሎም እንዲደርቅ እተወዋለሁ:: ተከታዩ ስራ በለስላሳ ድቡልቡል ድንጋይ ኣማካኝነት ውስጡንም ላዩንም እሞርደዋለሁ፣ የዚህ ዋናው ጥቅሙ ማሰሮው እንዲለሰልስና እንዲያብረቀርቅ ነው:: ቀጥሎም በማሰሮው ላይ የቀረ ብናኝ ምናምን እንዳይኖር በንጹህ ቁራጭ ጨርቅ እጠራርጋለሁ:: በዚህ ሂደት እኔ ይህን ስሰራ ልጆቼም የመተኮሻውን እንጨትና ገለባ፣ የማቃጠያውን ምድጃ በመስራት ያግዙኛል:: መቼም ለኣንድ ማሰሮ ወይም ለኣንድ ምጣድ ተብሎ እሳት ኣይነድም፤ ብዙ የሸክላ እቃዎች በመልክ በመልካቸው ከላይ በገለጽኩልህ ሁኔታ መጠራቀም ኣለባቸው፤ ምክንያቱም እንጨቱም ገለባውም በጉልበት (እራቅ ወዳለ ቦታ በመሄድ ለማለት ነው) ወይም በግዢ ስለሚመጣ እንዳንከስር ኣንዴ ኣጠራቅመን ነው የምናቃጥለው:: በማቃጠያው ኣውድማ ላይ ኣመድ እንነሰንሳለን ፣ ከዚያም እንጨት እንረበርብበታለን:: እዚህ ላይ የምነግረህ ገለባ ኣድርገን በሰፊው ከማቃጠላችን በፊት*

*በሚነደው እሳት ዙሪያ እንጨቶች ኣቁመን ወይም ከዚህ ቀደም የተሰባበሩ ሸክላዎችን ደርድርን ኣዲሶቹን ሸክላዎች በእሳቱ ዙሪያ በማቆም በእሳቱ ወላፈን እንዲለበለቡ እናደርጋለን:: ለዚህ ስራ ግን ብዙ እንጨት ኣናነድም ይህ በእሳት የማለማመዱ ተግባር «ኡሬ» ይባላል:: «ኡሬ» ማለት በደንብ ከመቃጠላቸው በፊት ሸክላዎቹን በእሳት ማለማመድ ማለት ነው:: በዚህም እያዟዟርን እናሞቀዋለን:: መብሰሉንም ለማረጋገጥ በእጃችን መታ መታ እናደርገዋለን፤ በዚህም ጊዜ እንደ ቆርቆሮ ቋ! ቋ! ቋ! ካለ በስሏል ማለት ነው፤ ነገር ግን እንደ ድብኝት ድው! ድው! ድው! ካለ ግን ገና ነው ኣልበሰለም ማለት ነውና እንደገና እናሞቀዋለን:: ቀጥሎ ያለው የመጨረሻ ስራ የሚቃጠልበት ኣውድማ ላይ እንጨቱን ሰባብረን በሚቃጠልበት መልኩ ከደረደርን በሁዋላ ባዘጋጀናቸው ኣሮጌ ድስቶች፣ እንስራዎችና ሌሎች መያዝ በሚችሉ ሰባራ ገሎች ላይ ኣዳዲሶቹን የሸክላ ስራዎች እናስቀምጥና ከስር በእንጨት ከላይ በገለባ የማቃጠሉ ተግባር ይከናወናል:: በእሳት መቃጠሉ ለሸክላው ጥንካሬ ይሰጠዋል:: ኣንዳንድ ጊዜ እዚያው በኣመድ ውስጥ ተዳፍነው ያድራሉ፣ ኣንዳንድ ጊዜም ከ3-4 ሰኣት የማቃጠል ተግባር በሁዋላ እሳቱ ሲበርድ፣ ፍሙ ሲከስም በጨርቅ እየያዝን ወደ ቤት ማስገባት ነው::*

በማቃጠያው ኣውድማ ላይኣመድ የሚነሰነሰው ለምንድነው? ኣልኳቸው «ኣየህ በመሬቱ ላይ እሳት ሲነድበት ከመሬቱ ላይ እንደ እንፋሎት የሚነሳ ንፋስ የመሰለ ነገር ኣለ፤ ያ ንፋስ ደግሞ ገና ያልጠነከሩትን ሸክላዎች ሊሰነጣጥቃቸው ይችላል:: ስለዚህ ኣመዱ ያንን መከላከያ ነው» በማለት መለሱልኝ::

እንዲያው በኣጋጣሚ ማሰሮው ቢሰነጠቅ ምን ታደርጉታላችሁ? ላልኳቸው በሰጡኝ ምላሽ::

*መቼም ስንጥቁ ከፍተኛ ካልሆነ በላመ ቀይ ኣፈር በውሀ እያራስን በስንጥቁ ላይ በመደምደም እናክመዋለን:: ይህንን የምናደርገው በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው፤ ምክንያቱም ከተነቃብን ደንበኛ ያሳጣናል፣ በሁዋላ ዞር ብሎ የሚያየን የለም:: ስንጥቁ ከፍተኛ ከሆነ ግን ሰባብረን እንደገና ከሚሰራው ኣፈር ጋር ኣደባልቀን ለሌላ ስራ እናዘጋጀዋለን:: ወይም እዚህ እንደነገርኩህ በእሳት ስናቃጥል ለሚቃጠለው ሸክላ ማስቀመጫ ይሆነናል፣ ሌላም ስራ ኣያጣም:: ኣንዳንድ ጊዜ ደግሞ ስንጥቁ ትንሽ ከሆነ የቁልቋል ውሀ እናፈስበትና ልሙን ኣፈር በዚያ ላይ እንደመድማለን ወይም በቁልቋል ውሀ ኣፈሩን ኣቡክተን በስንጥቁ ላይ እናሽበታለን:: ስንሸጥ ከተነቃብን በቅናሽ ዋጋ እናስረክባለን:: ይህ ሁሉ ካልተሳካም መቼስ ምን ይደረጋል ወደ ቤት መመለስ ነው::*

ዋናውን የማቃጠሉን ስራ ከመስራታችሁ በፊት «ኡሬ» ያሉትን፣ ማለማመዱን ለምን ኣስፈለገ? ከመጀመሪያው ለምን በእሳት ውስጥ ኣላቃጠላችሁም? ላልኳቸው ሲመልሱ

*«እሱማ ኣይሆንም፣ ኣንዴ እሳት ከገባ በእጃችን መታ መታ ኣድርገን መብሰሉን እንዴት እናረጋግጣለን? መጀመሪያኮ ለእሳት መዘጋጀትና መብሰሉን ማረጋገጥ ይገባል፤ ደግሞም እኮ ቅዝቃዜ ላይ የቆየ ሸክላ በሀይለኛ ሙቀት ውስጥ ድንገት ብንከተው የእሳቱን ቃጠሎ ስለማይቋቋም ሊሰባበር ይችላል»::*

ወይዘሮ ብዙነሽ ገነሞ ቀደም ሲል ከስራቸው ማሰሮዎች ኣንዱን ኣሳይተውኛል:: ማሰሮው የኣፉ መጠን ዙሪያ 13፣ ቁመቱ 25፣ የሆዱ መጠነ ዙሪያም 51፣ የከንፈሩ

ውፍረትም 0.5፣ የጉሮሮው መጠነ ዙሪያ 20 ሳንቲሜትር ነበር:: (የኣሀዞቹ መስፈሪያ ሳንቲሜትር ነው)::

የ«ኦኮቴ» (ማሰሮ) ቅርጽ ከታች ድቡልቡል (ክብ) እና ሆደ ሰፊ ሲሆን ከወደ ኣንገቱ ብርሌ ቅርጽ ይኖረዋል:: ከብርሌ ቅርጽ የሚለየው ጉሮሮው ሰፊ በመሆኑ ነው:: የኣፉ ከንፈርም እንደ ብርሌ ከንፈር በሰፊው ባይረዝምም ለጠጥ ያለ ነው:: ይህ ለጠጥ ያለ የኣፉ ከንፈር በእሳት ላይ ሲጣድና ሲወርድ በቀላሉ ለመያዝ ከመርዳቱም በላይ ገንፎው ሲገነፋም ማሰሮው እንዳይወድቅ በእጅ ደገፍ ለማድረግ ይረዳል:: በፎቶግራፍ 11 ላይ ሁለቱም ማሰሮዎች (በኣፉ የተደፋውና በጊርጊራ ላይ የቆመው) ለኣንድ ኣላማ የተዘጋጁ በመሆናቸው ቅርጻቸው ኣንድ ኣይነት ነው::



*ፎቶግራፍ 11:- የገንፎ ማገንፊያ ማሰሮዎች፣ ማቅረቢያው ቆሪ እና መመገቢያ የቀንድ ማንኪያዎች::*

በጊርጊራው ላይ ያለው ማሰሮ በውስጡ ጠፍጣፋ እንጨት ይዟል:: ይህ ጠፍጣፋ እንጨት «ሀጡማ» «Haaxumaa» (ማማሰያ) የሚባለው ነው:: ይህ ማማሰያ ሌሎች ብሄረሰቦች (ለምሳሌ የኣማራው) እንደሚጠቀሙበት ድቡልቡል ኣይደለም ቅርጹ:: ጠፍጣፋ የሆነበትን ምክንያት የባህሉ ባለቤቶች ሲናገሩ ገንፎውን እስኪበስል ድረስ በደንብ እያገላበጡ ለመላግ እና ለማዋሀድ ስለሚያገለግል ነው ይላሉ::

***ኣገልግሎት:-*** «ኦኮቴ» (Okkotee) ማሰሮ ልዩ ልዩ ምግቦችን ለማብሰል የሚረዳ ቢሆንም በኦሮሞዎች ባህል ግን ዋና ጠቀሜታው ገንፎን ለማገንፋት ነው:: ይሁንና ገንፎውን ለማገንፋትም ሆነ ሌሎች ምግቦች (ንፍሮ፣ ኣሹቅ፣ ኣጥሚት ወዘተ.) ከማብሰል በፊት ገገርዎቹ ያሚሹታል:: ሙሽቱ በሞራ፣ በጉሎ ሊሆን ይችላል:: ገንፎ ከማገንፋትና ሌሎች ምግቦችን ከማብሰል በፊትም ንፍሮ እና ኣሹቅ ወዘተ. ለማደርጀት እየተባለ ይቀቀልበታል:: የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች «ኦኮቴ»ን የባህላዊ ምግባቸው መሰረት ጣይ እንደሆነ ይቆጥሩታል:: ምክንያቱም ባህላዊ ምግባቸው የሆነውን ገንፎ ማገንፊያ ነውና:: የገንፎ ማገንፊያው «ኦኮቴ» ሲጠራ ከእርሱ ጋር ኣብረው የሚያገለግሉ እቃዎችም ብቅ ይላሉ::



*ፎቶግራፍ 12:- የገንፎ ማብሰያና መመገቢያ እቃዎችን በማስተዋወቅ ላይ::*

ከዚህ በላይ እንደሚታየው በፎቶግራፍ 12 ገንፎን ኣብስሎ እስከ መመገብ ድረስ የማይነጣጠሉ ተፈላጊ እቃዎችን ነው ልጅቱ በማስተዋወቅ ላይ ያለችው:: በዚህም መሰረት ተፈላጊው የበሶ ዱቄት በወንፊት ከተነፋ በሁዋላ በክንዷ ስር በሚታየው ማሰሮ ይበስላል:: የበሰለው ገንፎ ክዳን ባለው ቆሪ ይገለበጣል:: በፎቶግራፉ ላይ እንደምትመለከቱት ቆሪውም «Qorii»ም በግራ እጇ የያዘችው ነው:: ክዳን ያለው

በመሆኑ ገንፎው እንዳይቀዘቅዝ ይረዳል:: በቅሪው አጠገብ የተነጠረ ቅቤ የሚያዝባት እቃ ትታያለች:: ይህች እቃ ጡዌ «Xuwwee» ትባላለች:: በገንፎው ውስጥ መሀል ለመሀል የሚፈሰው ቅቤ የሚቀዳው ከዚች ጡዌ ነው:: በተያያዘ ሁኔታ የምናየው ገንፎውን ያለ እጅ ንክኪ ለመብላት ሲፈለግ የሚያገለግለውን ፋል-ኣና «Fal'aana» እናገኛለን:: ይህንንም የቀንድ ማንኪያ ፋል-ኣና«Fal'aana» በቀኝ እጇ ይዛ የኦሮሞ ባህላዊ የገንፎ ኣበላል እንዲህ ነው እያለች ስታስተዋውቅ ያሳያል ፎቶው:: ሀጂ ኣብዱልጀዋድ እንዳረጋገጡት የኦሮሞዎች ባህላዊ ምግብ የሆነው ገንፎ በኦኮቴው ተሰርቶ ሲቀርብ የማገንፊያው እቃ እና ምግቡ የኦሮሞን ባህል በጋራ ያመለክታሉ:: የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች «ኦኮቴ»ን የባህላዊ ምግባቸው መሰረት ጣይ እንደሆነ ይቆጥሩታል::

***ባህላዊ ፋይዳ:-*** «ኦኮቴ» (Okkotee) ማሰሮ ከጥንት ጀምሮ ባህላዊ የሆነውን የገንፎ ምግብ ማገንፊያ በመሆኑ የወረዳውን ኦሮሞዎች ባህል ያንጸባርቃል:: ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ እንደሚያረጋግጡት ባህላዊ የሆነው የገንፎ ምግብ በኦኮቴው ሲገነፋና ገንፎው የሚቀርብባቸው እቃዎች ሁሉ በጋራ የኦሮሞን ገንፎ የማገንፋትና የኣቀራረብ ባህል ስለሚያመለክቱ የ«ኦኮቴ»ው ባህላዊ ፋይዳ ነጥሮ ይወጣል::

በሌላ በኩል ኦሮሞዎች በኣንድ ነገር ላይ ቅር ሲላቸው በንግግራቸው ጣልቃ «ኦኮቴ!»-«ኦኮቴ!» .... የሚሉት የኣነጋገር ዘዬ (ፈሊጥ፣ የኣነጋገር ልማድ) ኣላቸው:: ይህ ኣባባል ከምን የመጣ ነው? የሚል ጥያቄ ያቀርብኩላቸው ኣቶ በቀለ ቱፋ ባህላዊ ኣነጋገሩን በተከታዩ ሀሳብ ያብራሩታል::

> *ኦኮ ማለት ውስጡ ባዶ የሆነ፣ እንደ ዋሻ የሆነ ነገር፣ይህ ደግሞ ከኣቅም ጋር የተያያዘ ነው:: ከረከሰ ነገር ጋር የተቆራኘ ማለት ነው:: ቀትረ ቢስ እንደማለት ነው:: ብዙውን ጊዜ ከሸክላ የሚሰሩ እቃዎች ኦኮ የሚለውንና ቀትረ ቀላል የሚለውን ያሟላሉ:: እንደ ኦኮቴ ለመሳሰሉ ቀላል እቃዎች ይህን ያህል ከፍተኛ ግምት ስለማይሰጥም እናቶች ዋና ዋና የሆኑትን እንደእንስራ፣ ጋን ፣ ምጣድ ሲሰሩ ህጻናት ግን እንደ «ኦኮቴ» በመሳሰሉት ላይ ይለማመዳሉ:: ስለዚህ ኣንድ ኦሮሞ «ኦኮቴ ነጃላ ታቴ» (Okkotee najala Taatee) ካለ ነገሩ ኣልጣመኝም፣ እንደምጠብቀው ኣልሆነልኝም ለማለት ነው ፍቺው እና ከባዶነት፣ ተስፋ ከማጣት ጋር በማያያዝ ነው «ኦኮቴ!» የሚሉት በኣነጋገራቸው መካከል::*

### 4.3.3. ጢሊቴ (XILIITEE)

በጎባ ወረዳ ከሚታወቁት የሸክላ ስራት ከሆኑ ባህላዊ እቃዎች ውስጥ ኣንዱ ጢሊቴ «Xiliitee» ነው:: የጢሊቴ ኣሰራር ቅርጽ የተለያየ ቢሆንም ሂደተ-ኣሰራሩ ግን ሌሎች የሸክላ እቃዎች የሚሰሩበት የኣሰራር ኣይነት በመሆኑ በዚህ ጽሁፍ የምናተኩረው በቅርጹ ላይ ይሆናል:: የጢሊቴን የተለያዩ ቅርጾች ለማየት ፎቶግራፍ 13ን ልብ ይሏል::

*ኣሰራር፡-* «ጢሊቴ» በተለያዩ መጠኖች ይሰራል፡፡ ቅርጹ ክብ፣ ሞላላ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡ የጥራት ደረጃውን የጨረሰ የሸክላ ኣፈር ተቦክቶ ተፈላጊው ደረጃ ላይ ከደረሰ በሁዋላ የተፈለገውን የጢሊቴ ቅርጽ ለማስያዝ በቁራጭ ጨርቅ (ብዙውን ጊዜ የጅንስ ቅዳጅ ነው) እና ለስላሳ በሆነ የቆዳ ቅዳጅ እና በእጅ እያስተካከሉ የቅርጽ ማውጣቱ ስራ ይከናወናል፡፡

ወይዘሮ ብዙነሽ ገነሞ «ጢሊቴ ኣሁን ኣሁን በሌሎች ዘመናዊ እቃዎች እየተተካ በእኛ ኣካባቢ በብዛት ባይሰራም ቀድሞ እንዴት ይሰራ እንደነበር ልንገርህ» ካሉኝ በሁዋላ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> *የሸክላ ኣፈሩን ካቦካን በሁዋላ መሬት እንዳይነካውና ከበኣድ ኣፈርና ሌሎች ነገሮች ጋር እንዳይቀላቀል በተነጠፈ ጨርቅ ላይ እናደርገዋለን፡፡ ኣሁን እንግዲህ ጢሊቴን ለመስራት ይበቃል የሚባለውን ጭቃ ደቦልቦል ኣድርገን ካዘጋጀን በሁዋላ እጃችንን ውሀ እያስነካን መጀመሪያ ዝርጉን የታችኛውን ክፍል እንዲሰፋ በምንፈልገው መጠን እጃችንን ጨበጥ ካደረግን በሁዋላ በእጃችን ጀርባ (በኣይበሉባ ማለታቸው ነው) በግራና በቀኝ የሚገኘውን ጭቃ ገፋ-ገፋ እያደረግን ዝርጉን ክፍል (ንጣፋዊ ክፍሉን) (Surface areaውን ማለታቸው ነው) እንሰራዋለን፡፡ ንጣፋዊ ክፍሉን ከሰራንና በክብ ወይም በሞላላ ቅርጽ ኣይነት ወደ ላይ ሆዱን እያሰፋንና እየለጠጥን ካስተካከልነው በሁዋላ ለሁለትና ሶስት ቀናት እንዲያድር ይደረጋል፡፡ ይህንን የምናደርገው ውሀውን እንዲመጥና እንዲደርቅ ነው፡፡ ቀጥሎም ቀደም ሲል የሰራነውን ጆሮ እንደሚፈለገው ብዛት እንቀጥልበታለን፡፡ በምንቀጥልበት ጊዜ ዋናውንና ቀደም ሲል የሰራነውን ጢሊቴ ትንሽ ቦርቦር-ቦርቦር ኣድርገን ጆሮውን እንደመሰካት እናደርግና ዙሪያውን በሸክላው ጭቃ እናጠናክረዋለን፡፡ ከዚያም በሁዋላ ቢሆን የሰካናቸው ጆሮዎች እንዲጠነክሩና ጆሮዎቹን ለማጠናከር ብለን ያሸንበት ጭቃ እስኪደርቅ ቀደም ሲል እንዳደረግነው ለ2 እና 3 ቀናት እናቆየዋልን፡፡ ቆይታውን እንደጨረሰ «ኡሬ» እናደርጋለን (ኡሬ ማለት በእሳት ማለማመድ ማሟሟቅ ነው) መብሰሉንም ለማወቅ በእጃችን መታ-መታ እናደርገዋለን፡፡ ስንመታው ቀጠን ያለ ድምጽ የሚሰጠን ከሆነ በስሏል ማለት ነው፣ ወፍራም ድምጽ ከሆነ ደግሞ ገና ስለሚቀረው በኩበት ወይም በእንጨት ፍም እንዲበስል እናደርጋለን፡፡ ተከታዩ ስራ በእንጨትና በገለባ ማቃጠል ነው፡፡ እንግዲህ ይህን ሁሉ ከጨረሰ በሁዋላ ነው ተሟሽቶ ለኣገልግሎት የሚዘጋጀው፡፡*

የጢሊቴዎች ክዳን የሚሰራው ከዚያው ከሸክላ ኣፈር ሆኖ በትክክል እንዲገጥም የዋናውን የጢሊቴ ኣፍ ስፋትና ቅርጽ ይይዛል፡፡ በዚህም መሰረት ለሞላላውም፣ ሞላላ ክዳን፣ ለክቡም፣ ክብ የሆነ ቅርጽ ያለው ክዳን ይዘጋጃል ማለት ነው፡፡

የጢሊቴ ጆሮ ብዛት ከ2 እስከ 4 ይደርሳል፡፡ በጆሮዎቻቸው ላይ ቀጫጭን ሲባጎ ወይም ቺንጊያ የሚያስገቡ ቀዳዳዎች ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ቀዳዳዎቹ ኣስፈላጊዎች ከሆኑ ጭቃው እርጥብ እንደሆነ ነው የሚሰራላቸው፡፡ የቀዳዳዎቹም ብዛት በእያንዳንዱ ጆሮ ላይ 2 ወይም 3 ኣንዳንዴም 4 ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቀዳዳዎቹ ዋና ኣገልግሎት ጢሊቴዎቹን በግድግዳ ላይ ለማንጠልጠል ነው፡፡ ሙያተኞቹ እንደሚሉት

ደግሞ ለውበትም ይፈለጋል፡፡ ጢሊቴዎች የመቆሚያ እግር ያላቸው ወይም የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እግር (መቆሚያ) ያላቸው ጢሊቴዎች መቆሚያዎቻቸው እንደ ጡት ወጣ ወጣ ያሉ እንጂ ረዥም የሚባሉ አይደሉም፡፡ እግር የሌላቸው ግን ልሙጥ እንደሆኑ ስለሚተዉ በመሬት ላይ እንዲሆኑ በተፈለገበት ጊዜ በዚያው በልሙጡ አካላቸው ይቀመጣሉ፡፡ በአጠቃላይ ጢሊቴዎች እንደሚፈለጉበት አላማ ጠበብ ወይም ሰፋ ተደርገው ይሰራሉ፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ካጋጠሙት ጢሊቴዎች ውስጥ ባለሁለት ጆሮ መያዣ ያለውና እግር የሌለው የሆዱ መጠነ ዙሪያ 52፣ ከአፉ አንደኛው ጫፍ እስከ ሌላው ጫፍ ያለው ዲያሜትር 20.5፣ ጥልቀቱ 8 ሳንቲሜትር ሲሆን እግር ያለው ደግሞ 4 ጆሮዎች የተገጠሙለት ሆኖ መጠነ ዙሪያው 57፣ ከአንዱ ጠርዝ ወደ ሌላው የአፉ ጠርዝ ያለው ርዝመት 22፣ ጥልቀት 9፣ የእግሩ ርዝመት 2፣ የእግሩ መጠነ ዙሪያ 7.5 ሳንቲሜትር መሆኑን በምልከታ ከተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የአንዳንድ ጢሊቴዎች አሰራር (አቀራረጽ) ከታች ዝርጉ ክፍላቸው (Surface area) ጠበብ ብሎ ወደ አፋቸው አቅጣጫ ወደ ዳርና ዳር እየተለጠጡና እየሰፉ ይሄዳሉ፡፡ የአንዳንዶቹ ደግሞ የታችኛው ክፍላቸው (Surface area) ሰፋ ብሎ ይሰራል፡፡ የባህሉ ባለቤት የሆኑት አቶ አለሙ ወርቁ እንደነዚህ አይነት ጢሊቴዎች «ቡናቀላ»ውን ለማብሰል ምቹ ናቸው ይላሉ፤ ምክንያቱም እንደ ምጣድ ዝርግ ናቸውና፡፡ የጢሊቴዎች ክዳን ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዋናውን ጢሊቴ አፍ ቅርጽ ቢይዝም በአብዛኛው የድስት እፊያ (መክደኛ) የመሰለ ለእጅ መያዣነትም ድቡልቡል ወይም ሲሊንደር ቅርጽ የሚመስል የሚገጠምለት ነው፡፡

*አገልግሎት፡-* ጢሊቴዎች አልፎ አልፎ ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዎች የሚሆን በቅቤ የተበሰበሰ በሶ እየቀረበባቸው መመገቢያ ከመሆን ባሻገር የቤት ውስጥም ጌጥ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ ታዋቂ የሆኑባቸው ባህላዊ ፋይዳ አላቸው፡፡

*ባህላዊ ፋይዳ፡-* የጢሊቴ «Xiliitee» አገልግሎት ከ«ቡና ቀላ» (አንዳንዶቹም «ቡና ቁሉ» ይሉታል) ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው፡፡ ለመሆኑ «ቡና ቀላ» (ቡና ቁሉ) ምንድነው?

«ቡና ቀላ» የኦሮሞዎች የእምነት እና የባህል መግለጫ ነው፡፡ ስለ «ቡና ቀላ» አቶ አለሙ ወርቁ እና ኣልፊያ ሀጂ እንደሚናገሩት የቡናው መጠን ከ12 እስከ 40 ድፍን (አንዳንዶች የተቀሸረ ቡናም ይሆናል ይላሉ) ይደርሳል፡፡ ይህ ቁጥር ግን ውስን አይደለም፤ እንደ ቤተሰቡ የቁጥር መጠን ሊጨምርም ሊያንስም ይችላል፡፡ የተዘጋጀው ድፍን ቡና (አንዳንድ ጊዜም የተቀሸረ ይሆናል) ይታጠብና በብረት ምጣድ እንዲበስል ከተደረገ በሁዋላ የበሰለውን ቡና በጢሊቴዋ ውስጥ በማድረግ በደንብ እስከሚርስ ድረስ የተነጠረ ቅቤ ያፈስሱበታል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በሌላው ጎን ደግሞ ጢቢኛ (ትናንሽ ሙልሙል ዳቦዎች) ይዘጋጃሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚከናወነው ወደ ማታ ሲሆን ጠዋት በከብቶች በረት

ውስጥ ቡና ከተፈላ በሁዋላ ከጢቢኛውም፣ ከቡና ቀላውም ትንሽ ትንሽ ተወስዶ በበረቱ ውስጥ በኣንድ በተወሰነ ቦታ ያስቀምጡታል:: ይህን የሚያደርጉት ከዋቅ (ኣምላክ) ጋር የሚያገናኘን ኣንድ መንፈሳዊ ሀይል ይወስደዋል ብለው ስለሚያምኑ ነው:: ይህ ደግሞ ለእኛም ሆነ ለከብቶቻችን ጤንነት ይሰጠናል የሚል እምነት ኣላቸው:: ይህ ባህላዊ እምነት «ዋቂፈና» (ኣምላክን መለመን) የሚሉት ነው::

በትንሽ በትንሹ የተቆነጠረውን «ቡና ቀላ» እና ጢቢኛውን የማስቀመጡ ተግባር ከተከናወነ በሁዋላ እዚያው በረቱ ውስጥ ከሽማግሌ እስከ ልጅ በደረጃ ይቀመጡና የ«ቡና ቀላ» እደላ ይጀመራል:: እደላውን የሚያከናውነው ኣባወራው እሱም ከሌለ ከእሱ ቀጥሎ ያለው በእድሜው ኣንጋፋ የሆነ ቤተዘመድ ይሆናል:: እሱም (ኣዳዩ) ከራሱ ይጀምርና እዚያ ለተሰበሰቡት ሁሉ እንዲቀምሱ ያደርጋል:: ይህ ኣይቱ ስርኣት ኣምላክን ከመለመን ጋር የተያያዘ ስርኣታዊ ክዋኔ ሲሆን «ኣቴቴ ጉዲፍና ነጌኛ በርባና» «Atetee Guddifanaa Nageenya Barbbanna» (ኣቴቴያችንን ከፍ ከፍ እናደርጋለን ሰላም እንፈልጋለን) በማለት ለዋቅ (ለኣምላክ) ምህላ ያቀርባሉ::

ሀጂ ኣብዱል ጀዋድ ኣዲ በበኩላቸው ጢሲቱዎች ከሸክላ ኣፈር መሰራታቸውን ያስታውሱና ስለሚሰጡት ኣገልግሎት ደግሞ ሲናገሩ «ትልቅ ኣገልግሎት ኣላቸው» ብለው ይጀምራሉ:: ሲቀጥሉም፣

> *ጢሲቱውን እሳት ላይ ከጣዱ በሁዋላ ድፍን ወይም የተቀሸረ ቡና ያበስሉበታል:: በበሰለው ቡና ላይ በቂ የሆነ የተነጠረ ቅቤ ያፈስሱበትና ያማስሉታል:: ቡናው በቅቤው በጣም እንዲርስ ይደረጋል:: ይህ ኣይነቱ ስርኣት እምነትን ማራመጃና መለማመኛ ነው:: እንደውቃቢም ይቆጠራል:: የታመመ ሰው ቢኖር ያቀምሱትና እንዲምረው ይለማመኑበታል:: ለሽማግሌዎችም ሰጥተው በኣፋቸው እንዲይዙ ካደረጉ በሁዋላ በበሽተኛው ሰውም ሆነ ከብቶች ላይ እንትፍትፍ እያሉ ይለማመናሉ:: ኣንድ ሰው ወደ ኣደንም ሲሄድ የሚመርቁት ቡና ቀላውን በማቅመስ ነው:: ከብቱንም ሆነ የታመመውን ሰው ማርልን ወደ ኣደን የሚሄደውም በደህና ይመለስ ይቅናው፣ በቀኝ ያውለው በማለት ይመርቁበታል::*



ፎቶ ግራፍ 13:- በተለያየ መጠንና ቅርጽ የተሰሩ ጢሊቴዎችና መክደኛዎቻቸው::

«ጢሊቴ» የ«ቡና ቀላ» ተግባር የሚከናወንበት እና ለምግብነት የሚቀርብበት ስለሆነ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ዘንድ በጣም የተከበረ እቃ ነው:: ክዋኔው በጥቅሉ «ቡና-ቀላ» (ቡና ቀሉ) ወይም «ጢሊቴ» ከተባለው እቃ ጋርና የቡና ስነስርኣታዊ ዝግጅት ጋር ይቆራኛል:: በፎቶግራፍ 13 ላይ የሚታየው ለ«ቡና ቀላ»ው የሚያስፈልገው ቁሳቁስ ነው:: በዚህም ከጢሊቴዎች ፊት ለፊት ድፍኑ ቡና ተቀምጧል፣ ማንኪያው ላይ ቅቤ ይታያል:: (ፎቶግራፉ በሚነሳበት ወቅት የተነጠረ ቅቤ ስላልነበረ በኣጋጣሚ የተገኘ ያልተነጠረ ቅቤ ነው በማንኪያው ላይ የሚታየው) የቀንድ ማንኪያውም «ቡና ቀላ»ው እየተመጠነ የሚታደልበት ባህላዊ እቃ ነው:: በዚህ ሁኔታ ጢሊቴና ቡና ቀላ፣ ቡና ቀላና ኦሮሞዎች፣ ኦሮሞዎችና ኣምላካቸው ይገናኛሉ:: ይህ ሂደት በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ዘንድ የጢሊቴ እቃዎችን ያሰለፈ ባህላዊ ፋይዳ ጎልቶ የሚታይበት ስርኣታዊ ክዋኔ ነው::

### 4.3.4. ጡዌ (XUWWEE)

የሸክላ ስሪት ከሆኑት የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ባህላዊ እቃዎች ውስጥ በጣም ትንሽ በሆነው ማሰሮ የምትመስለው «ጡዌ» (Xuwwee) የተባለችው እቃ ነች:: ጡዌዎች መልከኛ ናቸው:: መልከኛ ተብለው ለመጠራታቸው ዋነኛው ምክንያት የነጠረ ቅቤ ማስቀመጫ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ወዝ ያላቸው ስለሆኑ ሊሆን ይችላል:: ወይም ኣነስ ኣነስ ተደርገው በመስራታቸውም ሊሆን ይችላል:: በፎቶግራፍ 14 ላይ የሚታዩት ጡዌዎች ለኣንድ ኣላማ ወይም ተመሳሳይ ኣገልግሎት እንዲሰጡ የተዘጋጁ ናቸው::

*ኣሰራር*፦ በጎባ ወረዳ የሸክላ እቃ መሰረታዊ የኣሰራር ሂደት ኣንድ ነው። ለሁሉም የሸክላ ስራት እቃዎች ኣፈሩን በማድረቅ፣ በመውቃት፣ በመንፋትና በማቡኳት ይጀመራል። ጡዌዎች ከማነሳቸው በስተቀር የማሰሮ ቅርጽ ያላቸውና ማሰሮም ስለሚመስሉ ኣሰራራቸውን በተመለከተ በማሰሮ ኣሰራር ላይ የተገለጸውን ማጤን ይቻላል። በዚህም መሰረት በዚህ ክፍል ከሌሎች የሸክላ ስራት ከሆኑ እቃዎች ለየት የሚሉበትንና በተለይም ጆሮኣቸውን እንዴት መግጠም እንደሚቻል ብቻ እናያለን።

ጡዌዎች በኣነስተኛና በመካከለኛ መጠን ይሰራሉ። መካከለኛዋ ጡዌ ከኣፏ ጀምሮ መሬት እስከሚይዘው ኣካሏ የመጨረሻ ጠርዝ ድረስ ያላት ርዝመት 15፣ የሆዷ መጠነ ዙሪያ 29፣ የኣንገቷ መጠነ ዙሪያ 13 ሳንቲሜትር ነው። የትንሿ ጡዌ ደግሞ፣ ርዝመት ከ12-14፣ የሆዷ መጠነ ዙሪያ 20፣ የኣንገቷ መጠነ ዙሪያ 10 ሳንቲሜትር ነው (ለተጠቀሱት ቁጥሮች ሁሉ መለኪያቸው ሳንቲሜትር ነው)። እዚህ ላይ የተጠቀሰው በእይታ ወቅት ተለክቶ የተገኘው እንጂ መጠናቸው እንደሚለዋወጥ ይታወቃል። ጡዌዎች እንደሌሎቹ እቃዎች ሁሉ በሙያተኛ የሚሰሩ ናቸው። ጡዌዎች ጆሮ ያላቸውና የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ጆሮ ያላቸው ጡዌዎች ጆሮኣቸው መያዣ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ጆሮ የሌላቸውን ግን ኣንገታቸውን እንደመያዣ መገልገል ይቻላል። ጡዌዎች ኣነስተኛ ከመሆናቸው የተነሳ ዋናው ኣካላቸው የሚሰራው በኣንድ ወጥ በሆነ ሁኔታ ሲሆን እንደ ጡዌው መጠን ጭቃው ተለክቶ፣ በዚያው በተለካው ጭቃ ብቻ ተሰርተው እንዲያበቁ ይደረጋል። ዋናው ኣካላቸው ከተሰራ በሁዋላ እንዲደርቅ ይደረጋል። በዚህ ሁሉ ሂደትም ጆሮኣቸው ለብቻ በቅርጽ ይሰራና በደረቀችው ጡዌ ላይ ተገጥሞ የተገጠመበት ዙሪያ በጭቃው ይታሻል። ጡዌዎች ባለ ኣንድ ጆሮ ናቸው። ከዚህ በላይ በተገለጸው የጡዌዎች ስራ በሁዋላ በሌሎች የሸክላ እቃዎች ኣሰራር ላይ እንደተገለጸው «ኡሬ» የማድረጉ (በእሳት የማለማመዱ)፣ የማቃጠሉና የመሳሰሉት ተግባራት ይቀጥላሉ። ጆሮ ያላቸው ጡዌዎች ከውስጣቸው ያለውን ቅቤ በተፈለገው የምግብ ኣይነት - ገንፎ፣ ጨጨብሳ፣ ጭኮ እና በመሳሰሉት ላይ ለማፍሰስ ጆሮኣቸው እንደመያዣ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ጆሮ የሌላቸው ከሆኑ ደግሞ ኣንገታቸው እንደብርሌ ኣንገት ገባ (ቀጠን) ብሎ የሚሰራ በመሆኑ ተጠቃሚው ያንን ኣንገት ይዞ ቅቤውን በምግቡ ላይ ሊያፈስ ይችላል።



*ፎቶግራፍ 14፡- የነጠረ ቅቤ ማቅረቢያ ጡዌዎች፡፡*

የጡዌዎች ሌላው ማስጌጫ መንገድ በኣንገታቸው እና በውጭኛው ዋናው ኣካላቸው ኣማካኝነት ንቅሳት የሚወጣላቸው መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የክብር እቃ በመሆናቸው እና በውስጣቸውም የሚገኘው ንጥር ቅቤ ተፈላጊ በመሆኑ በተለየ ቦታ ተሰቅለው ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡ ለዚህም ደግሞ የጠፍር ጥብጣብ (Strap) ሊያስፈልጋቸው ነው፡፡ ይህ የጠፍር ጥብጣብ በኣንገታቸው ዙሪያ ይታበትና በሶስት ቅርጽ ወደ ላይ ከፍ ብሎ በኣንድ የጋራ ነጥብ ላይ ሊገናኝ ይችላል (ከግራ ወደ ቀኝ ሁለቱን ጡዌዎች ይመልከቱ)፡፡ የጥብጣቡ የተወሰነው ጫፍም ተረፍ ብሎ ወደታች በጡዌዎች ኣካል ላይ ማለፍ ኣለበት፡፡ ይህም እንደ ኣልፊያ ህጂ ኣገላለጽ ለውበት ሲባል የሚደረግ ነው፡፡ ከጡዌው ኣፍ በላይ ያለው ተንጠልጣዩ ጠፍር የሚያገለግለው ጡዌውን በግድግዳ ላይ ለመስቀል ብቻ ሳይሆን ወደ መንገድም ይዘው ሲሄዱ በእጅ ለማንጠልጠልም ነው፡፡ ጡዌው ከጠፍሩ ሾልኮ እንዳይወድቅ የጡዌው ከንፈር ደግፎ እንደሚይዘው ልብ ማለት ይቻላል፡፡ ከጡዌ ውስጥ ቅቤ ለማውጣት ተገልጋዩ እስካልፈለገ ድረስ ማንኪያ የግድ ኣያስፈልግም፤ ማንኪያው ምናልባት የሚያስፈልገው በኣካባቢው ቅቤውን ለማቅለጥ እሳት የሌለ እንደሆነ ነው፡፡ ቅቤው የደደረ ከሆነ እና በኣካባቢው እሳት ካለ ጡዌውን እሳቱ ፍም ላይ ጣድ ማድረግ ነው፡፡ ቅቤው ሲቀልጥ የጡዌውን ኣንገት ወይም ጆሮውን ይዞ ኣስጎንብሶ መቅዳት ብቻ ነው፡፡ ጡዌዎች ኣልፎ ኣልፎ በታበተባቸው ጠፍር ላይ በዛጎልና በጨሌ ሊዋቡ ይችላሉ፡፡ እንደነዚህ ኣይነቶቹ ታዲያ በእሳት ላይ የማይጣዱ መሆን ኣለባቸው፡፡ ሌሎች ግን ልሙጥ ኣካል ነው ያላቸው ከንቅሳታቸው በስተቀር፡፡ ጡዌዎች ክዳን ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ክዳኑ ክስንደዶ ተሰፍቶ ይዘጋጅና በወደመያዣው ደግሞ ረዘም ያለ የቅል ኣንገት ይገባበትና ለመያዝ ምቹ ይሆናል፡፡ የቅሉ ጥቅም ጡዌው እንዲያምር እና መስህብነት እንዲኖረው ነው፡፡

*አገልግሎት፡-* ጠዋዎች የሚሰጡት አግልግሎት በመጠናቸው የሚለካ ነው፡፡ ጠዋዎች በተለያዩ ቅመማቅመሞች እና መልካም መኣዛ ባላቸው ባህላዊ እጽዋት የተነጠረ ቅቤን እስከመጠቀሚያው ቀንና ቦታ ድረስ ማስቀመጫና ማቅረቢያ ናቸው፡፡ በመጠን አነስተኛ በመሆናቸውም ለመያዝ ይመቻሉ፡፡ የጠዋዎች አነስተኛ መሆን ቦታው እራቅ ቢልም እንኳን በማእድ ወቅት በቆሪዎች ለሚቀርቡ ምግቦች ንጥር ቅቤ ይዘው ከሁዋላ የሚከተሉ የባህል እቃዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩልም በበኣላት እና በድግስ ቀን ወይም እንግዳ በመጣ ቀን ለመመገቢያ (ለማጣቀሻ) የሚሆን ምርጥ ንጥር ቅቤ ማቅረቢያ እቃዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ጠዋውን በወይራ እንጨት በማጠንና በማቆራሸት ከዚያም በሁዋላ በንጹህ ጨርቅ በማሸት፣ የተፈለገውን ቅቤም በማንጠር፣ መኣዛውንና ሽታውን ሳይለውጥ ሸጋ ጠረንና ጣእም ኖሮት ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጥ ጠዋዎች ተፈላጊና ተወዳጅ የኦሮሞዎች ባህላዊ እቃዎች ናቸው፡፡

### 4.3.5. ጃዩ (JAAYII)

ጃዩ (Jaayii) የማሰሮ ቅርጽ ያላት ስትሆን ከጠዋ በለጥ፣ ከማሰሮ ኣነስ የምትል የሸክላ ስሪት የሆነች የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህላዊ እቃ ነች፡፡

*ኣሰራር፡-* «ጃዩ» ብዙ ጊዜ ባለጆሮኣም ነች፡፡ ኣፏም ከጠዋ ይልቅ ሰፋ ብሎ ይሰራል፡፡ የኣሰራር ሂደቷ ከጠዋ የኣሰራር ሂደት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሸክላ ሰሪዋ ወ/ሮ ብዙነሽ ገነሞ

> *«ጃዩ ከማነሷ እና ብዙውን ጊዜም ጆሮ ያላት ከመሆኗ በስተቀር ያው ማሰሮ ማለት ነች፣ ማሰሮ እንደሚሰራው ሁሉ ለስራ የተዘጋጀው ኣፈር ከተቦካ በሁዋላ፣ የተቦካውን ጭቃ በጨርቅ ላይ ኣድርጎ ከሆዷ ጀምሮ ቅርጽ የማውጣቱ ስራ ይከናወናል፡፡ ከዚያ ወዲያ ያለው የኣሰራር ቅደም ተከተል ሁሉ ያው ለማሰሮው ስራ የነገርኩህ ነው» በማለት ኣጠቃለዋል፡፡*

የዚህ ጥናት ኣቅራቢ በምልከታው እንዳረጋገጠው ቁመት 23፣ የሆዷ መጠነ ዙሪያ 35፣ የብርሌ ቅርጽ ያለው ጉሮሮዋ 12፣ የከንፈር ውፍት 0.5፣ የኣፏ ዲያሜትር 16፣ የመያዣው ጆሮ ርዝመት 15፣ የኣንገቷም ርዝመት 6 ሳንቲሜትር ነው (የሁሉም ኣሀዞች መለኪያ ሳንቲሜትር ነው)፡፡ ይህ ግን በኣጋጣሚ ከተገኘችው ጃዩ በተገኘው መረጃ መሰረት እንጂ ሰሁልጊዜው መጠኗ ይኸው ብቻ ነው ማለት ኣይደለም፡፡

*አገልግሎት፡-* የጃዩ (Jaayii) ኣገልግሎት ከገበታ ወይም ከትልቅ ቆሪ ኣገልግሎት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚሁ ክፍል በመጀመሪያቹ ገጾች ላይ እንደተጠቀሰው ገበታ የተባለው ባህላዊ የኦሮሞዎች እቃ «ቡራቶ» (በቅቤ የታሸ ምግብ) ወይም ገንፎ ለድግስ ወይም በደቦ ስራ ወይም በሰርግ ወቅት የሚቀርብበት ትልቅ መመገቢያ ነው፡፡ በገበታ ወይም በቆሪ ቀርቦ ገንፎውን በመመገብ ላይ እንዳሉ ቅቤ ቢያንስ (እጥረት ቢያጋጥም) በጃዩዋ ከተያዘው ይፈስላቸዋል (ይቀዳላቸዋል)፡፡ በዚህ ሁኔታ ጃዩ የመጠባበቂያ ንጥር ቅቤ

መያገር ባህላዊ እቃ ነች ማለት ነው። በኣጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ጡዌዎች እና ጃዩዎች የመጠን መለያየት ካልሆነ በስተቀር በሚሰጡት ኣገልግሎት ተመሳሳይ ናቸው። ይሁን እንጂ ጡዌዎች መጋቢነታቸው ለቆሪዎች ሲሆን ጃዩዎች ግን ቁርኝታቸው ከገበታ ጋር ነው እንደ ኣቶ በቀለ ቱፋ ኣገላለጽ። ገበታ በሚሾምበት ማእድ ላይ በተለይም በሰርግ ወቅት ቅቤ ማነሱንና ኣለማነሱን የሚከታተሉ ሰዎች ይመደባሉ። ይሁን እንጂ በኣጋጣሚ ሊዘናጉ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ታዲያ እንግዶቹ ቅር ተሰኝተዋል ብለው የሚያምኑ የኣካባቢው ኣዛውንት «ገበታን ጎጋ ጅራ ገሩ ማል ኑ ወያ?» (Gabataann Gogaa jira garuu mal nu wayya?) ገበታው እየደረቀ ነውና ለነገሩ ምን ይሻለናል? ይላሉ በዘዴ። ከእማሬያዊ ፍችው ወደ ፍካሬያዊ ፍችው ስንመጣ የቀረበው ምግብ ቅቤ ኣንሶታልና ኣስቡበት የሚል ነው። ወዲያው በቅመም የነጠረ ቅቤ የያዘች ጃዩ ከተፍ ትላለች።

### 4.3.6. ወሾ (WASHOO)

ወሾ ማለት ኣፈ ሰፊ የሆነ እንስራ ማለት ነው። ከመደበኛ እንስራ የሚለየው ኣፉ በመስፋቱ ነው። ወሾ፣ የሸክላ ስሪት ከሆኑ እቃዎች ውስጥ ኣንዱ ነው።

*ኣሰራር፡-* የእንስራን (ወሾን)ኣሰራር የነገሩኝ ወ/ሮ ደመቀች ሺኮ ናቸው። ወ/ሮ ደመቀች ሺኮ ከጎባ ከተማ ደቡባዊ ምስራቅ ፈረስ መጋለቢያ ኣካባቢ ተወልደው ያደጉ የ30 ኣመት ሴት ናቸው። በፈረስ መጋለቢያ ኣካባቢ በርካታ ሸክላ ሰሪዎች ስላሉ የሸክላ ኣሰራርን ልምድ መቅሰማቸውን በኩራት ይናገራሉ። በዚህም መሰረት ላለፉት 12 ኣመታት ልዩ ልዩ የሸክላ ስሪት የሆኑ እቃዎችን ሲሰሩ እንደቆዩ ያስረዳሉ። ወ/ሮ ደመቀችን እንስራ (ወሾ) እንዴት ይሰራል? በማለት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን መልስ ሰጥተውኛል። ይሁንና የሸክላው ኣፈር መጥቶ እስከሚቦካ ድረስ ያለውን የኣሰራር ሂደት ቀደም ሲል የሌሎችን እቃዎች ኣሰራር ስንጠቅስ የተመለከትን በመሆኑ ኣሁን የምንነሳው ጭቃውን እጥቅም (ስራ) ላይ ከማዋል ጀምሮ ያለውን የኣሰራር ሂደት ነው። እናም ወ/ሮ ደመቀች ሺኮ ይቀጥላሉ።

> *እንስራን (ወሾን) ለመስራት ጭቃውን ወደ እቃነት ለመለወጥ የሚሰራበት ሰፋ ያለ ጨርቅ፣ ቅርጽ ለማውጫ በተለይ የጅንስ ቅድ የሆነ ኣነስተኛ ጨርቅና ለስላሳ የቆዳ ቅዳጅ፣ ብረት (ቦንዳ)፣ ሳሳ ያለ የቀርከሀ ቁራጭና ውሀ ተፈላጊዎች ናቸው። እነዚህ መሳሪያዎች ከተገኙ በሁዋላ ወደ ስራው መግባት ነው። ጭቃውን በሰፊው ጨርቅ ላይ ኣድቦልቡዬ በማስቀመጥ እጄን በቡጢ መልክ ከጨበጥኩ በሁዋላ በውሀ እያራስኩ ያንን የተድቦለቦለ ጭቃ በእጄ ጀርባ (በኣይበለሳ ማለታቸው ነው) ወደ ጎንና ጎን እያሰፋሁ ከሆዱ እጀምርና ወደላይ እየሳብኩ-እየሳብኩ እስከ ኣንገቱ ድረስ እንዲለጠጥ ኣደርገዋለሁ። የምፈልገውንም መጠን በኣይነ ግምትና እንደደንበኛ ፍላጎት ኣሰፋዋለሁ ወይም ኣጠብበዋለሁ። በምሰራበት ጊዜ ጣቶቼን በውሀ የማርሰው ጭቃው በእጄ ላይ እየተላከከ እንዳይጣበቅና ለስራዬ እንቅፋት እንዳይሆንብኝ ነው። ወደዳርና ዳር ገፋ በማድረግ እያሰፋሁት የመጣሁትን እንስራ በጅንስ ቅዳጅ ጨርቅ ወይም በቆዳው*

እየላግሁ ወደ ላይ እየሳብኩ እስከ ኣንገቱ ብዙም ውፍረት እንዳይኖረው እየተጠነቀቅሁ ኣወጣዋለሁ:: የእንስራውን (የወሾውን) የኣንገት ቅርጽ እና ለጠፕ የሚለውን የከንፈሩን ቅርጽ ካወጣሁ (ከሰራሁ) በሁዋላ እንዲደርቅ ለ2 እና ለ3 ቀናት እተወዋለሁ:: የማስቀምጠው በቤት ውስጥ፣ በጥላ ቦታ ሊሆን ይችላል:: በመድረቅ ላይ እንዳለም በእንስራው ግራና ቀኝ የሚሰኩትን ጆሮዎች ቅርጻቸውን እሰራለሁ:: የሰራሁኣቸውን ጆሮዎች እንደ እንስራው ሁሉ እንዲደርቁ ኣስቀምጣቸዋለሁ:: ቀጥሎ ለ3 ቀናት እንዲደርቅ የተውኩትን እንስራ በኣፉ በኩል ከደፋሁ በሁዋላ በመቀመጫው በኩል የተጋገረውን ጭቃ በብረት (በቦንዳ) ፈቅፍቄ በማንሳት ክፍት እንዲሆን ካደረኩኝ በሁዋላ ከጎንና ከጎኑ የቀረውን የመጨረሻ ጠርዝ መነሻ በማድረግ ሌላ የተቦካ ጭቃ ኣምጥቼ በእጄ እየላግሁትና እየሳብኩኝ የመቀመጫውን (የቂጡን) ቀዳዳ እደፍናለሁ:: በዚህ ኣይነት ኣሰራር የመጨረሻውን ቀዳዳ ስደፍን የእንስራው እንብርት ተዘጋ ማለት ነው:: ልብ በል መጀመሪያ ስሰራው የሆዱን ክፍል ጎንና ጎን ኣሰፋሁ እንጂ ቂጡ ክፍት ወይም ኣላስፈላጊ ጭቃ እንደተከመረበት ነው:: ስለዚህ ኣሁን ከሶስት ቀናት በሁዋላ በኣፉ ደፍቼ ቂጡን መድፈን ሊኖርብኝ ነው:: የእንስራው ቂጥ ከተደፈነ በሁዋላ እንደገና እንዲደርቅ ለ3 ቀናት ይቀመጣል:: የሚቀጥለው ተግባር የተዘጋጁትን ጆሮዎች በቦታቸው ማያያዝ ነው:: ጆሮዎቹን ለማያያዝ መጀመሪያ የሚያያዙበት ቦታ በመጠኑ ሰርሰር-ሰርሰር ካደረግሁኝ በሁዋላ ወይም በትንሹ ሰርሰር-ሰርሰር ኣደርግና ከገጠምኳቸው በሁዋላ የተገጠሙበትን ቦታ ዙሪያውን በኣዲስ ጭቃ እያሸሁ እንዲጠብቅ ኣደርጋለሁ:: ቀጥሎም እንዲደርቅ ለ2 ቀናት በጥላ ስር ይቆያል:: ከቆይታው በሁዋላ በብረት (በቦንዳ) እየፋቅሁ ሸካራ የሆነውን ነገር ለማስለቀቅ እሞክራለሁ:: ይህንንም የእንስራውን የውጭውንና የውስጡን ክፍል በመፋቅ ነው የማስተካክለው:: መፋቁ በዚህ ብቻ ኣያበቃም ይልቁንም የድንጋይ ኣሎሎ ኣመጣና ውጭውንም ውስጡንም ኣሸበታለሁ:: በዚህ ወቅት ትንሽም ሆነ ትልቅ ሸካራ እየተዳመጠ ይወገዳል:: እዚህ ላይ ኣሎሎ እንጂ ሌላ ድንጋይ እንደማልጠቀም ልብ ማለት ያሻል:: ሌላ ድንጋይ ከተጠቀምኩ ይፈቀፍቀውና የባሰውን ሸካራ ስለሚያደርገው ከኣሎሎ ድንጋይ ውጭ ሌላ ድንጋይ ኣያስፈልግም:: በዚህ ላይ እያለ ምንም እንኳን ስራው ባያልቅም እንስራ ሆነ የሚለው ደረጃ ላይ ደርሷል:: ተከታዩ ስራ እንስራውን (ወሾውን) «ኡሬ» ማድረግ ነው:: «ኡሬ» ማለት ሸክላዎቹ በሀይለኛ እሳት ከመቃጠላቸው በፊት እሳቱን ማለማመድ ወይም ማሟሟቅ ማለት ነው:: ሳናሟሙቅ በሀይለኛው እሳት ውስጥ ብንከተው መጀመሪያውኑ ቅዝቃዜ ኣለውና እሳቱን ከመቋቋም ይልቅ ብትንትኑ ስለሚወጣ ነው: እናንተ በትምህርታችሁ ቀዝቃዛና ሙቀት ሲገናኙ እቃን ይሰብራል እንደምትሉት:: ለማሟሟቅም ኩበት ወይም የእንጨት ፍም እንጠቀማለን:: በዚህም እያሿሿርን እናሟሙቀዋለን:: የሚቀጥለው ተግባር ኣመድ በተነሰነሰበት የማቃጠያ ኣውድማ ላይ እንጨት ረብርበን የሚቃጠሉትን የሸክላ ውጤቶች ከስር በእንጨት ከላይ በገለባ ኣድርገን ማቃጠል ነው:: ቃጠሎው ከ3 እስከ 4 ሰኣት ይወስዳል:: የማቃጠሉ ተግባር ካበቃ በሁዋላ እዚያው ኣመዱ እንደተዳፈነበት ቢያድርና ጠዋት ቢነሳ ይመረጣል፤ ምክንያቱም ወዲያው ብናወጣው እውጭ ካለው ቀዝቃዛ ኣየር ጋር ሲገናኝ ቢያንስ ሊሰነጠቅ ይችላልና:: ከቃጠሎው በሁዋላ እንስራው መብሰሉን የምናረጋግጠው ጥቁር ከሆነ ነው:: ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ ሳር እናቃጥልና እንስራውን በሚቃጠለው ሳር ላይ እናስቀምጠዋለን:: በዚህን ጊዜ ጥቁረት ካመጣ በስሏል ማለት ነው፤ ካልጠቆረ እንደገና በእሳት ውስጥ መጨመር ኣለብን:: መብሰሉን ለማረጋገጥ በእኛችን መታ መታ የምናደርገው እንደ ምጣድ ያለውን ሸክላ ነው እንጂ እንስራን በሳር ኣቃጥለን ጥቁር መሆን ሲጀምር ነው መብሰሉ የሚረጋገጠው:: የማቃጠያው ኣውድማ ላይ ኣመድ የምንነሰንሰው መሬቱ ርጥበት ስላለውና እሳት ሲነድበት እንፋሎቱ ሲነሳ ሸክላዎቻችንን ስለሚያበላሽብን ነው:: በኣጠቃላይ ከቃጠሎው በሁዋላ ስራው የተጠናቀቀ

*ስለሆነ ለሽያጭ ወይም ከተሟሸ በሁዋላ ለኣገልግሎት ብቁ ይሆናል::*



*የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ባህላዊ እቃ፣ ወሸ::*

*ኣገልግሎት፡-* ወሸ በተለያዩ ቦታዎች ልዩ ልዩ ግልጋሎቶችን ይሰጣል:: ከእነዚህም ውስጥ ወተት ማጠራቀሚያና መናጫ እንዲሁም ውሀ መቅጃ በመሆን የሚሰጣቸው ግልጋሎቶች ተጠቃሾች ናቸው::

*ባህላዊ ፋይዳ፡-* ወሸ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ዘንድ በተለይ በሰርግ ወቅት በርካታ ተጋባዦችን ለማስተናገድ ሲባል ገንፎ ማገንፊያ በመሆን ከዘወትራዊ ኣገልግሎቱ በላይ የብሄረሰቡን ባህላዊ የወሸ ኣጠቃቀም ያመለክታል::

## 4.3.7. በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ባህል የቡና ስርኣት ማከናወኛ ቁሳቁስ

በፎቶግራፍ 15 የሚታዩ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ቡናን ከማፍላት ጀምሮ ተጠጥቶ እስከሚያበቃ ድረስ ያለውን ስርኣታዊ ክዋኔ የሚተገብሩባቸው ናቸው:: እቃዎቹ የእንጨት፣ የሸክላ፣ የቅል እና የስፌት ውጤቶች ናቸው:: እነዚህ ከተለያዩ ጥሬ እቃዎች ወደ ባህላዊ እቃነት ተለውጠው ስርኣታዊ የቡና ማከናወኛ የሆኑ ቁሳቁስ፣ ከቅል ከሚሰሩት የቡና ቁሉዎች በስተቀር በወረዳው ውስጥ ያሉ ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች ይገለገሉባቸዋል:: ከቅል የሚሰሩት የቡና መጠጫ እቃዎች ግን ይበልጡኑ የኦሮሞን ባህል የሚያንጸባርቁ ጥንታዊና ባህላዊ ቁሳቁስ ናቸው:: እነዚህ ቁሳቁስ ከግራ ወደቀኝ ቡና መጠጫ ቅል «ቁሉ ቡና» «Quluu buna»፣ የእጣን ማስቀመጫ ሙዳይ «ጊልጊሊ ሂጣና» «Gilgilii hixaanaa»፣ የቡና ሙቀጫ «ሞዬ ቡና»

«Mooyyee buna»፣ ጊርጊራ የእጣን ማጨሻ «ጊርጊራ» «Girgiraa»፣ የቡና ዱቄት ማስቀመጫ ከቅል የተሰራ «ቡቄ ቡና» «Buqqee buna»፣ የሸክላ ጀበና «ጀበና ፋራ» «Jabanaa Faaraa»፣ ማቶት «ጃሊቲ» «Jaliitii»፣ የቡና መውቀጫ ዘነዘና «ሙካ ቱማ ቡና» «Muka-tumaa buna» ናቸው:: በማንቆርቆሪያ ቅርጽ የተሰራው የሸክላ ውጤት ግን በዚህ ዝርዝር ውስጥ ኣልተጠቀሰም::

የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦችን ቁሳዊ ባህል ሳጠና ጥያቄ ያቀረብኩላቸው ሰዎች በተለያዩ የእድሜ እርከን ላይ ያሉና ባህሉን ያውቃሉ ያልኳቸውን ከወጣት እስከ ኣዛውንት ሁለቱንም ጾታዎች ያካተቱ ናቸው:: ይሁንና በፎቶግራፍ 15 ላይ የሚታየውን ጀበና ወጣቶቹ የኦሮሞ ባህላዊ እቃ ነው ሲሉ የ88 ኣመቱ እድሜ ባለጸጋ የሆኑት ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ግን በዚህ ሀሳብ ኣይስማሙም:: እሳቸው የሚሉት በፎቶው ላይ ያለው ጀበና ዘመን ኣመጣሽ እንጂ ነባሩን የኦሮሞን ባህል የሚያንጸባርቀው ጀበና ኣይደለም::




*ፎቶግራፍ 15፡- የቡና ስርኣት ማከናወኛ ልዩ ልዩ ቁሳቁስ::*

*ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ ኣሁን በፎቶው ላይ የማየውን ጀበና ይጠቀሙበት የነበሩት ኣማራዎች ናቸው:: በዚህም ምክንያት ብሄረሰቦች (የኣማራንና የኦሮሞን ማለታቸው ነው) ኣብረው ለብዙ ጊዜ ከመኖራቸው ጋር ቀስ በቀስ ኦሮሞዎቹም ይህንኑ ጀበና መጠቀም ስለጀመሩ የኣሁኑ ትውልድ ወጣቶች የኦሮሞን ባህል ያንጸባርቃል ቢሉ ኣያስገርምም፤ እነሱ ያንን የቀድሞ፣ ኦሮሞዎች ይጠቀሙበት የነበረውን የቡና ጀበና ኣይተው ኣያውቁምና በማለት ይናገራሉ::*

ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ የኦሮሞን ባህል በትክክል ያሳያል የሚሉት የጀበና ኣይነት በዚሁ ክፍል ፎቶግራፍ 11 ላይ ያየነውን ኦኮቴ (ማሰሮ) «Okkotee» የሚመስለውን ነው:: የቡና ጀበናው «ኦኮቴ» «Okkotee» ይምሰል እንጂ በመጠኑ ትንሽነት እና ጆሮኣም በመሆኑ ይለያል:: የሆዱም ስፋት እንደ ገንፎ ማገንፊያው ኦኮቴ «Okkotee» ሳይሆን ኣነስ ብሎና ሾጠጥ ብሎ የሚሰራው ነው:: እንደ ዘመነኛው ጀበና ለቡናው ማንቆርቆሪያ (መቅጃ) የሚሆን ጡት ስለሌለውም የሚቀዳው ጆሮውን በመያዝ በኣፉ በኩል ነበር:: ይሁንና ጀበና እንዴት ይሰራል?

***የጀበና ኣሰራር፡-*** ጀበና ኣነስተኛ ከሆኑት የሸክላ ስሪት እቃዎች ውስጥ የምትመደብ ነች:: ስለ ሂደተ-ኣሰራሯ ወ/ሮ ደመቀች ሼኮ የሚሉት ኣላቸው::

*ኣንድ ጀበና ሊያሰራ የሚችል ጭቃ ይመጠንና ተድቦልቡሎ በተነጠፈ ጨርቅ ላይ ይደረጋል:: ከዚያም ከታች (ከመቀመጫዋ) ጀምሮ የብርሌ ኣንገቷን ማውጣት እስከሚቻል ድረስ ጭቃውን እየሳቡ፣ እየሳቡ፣ እየሳቡ በመለጠጥ መስራት ነው:: በዚህም ትለሰልሳለች፣ ትለሰልሳለች ከዚያም ቀስ እያለች ትሳባለች:: ትርፍ ጭቃ ወደ መቀመጫዋ ላይ ሊኖራት ይችላል:: በትርፍነት ያለው ጭቃ ለጊዜው እንደመቀመጫ ያገለግላል:፤ ይሁን እንጂ የመጀመሪያ ስራዋ እንደተጠናቀቀ ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት መድረቅ ኣለባት:: ከ2 ወይም ከ3 ቀናት ቆይታ በሁዋላ በመቀመጫዋ ስር ያለውን ትርፍ ጭቃ ቀስ በቀስ እየፈቀፈቁ ማንሳት ነው:: እንደ እንስራ ጆሮ ኣሰራር ሁሉ የጀበና ጡት እና መያዣ ጆሮዋ ለብቻ ተለክተው ከተሰሩ በሁዋላ ቀደም ሲል የተሰራው የጀበና ኣካል መድረቁ ተረጋግጦ ይገጠሙላታል:: በሚገጠሙበት ወቅት ከዋናዋ ጀበና ጋር የተያያዙበት ቦታ ዙሪያውን በጭቃ ይለሰናል:: ቀጥሎም እንድትደርቅ ለ2 ወይም ለ3 ቀናት በቤት ውስጥ እንድትቆይ ይደረጋል:: ጀበና የምትሰራው ከጡቷና ከጆሮዋ በስተቀር ኣንድ ጊዜ ወጥ በሆነ ሁኔታ ነው እንጂ እንስራ ኣፉ ተደፍቶ መቀመጫው (ቂጡ) እንደሚሰራ ሁለት ጊዜ ኣትሰራም:: ከሌሎች የሸክላ ስሪት ከሆኑ እቃዎች ጋር ሲነጻጸር የጀበና ስራ ይከብዳል:: ስለዚህም ደንበኛ ሙያተኞችን ይጠይቃል:: የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ስራዋን የጨረሰች ጀበና እንደ ሌሎች ሸክላዎች ሁሉ በእሳት ከመሟሟቅ ተነስታ በቃጠሎ ኣልፋ ለሽያጭና ለኣገልግሎት ትደርሳለች:: ለማለስለስ በሚደረገው ጥረት በጀበና ውስጥ እጅን ኣስገብቶ ማለስለስ ስለማይቻል የማለስለሱ ስራ በለስላሳ ጨርቅ ኣማካኝነት መጀመሪያውኑ መጠናቀቅ ኣለበት:: ጀበና ከኣነስተኛ የሸክላ እቃዎች ብትመደብም ትልቅና ትንሽ ጀበናዎች ይሰራሉ:: ያም ሆነ ይህ የጀበና፣ የእንስራና የማሰሮ ስራ እንደምጣድ ስራው ወዲያውኑ ኣይቀላጠፍም:: ምጣድ ዝርግ በመሆኑ በእጅ እንደልብ ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ ጸሀይና ንፋስ እንደልብ ያገኘዋል:: እንደ ጀበና ኣይነት እቃዎች ግን ቀስ በቀስ የሚነሳላቸው ጭቃ ሁሉ ስላለ ጭቃው ተነስቶ እስከሚደርቁ ጊዜ ይወስዳሉ:: ምክንያቱም 1ኛ ጆሮኣቸው፣ ጡታቸው*

*በሁዋላ ላይ የተቀጠለ ስለሆነ ለመድረቅ ተደጋጋሚ ጊዜ ይወስዳሉ:: 2ኛ እንደ ጀበና፣ እንስራ ማሰሮ ያሉት በመቀመጫቸው ላይ የሚገኘው ጭቃ ተደራቢ ስለነበርና ቀስ በቀስ እየተወገደ ስለመጣ በደንብ መድረቅ አለበት ለዚህም ጊዜ ያሻል::*

በዚህ ጥናት ወቅት በምልከታ የተገኘችው ጀበና ቁመት 21፣ የአንገት መጠነ ዙሪያ 12፣ የሆድ መጠነ ዙሪያ 45፣ የጆሮ ርዝመት 14፣ የጡት ርዝመት 7 የአፏ አካባቢ መጠነ ዙሪያ 15 ሳንቲሜትር መሆኑን በመለካት ለማረጋገጥ ተችሏል (መለኪያው ለሁሉም አሀዞች ሳንቲሜትር ነው)::

እንደ ወ/ሮ ደመቀች ሼኮ ኣባባል እየተሰሩ ያሉትን የሸክላ እቃዎች በጸሀይ ላይ እውጭ እንዲቆዩ ማድረግ ደረጃቸውን ሳይጠብቁ ቶሎ እንዲደርቁ ስለሚያደርጋቸው የመበላሸታቸው አጋጣሚ የሰፋ ነው:: ስለዚህ በቤት ውስጥ ወይም በጥላ ስር ማስቀመጥ ተመራጭ የሚሆነው ቀስ በቀስ ደረጃቸውን እየጠበቁ ውሀቸውን እንዲመጥጡ ለማድረግ ነው::

ወደ ፎቶግራፍ 15 ስንመለስ ከግራ ወደ ቀኝ በቀዳሚው ረድፍ ላይ የቡናውን መጠጫ ቁሉ (ከቅል የተሰራ መጠጫ እናገኛለን):: ቁሉ «Quluu» በተፈጥሮ ልዩ ቅርጽ ካለው ቅል የሚሰራ መጠጫ ነው:: ተፈላጊው ቅል መጀመሪያውኑ የቁሉ ተግባር (ለመጠጫ) ለመመረጥ በተፈጥሮው የስምንት ቁጥር (8) የመሰለ ቅርጽ መያዝ ይጠበቅበታል:: የዚህ ኣይነት ቅርጽ ካለው በእጅ ጨብጦ ለመያዝና ለመጠጣት ኣመቺ እንደሚሆን ይነገራል:: ቁሉን «Quluu»ን ለማስዋብ ሲባል በቅሉ ኣካል ላይ ጥበባዊ ስራ የታከለበት ንቅሳት ይነቀሳል:: በፎቶግራፉ ላይ የሚታየው ቁሉ ልሙጥ (ንቅሳት ያልወጣለት) ቢሆንም በኣንዳንድ ቁሉዎች ግን የንቅሳቱ ጥበባዊ ስራ ይታያል:: (ፎቶግራፍ 16ን ይመልከቱ) በዚህ ምስል ምንም እንኳን ልጅቱ በማስተዋወቅ ላይ ያለችው ቁሉ «Quluu» የቡናም ባይሆን ከወደ ኣፉ የተነቀሰ መሆኑንና ሌላውም ክፍሉ በዛጎሎች የተጌጠ መሆኑን ማጤን ይቻላል:: የቡና መጠጫ ቁሉ «Quluu» ቡናን ብቻ ሳይሆን ፈሳሽ የሆኑ መጠጦችን ለመጠጣትም ያገለግላል:: ዘመናዊ ብርጭቆ ባልነበረበትና ኣሁንም በሌለበት ቦታ ሁለገብ ኣገልግሎት ይሰጣል::



*ፎቶግራፍ 16:- የማማጊያ ወተት የምትይዘዋን ቅል (ቁሉ ኡነታ) በማስተዋወቅ ላይ::*

ወደ ፎቶግራፍ 15 ስንመለስ ከቡና መጠጫው ቁሉ «Quluu» ቀጥሎ እጣንን ለመያዝ የምታገለግል ኦሮሞዎች ጊልጊሊ (Gilgilii) ይሏታል፣ ኣማራዎች «ሙዳይ» በማለት የሰየሟት ከስንደዶ ሰበዝ እና በቀለም በተነከሩ ልዩ ልዩ ኣለላዎች ኣምራና ተውባ የተሰፋች ቁስ (የእጣን መያዣ እቃ) ትገኛለች:: ከሙዳይዋ በሁዋላ ባለክዳን የእንጨት ሙቀጫ ኣለ:: ሙቀጫው ከዝግባ ወይም ከግራር እንጨት ተፈልፍሎ የተሰራ ሊሆን ይችላል:: ቀጥሎ ያለችው ከሸክላ የተሰራች ጊርጊራ ነች:: ይህች ጊርጊራ መያዣ ጆሮ ተበጅቶላታል:: ጊርጊራዋ (የእጣን ማጨሻዋ) ከዋናው የኣካሏ ጠርዞች የተውጣጡ ቅጣይ ኣካላት ከኣራት ኣቅጣጫ ተነስተው በጊርጊራዋ መሀል ለመሀል ኣንድ የጋራ ነጥብ ሰርተዋል:: ይህም በቀላሉ በእጅ እንድትያዝ የሚያደርጓት ናቸው:: ይህች የእጣን ማጨሻ ባህላዊ እቃ የተሰራችው ከሸክላ ነው:: ከእጣን ማጨሺያው ጊርጊራ ቀጥሎ በጥቅም ላይ ከዋለው የተረፈ የቡና ዱቄት የሚቀመጥባት ከቅል የተሰራች የቡና ዱቄት መያዣ ቅል ቡቄ ቡና «Buqqee buna» ነች:: እነዚህም ሁለት ሲሆኑ በጀበናው ግራና ቀኝ ተቀምጠዋል::



*ፎቶግራፍ 17:- -የጀበና አገልግሎት እንዲህ ነው::*

በፎቶግራፍ 17 ላይ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብን የቡና ስርኣታዊ ኣጠቃቀም የምታሳይ ልጅ ትታያለች:: የጀበናውን ኣጠቃቀም በተመለከተ በጡቱ በኩል ቡናው ወደ መጠጫው ቁሉ «Quluu» እንዴት እንደሚቀዳ ኣያያዙን እያመለከተች ነው:: በኣጠገቡ የሚገኙት ቁሉዎችም በልዩ ልዩ መጠን ነገር ግን በኣንድ ኣይነት ቅርጽ ይታያሉ:: ይህ ባለ 8 ቁጥር ቅርጽ ለቡና መጠጫ ቁሉዎች የጋራ ቅርጻቸው (መታወቂያቸው) ይመስላል:: (ፎቶግራፍ 17ን ይመልከቱ):: ኦሮሞዎች ቡናን በወተት መጠጣት ባህላዊ መታወቂያቸው ነው:: ከብቶች በብዛት የሚያረቡትም ከእንስሳቱ የሚያገኙት ልዩ ልዩ ተዋጽኦ የምግቦቻቸው ምንጭ እንደሆነ ከግምት በማስገባት ነው:: በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች በተለይ የቡናው ስርኣታዊ ክዋኔ ኣባወራ ከቤተሰቦቹ ጋር በኣንድነት የሚቀመጥበት ትልቁ ኣጋጣሚ ነው:: እንግዳ ሲመጣ «ቡና እናፍላ» የሚለው የብዙዎች ኢትዮጵያውያን ብሄረሰቦች ኣባባል በኦሮሞዎችም ዘንድ «ቡና ላፍላ» «ቡና ደንፊሱ» «Buna Danfisuu» በማለት የሚጋብዝ በመሆኑና በተለይም ስርኣታዊ ክዋኔው ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቁሳቁስ ስለሚታጀብ የኦሮሞዎችን ባህላዊ ፋይዳ የሚያመለክት ነው::

***አገልግሎት፡-*** ቡና ለጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች አይነተኛ የሱስ መጠጥ ነው፡፡ ቡና ሲነሳ ደግሞ ጀበናው አይቀሬ ነው፡፡ የጀበና ዋና አገልግሎት ታዲያ ቡናን ለማፍላት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን-አሁን ለፍጥነት እየተባለ የጀበና አገልግሎት በማንቆርቆሪያ እየተተካ ነው፡፡ ይሁንና ብዙዎቹ የብሄረሰቡ አባላት ለምሳሌ ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ አሚንን የመሳሰሉ በሰጡት አስተያየት የማንቆርቆሪያው ቡና በጀበና የሚፈላውን ያህል አይጥምም፡፡

***ባህላዊ ፋይዳ፡-*** የጀበና ባህላዊ ፋይዳ መታያ መድረኩ ሰፊ ነው፡፡ እንግዳን ለመቀበል፣ ቤት ጭር እንዳይል ሲፈለግ፣ከጎረቤት ጋር ለመጫወት፣ ውቃቢን፣ አቴቴንና ቦረንትቻን ለመዘከር፣ ለጫት ማወራረጃ፣ ለጸብ ማርከሻ፣ ለእርቅ ማስፈኛ፣ በበአላት ወቅት ወዘተ. ሁሉ ቡናን ማፍላት የተለመደ የየወቅቱ፣ የየእለቱ ከዚያም ሲያልፍ የጠዋትና ማታ ልምድ ነው፡፡ ቡናው ሲቆላ ታዲያ ጀበና መታጠቡ አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ ቡናና ጀበና፣ ጀበናና ቡና እጅና ጓንት ሆነው አብረው ይጓዛሉ፣ አብረው ይደምቃሉ እናም የጎባ ወረዳ ኦሮሞችን ባህላዊ ፋይዳ ያንጸባርቃሉ፡፡

## 4.4. ከቅል የሚሰሩ ቁሳቁስ

ከቅል የሚሰሩ ቁሳቁስ በሚለው ርእስ «ቁሉ ኡነታ»ን፣ «ቡቄ ቡና»ን፣ «ቁሉ ቡና»ን፣ «ጉቹማ»ን እና የውሀ ቅል ወይም የስግደት (የሰላታ ቅል) የተባሉትን መገልገያ ቁሳቁስን እንመለከታለን፡፡

### 4.4.1. ትውራዊ ዳራ

ቅል ጥንታዊነት ያለው ለመጠጫና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የእቃ አይነቶች የሚሰሩበት በተፈጥሮ የሚገኝ ተክል ነው፡፡ ቅል እንደ ሀረግ በዛፍ ወይም በአጥር ላይ እየተሳሳበ ሲያድግም የሚችል ነው፡፡ ቅል በኢትዮጵያ ለውሀ መቅጃ፣ ለቡና መጠጫ ወይም ለጥራጥሬ፣ ሽሮና ድልህ፣ ቅቤና የመሳሰሉትን ሁሉ ማስቀመጫ በመሆን ያገለግላል፡፡

ቅል እንደቅርጹ እየተፈለገ የተለያዩ የቤት ውስጥ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ይሰሩበታል፡፡ «ሰዎች በእለት እለት ህይወታቸው የሚያስፈልጓቸውን መያዣዎች እና ልዩ ልዩ እቃዎች ከቅል ፍሬ የሚገኘውን ቅል በመጠቀም ይሰራሉ (ያዘጋጃሉ)» ሲልቨርማን (Silverman,) 1999፣39)፡፡ በእርግጥም እንደሚታወቀው የቅል አገልግሎት በየአገሩ የተስፋፋ ነው፡፡ ይህም በቅርቡ የተጀመረ ሳይሆን ጥንታዊነት ያለው ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ቀደምት የእደጥበብ ውጤት ባለቤቶች እንደነበሩ የታሪክ ድርሳናት ያረጋግጣሉ፡፡

*«ከኢንዱስትሪ ኣብዮት በፊት እንደ ኣውሮፓውያን ሁሉ ኢትዮጵያውያን ህዝቦች ፍላጎታቸውን ለማርካት እና መጠቀሚያ ይሆኑኣቸው ዘንድ የሚያገለግሏቸውን ቁሳቁስ ለመስራት ከመጀመሪያዎቹ ዘመናት ጀምሮ የራሳቸው የሆኑ የእደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎችን ያራምዱ ነበር» ሪቻርድ ፓንክረስት (Richard Pankhurst 1964፣ 221)::*

የቅል ተክል በየጓሮውና የኣየር ጠባዩ ኣመቺነት ባለው ቦታ ሁሉ ሊበቅል የሚችል በመሆኑና ለመስራትም ቀላል ስለሆነ በኢትዮጵያ የተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ህዝቦች ይጠቀሙበታል:: ግርማ መንግስቱ በኦሮሚያ ክልል በወለጋ ዞን ነቀምት ከተማ የሚኖሩና በኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ናቸው:: በኢትዮጵያ የሚገኙ ኦሮሞዎች ባህል ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ በመሆኑ በተለይ ስለ ቅል ኣገልግሎት እንዲገልጹልኝ ጠይቂ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ለምሳሌ ቅል በወለጋ ኣኬሌ «Akeelee» የሚል ስም ተሰጥቶት ለሁለት ቦታ እየተከፈለ (እየተሰነጠቀ) ንፍሮ፣ የባቄላ ኣሹቅ እና የመሳሰሉትን የምግብ ኣይነቶች በነፍስ ወከፍ ወይም ለጋራ መጠቀሚያነት ያውሉታል:: በጥቅሉ ቅል በቀላሉ የሚገኝና ስራውም ኣድካሚ ካለመሆን ጋር ተዳብሎ ሰዎች በቅል ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ሳይዳርጋቸው ኣልቀረም:: በተለይ ለኣያያዝ ቀላልና ኣመቺ መሆኑንም ብዙ ሰዎች ይመሰክራሉ «በኢትዮጵያ ብዙ ሰዎች ከቅል የተለያዩ መያገዎችን ይሰራሉ .... በእርግጥም ተክሉ በየቦታው ይገኛል .... የቅል ተክል በየጓሮው ሊበቅል የሚችል ነው» ሲልቨርማን (Silverman, 1999፣ 32)::

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት በቅል ተጠቃሚ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ብሄረሰቦች ውስጥ ኦሮሞዎችም ይገኙበታል:: በተለይ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ቅልን ለቡና መጠጫ፣ ማስቀመጫ ወደ መንገድም ሲሄዱ የውሀ ስንቅ መያዣ ኣድርገው ይገለገሉበት እንደነበር ኣቶ በቀለ ቱፋ ይናገራሉ:: ከዚህም በላይ የኦሮሞዎች ዋና መጠጥ የሆነው ቡና በወተት ለኣባወራውና ለደራሽ እንግዳ የሚሰጣቸው በቅሉ ነው:: የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎችም ይህንኑ የሚጋሩ በመሆናቸው በወረዳው ውስጥ የቅል ቁሳቁስ ኣሰራሩንና ኣጠቃቀምን በተከታዩ ጽሁፍ እንቃኛለን::

## 4.4.2. የተለያየ መጠንና ቅርጽ ያላቸው የቅል ቁሳቁስ

ቅሎች በተፈጥሮ የሚገኙ ተክሎች እንደመሆናቸው መጠን ሌሎች ከእንጨት፣ ከሸክላ፣ ከስፌት ወዘተ. እንደሚሰሩት ቁሳቁስ ቅርጽ ማውጣትና መጠናቸውን ማተለቅ ወይም ማሳነስ ላይ ብዙም ትኩረት ሲሰጥ ኣይታይም:: ይሁንና በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች የቅል ኣጠቃቀም ባህል እንደሚስተዋለው ኣንድ ቅል ለግልጋሎት ተፈልጎ ነገር ግን መጠኑ የሚያንስ ሆኖ ከተገኘ ከኣፉ ኣካባቢ ጀምሮ ወደላይ ስፌት ይሰፉበትና ያተልቁታል:: በሌላ በኩል ትልቁን ቅል ማሳነስ ከተፈለገም በስለታም መሳሪያ እየከረከሙ ያሳጥሩታል:: ከዚህ ውጭ ተፈጥሮኣዊ የሆኑትን ቅሎች በተገኙበት ሁኔታ ግልጋሎት ላይ ከማዋል በስተቀር እንለውጣቸው (እንቀይራቸው) ብለው ብዙም ሲጨነቁባቸው ኣይታዩም

ተገልጋይ የሆኑት የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት:: በሌላ በኩል ኣንዳንድ ቅሎችን በጨሌና በዛጎል እንዲሁም በጠፍር ጥብጣብ «ሳምሳ» እንዲያጌጡ ያደርጓቸዋል:: ከዚህ በላይ በኣጭሩ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የቅል እቃ መጀመሪያውኑ የሚዘጋጀው ለተፈለገው ግልጋሎት ጠቃሚ የሆነ ቅርጽ ኣለው የተባለ ቅል ሲገኝ ነው:: ከዚህ እውነታ በመነሳት በዚህ የጥናቱ ንኡስ ክፍል ኣምስት የቅል ቁሳቁሶችን እንመለከታለን:: እነዚህም «ቁሉ ኡነታ» (Quluu Unaataa) የማማገያ ቅል፣ «ቡቄ ቡና» (Buqqee buna) የቡና ማስቀመጫ ቅል፣ «ቁሉ ቡና» (Quluu buna) የቡና መጠጫ ቅል፣ «ጉቹማ» (Guchuma) የወተት መናጫ እና «ቁሉ ቢሻን ወይም ቁሉ ሰላታ» (Quluu bishaan yookan quluu salaataa) የውሀ ቅል ወይም የስግደት የሰላታ ቅል ናቸው:: ከዚህ በላይ በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሰረት ይቀርባሉ::

#### 4.4.2.1. ቁሉ ኡነታ (Quluu Unaataa) የማማገያ ቅል

የኣንድ ነገር ስያሜ በኣጋጣሚና ሆን ተብሎ ከልዩ ልዩ ነገሮች ጋር ለምሳሌ ከቅርጹ፣ ከሚሰጠው ኣገልግሎት ወይም በተፈጥሮ ካለው ባህሪ ወዘተ. በማያያዝ ሊሰጥ ይችላል:: በዚህም መሰረት «ቁሉ ኡነታ» የማማገያ ቅል የተባለው የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህላዊ እቃ ስሙን ያገኘው በሚሰጠው ኣገልግሎት መነሻነት ይመስላል:: ምክንያቱም በኦሮምኛ ቋንቋ «ኡና» (Unaa) ማለት ፉት ማለት ነው:: «ኡነቺሱ» (Unachiisuu) ማለትም ምግብን በፈሳሽ ማወራረድ ማለት ነው:: ከዚህ በመነሳት የማማገያ ፈሳሽ (ብዙውን ጊዜ ወተት) የምትይዘውን ቅል «ቁሉ ኡነታ» (Quluu Unaataa) የማማገያ ቅል ብለው ሰየሚት::

*ኣሰራር፡-* ኣንዲት ቅል በተፈጥሮ የተሰራች ብትሆንም፣ ለምትሰጠው ግልጋሎት ትመጥናለች የተባለች የቅል ኣይነት ትቆረጥና ውስጧን በመቦርቦር ያልተፈለገውን ፍሬ እና ሌሎች ኣላስፈላጊ ነገሮችን በማውጣት የማዘጋጀቱ ተግባር ኣንድ ይባላል:: በዚህም መሰረት በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ዘንድ የተለመደችው «ቁሉ ኡነታ» የማማገያ ቅል ኣጠር ብላ ድርፏጫ የሆነች (ኣጭርና ጎነ ሰፊ የሆነች) ነች:: በዚህ ጥናት ኣቅራቢ እይታ የገባችው «ቁሉ ኡነታ» የማማገያ ቅል ቁመት 17፣ የሆዷ መጠነ ዙሪያ 43፣ የኣፏ መጠነ ዙሪያ 15፣ ከኣፏ የመጨረሻ ጠርዝ ወደ ሰፊው ሆዷ ኣጠፍ እስከሚልበት ድረስ ያለው ርዝመት 6 ሳንቲሜትር ነው:: (የሁሉም ኣሀዞች መስፈሪያ ሳንቲሜትር ነው) ከዚህ በላይ የተዘረዘረው መጠን ገላጭ ኣሀዝ በኣጋጣሚ በተገኘችው «ቁሉ ኡነታ» የማማገያ ቅል ላይ የተገኘ እንጂ የሁልጊዜው የማማገያ ቅል መጠን ይኸው ነው ማለት ኣይደለም::

«ቁሉ ኡነታ» የማማገያ ቅል መስህብነት እንዲኖራት ከላይ ወደታች በጣሳ ቅርጽ የመጣውና የዋናው የሆዷ ኣካል ከሚጀመርበት መጋጠሚያ ጀምሮ የጠፍር ጥብጣቦች (Straps) ይታበቱባታል:: የጠፍር ጥብጣቡ «ሳምሳ»ው ኣሰፋፍ መጀመሪያ ሰፋ ያለ ጠፍር (1.5 ሳንቲሜትር ስፋት ያለው) በመጋጠሚያው ዙሪያ እንደመቀነት ይያያዛል::

ቀጥሎም ሌሎች በቀጫጭኑ የተተለተሉ የጠፍር ጥብጣቦች መንታ-መንታ ወይም ሶስት እጥፍ እየሆኑ ኣንዳንዴም ኣንድ ጠፍር ብቻ እየሆነ መነሻቸውን እንደመቀነት በታበተው የጠፍር ጥብጣብ «ሳምሳ» ላይ በማድረግ ወደታች ይንዠረገጋሉ:: ይሁን እንጂ በጮጮ ወይም በማለቢያ ላይ እንደሚታበቱት ጥብጣቦች ብዛት የላቸውም:: ኣንዳንድ የማማጊያ ቅሎች በጨሌና በዛጎል የሚዋቡም ቢሆኑ (በፎቶግራፍ 16 ላይ ልጅቱ እያስተዋወቀች ያለችውን ማየት ይቻላል) በሌላ በኩል ኣንዳንድ የማማጊያ ቅሎች በጨሌና በዛጎል ላይዋቡ ይችላሉ:: ፎቶግራፍ 18ን ከግራ ወደ ቀኝ በ3ኛው ረድፍ ላይ ያለችውን ያጤኗል:: «ቁሉ ኡነታ» የማማጊያ ቅል ኣልፎ ኣልፎ በፎቶግራፍ 18 ላይ እንደሚታየው የኣፏ ዙሪያ ለእጅ መያዣነት በሚያመች ሁኔታ ዙሪያውን በስንደዶ ስፌት ይሰፋበታል::



*ፎቶግራፍ 18:- ለተለያየ ኣገልግሎት የሚውሉ የቅል ስሪት የሆኑ ቁሳቁስ::*

የቅል ኣዘገጃጀት ለሁሉም የቅል እቃዎች ተመሳሳይ በመሆኑ ባለሙያዋ ወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም የሰጡትን መግለጫ ማንበብ ይቻላል:: ወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም የት ተገኙ? የዚህ ጥናት ኣቅራቢ ጎባ ወረዳን በስተደቡብ ወደሚያዋስነው መና ኣንጌቱ ወረዳ በሄደበት ጊዜ የተለያየ ቅርጽ ያላቸው ቅሎች ወተትና ቅቤ ሲሸጥባቸው በማየቱ በዚያው ገበያ ውስጥ የቅልን ኣዘገጃጀት ጠይቆ ነበር:: ወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም በጎባ ወረዳ የሪራ ነዋሪ ይሁኑ እንጂ በኣንጌቱ ከተማ በገበያ ውስጥ ወተት በመሸጥ ላይ እያሉ ከተናገሩት የቅል ኣዘገጃጀት የሚከተለው ይገኝበታል::

> *ቅል የተክል ዘር ሲሆን በጥቅም ላይ እስከሚውል ከ4 እስከ 5 ወራት ይቆያል:: ከዚህ በሁዋላ ኣገልግሎት ላይ ለማዋል በመጀመሪያ ተፈላጊውን ቅል ከኣናቱ መቁረጥ፣ ከዚያም በቀጭን ዘንግ እየፈቀፈቁ ፍሬውን ማውጣት:: ቀሪውን ፍሬ ለማውጣት ኣመድ ወይም ኣፈር ከውሀ ጋር ቀላቅሎ ለኣንድ ሳምንት ማስቀመጥ:: ይህ ሁሉ ከመደረጉ በፊት ግን ቅሉ የጎመራ ወይም የበሰለ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል:: የውሀና የኣመድ ቅልቅሉን የያዘውን ቅል ኣፉን በእበት ኣፍኖ በከብቶች ፍግ ውስጥ*

*ማስቀመጥ:: በእበት የሚታፈነው በውስጡ ያለው እንዲብላላ እና የውስጡን ፍቅፋቂ እንዲያስለቅቅ ነው:: ይህ ሁሉ ከተወገደ በሁዋላ የላይኛው ኣካሉ እንዲያብረቀርቅ እና እንዲለሰልስ የሾላ ዛፍ ልጥ ይጨቀጨቅና (ይወቀጥና) በውሀ ተደርጎ በእሳት ላይ ይጣዳል:: ቅሉም በተጣደው ውሀ ውስጥ ይቀመጣል:: የቅሉ ውስጠኛ ክፍል የበለጠ እንዲጠራም የሞቀው ውሀ ይጨመርበታል:: የውስጥና የውጭ ኣካሉ በደንብ ከጸዳ በሁዋላ በወይራ ይቆራሻል:: የቅሉ ኣፍ ዙሪያውን በለሰለሰና በቀጭን ጠፍር ይሰፋል:: ቅሉ ወስፌ እንዲቀበል በውሀ መራስ ኣለበት:: በወስፌ የወጣውን ቀዳዳ እየተከተሉ የለሰለሰውን ቀጭን ቆዳ በቅሉ ኣፍ ዙሪያ በጅማት ወይም በችንጋ መስፋት ነው:: ይህ ስፌት ለቅሉ ጥንካሬና ውበት ይሰጠዋል:: ከዚያ በሁዋላ ለኣገልግሎት ብቁ ይሆናል::*

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የቅል እቃ ኣዘገጃጀት በወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም የተነገረው ሲሆን፣ ቅሉ ውበት እንዲኖረው ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ያለውን ኣሰራር በተመለከተ ደግሞ የኣንጌቱ ከተማ ነዋሪ እና የኣንጌቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር የሆኑት ኣቶ ኣብዱርቃድር ኣቡበከር የሚከተለውን ይናገራሉ::

*የስምንት ቁጥር ቅርጽ ያለው ቅል ተመርጦ ይዘጋጃል:: ለጌጥ ሲባል የጠፍር ጥብጣብ (Straps) ዙሪያውን በኣራት መንታ እስከ 8 ቁጥር ቅርጽ እስካለበት (እስከ ወገቡ) ድረስ ይታበታል:: ጥብጣቡ ኣንዳንዴም ከወገቡ ወረድ ይላል:: ከዚያም እነዚሁ ጥብጣቦች እያንዳንዳቸው በ4 እና 5 ሽንሽን ተሸንሽነው መሬት እስከሚነኩ ድረስ ይንጠለጠላሉ:: የቅሉ እቃ መሬት በሚቀመጥበት ጊዜ ሽንሽን ጠፍሮቹ መሬቱን ያለብሱታል:: ከላይ ሰፋፊ ሆኖ እና ከታች ደግሞ ቀጫጭን ሆኖ በወረደው ጠፍር ላይ ዛጎሎች በተርታ ይታበቱበታል:: የሚታበቱትም በችንጋ እየተሰፉ ሊሆን ይችላል:: ጥንት ግን በ«ጺዬ» (Dhiyee) በተባለ ቀጭን ጠፍር ነበር የሚታበቱት:: ከላይ የመጡ የጠፍር ጥብጣቦች የቅሉ መካከለኛ ኣካል (8 ቁጥር ቅርጽ ላይ) ሲደርሱ በጠፍር ጥብጣብ መቀነት ይደረግላቸዋል:: በሌላ በኩል የጠፍሩ ጥብጣብ የቅሉን ኩሬ (መክደኛ) አቅፎ እንዲይዝ ስለሚፈለግና በእጅ ለማንጠልጠልም ሲባል ረዥምም ነው:: ክዳኑና ዋናው ቅል መጋጠሚያ ላይ በተለይ የእናት ቅሏ ኣፍ ዙሪያውን «ከላላ» (Kalaalaa) በተባለ ከስንደዶ የተሻለ እና ሀረግ በሚመስል ጠንካራ መስፊያ ይሰፋል:: «ከላላ»ው እንደ ኣለላ ቀለም ባይኖረውም ጠንካራ ነው:: የማለቢያ ጩጬ ክዳንም ይሰፋበታል:: ብዙውን ጊዜ ከላላውን የሚጠቀሙበት ሁለቱ ማለትም ክዳኑና ዋናው ቅል በሚጋጠሙበት ዙሪያ ጠርዝ ላይ በመስፋት ነው::*

የጠፍር ጥብጣቦቹ ውበት ከመስጠት ባሻገር ያላቸው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንዲገልጹልኝ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ኣቶ ኣብዱርቃድር ኣቡበከር የሚከተለውን መልሰዋል::

*ቀደም ሲል እንደገለጽኩልህ የጠፍር ጥብጣቦች ዋናው ኣገልግሎት ለባህላዊው እቃ ውበት መስጠት ነው:: ከዚህ ሌላ በኦሮሞ የባህል እቃዎች ላይ የጠፍር ጥብጣብ ማበት የተለመደ በመሆኑ የብሄረሰቡን ባህል ማንጸባረቂያም ነው:: በተጨማሪም የጥፍር ጥብጣቦቹ ልዩ ልዩ ቀለማት ያሏቸውን ጨሌዎችና ዛጎሎች በቀጫጭን የጠፍር ጥብጣቦች ወይም በችንጋ ለማሰር (ለመስፋት) ስለሚያገለግሉ እና ጨሌዎቹም ለእቃው የውበት ምንጭ በመሆናቸው የጥብጣቦቹ ኣስፈላጊነት ከዚህም ኣንጻር ይለካል::*

ይህ ከዚህ በላይ የቅሎች አዘገጃጀትና በኣንዳንዶቹም ላይ የጠፍር ጥብጣብ «ሳምሳ» ኣጠቃቀምና ኣጊያጥ ለቅሎች ሁሉ እውነት ይመስላል::

*ኣገልግሎት፡-* «ቁሉ ኡነታ» (Quluu Unaataa) የማማጊያ ቅል ኣባወራው (የቤቱ ባለቤት) ምግብ ሲመገብ ወይም እንግዶች እንዲያምጉባት (በውስጧ ባለው ወተት ምግብ እንዲያወራርዱባት) ወይም ሌሎችም ሰዎች እንዲያምጉባት በክብር የምትቀመጥ የወግ እና የባህል እቃ ነች:: ከዚህ በተጨማሪም የጌጥ እቃ ሆና ቤት ታደምቃለች::

### 4.4.2.2. ቡቄ ቡና (Buqqee Buna) የቡና ማስቀመጫ ቅል

«ቡቄ ቡና» የቡና ማስቀመጫ ቅል በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ግልጋሎት ላይ ከሚውሉ የቅል ስራት ከሆኑት እቃዎች ኣንዷ ነች::

*ኣሰራር፡-* «ቡቄ ቡና» በተፈጥሮ የምትገኝ ቅል በመሆኗ የምትዘጋጀው ከዚህ በላይ በወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም በተገለጸው መሰረት ነው:: ለ«ቡቄ ቡና» የምትመረጠው ቅል ከወደ መቀመጫዋ ሰፋ ብላ ወደ ኣፏ መዳረሻ ላይ ሾጠጥ የምትልና ኣፈጠባብም ነች:: ብዙውን ጊዜ ታስቦ የሚሰራላት ክዳን የላትም:: ክዳን እንዲኖራት ከተፈለገም የበቆሎ ቆረቆንዳ ወይም የተጠቀለለ ጨርቅና ፌስታል ይጠቀማሉ:: ምንም ኣይነት የጨሌና የዛጎል ጌጦች የሏትም:: «ቡቄ ቡና» የቡና ማስቀመጫ ቅሎች በፎቶግራፍ 15 ላይ በጀበናው ግራና ቀኝ የተቀመጡት ናቸው::

*ኣገልግሎት፡-* «ቡቄ ቡና» (Buqqee Buna) ብዙውን ጊዜ ተቆልቶ የተወቀጠ የቡና ዱቄት ትይዛለች:: ኣንዳንዴም ቅሽሩን ወይም ድፍኑን ቡና ሊያስቀምጡባት እንደሚችሉና ስሟንም ያገኘችው ከምትሰጠው ግልጋሎት መሆኑን የባህሉ ባለቤት የሆኑት ኣቶ በቀለ ቱፋ ያስረዳሉ::

### 4.4.2.3. ቁሉ ቡና (Quluu Buna) የቡና መጠጫ ቅል

«ቁሉ ቡና» (የቡና መጠጫ ቅል) ከተፈጥሮ ከበቀለው የቅል ተክል የተገኘ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት የረጅም ጊዜ ባህላዊ እቃ ነው::

*ኣሰራር፡-* «ቁሉ ቡና» (የቡና መጠጫ ቅል) መጠኑ ይለያይ እንጂ ቅርጹ በኣብዛኛው የ8 ቁጥርን ይመስላል:: በዚህም መሰረት ከስር ደርፏጫ (ኣጭርና ጎነ ሰፊ) ሆኖ ከመካከሉ ላይ እንደስምንት ቁጥር ገባ ያለ ቅርጽ ይኖረዋል:: ይህ ገባ ያለው ቅርጹ መያገም በመሆን ያገለግላል:: ከመጨበጫው (ከመያገሙ) በላይ የታችኛውን ደርፏጫውን ኣካሉን የመሰለ ኣጭርና ጎነ ሰፊ የሆነ ቅርጽ ኣለው:: ከላይና ከታች ያለው ደርፏጫ ኣካሉ ብዙ ፈሳሽ እንዲይዝ ይረዳዋል:: የቡና መጠጫ ቅል በተፈጥሮ ለዚሁ ተግባር ይጠቅማል የሚባል ቅል ተመርጦ ነው ግልጋሎት ላይ የሚውለው:: ቅሉ ለኣገልገሎት እስከሚበቃ

ድረስ ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑት ቅሉን የማጽዳት ተግባራት ቀደም ሲል ወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም ስለ ቅል ኣዘገጃጀት የሰጡትን መግለጫ ያጤኗል:: «ቁሉ ቡና» ቡና መጠጫ ቅል ትንሽ፣ መካከለኛና ከፍተኛ መጠን ኣለው:: የዚህ ጥናት ኣቅራቢ በምልከታው ወቅት ትንሹንና ትልቁን ለማየት እድል ኣግኝቷል :: በዚህም መሰረት ትንሹ «ቁሉ ቡና» ቁመት 11፣ የደርፏጫው ክፍሉ መጠነ ዙሪያ 15፣ የኣፉ መጠነ ዙሪያ 21.5፣ የሆዱ መጠነ ዙሪያ 33 ሳንቲሜትር መሆኑን በመለካት ለማረጋገጥ ተችሏል:: ይሁን እንጂ መጠናቸው እንደፈላጊዎቻቸውና እንደቅሉ ተፈጥሮ ሊለያይ ይችላል:: በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህል «ቁሉ ቡና»ው (የቡና መጠጫው) ለህጻናት፣ በመካከለኛና በከፍተኛ እድሜ እርከን ላይ ለሚገኙ የብሄረሰቡ ኣባላት የየራሳቸው መጠጫ ኣላቸው::

*ኣገለግሎት:-* «ቁሉ ቡና» የቡና መጠጫ ቅል እንደመጠሪያ ስሙ ሁሉ ቡና ይጠጡበታል:: ይሁን እንጂ እንደ ወተት እና ብርዝ የመሳሰሉ ፈሳሾችንም እንደሚጠጡበት ይታወቃል::

*ባህላዊ ፋይዳ :* የወተት ቡናና ኦሮሞዎች የጠበቀ ግንኙነት ኣላቸው:: ኣንድ ኣባወራ የራሱ የሆነ መጠጫ «ቁሉ ቡና» ኣለው:: በ«ቁሉ ቡና»ው የቀረበለትን የወተት ቡና እየጠጣ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከቤተሰቡ ጋር ወይም ከጎረቤት ወይም ከደራሽ እንግዳ ጋር ባህላዊ ወግ እየተጫወቱ የሚጠጡበት ስርኣታዊ ክዋኔ የ«ቁሉ ቡና»ን ባህላዊ ፋይዳ ያመለክታል:: በዚህ ኣይነት የወተት ቡናና «ቁሉ ቡና»፣ ቁሉ ቡናና ኦሮሞዎች ሳይነጣጠሉ የቆዩ በተለይ እንደኣሁኑ ዘመናዊ ስኒዎችና ብርጭቆዎች ከመምጣታቸው በፊት ሲያገለግሉ የነበሩ ዛሬም ኣልፎ ኣልፎ በየገጠሩ የሚያገለግሉ ናቸው::

#### 4.4.2.4. ጉቹማ (Guchuma)

የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህላዊ የቅል ውጤት ከሆኑት እቃዎች ውስጥ ጉቹማ «Guchuma» (ኣንዳንድ ኣካባቢም «Waacaa») የሚሉት ኣንዱ ነው:: ጉቹማ ወይም ዋጫ በፎቶግራፍ 18 ላይ ከሚታዩት የቅል እቃዎች ሁሉ ረዥሙ ነው:: ኣሰራሩም ከሌሎቹ ይለያል:: በመጀመሪያ ደረጃ ለኣገልግሎቱ ሲባል ተፈላጊውን ቅርጽ የያዘ ቅል ይፈለጋል:: ይህ የእቃ ኣይነት ከወገቡ ጀምሮ እስከታችኛው መጨረሻ ኣካሉ ድረስ ከቅል መዘጋጀት እና ሰፊ መሆን ኣለበት:: ከኣቶ ኣለሙ ወርቁ በተሰጠኝ መረጃ መሰረት ከወገቡ ጀምሮ እስከ ኣፉ መጨረሻ ድረስ የስንደዶ ስፌት የሆነ ኣካል ይገጠምለታል:: ኣገጣጠሙ ስንደዶውን ከጠርዙ መጨረሻ ትንሽ ወረድ ኣድርጎ በመስፋት ይጀምርና ወደ ላይ እያደገ ይሄዳል:: ለኣፉ መክደኛ «ኩሬ» (ክዳን) ከስንደዶ ስፌት ይዘጋጅለታል:: ከትንሽነቱ በስተቀር በቅርጹ «ባሬ» (Baarree) የሚባለውን ባህላዊ እቃ ይመስላል:: «ባሬ» ማለት ለወተት መናጫ የሚያገለግል ኣንዳንድ ኣካባቢ ሙሉ በሙሉ ከስንደዶ ስፌት፣ ሌላ ኣካባቢ ደግሞ ከወገቡ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ቅል የሆነና ቅሉም ሰፋት ያለው ኣይነት እቃ ነው:: ጉቹማ «Guchuma» በፎቶ 18 ላይ እንደሚታየው የቆዳ

(የለሰለሰ የጠፍር ጥብጣቦች) በዙሪያው በጌጥነት እንዲያገለግሉ ይታበቱበታል ወይም ይሰፋበታል። የጉቼማ ክዳን ረዘም ብሎ ከወደ ጫፉ ጠፍጣፋ የሆነ፣ በጨሌ የተከፈከፈ ነው። ክዳኑን እና ዋናውን ጉቼማ የሚያገናኝ የቀንድ ወይም የቅል ሲሊንደር (Cylinder) መሳይ ቅርጽ ተቆርጦ ይገባበታል በዚህም በቀላሉ ለመክፈት፣ ለመዝጋትና ለመያዝም ያገለግላል። በመስክ ጥናት ላይ በምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት የጉቼማ (Guchuma) ቁመት በአማካይ 29፣ ከዚህ ውስጥ የቅሉ ብቻ ርዝመት 15፣ የቅሉና ከስፌት የተሰራው መክደኛ መጋጠሚያ መጠነ ዙሪያ 35፣ የቅሉ የእጅ መጨበጫ መጠነ ዙሪያ 25፣ የቅሉ ዋናው የሆዱ መጠነ ዙሪያ 44፣ ከክዳኗ ጫፍ እስከምትከደንበት ድረስ ያለው ርዝመት 7፣ የክብ ሲሊንደሩ ርዝመት 3.5 ሳንቲሜትር መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህ ግን እንደ ቅሉ ትልቅነትና ትንሽነት ሊለዋወጥ የሚልች አህዝ ነው። (የተጠቀሱት አሀዞች በሙሉ መስፈሪያቸው ሳንቲሜትር ነው)።

*አገልግሎት፡-* የጉቼማ «Guchuma» እቃ አገልግሎት ለወተት መናጫና መያገ መሆን ነው። ወተቱ ሳይከመጥጥ እንዲቆይ ሲፈለግ የሚመረጠው ጉቼማ ነው። ለዚህም ሲባል በወይራ እንጨት ታጥኖና ተቆራሽቶ፣ ውስጡ በንጹህ ጨርቅ ተወልውሎ ይጸዳል።

*ባህላዊ ፋይዳ፡* አንዳንድ ጊዜ በርከት ያሉ እንግዶች በሚኖሩበት ወይም በሰርግ እና በደቦ ስራ ወቅት ወተት በ«ጉቼማ» (Guchuma) ከቀረበ በሁዋላ እየተቀዳ ለጠጪዎች ይሰጣል። በዚህ ሁኔታ ባህላዊው እቃ ሰፊ አገልግሎት ይሰጣል።

### 4.4.2.5. የውሀ ቅል ወይም የስግደት፣ የሰላታ ቅል (QULUU BISHAAN YOOKAN QULUU SALAATAA)

*አሰራር፡-* የቅል ስራት ከሆኑ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ባህላዊ እቃዎች ውስጥ የስግደት፣ የሰላታ ቅል «ቁሉ ሰላታ» «Quluu Salaataa» የሚባለው አንዱ ነው። «ቁሉ ሰላታ» የስግደት ቅል የሚሰራው መጀመሪያውኑ ለዚህ ያመቻል ተብሎ ከተገኘ የቅል አይነት ነው እንጂ ማንኛውም የተገኘ ቅል ሁሉ አይሆንም። በፎቶ 10 ላይ እንደሚታየው ከወደ መቀመጫው የብርሌ ቅርጽ ይዟል። በዚህም መሰረት ሆደ ሰፊ (ትልቅ እቃ ነው)። ወደ ላይ ከፍ ሲልም የብርሌ አንገት ቅርጽ ያለው በመሆኑ ለመያዝ ወይም ለማንጠልጠል እንዲረዳ ገመድ ማሰሪያ የሚሆን ገባ ያለ እጀታ አለው። ቀጥሎም ትንሽ ሰፋ ያለ ይሆንና ከወደመጨረሻው (ከወደ ጫፉ) ጠበብ እና ሾል እያለ ይዘልቅና ያበቃል። አፉ ጠባብ መሆኑንም ልብ ማለት ያሻል። ቅሉ በተፈጥሮ እንደመገኘቱ ሁሉ አዘገጃጀቱ ከዚህ ቀደም በሌሎች የቅል ስራት በሆኑ እቃዎች ላይ ያለው አይነት ነው።

*አገልግሎት:-* «ቁሉ ሰላታ» (Quluu Salaataa) የሚባለው የእቃ አይነት ሙዳ[8] (Muuda) የሚሄዱ የእምነቱ ተከታዮች ውሀ የሚይዙበት ነው:: ውሀውንም ስግደት ከመጀመራቸው በፊት እጃቸውንና እግራቸውን በመታጠብ ንጽህናቸውን ይጠብቁበታል:: ሲጠማቸውም ሊጠጡት ይችላሉ:: ገባ ያለው የቁሉው ኣንገት ላይ ገመድ ከታበተበት በሁዋላ ተጠቃሚው ግለሰብ በኣንገቱ ኣስገብቶ በጎኑ በኩል ያንጠለጥለዋል ወይም በዱላ ላይ ያስርና በትክሻው ይይዘዋል::

በሌላም በኩል የሰላታ (የስግደት) ቁሉ ሙስሊም የብሄረሰቡ ኣባላት ለስግደት የሚሆን የመተጣጠቢያ ውሀ በቤት እና ከቤት ውጭ ይዘውበት ይሄዳሉ:: የስግደት ቁሉ ኣፍ እጅግ ጠባብና በመጠኑም (በይዘቱ) ከቡና ቁሉ የሚበልጥ ነው:: የቁሉው ኣንገት ገባ የማለቱ (ስምንት ቁጥር ቅርጽ የመስራቱ) ሌላው ጥቅምም ኣንገቱን በእጅ ይዞ ለማስታጠብና ለመታጠብም መርዳቱ ነው::

*ባህላዊ ፋይዳ:-* የ«ቁሉ ሰላታ» ባህላዊ ፋይዳ በተለይ ከሀይማኖታዊ ስርኣት ጋር የተያያዘ ነው:: ሀጂ ፈቂ ሀሰኖ ይህንን በተመለከተ ተከታዩን ሀሳብ ይሰነዝራሉ::

> *ዛሬ ዛሬ የቧንቧ ውሀ በየትኛውም ቦታ እንደልብ በመግባቱ ግልጋሎቱ እየቀነሰ መጣ እንጂ የ«ቁሉ ሰላታ» እቃ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነበር:: ኣንድ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ውሀ ይዞበት ወደ መስጊድ ከገባ በሁዋላ ከመስገዱ በፊት ንጽህናውን ለመጠበቅ የሚጠቀመው ከ«ቁሉ ሰላታ» ከሚያገኘው ውሀ ነበር:: የሀይማኖቱ ተከታዮች ወደ መንገድ ሲሄዱም የ«ቁሉ ሰላታ»ን እቃ ገባ ካለው ቅርጹ ላይ በገመድ ካሰሩ በሁዋላ በትከሻቸው ያንጠለጥሉታል:: በማንኛውም ቦታ በተለይም ወንዝ በኣቅራቢያው በማይገኝበት ስፍራ ለስግደት ሲዘጋጁ ኣስቀድመው ንጽህናቸውን የሚጠብቁት በ«ቁሉ ሰላታ» ከያዙት ውሀ እየቀዱ ነው:: ከዚህም በላይ ሲጠማቸው የሚጎነጩትን ውሀ የሚያገኙት ከዚሁ እቃ ነው:: በተለይ በቆላማው የጎባ ወረዳ ኣካባቢ የሚገኙ የኦሮሞ እስላሞች «ቁሉ ሰላታ»ን ይጠቀማሉ:: የውሀ ስንቅ መያዣ ከመሆን ጋር የሚሰጠው ተጨማሪ ግልጋሎቱ የ«ቁሉ ሰላታ»ን ባህላዊ ኣጠቃቀም ያንጸባርቃል::*

## 4.5. የስፌት እቃዎች

በዚህ የጥናቱ ንኡስ ክፍል ተተኳሪ የሆኑት «ኤለምቱ»፣ «ጨኢጮ» ወይም «ጬጮ»፣ «ጡንጦ»፣ «ባሬ»፣ «ኮቦ»፣ «ሌማት» እና «ቡሬ» በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ቁሳቁሶች በዚሁ ቅደም ተከተል መሰረት ይቀርባሉ::

---

[8] *ሙዳ - ሙዳ (Muuda) ማለት የእምነቱ ተከታይ የሆኑ የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት ወደ ባሌው ሼክ ሁሴን፣ ወደ ኣዮ ሞሚና፣ ሶፍ ኡመር ወዘተ. በመሄድ የሚለማመኑበት ከዋቅ (ኣምላክ) ጋር እንገናኝበታለን ብለው የሚያስቡበት የጉዞ ስርዓት ነው::*

## 4.5.1. ትውራዊ ዳራ

የስፌት ስራ ቀደምትነት ካላቸው የእደጥበብ ውጤቶች አንዱ ነው:: ይህ የሴቶች ብቻ የሆነው ባህላዊ ተግባር የሴቶች የሙያ ደረጃ መለኪያም እንደሆነ ሲነገር ቆይቷል:: «የስፌት ስራ በጣም አስፈላጊ፣ በስፋት የሚሰራበትና ሲሰራበትም የቆየ የሴቶች የስራ ውጤት ነው» ሪቻርድ ፓንክረስት (Richard Pankhrust 1964፣ 234):: እንደ ሪቻርድ ፓንክረስት አገላለጽ የእንቅብ፣ የሌማት፣ የመሶብ፣ የአገልግል፣ የወንፊት እና የመሳሰሉት የስፌት ስራዎች ባህላዊ የአማራው ብሄረሰብ የስራ ውጤቶች ይሁኑ እንጂ የሁዋላ ሁዋላ ሌሎች ብሄረሰቦችም ሲሰፏቸውና ሲጠቀሙባቸው ኖረዋል፤ አሁንም እየተገበሩት ነው:: «የስፌት ስራ ጠንካራና መሰረታዊ የሆኑ ስንደዶች እየተሰባጠሩ የሚሰሩበት ቴክኒካዊ ስራ ሲሆን ዝርግ እና ለልዩ ልዩ ነገሮች መያገ የሚሆኑ እቃዎች የሚሰሩበት የእደጥበብ ውጤት ነው» ስፔር ኤፍ ጂ ሮበርት (Spier F.G. Robert 1970፣ 71)::

ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን የጎባ ወረዳ ነዋሪ እና በስፌት ስራ ኣንቱ የተባሉ ናቸው:: እሳቸው እንደሚናገሩት የስፌት ሙያን መስራት የጀመሩት ለኣቅመሄዋን ከመድረሳቸው ጥቂት ቀደም ብለው ሲሆን በኣሁኑ ጊዜ የ64 ኣመት ሴት ቢሆኑም መስፋታቸውን ኣላቆሙም:: የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች የስፌት ስራን መቼ እንደጀመሩ የሚያቁት ነገር ካለ ኣልኳቸው::

> *በርግጥ መቼ እንደጀመሩ ታሪክን ጠቅሼ የምናገረው ነገር ባይኖረኝም እኛ ልጆች ሆነን እናቶቻችን ሲሰፉ እናይ ነበር:: ያን ጊዜ ታዲያ እንደኣሁኑ በኣለላና በክር መስፋት ኣይታወቅም ነበርና ሁሉም ሴቶች ይሰፉ የነበረው በስንደዶ ብቻ ነበር:: ኣሁን ግን ተሻሽሎ በሀረግ፣ በኣለላ፣ በክር ሁሉ መስፋት ተለመደ:: በዚህ በደጋው ኣገር ባይለመድም በቆላማ ኣካባቢዎች በዘንባባም ይሰፋል:: የምንሰፋው የስፌት ኣይነት የኮከብ፣ ዚግዛግ፣ የሶስት ቅርጽ ሁሉ ነበር:: ስንደዶና ወስፌ ዋና የስፌት ስራ መሳሪያዎቻችን ናቸው:: ከዚህም በላይ የስፌት እቃዎቻችንን ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ጨሌዎችና ዛጎሎችም ማስጌጥ እየተለመደ መጣ:: መጀመሪያ ግን ኣሁን በጠቀስኩልህ ማስጌጫዎች ኣንገታቸውና ግንባራቸው ላይ እያደረጉ የሚዋቡባቸው ሴቶች ብቻ ነበሩ:: የሁዋላ ሁዋላ ግን የስፌት እቃዎችንም ማስጌጥ ተጀመረ:: እኔ በበኩሌ የስፌትን ሙያ፣ ኣያያዝን፣ የስንደዶ ኣጠማዘዝን፣ በወስፌ እንዴት እንደሚወጋ የለመድኩት ከእናቴ ነው:: እኔ በእድሜዬ እስከማውቀውም የስፌትን ስራ የሚያከናውኑት ሴቶች ብቻ ናቸው::*

የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ኣኗኗር በእጅጉ የተቆራኘው ከከብት ጋር በመሆኑና ከከብቶች የሚያገኟቸውን ወተት እና የወተት ተዋጽኦዎችን ለማስቀመጥ ባደረጉት ጥረት ቀስ በቀስ የስፌት ስራን እያስፋፉ እንደመጡ ይነገራል:: በተለይ ስራውን ለመጀመር ምክንያት የሆናቸው የወፎች የጎጆ ኣሰራርም እንደሆነ በመላምት ከሚነገሩት ኣፈታሪኮች ማገናዘብ ይቻላል:: ይህን በቅርበት ለማየት የረዳቸው ደግሞ ከብቶችን በጫካ ኣካባቢ

ባለው የሳር ግጦሽ ላይ ሲያስማሩ በየዛፉ ላይ ከሚያዩት የወፍ ጎጆ ነው። የወፍ ጎጆ አሰራር ጥልፍልፍ በመሆኑ ያንን ያየ የመጀመሪያው ሰው ያየውን ለሚስቱ ነገራትና እሷ እየሞከረችው ቀስ በቀስም ስራውን እየተካነችበት መጣች በማለት የሚነገሩ አፈታሪኮች ቢኖሩም፣ ለዚህ በሰነድ የተደገፈ እውነተኛ የታሪክ ማረጋገጫ ኣላጋጠመኝም።

የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ለልጆቻቸው የሚሰጡትን ፍቅር ያህል ለከብቶቻቸው ይሰጣሉ፤ ለከብቶቻቸው የሚሰጡትን ክብር ያህል ደግሞ ለወተት መያዣ እቃዎቻቸው ያበረክታሉ። ይህ ኣብሯቸው የነበረ፣ ወደፊትም በዚሁ መልኩ ኣብሮ የሚኖር ባህላቸው ይመስላል። የልዩ ልዩ በኣላት፣ የሀይማኖት ስርኣት፣ የሰርግና የተዝካር ማስተናገጃ እና ማድመቂያ የሆኑ የወተት መያዣ ባህላዊ እቃዎቻቸውን በክብር የሚይዙትም፣ የሚያስጌጧቸውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል። «የስፌት ስራ በኣለም ህብረተሰብ ዘንድ ሁሉ ጥንታዊነት ያለው ስራ ነው፤ ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የስፌት ስራ የራሱ የሆነ ልዩ የኣሰራር ጥበብ ያለው በመሆኑም ሁሉም ተመሳሳይና ኣንድ ኣይነት የሆነ ግምት የለውም በጥበቡ ላይ» ሲልቨርማን (Silverman 1999፣ 51)። እንደ ሸክላ ስራ ውጤቶች ሁሉ የስፌት ስራ የሆኑ ቁሳቁስ በየሰው ቤት ሁልጊዜም መጠቀሚያዎች ናቸው። ኣህመድ ዘካሪያ (Ahmed Zekaria) «Harari Basketry Through the Eyes of Amina Ismael Sherif» በሚለው ጽሁፋቸው «የስፌት ስራ የሴቶች መታወቂያ እና የእነሱ ስራ እንደሆነ የሁልጊዜም መጠቀሚያ ... ነው» (1999፣51) ሲሉ ገልጸዋል። የኦሮሞዎችን ባህል የሚያንጸባርቁ የስፌት እቃዎችን በተከታዮቹ ቁጥር 19 እና 20 ፎቶግራፎች መመልከት ይቻላል።

ተፈላጊውን የስፌት እቃ ከግቡ ለማድረስ ስንደዶ ዋናው ጥሬ እቃ ነው። ከስንደዶው ሰበዝ ጋር እንደኣስፈላጊነታቸው በተለያዩ ቀለሞች የተነከሩ (የቀለሙ) ኣለላዎች ይኖራሉ። ወስፌና ውሀም የስፌቱን እቃ ለመስራት ኣስፈላጊ ናቸው። ኣሁን ኣሁን ደግሞ የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ክሮች በስንደዶው ሰበዝ ላይ በማዞር መስፋትም ተጀምሯል። እንደነዚህ ኣይነቶች የስፌት ስራዎች ለጌጣቸው ሲባል ተፈላጊ በመሆናቸው በኣንዳንድ ቤቶች ግድግዳ ላይ ይሰቀላሉ። ይህ ኣይነቱ ስራ ምንም እንኳን በኣማራው ህብረተሰብ ዘንድ የተዘወተረም ቢሆን በተለይ በከተማ የሚገኙ የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላትም ቤታቸውን ያስጌጡበታል። በዚህም ምክንያት የስፌት ስራ ለጥቅሙ፣ ቤትን ለማስዋብና ለኣይን ማራኪነቱ እንዲሁም ልዩ የሴቶች መለያ ሆኖ ያገለግላል ማለት ነው።

የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ከስፌት የተሰሩ የወተት እና የቅቤ መያዣዎቻቸው ላይ ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ጨሌዎችና ዛጎሎችን በረድፍ በረድፍ ይደረድሩባቸዋል። የፍየልና የከብት ቆዳ በማልፋትና በማለስለስ በቀጭኑ እየተለተሉ የጠፍር ጥብጣቦቹን ከእቃዎቹ

መቀመጫ እስከሚተርፉ ድረስ ያንጠለጥሉባቸዋል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ለእቃዎቹ ካላቸው አክብሮት በመነጨ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የተዘጋጁ እቃዎችም መስህብነት ይኖራቸዋል፡፡ እንዲህ ያሉ ጡንጦዎች በተለይ ለኣባወራ ቀዝቃዛ ወተት ማስቀመጫ፣ ለተከበረ እንግዳ ወተት ማቅረቢያ፣ ለቡና የሚሆን ወተት መያዣ እና ልጅ ተድራ ስትሄድ በስጦታ መልክ የሚበረከቱ ናቸው፡፡ ቀጥሎ ኣንድ በኣንድ ለማየት እንሞክራለን፡፡

## 4.5.2. ኤሌምቱ (ELEMTUU) ማለቢያ

«ኤሌምቱ» ማለቢያ የተባለችው ባህላዊ እቃ ከምትሰጠው ኣገልግሎት ኣኳያ ስም የተሰጣት ይመስላል፡፡ «ኤሌምቱ» (Elemtuu) ማለቢያ ማለት ቃል በቃል ሲፈታ «ማለቢያ» ወተት የሚታለብበት እቃ ማለት ነውና፡፡ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ከፍተኛውን ክብር ከሚሰጧቸው የባህል እቃዎቻቸው ኣንዷ ነች፡፡ በኣብዛኛው ወተትና ኦሮሞዎች ኣይለያዩምና «ኤሌምቱ» ያልናት ማለቢያችን ስለሆነች ነው ይላሉ፡፡ የኤሌምቱን ኣሰፋፍ ወ/ሮ ራሂማ መህመድ ኣማን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

**ኣሰፋፍ (ኣሰራር)፡-**

*ሁለት ወይም ሶስት ሰበዞች እናመጣና በኣንደኛው ጫፍ ትንሽ ክብ ከሰራን በሁዋላ ሌላውን ጫፍ ሰበዙ ረጅም እንደሆነ እንተወዋለን፡፡ በሰራነው ቀለበት መሰል ጅምር ላይ የተሰነጠቀ ስንደዶ እናዞርበትና ቀለበቱ (ክቡ) እንዲጠነክር እናደርጋለን፡፡ ከዚያም በወስፌ እየወጋን በኣንድ ጫፍ የተውነውን ረጅም ሰበዝ እየተከተልን ኣክርማውን (የተሰነጠቀውን ስንደዶ) በላዩ ላይ እያዞርን ስፌታችንን እንቀጥላለን፡፡ ይህን ሁሉ ስናደርግ ሰበዙን ክብ እንደመስራት ሰበር እያደረግን እንጂ ዝም ብለን ዝርጉን ተከትለን ኣንጓዝም፡፡ እንደ ትንሽ የቀለበት ክብ ኣድርገን መጀመሪያ የጀመርናት «ውጢኒ» (Wixinee) ጅምር ትባላለች፡፡ «ውጢኒ» ማለትም የተወጠነ፣ የተጀመረ፣ ጅምር ማለት ነው፡፡ ይሁንና የስፌት ሂደቱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው የስፌት ሙያተኛን ይጠይቃል፡፡ የስፌት ስራችንን በቀጠልን ቁጥር ጅምር የነበረው እያደገ፣ እያደገ ይሄዳል፡፡ በዚያው የኣሰፋፍ ሂደት ከቀጠልን ዝርግ ሰፌድ ሊሆን ይችላል፡፡ የእኛ ኣላማ ግን «ኤሌምቱን» ማለቢያን መስፋት በመሆኑ ዝርግ እንደሆነ ትንሽ ካዞርን በሁዋላ ይበቃዋል የሚል ግምት ላይ ስንደርስ የ«ሀ» ቅርጽ እንዲይዝ ወደላይ ቀልበስ እያደረግን ስፌታችንን እንቀጥላለን፡፡ ኣሁን ወደ መቀመጫው ኣካባቢ ነውና ትንሽ ወደ ላይ ወጣ እስኪል ኣክርማውን ካዞርንበት በሁዋላ መሀል ወገቡ ላይ ሰፋ ማለት ስላለበት ወደ ጎንና ጎን እያለጠጥነው መስፋታችንን እንቀጥላለን፡፡ ወደ ኣፉ መዳረሻ ኣካባቢ ከመድረሳችን በፊትና ወገቡን ኣለፍ እንዳልን ሰብሰብ (ጠበብ) እያደረግን፣ ሰበዙንም ሳሳ እያደረግን እስከምናጠናቅቅ ድረስ እንሰፋለን፡፡ በዚህ ኣይነት የኣሰፋፍ ሂደታችን ወቅት ሰበዝ ያነሰ ሲመስለን ሌላ እንሳጋለን (እንሰካለን)፡፡ በድምዳሜው ኣካባቢ ሰበዙን እያሳሳን-እያሳሳን እንጓዝና የመጨረሻ ነው በምንለው ጠርዝ ላይ በኣክርማው ጥብቅ ኣድርገን በማያያዝ እንቋጥላለን፡፡ እስካሁን የገለጽኩልህ የኣሰፋፉን ሂደት ሲሆን ለስራው ሰበዝ[9]፣ ኣክርማ[10]፣ ወስፌ፣ ውሀ ተፈላጊዎች ናቸው፡፡ በመቀረጫው ኣካባቢ ከመድረሳችን በፊት ትንሽ ሲቀረን የምንሳጋው*

---

[9] ሰበዝ- የተሰነጠቀ ስንደዶና ኣክርማ በላዩ ላይ እየተጠመጠበት የሚሰፋና የሚያያዝ ያልተሰነጠቀ ስንደዶ፣ የስፌት ሳር

[10] ኣክርማ- የስንደዶ ውጤት የሆኑ እቃዎችን ለመስፋት የሚያገለግል የሳር ኣይነት

*(የምንሰካው) ሰበዝ ሳሳ ማለት ኣለበት ያልኩህ ኩሬዋ (መክደኛዋ) የምትገጥምበት ቦታ ስለሆነ መወፈር ስለሌለበት ነው። «ኤሌምቱ» ማለቢያዋ እንድታምር የምንፈልግ ከሆነም በቀለም የተነከሩ ኣለላዎች ሊያስፈልጉን ይችላሉ። ስለዚህ ኣለላው ማረፍ ኣለበት በምንለው ክልል ላይ እንደምንፈልገው የቅርጽ ኣይነት እያሰባጠርን እናስገባዋለን። ኣለላው ማረፍ የለበትም ለምንልበት ቦታ ላይ ግን ያንኑ ኣክርማ (ስንጥቅ ስንደዶ) እናዞርበታለን።*

የኤሌምቱዋን (የማለቢያዋን) ትልቅነትና ትንሽነት በምን እየለካችሁ ነው የምትሰሩት? ላልኳቸው ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን «በኣይነ ግምት እንጂ ምንም መለኪያ የለንም» በማለት መልስ ሰጥተዋል። ይሁንና የዚህ ጥናት ኣቅራቢ በእጃቸው ይዘዋት የነበረችውን ማለቢያ ለክቶ እንዳረጋገጠው ቁመት 21፣ የሆዷ መጠነ ዙሪያ 50፣ ከወደ ኣፏ ቁልቁል የሚመጣው ስፌትና የዋናው ሆዷ መጋጠሚያ መጠነ ዙሪያ 27፣ ከወገቧ እስከ እግሯ (መቆሚያዋ) የመጨረሻ ጠርዝ ድረስ ያለው ርዝመት 14፣ የኣፏ መጠነ ዙሪያ 30፣ የእግሯ ውጫዊ ዲያሜትር (ከኣንዱ ጠርዝ ወደ ሌላው ያለው ርቀት) 7፣ በክብ ቅርጽ እግሮቿ መካከል ላይ ያለውና ሲጀመር የሰፌድ ቅርጽ የያዘው ዝርግ (Surface area ው) ርዝመት 5፣ የኣፏ ዲያሜትር 8 ሳንቲሜትር መሆኑን ማጤን ተችሏል። (ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ኣሀዞች በሙሉ መለኪያቸው ሳንቲሜትር ነው)።

የስፌቱ ስራ ከተጠናቀቀ በሁዋላ ኣስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ጨሌዎችና በነጭ ዛጎሎች እንዲሁም በጠፍር ጥብጣቦች የማስጌጡ ተግባር ይቀጥላል። የማስጌጡን ስራ ግን ሁልጊዜ ሰፊቹ ሴቶች ላያከናውኑት ይችላሉ። ለምሳሌ ወ/ሮ ለይላ ኢብሮ ስፌቱን ካጠናቀቁ በሁዋላ የማስጌጡን ስራ ሌላ ሙያተኛ ቀጥረው እንደሚያሰሩና ጨሌዎቹንና ዛጎሎቹን ለሚሰካላቸውና የጠፍሩን ጥብጣብ «ሳምሳ»ውን ለሚያብትላቸው ለእያንዳንዳቸው ብር 10 እንደሚከፍሉ ኣረጋግጠውልኛል። ከዚህ በላይ የተገለጸው ሁለቱ ሙያተኞች የተናገሯቸው የ«ኤሌምቱ» (ማለቢያ) ኣሰፋፍ ሂደትን ሲሆን ቀጥሎ ከፎቶግራፍ ጋር የተገናዘበ መግለጫ ይሰጣል።



*ፎቶግራፍ 19፡- የስፌት ሙያተኛዋ ወይዘሮ ሌይላ ኢብሮ በመስፋት ላይ እያሉ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው*

የስፌቱ ስራ ከተጠናቀቀ በሁዋላ የማስጌጡ ስራ ይከናወናል:: ኦሮሞዎች ብዙ ጊዜ የወተት እቃዎቻቸውን ማስጌጥ የሚፈልጉት የተለያዩ ቀለም ባላቸው ጨሌዎች እና ዛጎሎች ነው:: ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው ጨሌዎቹና ዛጎሎቹ በቅደም ተከተል በቀጫጭን የለፉ የጠፍር ጥብጣብ ውስጥ ያልፋሉ:: ጨሌዎቹም በቿንጊያ እና በቀጫጭን ጠፍሮች እየተሰባጠሩ ይደረደራሉ::: በብዙ እቃዎቻቸው ላይ እንደሚታየው ጨሌዎቹ እና ዛጎሎቹ አይደባለቁም:: ለዚህ የባህሉ ባለቤቶች የሚሰጡት ምላሽ «ጨሌዎች በመጠን (በክብደት) አነስተኛ ስለሆኑና ዛጎሎቹ ደግሞ ትላልቆች ስለሆኑ አብረው ባንድ ተርታ ቢሰለፉ፣ ትላልቆቹ ዛጎሎች የትናንሾቹን ጨሌዎች ውበት ይደብቃሉ» ይላሉ:: ከዚህም በላይ ሁለቱን በተጣማሪነት ለመስፋትም አያመችም ባይ ናቸው:: በአብዛኛው ከጨሌ ይልቅ ዛጎልን ይጠቀማሉ:: በፎቶግራፍ 20 ከግራ ወደ ቀኝ በሁለተኛ ረድፍ ላይ ያለችውን ማለቢያ ማየት ይቻላል::

በፎቶው ላይ የምትታየው ኤሌምቱ «Elemtuu» (ማለቢያ) ዛጎሎቿ ከላይ ወደ ታች 3 ወይም 4 እየሆኑ በተርታ ተደርድረዋል:: በአንዱ ድርድርና በሌላው መካከል የተወሰነ ክፍት ቦታ ኣለ:: ዛጎሎቹ በጠፍሩ ጥብጣብ ላይ በቀጫጭን የጠፍር ክር የተያያዙ ናቸው:: ዛጎሎቹ የተሰፉባቸው ሰፋ ያሉት የጠፍር ጥብጣቦች ከየአቅጣጫው ከመጡ በሁዋላ ከኩሬዋ (ከክዳኗ) በላይ ከሚታየው ማንጠልጠያ ጋር ይገናኛሉ::: እነዚህ የጠፍር ጥብጣቦች ከመክደኛዋ ጋር የተሰፉም በመሆናቸው ክዳኗ እንዳትወድቅ ዘብ የቆሙ ናቸው::

ከታች ያለው ኣካሏ ሰፋ ብሎ መጥቶ ወገቧ ላይ ሲደርስ እስከ ማለቢያው ኣፍ ድረስ ጠበብ እያለ (ሰበር እያለ) ይቀጥላል ስፌቱ:: ይህ ልዩ ክህሎትን ይጠይቃል:: ችሎታን ይፈታተናልና ነው:: ሰበር ከሚልበት ኣካባቢ ጀምሮ እስከማብቂያው በቀጭን ስንደዶ ሰበዝነት የሚጎዝ ነው::: ስፌቱ ሰበር ካለበት ከወገቧ ጀምሮ ወደታች ኣለፍ ኣለፍ በማለት የታበቱ የጠፍር ጥብጣቦች መሬት በሚነኩበት ቁመት እየተሰባጠሩ ይታበታሉ:: (እነዚህ ጥብጣቦች መሬት የሚነኩት ማለቢያዋ መሬት ላይ ስትቀመጥ መሆኑን ያጤኗል)::

የኤሌምቱ «Elemtuu» (ማለቢያ) ኩሬ (መክደኛ) እንደ ማለቢያዋ ሁሉ ከስፌት ይዘጋጅ እንጂ መሀል ለመሀል የሚሰፋለት ከፍየል፣ ከድኩላ ወይም ከሚዳቋ የተገኘ ቀጭን እና ቀዳዳ ያለው ቀንድ ይገጠምለታል:: ቀንዱ አስቀድሞ መለስለስና ለዚሁ ተግባር በደንብ መዘጋጀት ኣለበት:: በዚህም መሰረት ቀዳዳው ይበሳል፣ ሻካራነቱንም ለማስቀረት ይላጋል:: ተፈላጊውም የቀንድ ኣይነት ቀጥ ያለ መሆን ኣለበት:: ቀንዱ ከኩሬዋ የመጨረሻ ኣናት ተረፍ ብሎ ወደ ላይ ከ5 እስከ 6 ሳንቲሜትር ሊረዝም ይችላል::

*ኣገልግሎት:-* «ኤሌምቱ» (Elemtuu) ማለቢያ ሁለት መሰረታዊ ኣገልግሎት ኣላት:: እነዚህም 1ኛ. ወተት ይታለብባታል 2ኛ. ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ወተት ማስቀመጫ ሆና

ታገለግላለች። የ«ኤሊምቱ» (ማለቢያ) ኩሬ (መክደኛ)፣ ክዳን በመሆን ከምትሰጠው ኣገለግሎት ባሻገር ብዙውን ጊዜ ልጆች ወተት ይጠጡባታል። እናቶች በሚያልቡበት ጊዜ ከባህላዊ ልምድ እንደሚታየው ጥጃ የሚይዝ ወይም እናቱ ስታልብ ከኣጠገቧ የማይለይ ህጻን በኩሬ (በመክደኛ) ወተት እዚያው (የሚታለብበት ቦታ) ይሰጠዋል። ህጻኑም የኩሬዋን ቀንድ ቀዳዳ በጣቱ ግጥም ኣድርጎ ይዞ በመጨለጥ ኩሬዋን ይመልሳል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኩሬዋ ላይ ያለው ቀጭንና ውስጡ ክፍት የሆነው ቀንድ ኣገልግሎት ጌጥ መሆን ብቻ ሳይሆን መክደኛዋ ሳትከፈት በቀዳዳው በኩል ለመጠጣትም ያስችላል። ኣልፍያ ሀጂ እንደነገረችኝ ከሆነ ደግሞ የቀንዱ ሌላው ተግባር ኣየር ወደ ወተቱ ማስገባት ነው። የሚገባው ኣየርም ወተቱ ቀዝቅዞ እንዲቀመጥ ኣስተዋጽኦ ያደርጋል። ማለቢያዋ ሁልጊዜም ለተግባሯ ኣዲስ ሆና መዘጋጀት ኣለባት። ኣዲስ የምትሆነውም በየጊዜው መልካም መኣዛ ባላቸው የወይራ እንጨቶች እየተቀራሸችና በንጹህ መወልወያ ጨርቅ እየተጠረገች ነው። ካልተቀራሸች የቆየ የወተት እርሾ ኣታጣምና ኣዲሱ ወተት ብዙም ሳይቆይ ሊረጋ ይችላል። ይህ ደግሞ ወተቱን ለተፈለገው ኣላማ እንዲውል ኣያደርገውም።

***ባህላዊ ፋይዳ፡-*** እንደ ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን ከሆነ የ«ኤሊምቱ» (ማለቢያ) ባህላዊ ፋይዳ ይበልጥ የሚታየው «ቡራቶ» የተባለውን የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህላዊ ምግብ በ«ገበታ» ተዘጋጅቶ በሚቀርብበት ወቅት የማወራረጃ ወተት ይዛ በመገኘቷ ነው።በተጨማሪም በሰርግ ቦታ፣ በስብሰባም ሆነ በህብረት ስራ ዘመቻ ላይም ወተት ይዘውባት ይሄዳሉ።

## 4.5.3. ጪጮ ወይም ጬጮ «CIICOO (CUUCOO)»

ከወተት እቃዎች ውስጥ ኣንዱ ነው። ጪጮን ለመስራት የሚያገለግለው ዋናው ጥሬ እቃ ስንደዶና የስንደዶ ውጤት የሆኑት ቀለም ንክር ኣለላዎች ናቸው። ኣሰራሩን በተመለከተ ከዚህ በላይ ለማለቢያ የተሰጠው ገለጻ እዚህም ላይ ይሰራል። ይሁን እንጂ በቅርጽ እና እቃውን በማደራጀት ደረጃ መጠነኛ ልዩነቶች ይታያሉ። ቀጥሎ ይህንን እናነባለን።

***ኣሰፋፍ (ኣሰራር)፡-*** ጪጮ ሲሰፋ ከታች ወጣ ያለ መሬት የሚይዝ መቀመጫ ይገጠምለታል። ይህም ጪጮውን በተፈለገ ቦታ ለማስቀመጥ ይረዳል። ከወደቂጡ ሰፋ ብሎ የ«ሀ» ቅርጽ በመያዝ እስከ ወገቡ ኣካባቢ ከተሰፋ በሁዋላ በመጠኑ የ8 ቁጥር ቅርጽ እንዲኖረው ይደረጋል። በመቀጠል ስፌቱ ወደላይ በረዘመ ቁጥር ወደ መክደኛው መጋጠሚያ እስከደረሰ ድረስ የነበረው የስምንት ቁጥር ቅርጽ እንደተጠበቀ ሆኖ በመጠኑ ሰፋ እያለ እስከ ክዳኑ መጋጠሚያ ይዘልቃል። መጋጠሚያው ኣካባቢ በመጠኑ ገባ ካለው የ8 ቁጥር ይልቅ ወጣ ያለ ቅርጽ ይኖረዋል። (ፎቶግራፍ 20ን ይመልከቱ)። መክደኛው በበኩሉ ከወደ ጫፉ ሾጠጥ ብሎ ከዋናው ጪጮ ጋር በሚጋጠምበት ኣካባቢ ሰፋ ይላል።

(መክደኛው ሰፋ ብሎ የተሰፋበትን ቅርጽ ሳይለቅ ከዋናው ጪጮ ጋር ይገጥማል)::

የጪጮው ክዳን ትልቅ በመሆኑ በክዳኑ እና በዋናው ጪጮ መጋጠሚያ መካከል ተለቅ (ሰፋ) ያለ ክፍል ኣለው:: በዚህም የተነሳ ክዳኑ ራሱ የኣንድ ትልቅ ኩባያ ይዘት ያህል ፈሳሽ ይይዛል:: ከወደ ኣናቱ ጀምሮ በወፍራም ስንደዶ እየተሰፋ የመጣው ክዳን ከዋናው እናት ጪጮ ጋር የሚጋጠምበት ቦታ ላይ በስሱ ይሰፋል:: ይህም በደንብ እንዲገጥም ታስቦበት የሚደረግ መሆኑን ኣልፊያ ሀጂ ትናገራለች:: የክዳኑ ሌላኛው ወይም የመጨረሻው ጫፍ ጅምር የምትመስል ዝርግ ስፌት ትገጠምለታለች:: ይህም ለመያዝ ቀላል ያደርገዋል:: የጨሌ ጌጥም በላዩ ላይ ይሰፋበታል:: ሌላውን የጪጮ ኣካል በየተወሰነ ርቀት ዙሪያውን በዛጎል ያስጌጡታል:: ዛጎሎቹ በተርታ የሚደረደሩት ቀደም ሲል በታበተው የቆዳ ጥብጣብ (Strap) ላይ ነው:: ዛጎሎቹ ታዲያ በዚያ ጥብጣብ ላይ በቀጭን ጠፍር እየተሰፉ ቁልቁል እስከ ጪጮው ወገብ ድረስ ይዘልቃሉ:: ዛጎሎቹ ቁልቁል መውረድ ብቻም ሳይሆን መስቀለኛ ቅርጽ እየሰሩም እቃውን ያስጌጡታል (ፎቶግራፍ 20ን ይመልከቷል)::



*ፎቶግራፍ 20፡- የስፌት ውጤት የሆኑ ልዩ ልዩ መጠን ያላቸው የወተት መያዣ ቁሳቁስ::*

የጠፍሩ ጥብጣብ «ሳምሳ» በሁለት መንገድ ይታበታል:: የመጀመሪያው ከጨጮው ወገብ (መካከል) ጀምሮ መክደኛውን ግራና ቀኝ ኣቅፎ ለማንጠልጠያነት እስከሚተርፍ ድረስ የሚዘልቀው ነው:: ሌላው ደግሞ በወገቡ ዙሪያ ከተሰፋው የጠፍር ጥብጣብ ተነስቶ በጥንድ በጥንድ እየሆነ መሬት እስከሚነካ ድረስ የሚታበተው ነው:: እነዚህ ጥንድ ጥንድ ወይም ጣምራ ጣምራ የሆኑ የጠፍር ጥብጣቦች ጌጠኛ መልክ እንዲኖራቸው ሲባል ተጎንጉነው የወረዱ ይመስላሉ:: ከመነሻቸውም ላይ ሁለት ሁለት ዛጎሎች ጌጠኛ በሆነ መልኩ ተሰፍተውባቸዋል:: (ኣሁንም ፎቶ 20ን ይመልከቱ):: ጨጮው በዚህ መልኩ ከተሰፋ በሁዋላ በውስጡ የሚቀመጠው ፈሳሽ እንዳይፈስና እንዲጠነክር ወይም ቀዳዳዎቹ እንዲደፈኑ ትኩስ የከብት ደም ይጨመርበትና ይቆያል:: ደም ባልተገኘ ጊዜም ጥቀርሻ ላይ ይሰቀልና ጢስ እንዲጠጣ ይደረጋል:: ከዚያ በሁዋላ በደንብ ተወልውሎ የጥንት መልኩን እንዲይዝ ያደርጉታል:: ጮጮዎች ሁሉ ኣንድ ኣይነት ባይሆኑም የተቀራረበ መጠን ሊኖራቸው ይችላል:: ብዙውን ጊዜ ሰፊዎቹ በኣይነ ግምት ስለሚሰፉት ኣንዱ ከኣንዱ ይበላለጣል:: በመስክ ጥናት ወቅት ለዚህ ጥናት ኣቅራቢ ያጋጠመው ጨጮ ቁመት 18፣ የሆዱ መጠነ ዙሪያ 43፣ የኣፉ መጠነ ዙሪያ 28፣ ኩሬዋ (መክደኛዋ) ከዋናው ጨጮ ጋር ለመግጠም ሰበር የምትልበት 2፣ የኩሬዋ መጠነ ዙሪያ ከወደ መግጠሚያዋ አካባቢ 28፣ በኩሬዋ ላይ ያለው የቀንድ ርዝመት 6፣ የቀንዱ ጫፍ መጠነ ዙሪያ 3፣ ኩሬዋ እና ቀንዱ የተገናኙበት ቦታ የቀንዱ መጠነ ዙሪያ 5.5፣ የጮጮዋ መቆሚያ (እግር) ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለው ርዝመት 10፣ ከቀንዱ ጫፍ እስከ መቆሚያው (እግሩ) ድረስ ያለው ርዝመት 29 ሳንቲሜትር ነው:: (የሁሉም አሀዞች መለኪያ ሳንቲሜትር ነው)::

*ኣገልግሎት:-* የባህሉ ባለቤቶች የሆኑት ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማንና ወ/ሮ ሌይላ ኢብሮ እንደሚያስረዱት ኣነስ ያለው የወተት ማስቀመጫ ሲሆን ከፍ ያለው ደግሞ ወተቱን ለመናጥ ያገለግላል:: ኣንዳንድ የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላትም ውስጡን በኣጥሚት ካሟሹ በሁዋላ ወተት ያልቡበታል:: ብዙውን ጊዜ እቃ ካልጠፉ በስተቀር ለጌጥነትም ስለሚፈለግ የታበተው የቆዳ ጠፍር እና ዛጎሎቹም ኣምረው እንዲታዩ የተወሰነ ቦታ በክብር ይቀመጣል::

*ባህላዊ ፋይዳ:-* የጨጮ ባህላዊ መገለጫ የተዳረች ልጅ ወደ ኣዲሱ ጎጆዋ ስትሄድ በስጦታ መልክ የሚበረከትላት መሆኑ ነው:: ከዚህ በተያያዘም በሰርጉ ወቅት ልጃገረዶች ሲዘፍኑ ወደ ላይ ከፍ ኣድርገው በመያዝ የዘፈናቸው ማድመቂያ በማድረግ ባህላዊ ፋይዳውን ይገልጹበታል::

የጨጮ (ጮጮ) ባህላዊ ፋይዳ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ብቻ ሳይሆን ሌላም ጠቀሜታ ኣለው:: ይህን በተመለከተ በድርያ ካም እና ኣልፍያ ሀጂ

*«ትልቁ ጮጮ የተዳረችን ልጅ ኣጃቢ ሰርገኞች ወደ ባሏ ቤት ይዘዋት በሚሄዱበት ጊዜ ወተት ይይዙበታል፤ የተያዘውንም ወተት በመንገድ ላይ በጮጮው ውስጥ እንዳለ እየተቀባበሉ በመቃመስ ይጠጡታል:: ይህም የኣንድነትና የስምምነት፣ እርጥብ ነገር እንዳያጠ ተስፋ የሚሰንቁበትና የመፈቃቀድ መግለጫ እንደሆነ ይቆጠራል» በማለት ያረጋግጣሉ::*

በጨጮው ላይ የታበቱት የጠፍር ጥብጣቦች ጨጮውን ከማስዋብ በተጨማሪ ሌላም ባህላዊ ፋይዳ ኣላቸው:: ኣብዱርቃድር ኣቡበከር ቀጥሎ ባለው መንገድ ይገልጹታል::

*ኣንዲት ልጅ በተዳረች ጊዜ እናቷ በጠፍር ታብቶ በጌጥ በተሸለመ ጮጮ ውስጥ «ቡራቶ» (የኦሮሞ ባህላዊ ምግብ) ታስቀምጥና ከውጭ ያለውን የጠፍር ጥብጣብ ከኣንድ ወገን በራሷ ኮድ (በምታውቀው መለያ ወይም በራሷ የኣስተሳሰር ዘዴ) ትቋጥርና ልጅቷ ከእናትና ከኣባቷ ቤት ወጥታ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ ኣስይዛ ትልካታለች:: ይህን «ቡራቶ» የያዘውንና የልጅቱ እናት በምታውቀው የራሷ ኣስተሳሰር ዘዴ ጥብጣቡ የታሰረውን ጮጮ መጀመሪያውኑ ከልጁ ዘመዶች የተመረጠች ሴት፣ ብዙውን ጊዜ ያገባች ታላቅ እህቱ፣ እሷም ከሌለች የኣባቱ እህት (ኣክስቱ) እቃውን ትረከብና በጫጉላ ቤቱ ውስጥ ትሰቅለዋለች:: ጮጮውን ማንም እንዳይነካም ትከታተላለች:: ልጅቱ በድንግልናዋ ከተገኘች ያ የታሰረ የጠፍር ጥብጣብ ሳይፈታ ተመልሶ ወደ ልጅቱ እናትና ኣባት ቤት ይላካል:: ነገር ግን ልጅቱ ድንግልናዋን ያልጠበቀች ከሆነ ይፈታና ይላካል:: መፈታቱንም መጀመሪያ የምታውቀው በኮድ ያሰረችው የልጅቱ እናት ስትሆን ቀጥሎም ቀስ በቀስ የልጅቱ ኣባት ወይም የቅርብ ዘመዶች ሊያውቁ ይችላሉ:: ይህ ኣይነቱ የጠፍር መፈታትና ኣለመፈታት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የተደረገ የመልእክት ልውውጥ ነው:: የመልእክት ልውውጡ በኣከዋወኑ መጠነኛ ልዩነት ቢኖረውም በኣማራው ባህል በዳቦ መካከለኛ ክፍል ብር ኣስቀምጦ ወይም ባዶውን ከመላክ ጋር ይመሳሰላል:: ሁለቱም የድንግልናን መኖርና ኣለመኖር ያበስራሉ ወይም ያረዳሉና::*

ይህንኑ ሁኔታ ስለ «ቆሪ» የተጻፈውንም ልብ ይሏል:: ኣከዋወኑ እንደየኣካባቢው፣ እንደየብሄረሰቡ የተለያዩ የመልእክት መለዋወጫ ባህላዊ ስርኣቶች እንደነበሩ ያረጋግጣል:: የጮጮ ሌላው ባህላዊ መግለጫ በኦሮሞዎች የኣቴቴ ስርኣታዊ ክዋኔ ወቅት የሚታየው ነው:: የኣቴቴውን ስርኣት ለማከናወን የተወሰኑ ሴቶች ወተት በጮጮ ይዘው ወደ መልካ (ወንዝ) ይሄዳሉ:: ኣቶ ኣለሙ ወርቁና ኣልፍያ ሀጂ እንደሚከተለው ይገልጹታል::

*በጎባ ወረዳ የሚገኙ የኦሮሞ ሴቶች ዝናብ ሲታጣ፣ ረሀብ እና የጦርነት ደመና ሲያንዣብብ ወዘተ. ከየቤቶቻቸው ወጥተው የእልልታ ድምጽ ሲያሰሙ ሌሎች የኣካባቢው ሴቶች በጮጮ ወተት፣ ጋዲ (ጥገት ላም የምትጋዳበት)፣ ኣቃሜ (የጥጃ ኣፍ መሸበቢያ)፣ ሲቂ (ዘንግ) እና ርጥብ ሳር ይዘው ይከተሏቸዋል:: በመንዝ ላይ እንዳሉ ወንዶች ካዩኣቸው ልማዳዊ ባህሉ ስለሚከለክላቸው ሴቶቹን ኣያቋርጡም፤ ምክንያቱም በሄድክበት ኣይቅናህ፣ ያሰብከው ኣይሳካልህ ወዘተ. የሚል ርግማን ያተርፋሉና:: ስለሆነም ቆመው ለሚጠብቋቸው ወንዶች በጮጮ የያዙትን ወተት ያጠጧቸዋል:: ወተቱ የሚያንስ መስሎ ከታያቸው በኣፋቸው እየተጎነጩ እንትፍትፍ በማለትና የያዙትን ርጥብ ሳር በመስጠት ይመርቋቸዋል:: በዚህ ሁኔታ የጮጮው ባህላዊ ፋይዳ ይጎላል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የጮጮው፣ የኣቃሚው እና የጋዲው መያዝ*

*«ኣምላካችን ታሪቀን የወተት እቃዎቻችንንና ስናልብ የምንገለገልባቸውን ቁሳቁስ እቤት ኣይዋለ» የሚል ኣንድምታ ኣለው።*

## 4.5.4. ጡንጦ (XUUNXOO)

እጅግ በጣም ታዋቂ ከሆኑት የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ ባህላዊና ከፍተኛ ክብር ከሚሰጣቸው የስፌት እቃዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የምትታወቀው ጡንጦ (Xuunxoo) የተባለችው የወተት መያገ ነች። ኣቶ በቀለ ቱፋ «ጡንጦ ማለት የያዘችውን ፈሳሽ በጣም ቀጭን በሆነ ሁኔታ የምታፈስ ወይም የምታወርድ ልክ ህጻን ልጅ እንደሚጠባው ጡንጦ ኣይነት ቀዳዳዋ የመርፌ ቀዳዳን የሚያክል በቀጭኑ የምታወርድ ማለት ነች» ይላሉ።

*ኣሰፋፍ (ኣሰራር)*፡- የጡንጦ ኣሰፋፍ ቀደም ሲል በ«ኤሌምቱ» በማለቢያ ኣሰፋፍ ሂደት ላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በዚህ ክፍል ለማሳየት የሚሞከረው ከፎቶግራፍ ጋር የተገናዘበ ገለጻ ነው። ጡንጦ በቀለም ባሸበረቀ የስንደዶ ሰበዝ እና ኣለላ ትሰፋለች፤ በልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ጨሌዎችና በባለ ነጭ ቀለም ዛጎል ትሽለማለች። እናት ጡንጦዋ በተለያየ ነገር ግን በተቀራረበ ቅርጽ ትሰፋለች። ኣንዷ ኣይነት ከወደ መቀመጫዋ ሰፋ እያለች በመሰፋት እስከወገቧ ኣካባቢ ከደረሰች በሁዋላ የ8 ቁጥር ቅርጽ በመያዝ እንደገና ስፌቱ እስከ ክዳኗ መጋጠሚያ ይደርሳል። (ፎቶግራፍ 20 ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በ4ኛ ረድፍ ላይ ያለችውን ይመልከቱ)። ይህችው ጡንጦ በስፌቷ ላይ ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ኣለላዎች የተለያየ ቅርጽ እንደተነደፈላት ይታያል። ይህንኑ ንድፍ ከቆዳው ጥብጣብ መካከል ማየት ይቻላል። የዛጎሎቹም ሆነ የጨሌዎቹ ኣደራደር ካሁን ቀደም በዚሁ ክፍል ለማለቢያ እቃ ላይ የገለጽነውን ይመስላል። ጡንጦን ለማስጌጥ በጥቅም ላይ የሚውሉትን ኣለላዎች እንደ ወ/ሮ ጊሹ ኣማን ኣገላለጽ የተለያዩ ቀለሞችን በመግዛት የተገዛውን የቀለም ዱቄት በምጣድ ላይ ኣድርገው በውሃ ከበጠበጡ በሁዋላ ራሳቸው ያቀልሙታል ወይም ከገበያ የተቀለመውን ኣለላ ይገዛሉ። የተቀለሙት ኣለላዎችም በጡንጦዋ ኣካል ላይ በተፈለገበት ቅርጽና ኣይነት እየተሰባጠሩ ይሰፋሉ።

የክዳኗም ኣሰራር ብዙም የተለየ ነገር ባይታይበትም በክዳኗ መሀል ለመሀል የሚያያዘው ቀጭን የፍየል፣ የድኩላ ወይም የሚዳቋ ቀንድ ከሌሎቹ ይልቅ ረዘም ማለቱ ነው። ይህም ያለምክንያት ሳይሆን ኣባወራው እስራ ውሎና ደክሞት ሲመጣ የሚጠጣው በዚያው በቀንዱ በኩል ስለሆነ ነው።

ሌላው የጡንጦ ኣሰፋፍ ሞዴል የሚታየው በፎቶግራፍ 21 ላይ በእናት በ«ኣዮ» (Ayyoo) እጅ ተይዛ ካለችው ጡንጦ ነው። ይህች ጡንጦ ከታችኛው ስፌቷ ጀምሮ ብዙም የቅርጽ ለውጥ ሳይታይባት በኣንድ ኣይነት፣ የጣሳን ቅርጽ ይዛ መሰፋቷ ነው። በእርግጥ ወደ ላይ እየተሰፋ በተሄደ ቁጥር ከታች ከሚታየው ቅርጽ ይልቅ ጠበብ እያለ እንደሄደ ይታያል። ያም ቢሆን በፎቶ 20 ላይ እንዳየናት ጡንጦ የጎላ ልዩነት የላትም።

በሁለቱም ፎቶግራፎች ላይ የሚታዩት ጡንጦዎች የጠፍር ጥብጣብ ከኣካላቸው ተርፎ ይታያል:: ሁለቱም ጡንጦዎች በመጠኑ ወጣ ብሎ የተሰፉ መቆሚያ እግር ኣላቸው::



ፎቶግራፍ 21:- ጡንጦ ይዞ ጭፈራ ለደስታ

የቆዳ ጥብጣቦቹ ብዙም የጎላ ክፍት ቦታ በማይታይበት ርቀት (በተቀራረበ ርቀት) ብዛታቸው ከ3-4 የሚደርስ ሆኖ በኣንድ ላይ ከተያያዙ በሁዋላ ቁልቁል ተለቅቀዋል::

***ኣገልግሎት፡-*** ጡንጦ በዘመድ ቤት በተደገሰ ድግስ ላይ ከነወተቷ ትገኛለች:: ከትዳር ጋር በተያያዘ ሁኔታ ደግሞ ለኣባወራው የቀዘቀዘ ወተት በሚተኛበት አልጋ በራስጌው በኩል ማቆያ ነች:: ባለቤቱ ኣስቀድማ ኣዘጋጅታ ነው የምታስቀምጥለት:: እንደ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ገለጻ ኣባወራው እንደገባ ወተት ስጡኝ ብሎ ኣይጠይቅም:: የምትሰቀልበትን ቦታ ያውቃልና ከጠማውና ካሰኘው ኣንስቶ ክዳኗን ሳይከፍት ወይም መጠጫ እቃ ሳያስፈልገው በኩሬዋ ላይ ባለው ቀንድ በኩል ማንቆርቆር ነው:: የኦሮሞ ባህላዊ ምግብ «ቡራቶ» ከተቀመጠለትም እየበላ የሚያምገው በጡንጦዋ ውስጥ ባለው ወተት ነው:: እሱ እየበላ እንግዳ ከመጣም ከዚያችው ጡንጦ የሚጋበዘው ኣባወራው ነው::

ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ገለጻቸውን ሲቀጥሉም ቤቷ የሞላላት እና የሚታለቡ ጥገት ላሞች ያሏት የጎባ ኦሮሞ ሴት ለኣባወራዋ በጡንጦ ከራስጌው ወተት ካልሰቀለች ሚስትነቷም ኣጠያያቂ ነው:: በኦሮሞ ባህል ላሞች እያሉት ውሀ ሲጠማው ውሀ

መጠጣት የተለመደ ኣይደለም ወተት እንጂ:: ጡንጦን የተከበረች ባህላዊ እቃ ነች እየተባለ የሚነገርላት ከትዳር ጋር መያያዟ ነው:: ምክንያቱም ለቤቱ ኣባወራ የቀዘቀዘ ወተት ማስቀመጫ ከመሆኗም በተጨማሪ የተዳረችን ልጅ ለመጠየቅ ሲፈለግ የመተያያ ወተት መያገርም በመሆን ታገለግላለችና ነው::

***ባህላዊ ፋይዳ፡-*** የጡንጦ ትልቁ ባህላዊ ፋይዳ በሰርግ ስርኣት ላይ ከምታበረክተው ግልጋሎት ይመነጫል:: ስለሆነም ሰርግ የጡንጦ ባህላዊ ጠቀሜታ መግለጫ መድረክ ነው ማለት ይቻላል:: ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ሊይላ ኢብሮ እና ወ/ሮ ጊሹ ኣማን ተከታዩን ሀሳብ ሰጥተዋል::

> *ኣንዲት ልጅ ከመዳሯ በፊት በእናት እና በኣባቷ ቤት እያለች ጡንጦዎችን ሰፍታ በጨሌዎች፣ በዛጎሎችና «ሳምሳ» (የጠፍር ጥብጣብ) ኣስጊጣ የራሷን የጎጆ መውጫ ታዘጋጃለች:: ሙሽሪት በሰርግ እለት ወደ ባሏ ቤት ስትሸኝ ከሰፋቻቸው ጡንጦዎች በኣንዷ ጡንጦ ወተት ተሞልቶ ይያዝላታል:: ስትደርስም ወደ ቤት ከመግባቷ በፊት በበራፉ ደፍ ላይ ወይም ኣካባቢ እንድትቀመጥ ይደረግና ወተቱን ያቀምሷታል:: በዚህ ሁኔታ ግልጋሎት ላይ የዋለችው ጡንጦ «የማቅመሻ ጡንጦ» «ጡንጦ ሁሲሳ» «Xuunxoo Hoosisaa» ትባላለች:: ይህም እርጥብ ኣትጪ የሚል መልእክት ኣለው:: ጡንጦ ለሚከበር እንግዳ ወተት ማቅረቢያ በመሆንም ግልጋሎት ታበረክታለች::*

ሌላው የጡንጦ ባህላዊ ፋይዳ መገለጫ ኣንዲት የኦሮሞ ሴት፣ ልጅ ኣዝላ ስትሄድ ከእጇ የጡንጦ ወተት የማይለያት መሆኑ ነው:: ሴትየዋ ይህን የምታደርገውም ልጇ ወተት ቢያስፈልገው ከጀርባዋ ሳታወርድና የጡንጦዋን ክዳን ሳትከፍት በቀንዱ ቀዳዳ ለማጠጣት ነባሩ ባህላዊ ስርኣት ይፈቅድላታልና ነው::



*ፎቶግራፍ 22:- እናት የዳረቻትን ልጅ ለመጠየቅ ወተቷን በጡንጦ እና የሰላም ኣርማ ሲቄዋን ይዛ በጉዞ ላይ::*

በሌላ በኩልም ኣንዲት የተዳረች ልጇን ለመጠየቅ የምትሄድ እናት «ኣዮ» (Ayyoo) በቀኝ እጇ የጡንጦ ወተት፣ በግራ እጇ ደግሞ ሲቄ (ዘንግ) ይዛ ነው ለመጠየቅ የምትሄድ ፎቶግራፍ 22 «ኣዮ» «ኣይቴ» እናት፣ እናቴ «ኣዮ»፣ «ኣይቴ» በጡንጦ ወተት ይዛ በጉዞ ላይ እንዳለች የሚያሳይ ነው:: ይህ ሁሉ የጡንጦዋ ባህላዊ ፋይዳ የተገለጸበት ነው:: በጥቅሉ ይህንን መሰል ግልጋሎት የምትሰጠው ጡንጦ እንዳትጎሳቆልና ያለ እድሜዋ እንዳታልቅ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጉላታል:: ይህም የተለያየ መኣዛ ባላቸው የወይራ እንጨቶች በማቆራሸትና በምቹ ቦታዎች በማስቀመጥ ይገለጻል:: ወ/ሮ ሌይላ ኢብሮ እና ወ/ሮ ጊሹ ኣማን

> *«የስፌት ውጤት የሆኑ እንደ ጡንጦ፣ ጪጮ፣ ኪላና የመሳሰሉት እቃዎች ተሰፍተው እንዳበቁ በመጀመሪያ የሚቆራሹት ቀለሀ፣ ኮምቦልቻና ጥድ በመሳሰሉት እንጨቶች ነው:: እነዚህ እንጨቶች ስለማያቃጥሉ ያልተደራጁ የስፌት እቃዎችን ለማቆራሸት ተመራጭ ናቸው:: እቃዎቹ በከብት ደም፣ በኣሬራና በፉሩሽካ ከተደራጁ በሁዋላ ግን የምናቆራሸው ጥሩ መኣዛ በሚሰጣቸው የወይራ ማእጠንት ነው» በማለት ያስረዳሉ::*

በየፎቶግራፎቹ ላይ ያየናቸውም ጡንጦዎች በጥንቃቄ መያዛቸው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: እንደ ኣልፍያ ሀጂ ገለጻ ጡንጦዎች ትንሽ፣ መካከለኛና ትልቅ ተብለው ይታወቃሉ:: መካከለኛ መጠን ያላት ጡንጦ ርዝመቷ 27 ሳንቲሜትር፣ የቀንዷ ርዝመት 5.3 ሳንቲሜትር፣ የሆዷ መጠነ ዙሪያ 41 ሳንቲሜትር እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል::

እንደየደረጃቸውና መጠናቸው ለመጠጫ፣ ለማለቢያና ለመናጫ ያገለግላሉ፡፡ በዚህም መሰረት ሁሉም ከወተት ጋር የቀረበ ቁርኝት አላቸው፡፡

### 4.5.5. ባሬ (BAARREE)

በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ዘንድ ከሚታወቁት ባህላዊ የስፌት እቃዎች አንዱ «ባሬ» (Baarree) ነው፡፡ ባሬ ከጮጮና ከጡንጦ ጋር ሲነጻጸር ትልቁ የስፌት እቃ ነው፡፡

*አሰፋፍ (አሰራር)፡-* የ«ባሬ» (Baarree) ጥበባዊ አሰፋፍ ከሌሎች የኦሮሞ ባህላዊ እቃዎች አሰፋፍ የጎላ ልዩነት የለውም፡፡ ልዩነት እንኳን ቢኖር በመጠንና በቅርጽ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጡንጦ፣ ጮጮ ወዘተ. ጋር ሲነጻጸር «ባሬ» በመጠን ትልቅ ነው፡፡ ትልቅነቱም ከሚሰጠው አገልግሎት አኳያ ነው፡፡ በአጠቃላይ የስፌት እቃዎች የአሰራር ጥበብ ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ «'ጎርፋና ጨጮ' ሁለቱም የስፌት ውጤት የሆኑ የወተት መያገ እቃዎች ናቸው፡፡ የሚሰሩትም ከተመሳሳይ ቁሳቁስ ነው፤ አሰፋፋቸውም በተመሳሳይ ቴክኒክ (ስልት) ነው፡፡ ነገር ግን በቅርጽ፣ በመጠን፣ እና በአጋጌጥ ይለያያሉ» ማርኮስ ባሲ (Markcos Bassi 1999፣ 78) በማለት ጽፈዋል፡፡

ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ አማን «ባሬ ሁለት አይነት የአሰፋፍ መንገድ አለው» ይላሉ፡፡ እነዚህም 1ኛው ሙሉ በሙሉ ከስንደዶ የሚሰፋውና 2ኛው ደግሞ ከወገቡ በላይ የስፌት እና ከወገቡ በታች ደርፊጫ ቅል የተገጠመለት ናቸው፡፡ በሁለተኛ ቁጥር ላይ የተጠቀሰውን የባሬ አይነት ለማዘጋጀት መጀመሪያ ተስማሚ ቅል መገኘት አለበት፤ ተስማሚ ቅል የሚባለው ደርፎጭ ያለ (ከጎንና ከጎኑ የሰፋ) ከወደ አፉ መዳረሻ ደግሞ ከተት ያለ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ቅሉ በስሎ ከተቆረጠ በሁዋላ ፍሬውንና አላስፈላጊ የሆኑትን ፍቅፋቂዎች እየፈቀፈቁ ወይም በሙቅ ውሀና በአመድ እንዲብላላ ከተደረገ በሁዋላ በመፈቅፈቅ ማስወገድ ነው፡፡ እንደ ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ አማን ቀጥሎ ያለው ተግባር ከቅሉ አፍ ትንሽ ዝቅ ብሎ በመጀመር ወደ ላይ ስፌት መስፋት ነው፡፡ ቅሉ ወስፌ እንዲቀበል የለዘበ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ብዙ ሳይደርቅ ነው ከስንደዶ ስፌት ጋር ለማያያዝ የሚሞከረው፡፡ የስፌቱን ስራ ወደ ላይ እያሳደጉ ይበቃል እስከሚባልበት መጠን ድረስ ይቀጥላል፡፡ የስፌቱ መጨረሻ አካባቢ ማለትም ወደ አፉ መጨረሻ አካባቢ ሰበዙን እያሳሱ መጨረስ ነው፤ ይህ ደግሞ መክደኛውን እንዲቀበል ያደርገዋል፡፡ በዚህ አይነት የተዘጋጀው «ባሬ» (Baarree) ከወገቡ በታች ቅል፣ ከወገቡ በላይ ደግሞ የስንደዶ ስፌት ነው፡፡ መክደኛውም በአፉ መጠን የሚሰፋ የድስት እፊያ የመሰለ የእጅ መያገ ያለው ነው፡፡ ግማሽ ስፌት፣ ግማሽ ቅል የሆነውን ባሬ ባለቤቶቹ ከፈለጉ የጠፍር ጥብጣብ «ሳምሳ» በማበትና ዛጎሎችን በመደርደር ማስዋብ ይቻላል፤ ወይም እንዲሁ ሊተውት ይችላሉ፡፡ ሌላው የ«ባሬ» አይነት ከስንደዶ ስፌት ብቻ የሚሰፋው ነው፡፡ ይህንን «ባሬ»ም በተመለከተ ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ አማን የሚሉት አላቸው፡፡

*ኣጀማመሩ ወይም ጅምሩ ቀደም ሲል ለ«ኤሌምቱ» ማለቢያ የነገርኩህ ሆኖ የዚህ ለየት የሚለው፣ ትልቅ እንደመሆኑ መጠን ጅምሩ ሰፌድ መስሎ ትንሽ ሰፋ ማለቱ ነው:: በኣይነ ግምት ወይም በስንዝር ለክተን ኣንድ ስንዝር ያህል ከሰፋን በሁዋላ የስፌት ስራችንን ወደ ላይ በመቀልበስ እናስኬደዋለን:: ወደ ቂጡ (ከወገቡ በታች ያለው) ኣካሉ ሰፋ እንዲል ስለሚፈለግ ኣሰፋፋችንን ወደ ጎን ለጠጥ እያደረግን እስከ ወገቡ እንዘልቅና በመቀጠል ሰብሰብ-ሰብሰብ እያደረግን ወደ ኣፉ መዳረሻ ላይ እያጠበብንና ሰበዛችንንም እያሳሳን ወደ ኣፉ ጠርዝ እንደርሳለን:: ይህን የምናደርገው መክደኛው በትክክል ግጥም እንዲል ነው:: ከዚህ በሁዋላ ያለው ስራ ኣስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሰፋ-ሰፋ ያሉ የጠፍር ጥብጣቦች (ሳምሳዎች) ማበት ነው:: በታበቱት የጠፍር ጥብጣቦች ላይ ዛጎሎችን ከላይ ወደ ታች እና ወደጎንም መሰፋት ነው:: እነዚህም ለባሬው ውበት ይሰጡታል:: ሁሉም ባሬዎች ግን የግድ የጠፍር ጥብጣብና ዛጎሎች ይኖሯቸዋል ማለት ኣይደለም:: የመጨረሻው ተግባር ማሟሸት ነው:: ለሙሽቱ ጥንት የከብት ደም ሳይቀር እንገለገል ነበር ኣሁን ኣሁን ግን ደሙን በመተው የገብስ ኣሻሮ ከፈጨን በሁዋላ ዱቄቱን ከወተት ጋር ቀላቅለን የባሬውን ውስጥ እናሸበታለን:: ባሬው የተፈለገው ለወተት መናጫ ኣገልግሎት ከሆነ ኣንገቱ ኣካባቢ ቱፌ ይወጣለታል:: በሌላ በኩል ለወተት ማርጊያ እንዲሆን ከተፈለገ ግን ቱፌ ኣይወጣለትም:: ሲሉ ኣጠቃለዋል::*

በስፌት ብቻ የተዘጋጀውን ባሬ በፎቶግራፍ 20 ላይ በቀኝ የመጨረሻ ጠርዝ የሚገኘውን ማየት ይቻላል::

በመስክ ምልከታ ወቅት ያጋጠመኝ «ባሬ» (Baarree) ቁመቱ 37፣ የወገቡ መጠነ ዙሪያ 60፣ ወደ መቆሚያው መዳረሻ ላይ ያለው መጠነ ዙሪያ 57፣ የኣፉ መዳረሻ መጠነ ዙሪያ 54፣ የኣፉ መጠነ ዙሪያ 38፣ ከኣፉ ጠርዝ መጀመሪያ ሰበር የሚልበት ቦታ ድረስ ያለው ርዝመት 4.5፣ መጀመሪያ ሰበር ከሚልበት እስከ ወገቡ ድረስ 15፣ ከወገቡ ጀምሮ እስከ መጨረሻ መቆሚያው ድረስ ያለው ርዝመት 17.5 ሳንቲሜትር መሆኑን በመለካት ኣረጋግጫለሁ:: (የሁሉም ኣሀዞች መስፈሪያ ሳንቲሜትር ነው):: ይህ ከዚህ በላይ ለናሙና የቀረበው ባሬ ለሁሉም ባሬዎች ይሰራል ማለት ኣይደለም:: ይሁንና የባሬ መጠን በኣማካይ ምን ኣይነት ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ሳይሰጥ ኣይቀርም::

***ኣገልግሎት፡-*** «ባሬ» (Baarree) በቤት ውስጥ ወተት ማጠራቀሚያ፣ እርጎ ማርጊያ፣ ወተት መናጫ በመሆን ከማገልገሉም በላይ ብዙ ጥገቶች ያሏቸው ኦሮሞዎች በሚያልቡበት ኣካባቢ ባሬውን ያስቀምጡና በማለቢያ የተቀበሉትን ማጠራቀሚያ ያደርጉበታል በማለት የቡርቂቱ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆኑት ኣቶ መርእድ ኣስፋው ነግረውኛል::

***ባህላዊ ፋይዳ፡-*** «ባሬ» (Baarree) በሰርግ ወቅት በ«ገበታ» ከሚቀርበው «ቡራቶ» ጋር ማማገያ የሚሆን ወተት ወይም እርጎ ሰንቆ ይቀርባል:: በደቦም ጊዜ ቢሆን ለጂጌኞች (በስራው ላይ ለተሳተፉ ሰዎች) የሚታደለውን ወተት ያቀርቡበታል:: በዚህ ኣይነቱ ግልጋሎት ላይ የተሰለፈ ባሬ በቀጥታ መጠጫ ባይሆንም ሰፋ ላለ የመስተንግዶ ተግባር ለትናንሽ መጠጫ እቃዎች መጋቢ በመሆኑ ባህላዊ ፋይዳው የጎላ ነው:: በዚህ

ኣይነቱ የግልጋሎት መድረክ ላይ የወጣ ባሬ በጊጥ የተሸለመ፣ በ«ሳምሳ» ጠፍር የተዋበ ሊሆን ይችላል።

### 4.5.6. ኮቦ (KOBOO)

«ኮቦ» የተባለው ባህላዊ የስፌት እቃ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብን ባህል ከሚያንጸባርቁት ባህላዊ እቃዎች ኣንዱ ነው። ኣዛውንቱ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ ኮቦን ለመስፋት ምን ኣይነት የስንደዶ ሳር እንደሚያስፈልግ እንደሚከተለው ይገልጹታል። «ኮቦ» (Koboo) «ዊጣ» (Wiixaa) ከሚባል የሳር ኣይነት ይሰፋል። «ዊጣ» (Wiixaa) ምን ኣይነት ሳር ነው? ብዬ ላቀረብኩላቸው ሲመልሱ «ዊጣ» (Wiixaa) ኣጠራሩ የኦሮምኛ ቋንቋ በመሆኑ እንጂ ስንደዶ ማለት ነው፤ ግን ጠንካራ የስንደዶ ጊቻ የሚባለውን የያዘ» በማለት ኣስረግጠዋል። እንዲህ ኣይነቱ ጠንካራ የስንደዶ ኣይነት የተፈለገው «ኮቦ» (Koboo) የተባለው እቃ እጅ ስለሚበዛበት በቶሎ እንዳይበጣጠስ ለማድረግ ነው።

*ኣሰራሩ፦* የመሶብ ቅርጽ ያለው ሆኖ መጠኑ ኣነስተኛ እና ጎድጎድ ያለ ነው። ከስርም ለመቆሚያ የሚያገለግል እግር ኣለው። የእግሩ እና ከላይ ያለው የመመገቢያ ኣካሉ ዙሪያቸውን በቆዳ ጠፍር ይለጎማሉ። ይህም ለጥንቃቄ እና እጅ እንዳይበላው፣ እድሜም እንዲያገኝ ታስቦ የተደረገ ነው። ከዚህም ጎን ለጎን ተጨማሪ ውበት እንደሚሰጠውም ይታመናል። ወ/ሮ ሊይላ ኢብሮ የኮቦ ስፌት የሚጀምረው ከትንሽ ክብ ሰፌድ ቅርጽ እንደሆነ ይናገራሉ። በደንብ ለመቆም እንዲችል ከእግሩ ወደ ውጭ ለጠጥ እየተደረገ ይሰፋል። የእግሩ ርዝመት በኣይነ ግምትና እንደሚሰፋው የኮቦ ኣይነት ከተመጠነ በሁዋላ ዋናው የመመገቢያ ኣካሉ ይሰፋል። ይህም ጎድጓዳ ነው። የመመገቢያ ክፍሉ ጎድጎድ እንዲል ታስቦ መሰራቱ ከሚቀርብበት ምግብ ኣንጻርም ታስቦ ይመስላል። ብዙውን ጊዜ ልጆች ቆሎ፣ ንፍሮ እና የመሳሰሉትን እንዲመገቡበት ይደረጋል። (በፎቶግራፍ 23 ላይ ከጽሁፉ በታች ወንፊቱን ተደግፎ ያለውን «ኮቦ» (Koboo) ልብ ይበሉ)። እዚህ ላይ ያለው «ኮቦ» ግን በቆዳ ዙሪያውን የተለጎመ ኣይደለም። በመስክ ጥናት ላይ ለእይታ የበቃው ኮቦ ጎድጓዳ የሆነው ኣካሉ ከኣንዱ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ መሀል ለመሀል ያለው ርዝመት 20 ሳንቲሜትር፣ የእግሩ ርዝመት 4 ሳንቲሜትር፣ ቁመት 10 ሳንቲሜትር መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።



*ፎቶግራፍ 23፡- ልዩ ልዩ ባህላዊ የስፌት እቃዎች፡፡*

***ኣገልግሎት፡-*** የ«ኮቦ» ኣገልግሎት ቆሎና ቂጣ የመሳሰሉትን በቁርስ ሰኣት መመገቢያ ሲሆን ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ለልጆች የጥራጥሬ ምግቦችም ማቅረቢያ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል እግር መሰል መቆሚያ የሌለው እና ኣነስተኛ ኮቦ ከሆነ ደግሞ የተቆላ ቡና ከብረት ምጣድ ላይ ለመጋፍ ይጠቅማል፡፡

***ባህላዊ ፋይዳ ፡-*** የ«ኮቦ» ባህላዊ ፋይዳ በይበልጥ ኣይሎ የሚታየው እረኞች ከተሰማሩበት መስክ ሲገቡ እስከእራት ድረስ ለመቆያ እየተባለ ቀለል ያሉ ምግቦች የሚሰጧቸው በመሆኑ፣ ከዚህም በስተቀር ኣባወራዎች ከብቶቻቸውን ካስገቡ በሁዋላ የራት ሰኣት እስከሚደርስ ድረስ እንደ ቂጣ፣ ቆሎና የመሳሰሉትን ወይም የተቆረጠ «ቡራቶ» የሚቀርብላቸው በኮቦ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከቤቶቻቸው በቅርብ ርቀት ተሰባስበው ለጭውውት የተቀመጡ የመንደሩ ኣዛውንትና ኣባወራዎች በ«ኮቦ» ተደርጎ ቀላል ምግብ ይቀርብላቸዋል፡፡

## 4.5.7. ሌማት (LEEMATII) ሌማቲ

ሌማት፣ በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህል የስፌት ስራ ውጤት የሆነ መመገቢያ እቃ ነው፡፡

***ኣሰፋፍ (ኣሰራር)፡-*** በቅርጽና በመጠን ይለያይ እንጂ የኣሰፋፉ ሂደት የሌሎች ስፌት እቃዎችን የኣሰፋፍ ጥበብ የተከተለ ነው፡፡ «የስፌቱ ጅምር የሚጀምረው ከዝርጉ ነው»

የሚሉት ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን የኣሰፋፍ ሂደቱን እንደሚከተለው ይገልጹታል::

> *ቀደም ሲል እንደገለጽኩልህ ለመስፋት የሚያገለግለን የስንደዶ ሰበዝ፣ ኣክርማ፣ ለማስጌጥ ከተፈለገ ደግሞ የተለያየ ቀለም ንክር የሆኑ ኣለላዎች፣ እግሩንና የመመገቢያውን ጠርዞች የምንለጉምበት የለሰለሰ ቆዳ፣ እጅ የሚርስበት ውሀ ናቸው:: ሌማቱን ለመስፋት ታዲያ መጀመሪያ የሰፌድ ቅርጹን ለመጀመር በሁለት እና በሶስት ሰበዞች ትንሽ ቀለበት ነገር ከሰራን በሁዋላ ባነሰበት ቦታ ሰበዙን እየሰገሰግን ኣክርማውን በሰበዙ ላይ ማዞር ነው:: የኣንድ ስንዝር ግማሽ ስፋት ያለውን የሰፌድ ቅረጽ ከሰፋን በሁዋላ እግሩን (መቆሚያውን) ለመስራት ሰበዙን ወደ ታች ሰበር-ሰበር በማድረግ መጀመሪያ መጠነኛ ክብ ቅርጽ ቀጥሎም ዘርጠጥ እና ለመጥ እያደረግን የሌማቱን ጠቅላላ ክብደት ይዞ በሚቆምበት ደረጃ ላይ እንዲደርስልን ዘርጠጥ እያደረግን ስፌታችንን እንቀጥላለን:: በመጨረሻ በኣይኑ ግምት በማየት የእግሩ ርዝመት መብቃቱን ካረጋገጥን በሁዋላ ዋናውን የመመገቢያ ኣካል (ምግብ ማስቀመጫውን) እንሰፋለን:: ጌጥ እንዲሆነው ኣለላ የሚያስፈልግም ከሆነ እያሰባጠርን በፈለግነው ቅርጽ ሶስት ማእዘን፣ ክብ ወዘተ. እንሰፋለን:: በመጨረሻም በእግሩና በዋናው መመገቢያ ዙሪያ ጠርዝ የለሰለሰ ቆዳ እንለጉምበታለን:: ይህ በእርግጥ ባለቤቱ እንደወደደ ነው::*

ለወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን፣ መጠኑን እንዴት ትወስናላችሁ? በማለት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ

> *«ድሮ እናቶቻችን ሲሰሩ እናይ ነበር ያም እውቀቱ ኣለን ያው እንደምታውቀው በሜትር ኣንለካም ትንሽ፣ መካከለኛ ወይም ትልቅ ሌማት ለመስፋት ስንፈልግ በኣይነ ግምት እያየን ይበቃል ልቁረጠው፣ ያንሳል ኣንድ ሁለቴ ላዙርበት እያልን ነው» ሲሉ መልሰዋል::*

ከዚህ በላይ በወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን የተገለጸውን ለማነጻጸር በፎቶግራፍ 23 ላይ በቀኝ የመጨረሻ ጠርዝ ከፊት ለፊት ያለውን ሌማት መመልከት ይቻላል:: ሌማቱ በመጠን ትንሽ ነው:: ተለክቶ በተገኘው መረጃ መሰረት የመመገቢያውና የዝርጉ ዲያሜትር 25 ሳንቲሜትር ሲሆን የእግሩም ርዝመት 32 ሳንቲሜትር ነው:: የዋናው መመገቢያ ኣካሉ መጠነ ዙሪያ 90፣ የእግሩ ጠርዝ መጠነ ዙሪያም 75 ሳንቲሜትር ነው:: የእግሩም ሆነ የመመገቢያው ጠርዝ ዙሪያቸውን ቆዳ ተለጉሞባቸዋል:: ፎቶግራፉን ይመልከቱ::

***የሌማት ኣገልግሎት:-*** ለወ/ሮ ራሂማ መሀመድ ኣማን ያቀረብኩላቸው ሌላው ጥያቄ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ባህል ሌማት ምን ኣገልግሎት ይሰጣል? የሚል ነበር:: ሲመልሱም

> *«ኣሁን እየቀረ ሄደ እንጂ ያኔ እኛ ልጅ በነበርንበት ዘመን ሰተቶ፣ ስስ ቂጣ (ሃጿ) ኣንዳንዴም ቆሪ ሳይኖር ሲቀር የተጨበጠ በሶ እላዩ ላይ እየተደረገ ይሰጠን ነበር፤ ኣሁን እኔ ከፍ ባልኩበት ጊዜ ደግሞ እንጀራ መብላት ሲለመድ እንጀራ ይቀርብበት ነበር:: ኣንዳንዴ ደግሞ ገንፎ የያዘ ቆሪ በላዩ ላይ ይደረግና እሱ እኮ እንደ ጠረጴዛ መሆኑ ነው (እየሳቁ) ያቀርቡበት ነበር:: ኣሁን ያ ሁሉ ቀርቷል» ኣሉና በረጅሙ ተነፈሱ::*

ለምን ቀረ? ኣልኳቸው «ዘመናዊ እቃ ከመጣ ወዲህ ሴቱም መስፋት ተወ፣ የሚገዛንም ስለሌለ ማን እሱን ይሰፋል (እየሳቁ) እሱን ከመስፋት ጊንዶ (ጉንዶ ማለታቸው ነው)፣ ሰፌዲ (ሰፌድ) መስፋት ይሻላል:: ኣገልግሎታቸው እስከ ኣሁን ያልተቋረጠ እነሱ ናቸው» ሲሉ ኣጠቃለዋል::

*ማህበራዊ ፋይዳ፡-* የሌማት ኣገልግሎት በሌሎች ቁሳቁሶች (ትሪ፣ ዝርግ ሳህን ወዘተ.) ከመነጠቁ በፊት በእንጀራ ወይም በሌሎች ምግቦች ተሞልቶ ከቀረበ በሁዋላ ተመጋቢዎች በዙሪያው ተኮልኩለው ወግ እያወጉ ስለሚመገቡበት ማህበራዊ ፋይዳው የጎላ ነበር:: ይህ ግን ይበልጥ ይታይ የነበረው ከተማ ነዋሪ በሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ ነበር::

### 4.5.8. ቡሬ (BUURREE)

የጎባ ወረዳ የኦሮሞ ባህላዊ የስፌት እቃዎች ውስጥ በመጠን ትልቁ ቡሬ (Buurree) ነው:: ትልቅ ከመሆኑ የተነሳም ሰፍቶ ለማጠናቀቅ የወራት ጊዜ ይጠይቃል::

*ኣሰፋፉ (ኣሰራሩ)፡-* እንደሌሎቹ የስፌት ስራዎች ሁሉ ረዥሙ የስፌት ስራ በ«ውጢኒ» (Wixinee) በትንሽ ጅምር ላይ መሰረቱ ይጣላል:: ቅርጻዊ ኣሰፋፉ ክብ ስለሆነ የሚጀመርበት (መሰረቱ) የሰፌድ ቅርጽ ይይዛል:: ሙያተኛዋ ወ/ሮ ሌይላ ኢብሮ የሰጡኝን ግምት ወስጄና ለክቼም ባረጋገጥኩት መሰረት መካከለኛ መጠን ያለው ቡሬ መቆሚያው (መሬት የሚነካው ኣካሉ ወይም መሰረቱ) ከ25 እስከ 30 ዲያሜትር ይሆናል:: የትልቁ ቡሬ ደግሞ ከዚህ እንደሚበልጥ ነው:: ይህን ለማረጋገጥ በፎቶግራፍ 24 በ«ሀ» እና በ«ለ» ላይ የቀረቡትን ሁለቱንም ቡሬዎች ማነጻጸር ይቻላል::



*ፎቶግራፍ 24-ሀ:- ሃያ አምስት ኪሎ ይይዛል የሚባለው መለስተኛው የዱቄት መያዣ ቡሬ*

በሰፌድ (በዝርግ) ቅርጽ መሰፋቱ የተጀመረው ቡሬ የተወሰነ ደረጃ ላይ ከደረሰ በሁዋላ የ«ሀ»ን ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጎ ወደላይ ሰበዙን እየቀለበሱ የስፌቱን ስራ ይቀጥላሉ:: ከመቀመጫው ጀምሮ እስከ መሀል ወገቡ ድረስ የትልቅ ዋዲያት ቅርጽ በመያዝ ጎንና ጎኑ እንደተፈለገው መጠን እየሰፋ ይሄዳል:: ወገቡ ላይ ሲደርስ በመጠኑ ሰበር በማድረግ፣ ግን ደግሞ ያንኑ የክብ ሲሊንደር ቅርጽ እንደያዘ ይሰፋል:: አሁንም የተወሰነ የስፌት ደረጃውን ከጨረሰ በሁዋላ በመጠኑ ሰበር ይልና ቅርጹን እንደያዘ ይቀጥላል:: በዚህ የኣሰፋፍ ሂደት ኣንደኛውን የኣሰፋፍ እርከን ሲጨርስ ወደ ሌላ እየተሸጋገረና እየጠበበ-እየጠበበ ወይም የ«ሀ» ወይም የጣሳ ቅርጹን ሳይለውጥ እየተሰበሰበ-እየተሰበሰበ እስከ ኣፉ መዳረሻ ይደርሳል:: በጣም ትልቅ የተባለው ቡሬ እስከ ኣፉ መዳረሻ ድረስ ስድስት እርከኖችን ተጉዟል:: የእርከኑ ኣስፈላጊነት ምንድነው? ብዬ ለጠየኳቸው ወ/ሮ ሌይላ ኢብሮ ሲመልሱ «ከታች በተነሳበት መልኩ ስፌቱ ይቀጥል ቢባል በጣም ከመስፋቱ የተነሳ ኣፉን እንዴት ማጥበብ ይቻላል? ስለዚህ ወደ ጠባቡ የኣፉ ክፍል ለመድረስ እያጠበብን-እያጠበብን መስፋት ኣለብን» ይላሉ:: የኣሰፋፉን ደረጃና ያለውን እርከን ከፎቶ 24 «ለ» ይመልከቱ::



*ፎቶግራፍ 24-ለ:- ሁለት ኩንታል ይይዛል የተባለው ትልቁ የዱቄት መያዣ*

ወ/ሮ ሌይላ እንደሚናገሩት ቡሬ ጠንካራ ሆኖ መሰፋት አለበት፡፡ በተለይም በቤት ውስጥ ለጌጥ የሚቀመጠው ሳይሆን ዱቄት መያገር ሆኖ የሚያገለግለው «ቡሬ» ከጠንካራ ስንደዶና ጊቻ እንዲሁም «ከላላ» በተባለው ጠንካራ ሀረግ መሰፋት አለበት፡፡ ምክንያቱም አደጋን መቋቋም እንዲችልና በቀላሉ እንዳይበላሽ ነው፡፡ በጣም ትልቅ ነው የሚባለውን ቡሬ ሰፍቶ ለማጠናቀቅ ከ6 ወራት በላይ እንደሚወስድ ወ/ሮ ራሂማ መሀመድም ያረጋግጣሉ «ስራው 6 ወራትና ከዚያም በላይ ጊዜን የሚወስድ ብቻ ሳይሆን ትእግስትንም ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ተፈላጊውን የመስፊያ ጠንካራ ስንደዶና ጊቻ፣ ከላላ (ሀረግ) ማጠራቀሙ በራሱ ትልቅ ስራ ነው ይላሉ» ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ አማን፡፡ ይሁንና ለዱቄት መያገር እንዲሆን የሚሰፋው ቡሬ ይህን ያህል ላቅ ያለ ሙያተኝነትን የሚጠይቅ አይደለም፤ ቀለም ንክር አለላዎችም አያስፈልጉትም፡፡ ዋናው ነገር የተፈለገውን መጠን ቅርጹን እየጠበቁ ከታች (ከመቀመጫው) ጀምሮ መስፋት ነው፡፡ ሙያተኞቹ ወ/ሮ ሌይላ ኢብሮና ወ/ሮ ራሂማ መሀመድ እንደሚሉት የ«ቡሬ»ው መቀመጫ ከመሬት ጋር የተገናኘ በመሆኑ በሚቀመጥበት ጊዜ አፈር እንዳይበላው ጠንካራ ቆዳ ይሰፋበታል፡፡ የአፉም ጠርዝ በቀጭን የለፋ ቆዳ ሊለጎም ይችላል፡፡ ይህም እጅ እንዳይበላውና ሰበዙ እንዳይለቅ ይረዳል ይላሉ፡፡

ሌላው የ«ቡሬ» (Buuree) አይነት በተለየ ጥበብና በእውቀት ሙያተኛ ሴት የሚሰፋው ነው፡፡ ይህ አይነቱ «ቡሬ» የተለያዩ ቀለም ንክር የሆኑ አለላዎች ያስፈልጉታል፡፡ አለላዎቹ በተለያዩ ቅርጾች (በሶስት፣ አራት፣ ክብ ወዘተ.) እየሆኑ ወይም ደግሞ በአግድም ዚግዛግ እየሰሩ ይሰፋሉ፡፡ አለላዎቹ እየተሰባጠሩ የሚሰፉበት ውበቱን ለመጠበቅና መስህብነት እንዲኖረው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በክዳኑ እና በዋናው የቡሬው አፍ ጠርዝ ዙሪያውን የለፋ ቆዳ በቀጭኑ ይለጎምበታል፡፡ ይህ ለየት ባለ ሁኔታና ሙያተኛ ሴት የሚሰፋው ቡሬ ቅርጹም ከዱቄት መያገሪው «ቡሬ» የተለየ ነው፡፡ ምንም እንኳን የሁለቱም ቡሬዎች የስፌት አጀማመር ተመሳሳይ ቢሆንም ለጌጥ የሚሰፋው ቡሬ እንደ ዱቄት መያገሪው ቡሬ ከታች በጣም ስፋት ያለው ወይም የዋዲያት ቅርጽ ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም ከታች ወደ ላይ የተቀለበሰው ሰበዝ በመጠኑ ሰፋ እንዲል ከተደረገ በሁዋላ፣ ቅርጹ እርከን እየሰራ ሳይለዋወጥ የጣሳን ቅርጽ እንደያዘ እስከ አፉ መዳረሻ መዝለቁ ነው፡፡



ፎቶግራፍ 25፡- በልዩ የአሰራር ጥበብ የሚሰራው ቡሬ

ለውበቱ ሲባል በሳሎን ቤት የሚቀመጠው ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በሙያተኛ ሴት የሚሰፋው ቡሬ መክደኛም በኣለላ ስፌት ከመሰፋቱም በላይ የተለያዩ ቀለም በኣላቸው ጨሌዎች ያስጌጡታል:: መክደኛው የድስት እፊያን ቅርጽ ቢይዝም ቁንጠኛ አሰፋፉ የተለየ ያደርገዋል:: ቁንጠኛነቱም የክዳኑ የእጅ መያዣው የሰፌድ ቅርጽ ወይም ዝርግ እና ክብ የሆነች ስፌት የተሰፋባት መሆኑ ነው:: ጨሌዎቹም የሚንጠለጠሉት በዚህችው ክብ ቅርጽ ላይ ዙሪያዋን ነው:: በክቧ ሰፌድ መሰል ቅርጽና በዋናው ክዳን መካከል ሲሊንደር ቅርጽ ያለው ቀንድ ወይም ወፍራም ፕላስቲክ ይገባበታል:: ፎቶግራፍ 25ን ልብ ይሏል:: በኣጠቃላይ የዚህ ኣይነት ቡሬ ለውበቱ ሲባል ቤት እንዲያደምቅ በሳሎን የሚቀመጥ ሲሆን በኣማራው ባህል ቤት ለማድመቅ ሲባል ከሚቀመጠው መሶበወርቅ ጋር ይመሳሰላል በኣገልግሎቱ::

የዚህ ጥናት ኣቅራቢ ለጌጥም ሆነ ዱቄት ለመያዝ የሚያገለግሉትን ቡሬዎች ለማየት እድል ኣግኝቷል:: 25 ኪሎ ዱቄት ይይዛል የተባለው መካከለኛ ቡሬ ቁመት 58፣ የኣፉ መጠነ ዙሪያ 71፣ ከኣፉ ዝቅ ብሎ ያለው መጠነ ዙሪያ 105፣ ከወደ መቀመጫው ከፍ የሚለውና ሰፋ ያለው ኣካሉ መጠነ ዙሪያ 140፣ የመቀመጫው መጠነ ዙሪያ 110፣ የመቀመጫው ዲያሜትር 27፣ የኣፉ ዲያሜትር 22 ሳንቲሜትር እንደሆነ ኣረጋግጧል:: (የኣሀዞቹ መለኪያ ሳንቲሜትር ነው):: «ቡሬ»ውን በፎቶ 24 «ሀ» ላይ ይመልከቱ::

ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

በጣም ትልቅ የተባለውና ሁለት ኩንታል ዱቄት ይይዛል ተብሎ የተገመተው «ቡሬ» ደግሞ ቁመቱ 144 ሳንቲሜትር፣ የወገቡ መጠነ ዙሪያ ሁለት ሜትር ከ25 ሳንቲሜትር፣ ከወገቡ በላይ ያለው አካሉ መጠነ ዙሪያ አንድ ሜትር ከ60 ሳንቲሜትር፣ የመቀመጫው ዲያሜትር 54 ሳንቲሜትር፣ የመቀመጫው መጠነ ዙሪያ 150 ሳንቲሜትር፣ የአፉ ዲያሜትር 25 ሳንቲሜትር፣ የአፉ መጠነ ዙሪያ 90 ሳንቲሜትር መሆኑን በተለካበት ወቅት የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል:: ሁለቱንም ቡሬዎች ከፎቶግራፍ 24 «ሀ» እና «ለ» ላይቶ ማመዛዘን ይቻላል::

*አገልግሎት:-* በተለይ በልዩ የአሰራር ጥበብ ያልተሰራው «ቡሬ» ዋና አገልግሎቱ የገንፎ ዱቄት ማስቀመጫ መሆን ነው:: ሀጂ አብዱልጀዋድ አዲ በ«ቡሬ» ውስጥ የሚቀመጥ ዱቄት ከተፈተገ ገብስ በጥንቃቄ የሚዘጋጅ ሲሆን ግልጋሎት ላይ የሚውለውም ወሳኝ የሆነ ችግር ለምሳሌ የሰው ሞት፣ በሰርግ፣ ወይም ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ወይም ደራሽ እንግዳ ከመጣ እንጂ በአዘቦቱ እንደሚደረገው ዱቄቱ እየተወሰደ በጥቅም ላይ አይውልም:: ከዚህ በላይ የተጠቀሰውንና ስለ «ቡሬ» አገልግሎት የተሰጠውን ሀሳብ በከዱ ገበሬዎች መንደር ያገኘሁኣቸው የ60 አመቱ አዛውንት ሀጂ መሀመድ አደምም ይጋሩታል::

በሌላ በኩል በልዩ ሙያተኛ ሴት የሚሰፋውና በአለላ ያጌጠው «ቡሬ» ግን አገልግሎት የሚሰጠው በቤት ውስጥ ማድመቂያ በመሆንና ለውበቱ ነው:: ይህም በተለይ በከተማ ለአይን እይታ በሳሎን ቤት ቦታ ተዘጋጅቶለት የሚቀመጥ ነው::

## 4.6. ከቆዳ የሚሰሩ እቃዎች

«የቆዳ ኦኮሌ» እና «አገልግል» የተባሉትን መገልገያ ቁሳቁስ በዚህ ክፍል እንመለከታለን::

### 4.6.1. ትውራዊ ዳራ

በኢትዮጵያ የቆዳ ስራ ረጅም እድሜ አለው:: «በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ ቁሳቁስ እንደ ኮርቻ፣ ጋሻ፣ ሰገባ ወዘተ. ባካተተ መልኩ በስፋት የሚሰሩት ከቆዳ ነው» ሪቻርድ ፓንክረስት (Richard Pankhurst 1964፣ 230-231)::

በቤት ውስጥ የመገልገያ በተለይም ከመመገቢያ ቁሳቁስ አንጻር ካየነው የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ብዙም የቆዳ ውጤቶችን ሲጠቀሙ አይታዩም:: ይህ ለምን ይሆን? ብዬ ጥያቄ አንስቼ ነበር:: አዛውንቶቹ ሀጂ አብዱልጀዋድ አዲ እና ሀጂ ፈቂ ሀሰኖ መልሱን የሚመልሱት ከኦሮሞዎች ከብቶችን ከመውደድ ጋር አያይዘው ነው:: ይህ ደግሞ ብዙ ጊዜ የሚደመጥ እውነታ ነው:: በዚህም መሰረት ሶስት ምክንያቶች ሰጥተውኛል:: እነዚህም:-

1. ኦሮሞዎች ከብቶችን ከማፍቀራቸው የተነሳ አርደው ወይም ገድለው በቆዳቸው ከሚጠቀሙ ይልቅ ከእነሱ የሚያገኙትን ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ስለሚበልጥባቸው ነው፡፡
2. የከብት ብዛት የጌትነት፣ የባላባትነት፣ ክብር ማስገኛ ከመሆኑም በላይ ለሽምግልና ለመመረጥ፣ ታዋቂነትን ለማጎናጸፍ የሚረዳ ስለሆነ እገሌ ይህን ያህል በረት ከብት አለው መባልን ይፈልጋሉ፡፡
3. የቆዳን ውጤት የመጠቀም እድል እንኳን ቢኖር መመገቢያ ቁሳቁስ ከማድረግ ይልቅ ለልብስና ለመሳሰሉት ማዋልን ይመርጣሉ፡፡

ይህም በመሆኑ በበኣል እና በልዩ ልዩ ዝግጅት ሰርግ፣ ተዝካር፣ (ሰደቃ) ወዘተ. ወቅት ከሚታረዱት እና በኣንዳንድ ኣጋጣሚ ለምሳሌ በህመም ወይም በከብቱ ላይ አደጋ ሲደርስ ከሚሞቱ ከብቶች የተገኙትን ቆዳዎች ለመኝታ፣ የወተት እቃዎቻቸውን ለማስጌጥ የሚውሉትን የጠፍር ጥብጣቦች (Straps) ለመስራት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ይሁንና በዚህ ክፍል ኣንድ ሙሉ በሙሉ የቆዳ ስራት የሆነ ቁስን፣ ሁለት የቆዳና የስንደዶ ውጤት የሆነ መመገቢያ እቃን እናያለን፡፡ እነዚህ ሁለት እቃዎች እንደ ኣስፈላጊነታቸው መመገቢያም ሆነ የምግብ መያገ በመሆን ያገለግላሉ፡፡


### 4.6.2. የቆዳ ኦኮሌ (OKOLEE GOGAA)

*ኣሰራር፡-* የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች የ«ኦኮሌ» የ(Okolee) ኣሰራር ሁለት ኣይነት ነው፡፡ እነዚህም የቆዳ እና የእንጨት ውጤቶች ናቸው፡፡ (ፎቶ 7ን ይመልከቱ)፡፡ ሁለቱም የኦኮሌ ኣይነቶች በሙያተኞች የሚሰሩ ናቸው፡፡ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ፣ የቆዳው ኦኮሌ ጥንት ከጎሽ ቆዳ ይሰራ እንደነበር ይተርካሉ፡፡ በዘመናችን ግን በሰል ያለ ኮርማ፣ የሰንጋ ወይም የትልቅ ከብት ቆዳ ነው የሚያስፈልገው፡፡ የፍየል፣ የበግ ወይም የመሳሰሉት የዱር እንስሳት ቆዳ ግን ለኦኮሌ ስራ ጥሩ እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ የሚሰጡት ምክንያት ስስ ስለሆነ በቀላሉ ይበጣጠሳል በማለት ነው፡፡

ቆዳው በእርጥቡ ከተቆረጠ በሁዋላ በራሱ በቆዳው ጥብጣብ ይያዛል፡፡ (ኣፉ ብቻ ሲቀር ዙሪያውን ይሰፋል)፡፡ በሚሰፋበት ጊዜ እንዳይበላለጥና እንዳይዛነፍ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ ሳይጨራመት እንዲቆይም ኣፈር ወይም ፍግ ይጠቀጠቅበትና ለሳምንት በጸሀይ ላይ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ መድረቁ ሲረጋገጥ የተፈለገውን ቅርጽ ጠብቆ እንዲቆይ በሞራ እያሹ ያለዝቡታል፡፡ በግራና በቀኝ የሚውል ማንጠልጠያም ከቆዳ ጠፍር ይዘጋጅለታል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

*ኣገልግሎት፡-* «ኦኮሌ» (Okolee) በቆላና በደጋ የተለያየ ኣገልግሎት ኣለው፡፡ የቆዳው ኣኮሌ በቆላ ኣካባቢ ከግመል ወተት ያልቡበታል፣ ውህም ይቀዱበታል፡፡ ግመል ረዥም በመሆኗ ቁጭ ብሎ ለማለብ ስለማይደረስባትና ኣድካሚነትም ስላለው ኣላቢው ማንጠልጠያውን በኣንገቱ ያስገባና ያልብበታል፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ «ኦኮሌ» ማርን ከቀፎ መሰብሰቢያም ነው፡፡ ሀጂ ኣብዱልጀዋድ እንደሚሉት ማርን ከቀፎ ለማጠራቀም ከእንጨቱ ይልቅ የቆዳው «ኦኮሌ» በጣም ተፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ማር ቆራጩ እዛፍ ላይ ሲወጣ ይዞት ይወጣና በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ያንጠለጥለዋል፡፡ ድንገት እንኳን ኣምልጦት ቢወድቅ ኣይሰበርም፡፡ ከዚህም በላይ ከእንጨቱ ይልቅ ኣፉ ሰፋ ስለሚል ማሩን እንደልብ ለመክተት ያገለግላል፡፡ ማሩን እየከተተ በጊቻ ገመድ ይዞ ቁልቁል ለመላክም ቀላሉ ይኸው የቆዳ ኦኮሌ ነው፡፡ ድምጽም ስለማይፈጥር ይመረጣል፡፡ በተለይ ከቆለኛ ኦሮሞዎች ኣኗያ ካየነው ከግመል ወተትን ለማለቢያ የመጠቀማቸው ሁኔታ ባህላዊ ፋይዳውን ያጎላዋል፡፡ በሌላም በኩል ማሩን በመቁረጥ ላይ ባሉበት ቦታ ሊመገቡበት ይችላሉ፡፡ ማሩን በሌላ እቃ እየቀነሱ ለመመገብ ሲታሰብም መጀመሪያ የሚቀርበው ከቆዳ በተሰራው ኦኮሌ ነው፡፡ የቆዳ ኦኮሌ በመጠን ትንሽና ትልቅ ተደርጎ ሊሰፋ ይችላል፡፡ ከእነዚህም ትንሹ በቆላ ኣካባቢ ወተት ለመጠጫነትም ያገለግላል፡፡ ፎቶግራፍ 26 ላይ ልጁ የቆዳ ኦኮሌን ኣጠቃቀም ሲያስረዳ ያሳያል፡፡



ፎቶግራፍ 26፡- የቆዳውን ኦኮሌ በማስተዋወቅ ላይ

## 4.6.3. ኣገልግል (GILGILII) ጊልጊሊ

*ኣሰራር፡-* ኣገልግል ሁለት ኣይነት አሰራር ኣለው፡፡ 1ኛው ከስንደዶ ስፌት ብቻ የሚሰሩ ሲሆን 2ኛው ደግሞ ከስንደዶ ከተሰሩ በሁዋላ ዙሪያውን በቆዳ የሚለጎመው ነው፡፡ በዚህ ላይ የምንመለከተው በቆዳ የሚለጎመውን ይሆናል፡፡

የተፈለገው ኣገልግል በተፈለገው መጠንና ቅርጽ በእውቅ ባለሙያ ሴት ይሰፋል፡፡ ኣሰፋፉ በቅርጽና በመጠን ከሚለያይ በስተቀር ከሌሎች የስፌት እቃዎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የስፌቱ ስራ ከተጠናቀቀ በሁዋላ በደንብ የለሰለሰ ቆዳ በመጠኑ ተቆርጦ ይዘጋጃል፡፡ የሚዘጋጀው የለሰለሰ ቆዳ ለመክደኛውም ሆነ ለእናት ኣገልግሉ የሚበቃ ያህል ነው፡፡

የለሰለሰው ቆዳ ምንም ኣይነት መሸብሸብ ሳያሳይ ከኣገልግሉ ጋር ልክክ ብሎ መግጠም ኣለበት፡፡ ለዚህም ሲባል ነው መጀመሪያውኑ ቆዳው እንዲለሰልስ የሚደረገው፡፡ የምትሰፋው ባለሙያ መጀመሪያ ከኣገልግሉ ከኣንድ ጠርዝ ትጀምርና ለስልሶ በተዘጋጀ ቀጭን የጠፍር ክር በወስፌ ቀዳዳውን እያዘጋጀች እና የጠፍሩን ክር በቀዳዳው እያስገባች ትሰፋለች፡፡ በምትሰፋበት ጊዜ ባለማቋረጥ ቆዳውን በእጇ እየሳበች ማስተካከል ይጠበቅባታል፤ ይህንን የምታደርገው ቆዳው ተሸብሽቦ ኣገልግሉን ቅርጽ እንዳያሳጣው ነው፡፡ በዚህም ኣይነት ዙሪያውን ታዳርሳለች፡፡ በመክደኛው ላይ የሚገጠመውም ቆዳ እንደ እናት ኣገልግሉ ሁሉ ከጠርዙ ጀምሮ በደንብ እየተወጠረ ዙሪያውን ይሰፋል፡፡ በመክደኛው መሀል ላይ ኣንድ ጠንካራ የቆዳ ገመድ ይሰፋበታል፡፡ ይህም ከዋናው ኣገልግል ጋር የተያያዙትን በተለምዶ ኣጠራር ጆሮ የሚባሉትን እና በጣምራነት ከዋናው ኣገልግል ጋር የሚሰፉትን የጠፍር ጥብጣቦች በኣንድነት በማያያዝ የኣገልግሉ ክዳን በደንብ እንዲገጥም ለማድረግ ነው፡፡

በዋናው ኣገልግል ክብ ዙሪያ በተወሰነ ርቀት ላይ የሚሰፉት ጥንድ ጥንድ የሆኑ የቆዳ ጥብጣቦች ዋናው ኣስፈላጊነታቸው በጉዞ ወቅት ኣገልግሉ እና መክደኛውን ኣቆራኝቶ ለማሰር ነው፡፡ ይህም በውስጡ ያለውን ምግብም ሆነ ሌላ ነገር እንዳይወድቅና ለኣያያዝም ምቹ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ እነዚህን ከተለያዩ ማእዘናት የመጡ መንታ የጠፍር ጥብጣቦች በክዳኑ መሀል ላይ በማገናኘት ኣንድ የጋራ ነጥብ እንዲሰሩ የሚያደርጋቸው በክዳኑ መሀል ላይ የተሰፋው (የተያያዘው) «ሳምሳ» የሚባል የጠፍር ጥብጣብ ነው፡፡ (ፎቶግራፍ 27ን ይመልከቱ)፡፡



ፎቶግራፍ 27:- ትልቅና ትንሽ አገልግል

በዋናው ኣገልግል ላይ የሚሰፉት ጣምራ ጣምራ የጠፍር ጥብጣቦች (በተለምዶ ኣጠራር ጆሮዎች) እንደ ኣገልግሉ መጠን በሶስት ወይም በኣራት ኣቅጣጫ ላይ ሊሰፉ (ሊያያዙ) ይችላሉ። ፎቶ 27 ላይ ትልቁ ኣገልግል ባለ ኣራት ጥብጣብ ሲሆን ከእሱ በላይ የተሰቀለውና ኣነስተኛው ደግሞ ባለ ሶስት ጆሮ የጠፍር ጥብጣብ ኣለው። ከዚህም በስተቀር በዋናው ኣገልግል በቅርብ ርቀት ላይ በግራና በቀኝ ሰፋ ያለ የጠፍር ማንገቻ ይሰፋበታል። ይህ ማንገቻ ትልቅ ኣገልግሎት ኣለው። በፎቶው ላይ እንደሚታየው በቤት ውስጥ ሲሆን በግድግዳ ላይ ለመስቀል ያመቻል። ወደ ውጭም ይዘውት ሲሄዱ በኣንገት አስገብቶ ለማንገት፣ ወይም በፈረስ ተቀምጠው የሚሄዱም ቢሆን በኮርቻው ቀዳማ ወይም ዳህራይ ላይ እንዲንጠለጠል ይረዳል። ዋናውንም ሆነ የኣገልግሉን መክደኛ የውስጠኛ ክፍል ምንም ኣይነት ቆዳ ኣይነካቸውም። በስንደዶው ብቻ እንደተሰፉ ይቆያሉ። ኣብዛኛዎቹ የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች መመገቢያ እቃዎች እንደ ጪጮ፣ ማለቢያ፣ ኪላ ወዘተ. የመሳሰሉት ውበት እንዲኖራቸው የሚደረጉት በተለያዩ ቀለማት ባሸበረቁ ጨሌዎችና ዛጎሎች በመሆኑ የእቃዎቻቸው ኣይነተኛ መለያ (መታወቂያ) እንደሆኑ ይታሰባል። እንደሌሎቹ የስፌት እቃዎች ሁሉ ኣገልግልም በክዳኑ ላይ እና በዋናው መያዣ ኣገልግል ጎን በተንዘረፈፉ የጠፍር ጥብጣቦች ላይ ልዩ ልዩ ቀለም ንክር የሆኑ ጨሌዎችና ዛጎሎች እንዲያደምቁት ይደረጋል። የባህሉ ባለቤቶች የሆኑት ኣልፊያ ሀጂ እና በድርያ ካዎ ይህን ኣስመልክተው የሚከተለውን ተናግረዋል። «ኦሮሞዎች ኣገልግልም ሲሰፉ እንደሌሎች የስፌት እቃዎቻቸው ጨሌዎችና ዛጎሎችን በጠፍሮች ላይ በመስፋት ውበት እንዲኖረው ያደርጋሉ። ይህም ለባህላዊ እቃዎች ኣይነተኛ መለያ ነው» ይላሉ።

***ኣገልግሎቱ፡-*** ኣገልግል ለተለያዩ ተግባራት በጥቅም ላይ ይውላል:: ጦርነት ሲኖር ኣብሮ ዘማች ነው:: በቤት ውስጥም ከተቀመጠ ምግቦችን ከመያገር ጀምሮ ልዩ ልዩ ነገሮች ይቀመጡበታል፤ ይህ ግን እንደ ባለቤቶቹ ፍላጎት የሚወሰን ነው:: በጎባ ወረዳ ያሉ ኦሮሞዎች ቂጣ፣ ጨጨብሳ፣ ጭኮ፣ ሸከካና የመሳሰሉትን ምግቦች ያስቀምጡበታል፤ ወይም ወደ መንገድ ሲሄዱም የስንቅ መያገርቸውና መመገቢያቸው ነው:: እረኞችም ከብቶቻቸውን ራቅ ወዳለ ቦታ ሲያስማሩ ምግባቸውን የሚሰንቁት በኣገልግል ነው::

ኣገልግልን በተመለከተ ያነጋገርኳቸው የኦሮሞ ተወላጆች የተለያየ ሀሳብን ያስተናግዳሉ:: ኣንዳንዶቹ ኣገልግል የኦሮሞ የባህል እቃ ሳይሆን በሁዋላ ላይ በሂደት በጥቅም ላይ የዋለ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ኦሮሞዎች ለከብቶቻቸው ሳርና ውሀ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ከመንቀሳቀሳቸው ጋር ለስንቅ መያገር እንዲሆናቸው ጥንቱንም ይጠቀሙበት የነበረ ነው ይላሉ:: ክርክሩ እንዳለ ሆኖ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ የቀረበበት ምክንያት ኣሰራሩንና ጠቃሚነቱን ማስተዋወቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ምናልባት ወደፊት ተመሳሳይ ርእስ ይዞ ለሚነሳ ኣጥኚ የመነሻ ፋይዳ ይኖረው ይሆናል ከሚል ግምት ነው::

***ባህላዊ ፋይዳ፡-*** ኣገልግል ስንቅ የሚሰነቅበት እንደመሆኑ መጠን በጦርነት ጊዜ ኣብሮ ዘማች ነው፣ በስደትም ወቅት ከሌሎች እቃዎች ይልቅ ኣብሮ የሚሰደድ ነው፣ የወረዳው ኦሮሞዎች ከብቶቻቸውን ለግጦሽ ራቅ ወዳለ ቦታ ሲያሰማሩም ሰንቀውበት ይጓዛሉ:: ስለሆነም ዘማቾቹም ይሁኑ ተሰዳጆቹ፣ እረኞችም ይሁኑ የእለት ተጓዦች በኣንድ ቦታ ተሰብስበው ይመገቡበታል:: በኣገልግል መሰነቁ ባህላዊ ፋይዳውን ሲያመለክት፣ ተሰብስቦ መብላቱ ደግሞ ማህበራዊ ፋይዳውን ይጠቁማል::

## 4.7. ከቀንድ የሚሰሩ እቃዎች

በዚህ ክፍል የምናተኩርባቸው መመገቢያና መጠጫ ቁሳቁስ፣ የቀድ ስራት የሆኑት ዋንጫ እና ማንኪያ ናቸው::

### 4.7.1. ትውራዊ ዳራ

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከቀንድ በሚሰሩ ቁሳቁስ መጠቀም ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ነው:: «የበሬ፣ የጎሽ፣ የዋልያ እና የሌሎችም ቀንዶች ለመጠጫ፣ የጎራዴ እጄታንና የመሳሰሉት እቃዎች በሙያው ጠበብቶች ሲሰሩ ነበር» ሪቻርድ ፓንክረስት (Richard Pankhurst 1964፣ 240)::

የቀንድ ስራ የዱር ኣውሬዎችን ከማደን ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው:: ጥንታውያን ሰዎች ኣውሬ ማደንን የሀይል ብቃት ማረጋገጫ፣ ሚስት ለማግባት እንደማሟያ ነጥብ ወዘተ.



ILS LIBRARY ADDIS ... SITY

በጥቅሉ ኣውሬ ገድሎ ግዳይ መጣል እንደዋና ነገር ስለሚቆጠርና በህብረተሰቡ ዘንድም ክብርና ዝናን ስለሚያስገኝ ኣውሬዎችን ሲገሉ የሚያገኙትን ቀንድ በልዩ ልዩ ጥበባዊ ብቃት እየሰሩ ለልዩ ልዩ ኣገልግሎት ማዋል የተለመደ ነበር።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ልማድ ከሚጋሩት ኢትዮጵያውያን ውስጥ የኦሮሞ ብሄረሰቦችም ይገኙበታል። በተለይ ኦሮሞዎች በተለያየ ምክንያት ካልሆነ የከብቶቻቸውን ቀንዶች ለዚህ ተግባር ባያውሉም የዱር ኣውሬዎችን እየገደሉ ግን የተለያዩ የቀንድ ውጤቶችን ሲሰሩ ቆይተዋል። እንደ ሀጂ ከዴ ጎበና ከሆነ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች በባህላዊ እደጥበብ የቀንድ ዋንጫዎችንና ማንኪያዎችን ይሰሩና ይጠቀሙ ነበር። ሙያተኞችም ኣልፎ ኣልፎ ነበሩ። ዛሬ ግን ኣውሬ ማደኑም ሆነ ከቀንድ ይሰሩ የነበሩ ልዩ ልዩ ቁሳቁስ በልማዳዊ እደጥበብ ሲሰሩ ኣይታይም። ይሁንና በዚህ ክፍል ለመመገቢያ ተግባር የሚውሉትን ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን።

### 4.7.2. ዋንጫ (WAANCAA)

ዋንጫ ከቀንድም ሆነ ከሸክላ ሊሰራ ይቻላል። በዚህ ላይ የምንመለከተው ግን ከቀንድ ስለሚሰራው የዋንጫ ኣይነት ነው። ምንም እንኳን በኣሁኑ ጊዜ ሲሰራና በጥቅም ላይ ሲውል ባይታይም፣ ቀደም ሲል የነበረውን ኣሰራርና ኣገልግሎት በተመለከተ ሀጂ ከዴ ጎበና የሰጡኝ መረጃ ቀጥሎ ያለው ነው።

> *የዱር እንስሳም ይሁን ለማዳ ቀንዱ ተፈላጊ ከሆነ ይቆረጥና ኣጥንቱ እንዲወጣ ይደረጋል። ኣወጣጡ ሁለት መንገዶች ኣሉት። ኣንደኛው በራሱ ጊዜ እንዲወጣ በጸሀይ ላይ ማቆየት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቀንዱን በወናፍ የእሳት ወላፈን እያሞቁ እንዲላላ በማድረግ ነው። ኣጥንቱ ከሁለቱ በኣንዱ ዘዴ ከወጣ በሁዋላ ቀንዱን ለተፈለገው የእቃ ኣይነት ለመስራት በመጀመሪያ የተፈለገውን የእቃ ኣይነት ቅርጽ ያለው ጠንካራ እንጨት ይዘጋጃል። እንጨቱ ሲመታ የማይፈረካከስ ወይም የማይሰነጣጠቅ መሆን ኣለበት። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የእንጨቱ ቅርጽ የሚወሰነው ከቀንድ ሊሰራ በታቀደው የእቃ ኣይነት ነው። ከዚህ በሁዋላ ቀንዱን በወናፍ የእሳት ወላፈን እያሞቁ ላላ ባለ ቁጥር የተቀረጸውን እንጨት ከትቶ ወደ ውስጥ መምታት ነው። የተፈለገው ቅርጽ ላይ ከተደረሰ በሁዋላ ቀንዱ እንዲጠነክር በእሳት ሳያሞቁ ማስቀመጥ ነው። ወደነበረበት ጥንካሬ እንደተመለሰ የገባውን እንጨት በመሮ እየሰረሰሩ ወይም እየፈረካከሱ ያወጡታል። ከዚህ በሁዋላ በውስጥም በውጭም ያለው የቀንዱ ኣካል እንዲለሰልስ ይደርጋል። ማለስለሻዎቹ ሰፋጭ (ባልጩት)፣ ስለታም ሰንጢ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ጦር ያለ ስለታም መሳሪያ የተገጠመለትና በሰው ሀይል የሚሽከረከር (እሳቸው እንደሸማኔ ማዳወሪያ የሚዞር ይሉታል) ኣለ። ይህንን መሳሪያ ኣንዱ ኣጥብቆ ሲይዝ ሌላው ሰው የቀንዱን ዋንጫ በኣፉ በኩል ወይም እንዲለሰልስ በተፈለገው በኩል ያዞረዋል። በዚህ ጊዜ እየተሞረደ ይለሰልሳል፣ ደንበኛውን ቅርጽም እየያዘ ይሄዳል።*

ሀጂ ከዴ ጎበና የመሳሪያውን ስም ለጊዜው ማስታወስ እንዳልቻሉ ከነገሩኝ በሁዋላ የኣሰራሩን ሁኔታ እንደሚከተለው ቀጥለዋል::

ከትልቅ ኣውሬ እና የቤት እንስሳት የሚገኘው ቀንድ ትልቅ ከሆነ ከወደ መቀመጫው ኣፍ (ቀዳዳ) ላይኖረው ይችላል:: ይሁን እንጂ ቀዳዳ ካለው፣ ከቀንድ የተገኘ ጠንካራ ጉራጅ ተቆርጦ፣ ይከረከምና በቀዳዳው በኩል በሀይል ማስገባት ነው:: ለማስገባት ግን ዋናው ተተኳሪ የቀንድ ዋንጫ በእሳት ወላፈን መላላት ይኖርበታል:: በዚህ ኣይነት በግድ የገባው ጉማጅ ቀንድ፣ የቀንዱ ዋንጫ እየደረቀና እየጠነከረ ሲሄድ ግጥም ብሎ ይይዛል::

ቅርጹንና ኣንዳንድ ንቅሳቶቹንስ እንዴት ያወጡለታል? በማለት ለጠየኳቸው ሲመልሱ

*«ቅርጹን ወይም የሸንትር ንቅሳቱን የሚያወጡት ቀደም ሲል በገለጽኩልህ ጦር መሰል ስለታም መሳሪያ ላይ የቀንዱን ዋንጫ በማዞር ነው:: መሳሪያው ስለታም ስለሆነ በዋንጫው ላይ መስመር እየሰራ ይሄዳል:: ቅርጹ (ንቅሳቱ) የተለያየ ኣይነት ቢሆንም እንኳ በተጠቀሰው የኣወጣጥ ዘዴ እየተጠቀሙ ይሰራሉ:: መሳሪያው የሌላቸው ደግሞ በስለታም ሴንጢ እየቦረቦሩ ጥበባዊ በሆነ መንገድ ሊያወጡለት ይችላሉ የዚህ ኣይነቱ ስራም የቀንድ ዋንጫ ንቅሳት ይባላል»::*



ፎቶግራፍ 28:- የቀንድ ስራት የሆኑ ዋንጫዎች

ኣንዳንድ የቀንድ ዋንጫዎች ወይም የቀንድ መለኪያዎች ከወደ መቀመጫቸው ለየት ያለ መቆሚያ ይሰራላቸዋል:: (ፎቶግራፍ 28ን ይመልከቱ):: ታዲያ ይህስ እንዴት ሊወጣላቸው (ሊቀረጽላቸው) ይችላል? ብዬ ላቀረብኩት ሲመልሱ

*መጀመሪያ ከወደ መቀመጫው ክፍት የሆነውን ለመድፈን ቅድም እንደነገርኩህ ጠንካራ የቀንድ ክፍል ተፈልጎ ይቆረጥና በልኩ ይከረከማል:: ኣንዳንዱ በዚያው ጨርሶ ተመትቶ የሚገጥም ሲሆን ኣንዳንዱ ግን ለተለየ ቅርጽ ሲባል ተረፍ እንዲል ይደረጋል:: እንግዲህ ይህ ተረፍ ያለው ነው በእግሩ በኩል የተለየ ቅርጽ እዚህ ፎቶ ላይ እንዳለው የሚወጣለት:: ይህንንም በሞረድ እየሞረዱ፣ በባልጩት እየላጉ፣ መሳሪያው ያላቸውም በመሳሪያው እያስተካከሉ ቅርጹን ያወጡለታል:: ለዚህ ኣይነቱም ሆነ ለሌላው ቅድም ለነገርኩህ ሙያተኛን ይጠይቃል::*


ለሀጂ ከዶ ሌላም ጥያቄ ኣክዬ ነበር:: ብዙውን ጊዜ ከኣፉ ክብ ቅርጽ ያለውና ሰፋ ያለ፣ ከወደ መቀመጫው ደግሞ ሾጠጥ ያለ ቅርጽ ነው የማየው፤ ሌላ ኣይነት ቅርጽ ያለው ዋንጫ ኣይሰራም? በማለት ላቀረብኩት ሲመልሱ፣

*እኔም በእድሜዬ ያየሁት ይኸንን የመሰለ ነው (በፎቶግራፉ ላይ ያለውን ማለታቸው ነው) ስሰማ ግን ፣ ባለቤቱ እንደወደደ ነው:: ኣራት ማእዘን ያለው እንጨትም በማስገባት ይሰሩታል ኣሉ:: እንደ ኣራት ማእዘን ጣሳ (ሳቅ እያሉ):: ቅድም እንዳልኩህ ግን ከወደ እግሩ ዘንግ ብቻ ሳይሆን በሚጠጣበት ጊዜ በእጅ ለመያዝም እንዲያመች ነው:: ኣንዳንድ ዋንጫ በሁለት እጅ ካልሆነ እኮ ኣይነሳም::*

የቀንድ ዋንጫ መስራት የወንዶች መለያና ተግባር ነው:: ለመስራት የሚያስፈልገውም ከወናፍ የሚገኘው የእሳት ወላፈን የሚከናወነውም በወንዶቹ ነው:: ስለሆንም የስፌት ስራ የሴቶቹ ብቻ መለያ (መታወቂያ) የመሆኑን ያህል የቀንድ ዋንጫ ስራም ለወንዶች መለያ ነው ማለት ይቻላል::

የቀንድ ዋንጫዎች በተለያየ መጠን ይሰራሉ:: በመስክ ላይ በታየው መሰረት ትልቅ ዋንጫ የሚባለው ወደ ኣፉ መዳረሻ ላይ ያለው መጠነ ዙሪያ 38፣ የወገቡ መጠነ ዙሪያ 31፣ ወደ መቀመጫው (መቆሚያው) መዳረሻ 24፣ ከኣንዱ የኣፉ ጠርዝ ወደ ሌላው ጠርዝ ያለው ርዝመት 12፣ ጠቅላላ ርዝመት 12.5፣ የዋንጫው መቀመጫ ዲያሜትር 5.5፣ ተቆርጦ በመቀመጫው በኩል የተገጠመለት ግጣም ዲያሜትር 5 ሳንቲሜትር መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል:: (የሁሉም ኣሀዞች መለኪያ ሳንቲሜትር ነው)::

***ኣገልግሎት:-*** ጥንት ከኣደን ጋር በተያያዘ ሁኔታ የክብር እና የጌጥ እቃ ሆኖ ይታይ ነበር:: ገዳይ ይጠጣ የነበረውም በቀንድ ዋንጫ እንደነበር ኣዛውንቱ ሀጂ ከዶ ይናገራሉ:: በኦሮሞ ባህል የቀንድ ዋንጫ ለብርዝ፣ ለእርጎ፣ ለወተት እና ለመሳሰሉት መጠጫ እንዲሆን ይጠቀሙበት ነበር:: ዛሬ ዛሬ ግን ሙያተኞቹም የሉም፤ ዘመናዊ የመጠጫ እቃዎች በተለያዩ ቅርጾችና ኣይነት የሞሉበት ወቅት በመሆኑ የቀንድ ዋንጫን ማግኘት ይከብዳል:: በፎቶግራፍ 29 ላይ ሁለቱ ሰዎች የቀንድ ዋንጫ ይዘው ኣሰራሩን ሲመለከቱ ነው የሚታዩት:: በኣጠቃላይ ከገዳይ መጠጫነት እና በባላባቶች ቤት ከመገኘቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጥንት የነበረው ባህላዊ ጠቀሜታ እና ኣገልግሎቱ በዚህ ዘመን፣ በዘመነኛ የመጠጫ እቃዎች ስለተቀማ ለእይታ እንኳን የሚገኘው በኣንዳንድ ቤቶች ነው::



ፎቶግራፍ 29፡- የቀንድ ዋንጫዎችን አሰራርና ቅርጽ ሲመለከቱ

*ባህላዊ ፋይዳ፡-* የቀንድ ዋንጫ በጥንቱ ልማድ የተከበሩ ሰዎች የሚባሉ ለምሳሌ ኣዳኞች፣ በሽምግልና ሚና የሚጫወቱ፣ በገዳ ስርኣት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ወዘተ. በጎባ ወረዳም ይሁን በሌሎች ቦታዎች የሚኖሩ ኦሮሞዎች መጠጫ እንደነበር ሀጂ ከዴ ጎበና በትዝታ ያስታውሳሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከኣገልግሎቱም በላይ ባህላዊ ፋይዳው በእጅጉ እንዲያመዝን ያደርገዋል፡፡

## 4.7.3. የቀንድ ማንኪያ (FAL'AANA GAAFAA)

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ከቀንድ ከሚሰሩት ባህላዊ መመገቢያ እቃዎች ኣንዱ የቀንድ ማንኪያ ነው፡፡

*ኣሰራር፡-* ከዱር ኣውሬም ይሁን ከቤት እንስሳ የተገኘው ቀንድ ከዚህ በላይ በቀንድ ዋንጫ ስራ ላይ በተገለጸው መሰረት ኣጥንቱ ከቀንዱ እንዲላቀቅ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም ቀንዱ መሀል ለመሀል እንዲሰነጠቅ ከተደረገ በሁዋላ ሁለቱም ተሰንጣቂ በእሳት እየታረቀ (በእሳት ወላፈን እንዲላላ እየተደረገ) የማንኪያን ቅርጽ በሚይዝ መልኩ በእንጨት ወይም በብረት መዶሻ መታ-መታ እየተደረገ ተፈላጊውን ቅርጽ ከያዘ በሁዋላ እጄታውን የማውጣቱ ስራ ይከተላል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ዳርና ዳሩ ይከረከማል፣ እንዲለሰልስም

በሞረድ ይሞረዳል፣ በሱፋጭ ይፋቃል፣ በስለታም ሰንጢ ይላጋል:: እጀታው እንደተፈላጊነቱ ረጅምም ኣጭርም ሊሆን ይችላል::

በቀጭኑ እየለሰለሰ፣ ዙሪያውን በደንብ እየተፋቀ የተሰራው የማንኪያው እጄታ ከወደ ጫፉ ሽንትር በማውጣት ያስጌጡታል:: ይህም በዋንጫው ላይ እንደሚታየው ንቅሳት መሆኑ ነው:: ኣንዳንድ የቀንድ ማንኪያዎች በእጀታቸው ጫፍ ላይ ብስ (ቀዳዳ) ይወጣላቸዋል:: ይህም ቀዳዳ ክር ወይም ሲባጎ የሚያስገባ መሆን ኣለበት:: ይህን የሚያደርጉት ማንኪያውን ለመስቀል (ለማንጠልጠል) እንዲያመቻቸው ነው:: በኣጠቃላይ ዋንጫውን ለመስራት ይጠቀሙበት የነበረው መሞረጃና ቅርጽ ማውጫ መሳሪያ ካለ በዚያ ይጠቀማሉ፤ ካልሆነ ግን በተገኘው ስለታም መሳሪያ እየፋቁ ማለስለስ፣ በእሳት እየለበለቡ የተፈለገውን ቅርጽ እንዲይዝ ማድረግ የቀንድ ስራ ተግባራዊ የሚሆንባቸው መንገዶች ናቸው::

*ኣገልግሎት:* - የቀንድ ማንኪያ (Fal'aana Gaafaa) የተባለው የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህላዊ እቃ፣ ባህላዊ ምግቦቻቸውን ገንፎ፣ ቡራቶ፣ ጨጨብሳ እና የመሳሰሉትን የእጅ ንክኪ በማያስፈልግበት ጊዜ ይመገቡበታል:: ከእቃ ውስጥ፣ ድልህ፣ በርበሬ፣ ሽሮ፣ ቅቤና የመሳሰሉትንም ለማውጣት ያገለግላል:: የውጭ ሀገራት እና የሀገር ውስጥ ዘመናዊ ማንኪያዎች በሌሉበት ጊዜ ሁሉ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ በኣንዳንድ ቤትም ለጌጥ እየተባለ በየግድግዳው ላይ መስቀልም የተለመደ ነበር ይላሉ ሀጂ ከዶ:: እሳቸው እንደሚሉት በኣሁኑ ጊዜ ኣልፎ ኣልፎ ያውም የጥንት ስሪት ካልሆነ የቀንድ ማንኪያ ማግኘት ኣስቸጋሪ ነው::



ፎቶግራፍ 30፡- ስርኣተ ኣቴቴ በቀንድ ማንኪያና በጠለቴ

የጥናታዊ ጽሁፉ ዋና ክፍል የሆነው ምእቷራፍ ኣራት የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያና የመጠጫ እቃዎችን ለማስተዋወቅ ሞክሯል:: በዚህም መሰረት ከእንጨት፣

ከሽክላ፣ ከስፌት፣ ከቅል፣ ከቆዳ እና ከቀንድ እየተሰሩ ብሄረሰቡን በረጅም ጊዜ ያገለግሉ የነበሩና ኣሁንም ኣልፎ ኣልፎ በማገልገል ላይ ያሉ ባህላዊ መመገቢያ እቃዎችን ከምልከታ እና ከቃለ-መጠይቅ የተገኘውን መረጃ መሰረት ባደረገ መልኩ የእቃዎቹን ኣሰራር፣ ኣገልግሎት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ በፎቶግራፍ ከተደገፈ ማብራሪያ ጋር ለማቅረብ ተሞክሯል።


ከዚሁ ጎን ለጎን በጎባ ወረዳ በተለይ በኣሁኑ ጊዜ ከሽክላ እና ከስፌት እቃዎች በስተቀር፣ ከመስሪያው ቁሳቁስ፣ ከሙያተኛ እጥረት እና ከኣዳዲስ ቴክኖሎጂ ወለድ ዘመናዊ እቃዎች ጋር ከመተዋወቅ ኣንጻር ወዘተ. የቀድሞ ባህላዊ እቃዎች በብዛት እንደማይሰሩና በግልጋሎት ላይ እንደማይውሉም ለመጠቆም ተችሏል።

የባህላዊ እቃዎቹ በቅርጽ፣ በመጠን ቢለያዩም ቴክኒካዊና ጥበባዊ ኣሰራራቸው ኣንድና ተመሳሳይ እንደሆነ፣ በተለይ ለማስጌጥ የሚጠቀሙባቸው የውበት መግለጫ ቁሳቁስ ጨሌ፣ ዛጎልና የለሰለሰ የጠፍር ጥብጣብ በሁሉም የእቃዎቹ ኣሰራር ላይ ተመሳሳይነት እንዳለው፣ በተለይ ሴቶቹ የሚሰፏቸው ኣንዳንድ የወተት እና ልዩ ልዩ የስፌት እቃዎች የስምንት ቁጥር ቅርጽ እንደሚይዙ፣ ሴቶች ወይም ወንዶች ብቻ የሚተገብሯቸው፣ ኣልፎ ኣልፎ ደግሞ ሁለቱም በጋራና በመረዳዳት የሚሰሯቸው የቁሳቁስ ኣይነቶች እንዳሉ ለመጥቀስ ተሞክሯል።

በዚህ ንኡስ የጥናቱ ክፍል የባህሉ ባለቤት ናቸው፣ ግንዛቤ ይኖራቸዋል የተባሉ ከወጣት እስከ ኣዛውንት የተጠየቁ ሲሆን እነሱም ተጨባጩንና የኣፈታሪክ መሰረት ያለውን እያጣቀሱ መረጃ ሰጥተዋል። ይሁንና መሰረተ-ኣፈታሪክ የሆነውን ከተጨባጭ የታሪክ ድርሳን ወደፊት ለመፈለግ ለሚደረገው ጥረት ኣጋዥ ሲሆን እንደሚችልም የጠቆመው ይህ ምእራፍ በዚሁ ያበቃል።

## 5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የመጨረሻ ምእራፍ በሶስት ማእዘኑ ውስጥ የተዘረዘሩትን በተቀመጡበት ቅደም ተከተል መሰረት ኣቀርባቸዋለሁ::




### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከፎክሎር ዘርፎች ኣንዱ በሆነው በቁሳዊ ባህል በተለይም በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰብ መመገቢያ ቁሳቁስ ላይ ያተኮረ ነው:: የመመገቢያ ቁሳቁሶቹን ኣሰራርና ኣገልግሎት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳቸውን ለማሳየት የሞከረው ይህ ጥናት ምልከታንና ቃለመጠይቅን የመረጃዎቹ ማጠናቀሪያ ዘዴ ኣድርጓል:: የእንጨት፣ የሸክላ፣ የስፌት፣ የቆዳ፣ የቅልና የቀንድ ስሪት የሆኑ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ያካተተው ጥናታዊ ጽሁፉ ኣላማውን ለማሳካትም በተለያየ የእድሜ እርከን ላይ የሚገኙ 28 መረጃ ሰጪዎችን ኣሳትፏል:: ከ28ቱ መረጃ ኣቀባዮች 20ዎቹ ከተተኳሪው ወረዳ፣ ኣንድ ኣጎራባች ከሆነው ከመና ኣንጌቱ ወረዳ የተገኙ የኦሮሞ ብሄረሰብ ኣባላት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 7ቱ ደግሞ በጎባ ወረዳ የተወለዱ፣ የኖሩና ባህሉን ያውቃሉ ተብለው ግምት የተሰጣቸው፣ እንዲሁም ከሙያቸው ኣኳያ እና መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የተጠቆሙ የሌሎች ብሄረሰብ ኣባላት ናቸው::

መረጃ ሰጪዎቹ የተገኙት በእውቂያ፣ በጥቆማ፣በመኖሪያቸው፣ በኣጋጣሚ (በመንገድ ላይ፣ በትምህርት ቤት፣ በገበያ በምግብና በሀዘን ቤት፣ በህዝብና በሀይማኖት በኣላት ወዘተ.) በመሆኑ መረጃዎቹ በቀጥታም፣ በተዘዋዋሪም የተሰበሰቡ ናቸው:: በቀጥታ በተገኘውም መረጃ ቢሆን ኣንዳንድ ግለሰቦች ኣንደበታቸውን ኣይንፈጉኝ እንጂ በመቅረጸ-ድምጽ ለመቀዳት፣ በቪዲዮ ለመቀረጽና ፎቶግራፍ ለመነሳት ፈቃደኛ ኣልነበሩም::

ጥናቱ የተነሳበትን ኣላማ ለማሳካት እያንዳንዱ ቁሳቁስ ከምን፣ እንዴት እንደተሰራና የሚሰጠውን ኣገልግሎት የተነተነ ሲሆን በተጨማሪም የብዙዎቹን ቁሳቁስ ባህላዊ፣ የኣንዳንዶቹንም ማህበራዊ ፋይዳቸውን ለመግለጽ ሞክሯል:: ይሁንና ቀደም ባሉት

ኣመታት ከእንጨት፣ ከሸክላ፣ ከስፌት፣ ከቆዳ፣ ከቅልና ከቀንድ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሲሰሩና የብሄረሰቡ ኣባላትም ሲገለገሉባቸው እንደነበር፣ በኣሁኑ ጊዜ ግን በብዛት ከሚሰራው የሸክላ ስራና በኣንዳንድ ግለሰቦች ከሚተገበረው የስፌት ስራ በስተቀር የሌሎቹ ሲሰሩም ሆነ በግልጋሎት ላይ ሲውሉ እምብዛም እንደማይታዩ በጥናቱ ተደርሶበታል:: ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ቴክኖሎጂ ወለድ ቁሳቁስ እንደኣሸን መብዛት፣ ቁሳቁሶቹን ለመስራት የሚውለው የጥሬ እቃና የሙያተኛ እጥረት፣ ባህላዊ እቃዎቹ የሁዋላ ቀርነት ተምሳሌት ሆነው መታሰባቸው፣ ኣዲሱ ትውልድ በተለይም የወጣቱ ክፍል ለቁሳቁሶቹ የሚሰጠው ኣናሳ ግምት ወዘተ. ናቸው:: ስለዚህ በኣሁኑ ወቅት በማይሰሩትና የተፈለገውን ያህል ግልጋሎት በማይሰጡ ቁሳቁስ ላይ የተሰበሰበው መረጃ ይሰሩ በነበሩበት ቀደምት ኣመታት የማየት እድሉ ከገጠማቸው ግለሰቦች ነው::

በጥናቱ እንደተደረሰበት የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች መመገቢያ ቁሳቁስ የብሄረሰቡን ባህል፣ ልማድና ወግ ወዘተ. የማሳየት ብቃት ቢኖራቸውም በጥንቃቄ ለመያዝና ለእንክብካቤ ግን ኣልታደሉም:: በዚህም ምክንያት ከመስመር እየወጡና ኣሻራ ሳይተዉ በመጥፋት ላይ መሆናቸው ታውቋል:: ለቅርሶቹ መባከንና መጥፋት ኣያሌ ምክንያቶችን መጥቀስ ቢቻልም ዋና ዋናዎቹ-በኣዛውንቶችና በወጣቱ መካከል የባህል መወራረስን የሚያጎለብተው መድረክ ኣለመኖር፣ ለብሄረሰቡ ኣባላት ትምህርት ኣለመስጠትና ቅስቀሳ ኣለማድረግ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሰራተኞች ኣናሳ መሆንና በተለይም የሙያተኛ እና የበጀት እጥረት፣ ቁሳቁሶቹንም የማሰባሰቢያ ቤተ-መዘክር ኣለመኖር፣ ወላጆች ስለቁሳዊ ባህል ኣስፈላጊነት ለልጆቻቸው ኣለመንገርና ሙያቸውን ኣለማሳወቅ፣ የወጣቱ ክፍል ገደብ የሌለው ግዴለሽነት ወዘተ. ናቸው:: እናም ምን መደረግ ኣለበት?

ከጥናታዊ ጽሁፉ ኣላማ እና ከተተኳሪው ወረዳ ኣንጻር መወሰድ ካለባቸው እርምጃዎች ውስጥ ቤተመዘክሮችንና ሙዚየሞችን በማደራጀት ቅርሶችን ከጥፋት መታደግ፣ ወጣቱና ኣዛውንቱ የሚገናኙበትን መድረክ ማዘጋጀት፣ ኮንፈረንስ፣ የፓናል ውይይት ወዘተ. ማዘጋጀት፣ ቅርሶች ለምርምርና ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዲውሉ በመልክ በመልካቸው ማስቀመጥ፣ በትምህርት ቤቶች ቁሳዊ ባህልን የሚያንጸባርቁ ቁሳቁሶችን ለመሰብሰብ እየተደረገ ያለውን ጥረት ማበረታታት ወዘተ. ጥቂቶቹ ናቸው:: ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ሌሎች መሰል እውነታዎች ካልተሟሉ ግን ኣያልነህ ሙላት «የኣገሩን ቱባ ባህል የማያውቅ ወጣት በኩሬ ላይ የሚንሳፈፍ ድፍን የደረቀ ቅል ማለት ነው» (1999፣4) ያሉት ሚዛን ያነሳል::

ኣንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ያለፉ ስራዎችን እርሾ ወስዶ የራሱን የሚያጎባጉበው ኣንድ ኣዲስና ረብ ያለው ነገር ይዞ ብቅ ለማለት ነው:: እናም በዚህ በኩል ከዚህ ጥናት ምን ተገኘ?

የዚህ ጥናት ኣቀራብ. ደጋግሞ እንደጠቆመው በዞኑም ሆነ በወረዳው መሰል ርእስ ይዘው የተሰሩ ጥናቶች ኣላጋጠሙትምና ይህ ጥናት በይዘቱም ሆነ በኣቀራረቡ ኣዲስ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል:: በሌላ በኩል ከምልከታውም ሆነ ከቃለ መጠይቁ በተገኘው መረጃ መሰረት ብሄረሰቡ ለመመገቢያ ቁሳቁሶቹ የሚሰጠው ክበሬታ ለራሱ ከሚሰጠው ክበሬታ ኣንጻር የሚለካ ነው:: ስለሆነም የቁሳቁሶቹ የኣሰራር ቅርጽና የኣጋጊያጥ ዘዴ የሰዎችን ቅርጽና የጌጥ ኣጠቃቀም ስልትን የያዙ በመሆናቸው የእቃዎቹ ተምሳሌትነት የብሄረሰቡ ኣባላት በተለይም የሴቶቹ እንደሆኑ ማጤን ተችሏል::

ኣንዳንድ ቁሳቁስ ላይ በተለይም «ሳምሳ» የተባለው የጠፍር ጥብጣብ የመልእክት መለዋወጫ ከመሆን ኣኳያ በተለይ በሰርግ ጊዜ የድንግልናን መኖርና ኣለመኖር ለማብሰርና ለማርዳት በመልእክት ኣስተላላፊነት የሚጫወተው ሚና ተረጋግጧል:: ከቃለ መጠይቁ በተገኘው መረጃ መሰረት ይህ ጉዳይ በብዙዎቹ የብሄረሰቡ ኣባላት የሚታወቅ ኣይመስልም::

ከእንጨት የሚሰሩ መመገቢያ ቁሳቁስ የስራታቸው ምንጭ በኣብዛኛው ከዋንዛ፣ ከኮሶ እና ከዝግባ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል:: ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ዋንዛ፣ ኮሶና ዝግባ በወረዳው መገኘታቸው ብቻ ሳይሆን ጸሀይንና ንፋስን የሚቋቋሙ፣ ለመቦርቦር ቀላል የሆኑ፣ ለኣፈርና ለውሃ በቀላሉ የማይጋለጡ፣ ክብደት የሌላቸው ወዘተ. ከመሆናቸው ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው::

ባህላዊ እቃዎቹ በተለይ ከእንጨት እንደ«ገበታ» እና «ቆሪ»፣ ከሸክላ እንደ «ጢሲቴ» እና «ኦኮቴ»፣ ከስፌት እቃዎችም «ጡንጦ»ን የመሳሰሉ ቁሳቁስ ከዘወትራዊ ኣገልግሎት ባሻገር የሀብታምነት ተምሳሌት፣ የቤት ገበና ደባቂ፣ እምነታዊ ስርኣትን ማከናወኛ፣ ስነቃልን ማንጸባረቂያ፣ ለትዳር ስምረት ማራመጃ ወዘተ. በመሆን የብሄረሰቡን ባህል እንዴት እንደሚያንጸባርቁ ለማሳየት ተሞክሯል:: ኣባባልን እያዋዙ በቁሳቁሶች ኣስታክኮ የመናገሩ ሁኔታ ዛሬ ይፋ ኣይውጣ እንጂ ጥንት የነበረ፣ ግን ደግሞ በብዙዎቹ የማይታወቅ ከመሆኑ ኣንጻር በዚህ ጥናት መገኘቱ ኣንድ እመርታ ሳይሆን ኣይቀርም:: በጥቅሉ የእቃዎቹ ኣያያዝና የሚሰጣቸው ክበሬታ በሰዎቹ፣ የሰዎቹም ክብርና ክበሬታ በእቃዎቹ ውስጥ የመታየቱ ሁኔታ በዚህ ጥናት ይፋ እንደሆነ ይገመታል:: በሌላም በኩል የሁሉም ጥሬ እቃዎች (የእንጨት፣ የሸክላ፣ የቆዳ፣ የቅልና የቀንድ) ስራት የሆኑ ቁሳቁስ የመጠንና የቅርጽ ልዩነት ካልሆነ የኣሰራር ጥበባቸው ጥንታዊነቱንም ሳይለቅ ተመሳሳይ እንደሆነ ታውቋል::

በሌላ በኩል ከጥንታዊ አጀማመራቸው ኣንጻር ሲታይ የስፌት እቃዎች የኣሰፋፍ ጥበብ እድገት እያሳየ እና የመስፊያ ቁሳቁሶቻቸውና የኣጋጊያጥ ስልታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ እንደመጣ በጥናቱ ተደርሶበታል::

ይነስም ይብዛ በጥናቱ የተገኘው አዲስ ነገር ጠቃሚ ክፍል ሊኖረው እንደሚችል ይታሰባል፡፡ ይሁንና ጠቃሚው ነገር ምንድነው? ማንንስ ይጠቅማል?

በቀዳሚነት የብሄረሰቡ አባላት ራሳቸውን በራሳቸው የሚያዩበት አንድ መስታወት ሊሆን እንደሚችል እሳቤው አለ፡፡ ይህ ደግሞ ታሪክና ባህላቸውን ለመመርመርና የበለጠ ለማወቅ በር ከመክፈት አኳያ መለስተኛ ጥቅም ይኖረው ይሆናል፡፡

የብሄረሰቡን ታሪክ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ወዘተ. ለሚመረምሩ ተነሳሾች እንደመለስተኛ ሰነድ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በተጨማሪም የነጋሪነት ሚና የሚጫወተው ቁሳዊ ባህል በአንድ ወቅት ለሚነሱ ጸሀፍት ያ ትውልድ እንዴት ነበር? ምን ነበር? ማን ነበር? በምን አይነት ቁሳቁስ ይጠቀም ነበር? የቁሳቁሶቹስ ባህላዊ ፋይዳ በምን በምን ይገለጻል? ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ድርሻ ሳይኖረው አይቀርም፡፡ ይህ ደግሞ የራስን ታሪክ ከውጭ ሀገር ጸሀፍት ብቻ ከመፈለግ አይንን በአይን የማየት ያህል ፋይዳ ይኖረው ይሆናል፡፡

የሰውን ስነልቡና ለሚመረምር፣ ጥንታዊ ቅርሶችን ለሚያጠና፣ ለህብረተሰብ ጥናት አትኩሮት ለሚሰጥ ወዘተ. አጥኚ ለረዥምም ጉዞው አንድ ርምጃ ሊሆነው ይችላል፡፡ በአጠቃላይ በቁሳዊ ባህል ላይ ተመስርተው አባባልን፣ ተረትና ምሳሌን፣ እንቆቅልሽን ወዘተ. በጥቅሉ ስነቃልን ለሚያጠኑ ግለሰቦች፣ ታሪክን ለሚመረምሩ ሰዎች ለምርምራቸው ስርጸት መንደርደሪያ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

የጥናቱ ግኝት እንደሚያረጋግጠው የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦች ቁሳዊ ባህል የተተኳሪውን ብሄረሰብ ወግ፣ ልማድ፣ ባህል የማንጸባረቅ ብቃት አለው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገራቸውን፣ ፈሊጣዊ አባባሎቻቸውን በጥቅሉም ስነቃሎቻቸውን ከቁሳዊ ባህላቸው ፈልፍሎ ማውጣት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የማእዳዊ አቀራረብ ስርኣታቸው፣ የትዳራቸው ስምረት፣ እንግዳ ተቀባይነታቸው፣ መልእክትን የሚያስተላልፉበት ልዩ ልዩ ስልት (በሰርግ፣ በምግብ ስርኣት ጊዜ ወዘተ.)፣ በተለይ የሴቶቹ የውበት አጠባበቅና አጋጊያጥ፣ ለአምላካቸው ምህላ የሚያቀርቡበት ስርኣታዊ ክዋኔ፣ ልዩ ልዩ እምነቶቻቸውን የሚያራምዱባቸው ክዋኔዎች፣ ዘፈኖቻቸው ወዘተ. ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የቁሳዊ ባህላቸው ነጸብራቅ ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ ደግሞ የብሄረሰቡን አባላት ከሌሎች ብሄረሰቦች የሚለያቸው የእነሱነታቸው መታወቂያ ነው፡፡ ከዚህም በስተቀር ዛሬ የደረሱበት የስልጣኔ መሰረት የትናንቱ ቁሳዊ ባህላቸው መሆኑም ሊታወቅ ይገባል፡፡

ስለሆነም አኩሪው ቁሳዊ ባህላቸው እንዳይጠፋና እንዳይበረዝ ነቅቶ መጠበቅ፣ አዲሱን ትውልድ ማሳወቅ፣ ቁሳቁሶቹን በማሰባሰብ ለአያያዝ ምቹ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ፡፡ ለህዝብ

እይታ የሚበቁበትን፣ ታሪክን የሚናገሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት። ለጥናትና ምርምር ስርጸት የሚውሉበትን ሁኔታ ማደላደል የሁሉም ድርሻና ሀላፊነት ሊሆን ይገባል። በተለይም ደግሞ የጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ተፈጥሮን ወደ ቁሳዊ ባህል ይለውጡበት የነበረ ዘዴያቸው እንዲንሰራራ ሙያዊ እገዛና ቅስቀሳ ሊደረግላቸው የግድ ነው።

ቁሳዊ ባህል መሰረቱ እደጥበብ ነው። እደጥበብ ደግሞ የሰዎች የኑሮ መሰረት፣ የስልጣኔ ፊር ቀያሽ፣ የታሪክና የባህል ነጋሪ ወዘተ. ነውና የበለጠ ዳብሮ መታየት ብሎም መጠናት ይገባዋል። ይህን ክፍል፣ ከኣራት መቶ ኣመታት በፊት ዘርኣያእቆብ ስለእጅ ስራ ኣስፈላጊነት በተናገሩት ልቋጨው። «ለኑሮህ ተስማሚ የሆነውን የእጅ ስራ ውደድ ... የእጅ ስራ በመስራት ኣትፈርበት የእጅ ስራ ለድሆች ሰራተኞች፣ ለኣንጣሪዎችና ለኣናጢዎች ለገባር ልጆች እንጂ ለታላላቆችና ለከበርቴዎች ልጆችስ ኣይገባም ኣትበል። ይህ ሀሳብ ግን ከትእቢተኛ ልብ ነው ...» (1984፣17)።

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳብ

ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ከመስመር የወጡበትና ኣሻራ ሳይተዉ እየጠፉ ያሉበት ሁኔታ የገዘፈና ስር የሰደደ ከመሆኑ ጋር የመፍትሄውም መንገድ ከተለያዩ ኣቅጣጫዎች የሚቀየስ ነው። በዚህም መሰረት ጥቂት የመፍትሄ ሀሳቦችን መሰንዘር ያስፈልጋል።

1. የባህሉ ባለቤት የሆኑትን የጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሄረሰቦችን ቁሳዊ ባህላቸው፣ ታሪካቸው እንደሆነና ሊኮሩበት እንደሚገባ ማሳወቅ።
2. በየትምህርት ቤቶች ቅርስን ከመጠበቅና ከመንከባከብ ኣኳያ ለተማሪዎች ትምህርት መስጠት።
3. ስለ ቁሳዊ ባህል የሚያስተምሩ ድራማዎችንና ትያትሮችን በክበባት ኣማካኝነት እያዘጋጁ ለመድረክ ማብቃት።
4. ኣዛውንቶች ስለነባሩ ቁሳዊ ባህላቸው የሚናገሩበትን መድረክ ማመቻቸት።
5. በልማዳዊ የእደጥበብ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን ማበረታታትና ሙያዊ እገዛ ማድረግ።
6. የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ኣቅሙ የፈቀደውን ያህል በመንቀሳቀስ የቀድሞ ቁሳቁስ ኣሰራር፣ ኣገልግሎት፣ ባህላዊና ታሪካዊ ፋይዳቸው ተሰንዶ እንዲቀመጥ ቢያደርግ ለወደፊት ብሩህ መንገድ ይከፍታል።
7. በኣንዳንድ ትምህርት ቤቶች እየታየ ያለው ቅርሶችን የማሰባሰብ ጥረት የሚጠናከርበትን ስልት መቀየስና የእያንዳንዱ ወጣት ኣእምሮ የቁሳዊ ባህል ማእከል የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ለነገ መባል የሌለበት ተግባር ነው።

# የተጠቀሱ ምንጮች


«ሀገሬ»፣ አለማየሁ ታደሰ (ተራኪ)፤ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሳምንታዊ ፕሮግራም፣ አዲስ አበባ፤ መስከረም 22 ቀን 1999::

ላጵሶ ጌ. ደሌቦ፤ የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግስት ታሪክ፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አንደኛ መጽሀፍ፣ 1982::

መሀመድ ሳላህ፤ «ባህልና ንድፈ ሀሳባዊ ግንዛቤው፤» መስከረም፤ በየሶስት ወር የሚወጣ፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ቅጽ 2 ቁጥር 7፣ 1974፤ ገጽ 67-84::

መሀመድ ከዲር፤ «ምግብ ነክ ስነቃል በአርሲ ኦሮሞዎች ዘንድ፤» አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 1988::

ሲዶኖቭ ማርቲን፤ ፓለቲካል ሳይንስ ቁስ አካልነት (ማቴሪያሊዝም) ምንድነው?፤ «የህብረተሰብ ምጣኔ ሀብታዊ መቅርጾች»፤ አሳታሚ የኖቨስት የዜና አገልግሎት ድርጅት፣ (የታተመበት ዘመን ያልተገለጸ) ፣ ገጽ 47::

ሽመልስ እጅጉ፤ «በሀረርጌ ክፍለ ሀገር በጨርጨር አውራጃ ኦሮሞ ብሄረሰብ ስርአተ ጋብቻ ላይ የሚሰሙ ስነቃላዊ አባባሎች፤» አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1981::

በላይነህ አሰጉ፤ «ስለ ቅርሳ ቅርስ አንዳንድ ነጥቦች፤» መስከረም፤ በየሶስት ወር የሚወጣ፣ ቅጽ 9፣ ቁጥር 38 ሰኔ 1981፤ ገጽ 6-45::

ተሾመ ፎርሲዶ፤ «የባህላዊ የቤት እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሀዲያ ብሄረሰብ፤» አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 1993::

አለም እሸቱ፤ መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ፤ አዲስ አበባ፣ የቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋክልቲ ህትመት፤ 1994::

አሰገደች አወቀ፤ «በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ የቤት እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች መዘርዝር ከነአገልግሎታቸው፤» አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ 1986::

አስመራ መምህራን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፤ ባህል ልውውጥ፤ (ያልታተመ) በግምት 1963፣ ገጽ 35::

አበበ መርእድ፤ «በባሌ ዞን በጎባ ከተማና አካባቢው ስለቦታዎች አሰያየም የተነገሩ አፈታሪኮች ትንተና፤» ዲላ የመምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ክፍለ ትምህርት፤ ለትምህርት ባችለር ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ 1995::

አቢይ ጽጌ እና ታመነ ታደሰ፤ «ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለልማት፤» መስከረም፤ በየሶስት ወሩ የሚወጣ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ ቅጽ 6 ቁጥር 25፤ መጋቢት 1978፣ ገጽ 7-27::

ኢትዮጵያን አንቃኛት፤ አስቻለው ጌታሁን (ተራኪ)፤ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ሳምንታዊ ፕሮግራም፣ አዲስ አበባ፤ መስከረም 5 ቀን 1999::

አያልነህ ሙላቱ፤ «ባህልና አብዮታችን፤» መስከረም፤ በየሶስት ወር የሚወጣ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ ቅጽ 3፣ ቁትር 10፤ መስከረም 1975::

________፤ «በድራማ እድገት ላይ የሚታዩ ችግሮች (ወፍ በረር ቅኝት)፤» ብሌን፤ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር የስነ-ጽሁፍ መጽሄት፣ አዲስ አበባ፣ ልዋ ማተሚያ ቤት፣ ቁጥር 4፤ ግንቦት 1999::

እንግዳየሁ ለገሰ እና ይልማ ጥበቡ፤ «ጎባ ከትናንት እስከ ዛሬ፤» ጎባና እድገቷ፤ 1979፤ ገጽ 6-7::

እንግዳየሁ ለገሰ፤ «የባሌ ዞን ገጽታ»፤ ትውውቅ፤ ናትኮ የህትመት ስራ ድርጅት፣ (የህትመት ዘመኑ ያልተገለጸ) ገጽ 19::

ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፤ የኦሮሞ ታሪክ-እስከ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፤ አዳማ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1996::

«ዘርኣ ያእቆብ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ (ከ1592-1685)፤» ህብር፤ በየወሩ የሚታየም ቁጥር 4፣ ነሀሴ 1984፤ ገጽ 17::

ዘሪሁን አስፋው፤ <u>የስነጽሁፍ መሰረታውያን</u>፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992::

የሱፎ በሀብቱ፤ «የኣርሲ ነገሌ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ የጋብቻ ስርኣት ስነቃልና ክዋኔው፤» ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 1990::

የጎባ ከተማ የህዝብ ኣደረጃጀት ጽህፈት ቤት፣ ኣመታዊ እቅድ መጽሄት (ያልታተመ)፣ 1999::

ጀቤሳ ኤጀታ፤ <u>የኦሮሞ ባህልና ኣጭር ታሪክ</u>፣ ኣዲስ ኣበባ፣ ኣርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989::

ጌታቸው ሀይሌ፤ <u>የኣባ ባህርይ ድርሰቶች ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር</u>፤ ሚኒሶታ፤ ኮሌጅ ቪል፣ 1995::

ጸጋ መለሰ፤ «የቤት ውስጥ እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሰሜን ወሎ በላስታ ኣካባቢ በግዳን ወረዳ፤» ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 1995::

ፈቃደ ኣዘዘ፤ «ትውፊት በስነጽሁፍ ውስጥ፤» <u>የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ መጽሄት</u>፤ ቁጥር 3፣ 1986፤ ገጽ 5::

________፤ <u>የስነቃል መምሪያ</u>፤ ኣዲስ ኣበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991::

________፤ <u>ሰሚ ያጡ ድምጾች</u>፤ ኣዲስ ኣበባ፣ ዲዛይንና ህትመት ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1996::

ፋሲል ተፈራ እና ሌሎችም፤ «የባህልና የቴክኒክ መሰረት ገንባታ በኣብዮቱ ሂደት፤» <u>መስከረም</u>፤ በየሶስት ወር የሚወጣ፣ ቅጽ 3፣ ቁጥር 12፤ መጋቢት 1975፤ ገጽ 50-73::

Arsi-Bale Rural Development Project. <u>Atlas of Bale Zone</u>. Regional State of Oromia, Bale Zone Department of Finance and Economic Development Printed at ABRDP sub unit, Asella. 2004.

Aylsi, Eric. <u>An Introduction to the study of African Cultures</u>. USA. James Currey; 1972.

Beals, Ralph, and Hurry Hoijer. <u>An Introduction to anthropology</u>. New York: USA. Macmillan company; 1953.

Central Statistical Authority. "The 1984 Population and Housing Census Analytical Report on Bale Region." Addis Ababa, 1959.

________. "The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia." Statistical Report, Addis Ababa, 1998.

Chojnacki, S. "The Preservation of Ethiopia's Cultural Heritage." <u>Dialogue twice a year</u> July – 1971: 7-18.

Fikre Tolossa. "Oromo Contribution to Ethiopian Civilization." <u>Ethiopian Review Monthly</u> March, 1993:24.

Georges Robert A, and Michael Owen Jones. <u>FOLKLORISTICS AN INTRODUCTION</u>. USA. Indian University Press, 601 North Morton Street, Bloomington. 1995.

Glassie, Henry. <u>Material Culture</u>. Indian University Press, 1999.

Goba "AANA" Administration Office. "Five Years Strategic Plan for Rural Water, Sanitation and Hygiene Program (2005/06-2009/10)." Unpublished, December, 2005.

<u>http://www.elearn.orizona-edu/sfair/fall449glossaryhtml12/19/2005</u>.

Kidd, Warren. <u>Culture Identity</u>. Great Britain. Antony Rowe Ltd, Chippenham, Wilts; 2002.

Kokob Publisher. ABC of Dialectical and Historical Materialism. Addis Ababa. Central Printing Press, (Publication Year is not specified).

Mann, Alan. The First Men: "Fire, the Magic Tool". Canada: Time Inc, 1973.

Marcos Bassi, "Every Woman is an Artist: The Milk Containers of Elema Boru." Ethiopia: Traditions of Creativity. Ed. SILVER MAN ROYMONDA. Hong Kong. University of Washington Press, 1999.

Mindaye Abebe. "The Oromo of Bale: A Historical Survey to 1974." M.A. Thesis in Hisotry Addis Ababa University, 2005.

Nizita, Richard. Peoples and Cultures of Uganda. Fountain Publishers :td, 1993.

Oakely P, Kenneth. Social Life of Early Man. "On Man's use of fire, with comments of Tool making and hunting." USA Aldine Publishing Company, 1961.

Pankhurst, Richard. "The Old-time handicrafts of Ethiopià." Ethiopian observer. Published in Ethiopia and Britain. Vol. viii no.3; 1964; 221-241.

Plant, B.A. Edith. Man's un written past. New York: Oxford University Press, 1942.

Roberts Warren E. "Material Culture: Folk Crafts." FOLKLORE and FOLKLIFE: FOLK CRAFTS. Ed. Richard M. Dorson. London: University of Chicago Press, ltd. 1972; 243.

Somjee, Sultan. Material Culture of Kenya. Nairobi; East African Educational Publishers Ltd, 1993.

Spier F.G. Robert. From the Hand of Man: Primitive and Preindustrial Technologies. USA. Boston New York. Atlanta: Houghton Mifflin Company, 1970.

## ኣባሪ ኣንድ

## የመረጃ ሰጪዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪዎች ስም | እድሜ | ስራ | የሚኖሩበት ቦታ | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ብሄረሰብ | ወረዳ | ከተማ | ገበሬ ማህበር | |
| 1 | ሀጂ ኣብዱልጀዋድ ኣዲ | 88 | ጡረተኛ፣ ስለ አንጨት ስራ አዋቂ | ኦሮሞ | ጎባ | - | ላሽቆና | |
| 2 | ሀጂ ፊቂ ሀሰኖ | 69 | የምስራቅ ጎባ ቀበሌ ሊቀመንበር | » | » | ጎባ | - | |
| 3 | ወ/ሮ ጊሹ ኣማን | 55 | የስፌት ስራ ሙያተኛ | » | » | ቡርቂቱ | | |
| 4 | ኣቶ መርእድ ኣስፋው | 80 | ግብርና | ኣማራ | » | - | » | |
| 5 | ኣቶ ኣለሙ ወርቁ | 48 | መምህር ስለ አንጨት ስራ አዋቂ | ኦሮሞ | » | ጎባ | - | |
| 6 | ሀጂ መሀመድ ኣደም | 60 | ግብርና | » | » | - | ከዱ | |
| 7 | ኣቶ ሹንካ ገርማሞ | 56 | ሽክላ ስሪ | ወላይታ | » | - | ፋሲል ሀንገሶ | |
| 8 | ወ/ሮ የሺ ተረፈ | 48 | ሴተኛ ኣዳሪ | ኦሮሞ | » | ጎባ | - | |
| 9 | ኣልፊያ ሀጂ | 19 | ተማሪ | » | » | - | መቸመና | |
| 10 | ኣቶ ኢብራሂም ኣብዱልጀዋድ | 27 | ግብርና | » | » | - | ላሽቆና | |
| 11 | ኣቶ በቀለ ገባቦ | 65 | ሽክላ ስሪ | ወላይታ | » | ጎባ | - | |
| 12 | ተማም ኑር ኢብራሂም | 22 | ተማሪ | ኦሮሞ | » | - | ኣሹታ | |
| 13 | ወ/ሮ ብዙነሽ ገነሞ | 54 | ሽክላ ስሪ | » | » | - | ፋሲል ሀንገሶ | |
| 14 | ወ/ሮ ኑሪያ ኢብራሂም | 50 | ስለ ቅል ስራ አዋቂ | » | » | - | ሪራ | |
| 15 | ኣቶ ኣብዱርቃዲር ኣቡበከር | 43 | ርእሰ መምህር | » | መና ኣንጌቱ | ኣንጌቱ | - | |
| 16 | ወ/ሮ ሌይላ ኢብሮ | 42 | የስፌት ስራ ሙያተኛ | » | ጎባ | - | ቡርቂቱ | |
| 17 | ሀጂ ከዴ ጎበና | 74 | ጡረተኛ ስለቀንድ ስራ አዋቂ | » | » | - | ሺፋሪዮ | |
| 18 | ኣቶ ጥላሁን ጥሩነህ | 35 | ሽክላ ስሪ | ኣማራ | » | ጎባ | - | |
| 19 | ኣቶ በቀለ ቱፋ | 48 | መምህር | ኦሮሞ | » | ጎባ | - | |
| 20 | ወ/ሮ ማክዳ ባህ | 51 | ባለትዳር | » | » | - | ሸደም | |
| 21 | ሀሰን ማማ ሙሳ | 23 | ተማሪ | » | » | - | ሲንጃ | |
| 22 | ኣቶ ግርማ መንግስቱ | 49 | መምህር | ኣማራ | - | - | - | ኢ.ኣ.ዩ በስነልሳን MA ተማሪ |
| 23 | በድርያ ካዎ | 19 | ተማሪ | ኦሮሞ | ጎባ | - | ኢላላ | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | ወ/ሮ ብዙነሽ ነጋሲ | 64 | ባለትዳር | » | » | - | ቡርቂቱ | |
| 25 | ወ/ሮ ዝናሽ ጥሩነህ | 47 | ሽክላ ስሪ | ኣማራ | » | - | ፋሲል ሀንገሶ | |
| 26 | ወ/ሮ ራህማ መሀመድ አሚን | 64 | የስፌት ሙያተኛ | ኦሮሞ | » | ጎባ | - | |
| 27 | ኣቶ ኣደም ቃሲም | 45 | ንብረት ክፍል | ኦሮሞ | » | ጎባ | - | |
| 28 | ወ/ሮ ደመቀች ሼኮ | 30 | የሸክላ ስራ ሙያተኛ | ኣማራ | » | ጎባ | - | |

## ኣባሪ ሁለት

## ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡ እና ሌሎችም በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተጠቀሱ ጥያቄዎች በ11 ካሴቶች የተቀረጹና የተጠቃለሉ ናቸው። በተጨማሪም በመቅረጽ-ድምጽ ለመቀረጽ ፈቃደኛ ያልሆኑ መረጃ ኣቀባዮችም ከተጠየቋቸው ጥያቄዎች ውስጥ ኣንዳንዶቹን በዚህ ናሙና ውስጥ ለማካተት ተሞክሯል።

### I. ለሁሉም የሚቀረቡ ኣጠቃላይ ጥያቄዎች

1. የቁሳቁሱ መጠሪያ ስም ምን ይባላል? ስሙስ እንዴት ሊሰጠው ቻለ?
2. ቁሳቁሱን ለመስራት ምን ምን ጥሬ እቃዎችን ትጠቀማላችሁ?
3. የቁሳቁሱ የስራ ኣጀማመር እንዴት ነው?
4. ይህንን ቁስ ሰርቶ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ቀን ይወስድቦታል?
5. የቁሳቁሶቹ መስሪያ ጥሬ እቃ ከየት ይገኛል?
6. የቁሳቁሱን መጠን ለመወሰን መለኪያችሁ ምንድነው?
7. ቁሳዊ ባህል እንዲጠበቅ ምን መደረግ ኣለበት ይላሉ?

### II. ለሸክላ ሰሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የሸክላ ስራ ማለት ምን ማለት ነው?
2. እርስዎ የሸክላን ኣሰራር ልምድ እንዴት ለመዱት?
3. በጎባ ወረዳ ውስጥ የሸክላ ስራ እንዴትና መቼ ተጀመረ?
4. ኣንድን የሸክላ እቃ ለምሳሌ «ማሰሮን» ውሰዱና ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለውን የኣሰራር ሂደት ይንገሩኝ።
5. «ወሾ» የሚባለው እቃ ምን ኣይነት ነው?
6. የ«ጢሲቴ» ኣገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ምንድነው?
7. ከማሰሮ፣ ከድስት፣ ከጀበና ለአሰራር የትኛው ይቀላል?
8. የሸክላውን መስሪያ ኣፈር ከየት ታገኛላችሁ? እንዴትስ ታመጡታላችሁ?
9. የ«ጀበና»፣ የ«ኣኮቴ»፣ የ«ጡዌ» ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ምንድነው?
10. በሸክላ ስራ ውስጥ «ኡሬ» ማለት ምን ማለት ነው?
11. በሸክላ ስራ ሂደት የማቃጠያው ምድጃ ለምን ኣመድ ይነሰነስበታል?
12. ሸክላ በመስራት ላይ እያለ ቢሰነጠቅ መፍትሄው ምንድነው?
13. ጥንት ከህብረተሰቡ ንቃተህሊና ዝቅተኝነት ሙያው ያን ያህል ላቅ ያለ ግምት ኣይሰጠውም ነበር። ኣሁንስ?

## III. ከእንጨት ስለሚሰሩ ቁሳቁሶች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. አንድን ከእንጨት የሚሰራ ቁስ ለምሳሌ «ገበታ»ን ውስዱና ያለውን የአሰራር ሂደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ይንገሩኝ?
2. «ቆሬ» ማለት ምን ማለት ነው? ገበታስ?
3. «ቆሬ» ለገበታ መሰረት እንደሆነች ይነገራል፡፡ ይህ ምን ያህል እውነት ነው?
4. የገበታንና የቆሬን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ይንገሩኝ?
5. በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህል «ገበታ» ትልቅ ቦታ የተሰጠው ለምንድነው?
6. የ«ገበታ»፣ የ«ቆሬ» ባህላዊ ፋይዳ የሚገለጸው ምን ጊዜ ነው?
7. በቁዱ ምን አይነት ምግቦች ይቀመጣሉ?
8. «ቆሬ» ምስጢር ጠባቂ፣ ገበና ከታች መባሏ ስለምንድነው?
9. ገበታ ተምሳሌታዊነት አለው የሚባለው ለምንድነው?

## IV. ከስፌት ስለሚሰሩ እቃዎች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. በጎባ ወረዳ ስፌት እንዴት ተጀመረ?
2. በጎባ ወረዳ ኦሮሞዎች ባህል ምን-ምን አይነት የስፌት እቃዎች ይዘጋጃሉ?
3. «ጡንጦ» ከትዳር ጋር መያያዙ ለምንድነው?
4. በጡንጦ፣ በጮጮ፣ ማለቢያ ላይ የሚታበቱት የጠፍር ጥብጣቦችና የጌጥ ጨሌዎችና ዛጎሎች ትእምርታዊ ፋይዳ ምንድነው?
5. በተለይ የሚታበተው ጠፍር «ሳምሳ» ምን ባህላዊ ፋይዳ አለው?
6. ለስፌት የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎች ምን-ምን ናቸው?
7. አንድ ጡንጦ፣ ማለቢያ ወይም ጮጮ ውሰዱና የአሰፋፍ ሂደቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ይንገሩኝ፡፡
8. ጡንጦ ማለት ምን ማለት ነው? «ኢለምቱስ»?

## V. ከቆዳ ስለሚሰሩ እቃዎች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. «ኦኮሌ» የተባለው የቆዳ ስራት እቃ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ምንድነው?
2. በቆዳ የሚለጎመው አገልግል እንዴት ይሰራል? የአሰራር ሂደቱን ይንገሩኝ? ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳውስ ምንድነው?
3. የ«ኦኮሌ»ን የአሰራር ሂደት ያስረዱኝ?
4. በጎባ ወረዳ ያሉ የኦሮሞ ብሄረሰቦች ከቆዳ ብዙም ቁሳቁሶችን ሲሰሩ አይታዩም፡፡ ለምን?

## VI. ከቅል ስለሚሰሩ ቁሳቁስ የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. አንድን የቅል ቁስ ወደ ቁሳዊ ባህል ለመለወጥ የሚደረገው የአሰራር ሂደት ምን ይመስላል?
2. የ«ቁሉ ቡና»፣ «ቁሉ ሰላታ» አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ምንድነው?


3. የቅል ቁሳቁስ ለምን ለምን አገልግሎት ይውላል?

## VII. ከቀንድ ስለሚሰሩ ቁሳቁስ የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. የቀንድ ዋንጫ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ምንድነው?
2. አንድን ቀንድ ወደ ቁሳዊ ባህል ለማብቃት የሚደረገው የአሰራር ሂደት ምንድነው?
3. በጥንታዊ አሰራር ቀንዱ ከየት ይገኝ ነበር?
4. በአሁኑ ጊዜ በቀንድ መጠቀምም ሆነ ቀንድን መስራት በተለይም በልማዳዊ ዘዴ ይሰራ የነበረው ቀርቷል ለምን?
5. ጥንት የቀንድ ቁሳቁስን ለምን-ለምን ይጠቀሙበት ነበር?
6. የቀንድ ማንኪያ አገልግሎት ምንድነው?

***ማሳሰቢያ:-*** ብዙዎች ጥያቄዎች እዚያው ከሚሰጡት መልሶች የሚመነዘሩም መሆናቸውን ያጤኗል።

## ኣባሪ ሦስት፡ የፎቶግረፍ መረጃ



ቃለ መጠይቅ፡- ከሀጂ አብዱጀዋድ ኣዲ ጋር



ቃለ መጠይቅ፡- ከሀጂ ፈቂ ሀሰኖ ጋር



ቃለ መጠይቅ፡- ከአቶ በቀለ ቱፋ ጋር

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY



ቃለ መጠይቅ፡- ከአቶ ኣለሙ ወርቁ እና ከሀሰን ማማ ሙሳ ጋር



ቃለ መጠይቅ፡- ከአቶ ኣለሙ ወርቁ፣ አልፊያ ሀጂ እና በድርያ ካዎ ጋር



ቃለ መጠይቅ፡- ከአቶ ጥላሁን ጥሩነህ ጋር



ቃለ መጠይቅ፡- ከሹንካ ገርማሞ ጋር



የስፌት ሙያተኛዋ በስፌት ሥራ ላይ




ልዩ ልዩ የአለላ አይነቶች



እነ «አዮ» ወተት በጡንጦ ሰንቀው ወደ ሰርግ ቤት
በመንዝ ላይ እንዳሉ



የሸክላ ገበያ



ወተትና የገበታ «ቡራቶ» አይነጣጠሉም




የአቴቴ ስርኣታዊ አከዋወንና ባህላዊ ቁሳቁስ



የሽክላ እቃ የሆነው ምጣድ በኣገልግሎት ላይ

## MAP OF GOBA WEREDA (By Peasant Association )




**Scale: 1 : 250,000**
**Source: Goba Wereda Educational Office, 1992 E.C.**

**መግለጫ**

ይህ ቴሲስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የእኔ ወጥ ስራ (Original) ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የድግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

**ሚያዝያ፣ 2000 ዓ.ም.**